# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

አዘጋጅ አባ ጎርጎርዮስ (M.A)
የሸዋ ሊቀ ጳጳስ

ሰኔ 1974 ዓ.ም የመጀመሪያ እትም
ህዳር 1986 ዓ.ም ሁለተኛ እትም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

## የማውጫ ገጽ ማስተካከያ


መቅድም ........ ገጽ ፱ የነበረው .... ገጽ ፫

መግቢያ ........ ገጽ ፲፫ የነበረው .... ገጽ ፲፩

ምዕራፍ ፩ ....... ገጽ ፳፪ የነበረው .... ገጽ ፳

ምዕራፍ ፪ ....... ገጽ ፴ የነበረው .... ገጽ ፳፰

ምዕራፍ ፫ ....... ገጽ ፴፫ የነበረው .... ገጽ ፴፭

ምዕራፍ ፬ ....... ገጽ ፵፰ የነበረው .... ገጽ ፵፯

ምዕራፍ ፭ ...... ገጽ ፷፩ የነበረው .... ገጽ ፹፱

ምዕራፍ ፮

ክፍል ፩ ...... ገጽ ፻፩ የነበረው .... ገጽ ፺፱

ክፍል ፪ ...... ገጽ ፻፱ የነበረው .... ገጽ ፻፫

ምዕራፍ ፯ ....... ገጽ ፻፴፬ የነበረው .... ገጽ ፻፴፪

ምዕራፍ ፰ ...... ገጽ ፻፵፫ የነበረው .... ገጽ ፻፵፭

ምዕራፍ ፱ ....... ገጽ ፻፶፬ የነበረው .... ገጽ ፻፶፪

ምዕራፍ ፲ ....... ገጽ ፻፷፯ የነበረው .... ገጽ ፻፷፬

ምዕራፍ ፲፩ ..... ገጽ ፻፸፰ የነበረው .... ገጽ ፻፸፯


ተብሎ ይነበብ

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


መቅድም ........................................ ፱

መግቢያ ........................................ ፲፫

ምዕራፍ ፤— ፩

— ኢትዮጵያና የክርስትና ሃይማኖት ................ ፳፪

ምዕራፍ ፤— ፪

— ከካሌብ እስከ ዮዲት ........................ ፵

ምዕራፍ ፤— ፫

— ከዮዲት በኋላ እስከ ዐፄ ይኩኖ አምላክ ........ ፵፯

ምዕራፍ ፤— ፬

— ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዘመነ መሳፍንት ........ ፸፰

ምዕራፍ ፤— ፭

— ከዘመነ መሳፍንት እስከ አሁን ................ ፹፩

ምዕራፍ ፤— ፮

ክፍል ፤— ፩

— የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት(ዶግማ) ፩፻፩


www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


አርእስት                                                    ገጽ

ክፍል ፡— ፪

— የታቦት ፣ የሥዕልና የመስቀል ክብር
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፩፻፱

ምዕራፍ ፡— ፯

— የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖና .......... ፩፻፳፬

ምዕራፍ ፡— ፰

— የአማላጅነት ትምህርት .................. ፩፻፶፯

ምዕራፍ ፡— ፱

— የቤተ ክርስቲያን አሠራርና ክርስቲያናዊ ትውፊት ፩፻፷፬

ነራፍ ፡— ፲

— ኢኩሜኒዝም እና
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፩፻፸፯

ምዕራፍ ፡— ፲፩

— የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ
ቲያን ሥሪት . . . . . . . . . . ፩፻፹፭


www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
# ሕያው መንፈሰዊ አባት፣

ጳጉሜን 1 ቀን 1982 ዓመተ ምሕረት የወጣው ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ መልኩም ሆነ ዜናው ከወትሮው ለየት ያለ ነው። መልኩ የወየበ ደም ይመስላል። አትኩረው ሲያዩት፣ የደበዘዘ ወይንግ ገፅታ፣ አልያም የገረጣ ሐምራዊ ቀለም ነው። መልስ መለልስ ላስተዋለው በስስቱም መልክ ሆነ በንድያው የጌታን ክቡር ደም ያስታውሰል። በቀራንዮ የፈሰሰውን የክርስቶስ ደም በሕሊና እየሳለ የመስዋዕትነትን ቅዱስነት በለሆሳስ የሚያስተለልፍ ድምፅ ከወረቀቱ ግዘፍ ነስቶ ይሠርፃል። ከዚሁ ገፅ፣ በቀኝ ዓምድ በኩል፣ «ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዐረፉ» የሚል ዜና በጥቁር ቀለም ሠፍራል። መስቀሉን በቀኝ እጅ የጨበጠው ምስላቸው ምዕመናንን ይሰናበታል።

ዳሩ ግን፣ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሬም ሕያው ናቸው። በሰዎች ልበና፣ በገዳማት አጸድ፣ በአድባራት ዓውደ ምሕረት፣ በቅኔ ማሕሌት፣ በቅድስቱ ዙሪያና፣ በሕገ ታበታት ማረፊያ መንበር ጭምር ሐዋርያዊ ድምፃቸው ያስተጋበል። «ልጆቼ ዓለማዩን ተከተሉ፣» የሚለው አባታዊ ምክራቸው አሁንም በወጣቱ ልብ በየሰንበት ት/ቤቱ ይንበገበጋል። «እኛ የመነከስነው ለፍትፍት አይደለም፣ የመስቀሉ ፍቅር ይግበችሁ» እያሉ ከጭንጫ ሰይሆን ከጥቂት የለሰለሰ ማሳ ላይ የዘሩት ፍሬ በብዙ ምእመናን ደም ስር ውስጥ ዘሬም ይዘዋወራል። ለእርሳቸው የነበራቸው፣ ያላቸውና ወደፊትም የሚኖር ፅኑ ፍቅር በቃለ እግዚአብሔር የተፈተለና በንጽሐ በሕርይ የተቋጨ ነውና ቢረሱት የማይረሳ፣ ዕፍ ቢሉት የማይጠፉ የማለዳ ጎሕ ነው።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የተገኙት በስእለት ነው። ወለጆ እናታቸው እማሆይ አስለፈች ከሣ ለደሴ መድኃኔ ዓለም ብፅዓት ሲገቡ «የተበረከ ልጅ ከሰጠኸኝ ለንተው ቀዳሽ አደርገዋለሁ»

www.ethiopianorthodox.org

ይሰሉ። ለዚህም ምክንያቱ ወንድ ልጅ አለድግ ብሏቸው ነው። ከአቶ ገበየሁ አሰዬና ከእማሆይ አሰለፈች በ1933 ዓ.ም. የተወለዱት አበ ጎርጎርዮስ ወደ ተቀደሰው የእግዚአብሔር ጎዳና ያመሩት ገና በሕፃንነታቸው ነበር። ወላጅ ዘመዶቻቸው፣ አበ ጎርጎርዮስ ገና በአንድ ዓመት ጨቅላ ዕድሜያቸው የእንጨት መስቀል ሠርተው ለማሳለም ይሞክሩ እንደነበር ያወሳሉ። መምህራቸው አለቃ ድንቁ አልፍ ሲሉ፣ ያኔ ሕፃኑ ድጓ እየገለበጠ ሲያይ «የእዚህን ልጅ መደረሽ ዕድሜ ለጥቶኝ ባሰየኝ» እያሉ በመገረም ይናገሩ እንደነበር ዘመዶቻቸው በመሪር ትዝታ ያስታውሳሉ።

በሕፃን ልባቸው የመስቀሉ ፍቅር የተለከለው አበ ጎርጎርዮስ፣ ያገራችንን መንፈሰዊ ዕውቀት በስፋትና በጥልቀት ገብይተዋል። ዝናቸው ከታወቀው የተለያዩ ኢትዮጵያ ገዳማትና ብቃታቸው ከተመሰከረላቸው ሊቃውንት ዘንድ፣ ዜማ፣ ትርጓሜ መጻሕፍት፣ አዕማደ ምስጢር፣ ባሕረ ሃሳብ፣ ቅኔ፣ ትምህርተ ሃይማኖት አጠናቅቀው ተምረዋል፣ አደላድለውም ተመርቀዋል።

ዘመናዊውንም ትምህርት በየደረጃው በብሩህ አእምሮዋቸው ቀስመው ከአቴና ዩኒቨርስቲ በቲኦሎጂ (ነገረ መለከት) በማስትሬት ዲግሪ ተመርቀዋል፣ ፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋም አጥንተዋል።

አበ ጎርጎርዮስ ልዩ በሆነና ፍቅርን በተመለ መንፈሰዊ ስሜት ዘወትር እንዲታሰቡ የሚያደርጓቸው አያሌ ቁም ነገሮች አሉ። ዋና ዋናዎቹ መንፈሰዊ አገልግሎታቸው፣ ትምህርታቸው፣ ሰብአዊ ባህርያቸው፣ የምርምር፣ የሥነ ጽሑፍና የማስተማር ተሰጥዎአቸው ናቸው።

አገልግሎታቸው ሠፊና መሠረት ያለው ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፖትርያርክ በነበሩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ በ1971 ዓ.ም. ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

ሆነው ከተሾሙበት ጊዜ አንስቶ ሕይወታቸው በመኪና አደጋ እስከከለፈበት እስከ ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም. ድረስ በጣም ድንቅና በርካታ ሥራዎችን አከናውነዋል። የዝዋይን የከህናት ማሠልጠኛ በገዳም ሥርዓት እንዲተዳደር አስወስነው በሺህ የሚቆጠሩ ከህናት እንዲሠለጥኑ፣ ብዙ መቶ ወጣቶች እንዲማሩና አባት እናት የሌላቸው ሕፃናት እንዲያድጉበት ከማድረጋቸውም በላይ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማነፅና በዚሁ ሥፍራ የተለያዩ የልማት አውታሮችን በመዘርጋት አርአያነት ያለው ተግባር ፈጽመዋል። መሬታዊ አከላቸው ራሳቸው በሰነፁት በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ማረፉም ያለ ምክንያት አይደለም። በሕይወት ዘመናቸውም ብሩሀና ቅዱስ ተግባራቸው ከዝዋይ ቅዱ ገብርኤል ገዳም ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

ትምህርታቸው ልቡናን ሰብሮ የሚገባ፣ በምሳሌዎች ክ… ሕሊናን የሚመስጥና ጥልቀት ያለው እንደነበር ይነገራል። ኪሉ… እንዳለ ምንጭ ውሃ ቢጎነጩት የማይሰለች፣ ይልቁንም መንፈሰዊ ፍቅርንና የጥበብን ፋና ከልብ ውስጥ የሚያጭር መሆኑ በውል የታወቀ ነው። ከአበ ጎርጎርዮስ የዕውቀት ገዕድ የተሰተፉት አንድ መንፈሰዊ አባት «ትምህርታቸው እንደ ዓ… ይ የሚቀዳ ነበር» በማለት ያወሰሉ። በጭሩ፣ እንደበታቸውም ሆነ ትምህርታቸው እንደ ፈሪሰዊ በሐሰት ከተሸፈነ መንፈሰዊ ልብ የሚወጣ ሰይሆን ከተዋሕደ እምነት አማናዊ ጥልቅ ፍቅር የሚመነጭ ፍቱንና የነጠረ ቃለ እግዚአብሔር ነበር።

ሰብአዊ በሕርያቸው ብዙ ሊባልለት የሚችል ነው። የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሰብአዊ በሕርያቸውና አስተሰሰባቸው ለየት ያለ እንደነበር በቅርቡ የሚያውቋቸው ሁሉ በአድናቆት ይመሠከራሉ። ስለርሳቸው በነሱ ቀጥር ስሜት የሚተናነቃቸው አንድ አባት ሲናገሩ «እርሳቸው ሀገራቸውን፣ ሕዝባቸውን የሚወዱ፣ በኢትዮጵያዊነት የሚያምኑ፣ እናት ለልጅዋ እንደምታስብ ሀገራቸውን የሚወዱ፣ ሥጋዊ ጥቅም የማያታልላቸው፣ በሃይማኖትም ሆነ በሀገራቸው

www.ethiopianorthodox.org

ጉዳይ አድርበይነት የሌለበቸው፣ ፍርሐት የሌለቸው፣ እውነት የሚናገሩ፣ ዕለትዋን ይሞታሉ እንጂ አድርበይነት አያውቁም» ይለሉ። እኒሁ አበት፣ አበ ጎርጎርዮስ በእግዚአብሔር ፍቅርና በትሕትና የታነፁ እንደነበሩ ሲያወጉ «በብሕትውና ዘመናቸው በደብረ ሊባኖስ የሰገዱበት የእጃቸው ፈለግ ሞፈር የሄደበት የበሬ ሜንቃ፣» እንደሚመስል ይናገራሉ።

ለወጣቶች የተለየ ፍቅርና ክብከቤ ያደርጉ እንደነበርና ከፍተኛ በሆነ አቀራረባቸው ቤተሰብ የሚያስረሱና ወጣቶችን «እናንተ የቤተክርስቲያን የስስት (የፍቅር) ልጆች ናችሁ፣ የሰንበት ተማሪዎች የቤተክርስቲያን ችግኞች ናችሁ» በማለት ወጣቱን ተስፋ በተለበሰ ሃይማኖታዊ ፍቅር ይከተኩቱ እንደነበር ከትምህርታቸው ገበታ የዘገነ አንድ ብልህ ወጣት በረጋ ስሜት ያወሳል።

በቅርብ የሚያውቋቸው መነከሰት፣ ወጣቶችና የሥጋ ዘመዶቻቸው ጭምር በአጽንኦት ደጋግመው የሚያነሱት አንድ ዐቢይ ጉዳይ አለ። ይኸውም በወገን፣ በወንዝ ልጅ፣ በዘመድ አለማመናቸው ነው። ስለዚህ ነገር አንድ ሌላ አበት ሲያነሱ «ከሁሉ ደስ የሚሉን በወገን፣ በዘመድ አለማመናቸው ነበር» ሲሉ፣ ሌላው ወጣት ደግሞ «አበ ጎርጎርዮስ ዘረኝነት የሌለቸው፣ በወገን የማያምኑ፣ ወንድማቸው እንኳን በሀገረ ስብከትህ ደብር ስጠኝ ቢለቸው ከሌሎቹ ለይተው ለእርሱ ሹመት ሊሰጡት እንደማይችሉ በጉባዔ በመነከሰት ፊት ያስታወቁ ፍጹም ሰው ናቸው» በማለት ይመሰክራል። የሥጋ ዘመዶቻቸውም፣ የርሰቸው ዘመድ መንፈሰዊ ዓለማቸውን የሚያራምድ ብቻ መሆኑን ሲያረጋግጡ፣ «የእርሰቸው ዘመድ ከመሆን በደ መሆን ይመረጣል፣» የሚል አበበል አለቸው።

አበ ጎርጎርዮስ የሃይማኖትና የታሪክ ተመራማሪም ነበሩ። በሕይወት ዘመናቸው ስምንት መጻሕፍት ደርሰዋል። እነርሱም፣

1) መሠረተ እምነት 2) የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ 3) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም

www.ethiopianorthodox.org

መድረክ 4) ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) 5) የስብከት ዘዴ (ኦርቶዶክሳዊ) 6) ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ 7) ሥርዓተ ኖሎት 8) ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ስስቱ ታትመው በጊዜው ተሠራጭተዋል።

መጻሕፍታቸው በምርምር ላይ የተመረኮዙ፣ ጥልቅ ምስጢር ያከተቱና በውብ ቃላትና አገላለጽ የተከሸኑ ናቸው። ይህ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ በስፋት የሚያወሳው መጽሐፍ ጠቃሚነቱ እጅግ የጎላ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘመነ ኦሪት፣ ኋላም የክርስትናን እምነት ከተቀበለችበት ወቅት አንስቶ እስከ ሁን የተጓዘችባቸውን ወጣ ገብ የታሪክ ሂደቶች ወለል አድርጎ የሚያሳይ፣ በስዕላዊ ቃላት የተከሏሉ ጥልቅ ሃሳቦችን ፍንትው አድርጉ የሚገልጽ ድንቅ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ የቤተ ክርስቲያናችንን መሠረተ እምነት (ዶግማ)፣ የታቦት፣ የሥዕልና የመስቀልን ክብር፣ የአማላጅነት ምስጢር፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊትና ሥሪት ግልጽ በሆነ በልተድበሰበሰ ሁኔታ አብራርቶ ያስረዳል። ኤኩሜኒዝም ወይም ዓለም ዓቀፍ የክርስቲያኖች ንቅናቄ ምንነት በውል የሚተነትንና ይልቁንም በንቅናቄው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ድርሻና ተሰትፎ በግልጽ የሚያቀርብ ነው። በ193 ገጾች ብቻ ታሪክን ከምስጢራት፣ መሠረተ እምነትን (ዶግማን) ከትውፊት ጨምቆና አስውበ ለማቅረብ መቻል የደራሲውን ችሎታ፣ ጥልቅ አስተሰሰብና፣ በሰል አመለካከት የሚመስክር ነው።

ከመጽሐፉ ጥቂት በመጥቀስ ያከተታቸውን ፍሬ አልማዞች ለማመለከት ያህል ፦ ልዩ አፍሪካዊ ስሜት ሲያንፀበርቁ «አፍሪካ የጨለማ ክፍለ ዓለም ተብላ ትጠራ እንጂ ብዙ ታሪከውያን ሰዎች ተፈጥረውበታል። ብዙ የሃይማኖት ሰዎችም ነበሩበት፣ ነገር ግን ኮጊዜ ብዘት፣ ከተተኪም መጥፋት የተነሳ ታሪኳ ሰርዶ እየለበሰ ሔደ፤ ሕዝቧም በልዩ ልዩ ቅኝ ገዥች በሀልና ሃይማኖት ስለተዋጠ ራሱን የማወቅ ችግር ገጠመው፣ ... ያን ጊዜ የበግ ቆዳ ለብሰ ወደ አፍሪካ የገባው ተኩላ የብዙ አፍሪካውያንን ደም እየመጠጠ

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ሁን አለ» ይላሉ። ኢትዮጵያን አስመልክተው ፡- «ኢትዮጵያ ነፃነቷንና አንድነትዋን አክብራ፣ አስከብራ የቆየች ለውጭ ወራሪም አልመች ያለችው በሃይማኖቷና በታሪክዋ እየተከለከለች ነው» ብለው ይገልፃሉ። ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ደግሞ «በጠቃላይ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መመኪያ አክሊላችን፣ ጥንተ መድኃኒታችን፣ የንጽሕና መሠረታችን ድንግል ማርያም መሆኗን ያውቃሉ» በማለት ያክላሉ። ከዚህም በቀር፣ «በቤተ ክርስቲያን የምእመናን ሕይወትና የመለእክት አገልግሎት የተሰናሰለ ነው። . . . እስከ ደም ጠብታ ድረስ ለክርስቶስ የመሰከሩ ሰማዕታት ቅዱሳን ናቸው፣» የሚለው አባባላቸው የቅዱሳንን ክብርና ምልጃቸውን በጉልህ ያስረዳል።

ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የበለፀገ እእምሮና መንፈሳዊ ብቃት የሠረፀው የዕውቀት ፍሬ ያማረና እጅጉን የሚማርክ ነው። ጠቢብ እምጠቢባን ንጉሥ ሰሎሞን «ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም» ይላል። ጥበብና ዕውቀት የሌለው ሕይወት ደግሞ በጨለማ የተሸፈነ ዱር ነው። አንድ ደገኛ መንፈሳዊ አባት «እንደ ኤልሳዕ ሥልጣን ቢኖረኝ እርሳቸውን (አባ ጎርጎርዮስን) በስመልስ ደስ ባለኝ» ነበር በማለት ለርሳቸው ያላቸውን ከፍተኛ አፍቅሮትና ክብር ይገልጻሉ።

ለሕያውነታቸው ሁነኛ ምስክር መጻሕፍታቸው ናቸው ማለት ይቻላል። አስተዋይ ልቡናና ለሃይማኖቱ ፍቅር ያለው ሰው ይህን መጽሐፍ ማንበብ ይኖርበታል። ምንነቱን ለማወቅና ጠልቆ ለመመራመር፣ ቀርቦ መዳሰስና አገላብጦ ማየት አለበት። ስለዚህም የአባ ጎርጎርዮስን ሕያውነት ምስጢር፣ የሃሳባቸውን ርቅቀትና ጥልቀት፣ ይልቁንም «ራስን የማወቅ ችግር» ግርደሽ ለመግፈፍ ይህን መጽሐፍ በጥሞና መዝለቅ መንፈሳዊ ዕርከታን ያስገኛል።

እሳታሚዎችና ወራሾቻቸው

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

አንድ ሕዝብ ወይም አንድ መንግሥት ራሱን ችሏል የሚባለው የፖለቲካና የኤኮኖሚ ነፃነት ሲኖረው ነው ፣ እየተባለ በዓለም ሸንጎ ይለፈፋል ፣ ይሰበካል ። ይሁን እንጅ ይህ ዕድል ለሁሉ አልተገኘም ። በማደግ ላይ ያሉ (ሦስተኛው ዓለም የሚባሉ) ብዙ አገሮች የፖለቲካ ነፃነት ቢኖራቸውም ፣ በኤኮኖሚ ደካሞች ስለሆኑ የጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አልቀረላቸውም ። ነፃነታቸውም ግማሽ ነው ። ይልቁንም ፤ ከአፍሪካዊነታቸው ጋር የማይስማማ ከቅኝ ገዥዎቻቸው የወረሱት ብዙ የባህል ውጥንቅጥ ስላለባቸው ፣ ከዚህ ሁሉ ለመላቀቅ በመጣር ላይ ይገኛሉ ፤ ምናልባትም አንድ ቀን ካሰቡት ሊደርሱ ይችሉ ይሆናል የሚል የተስፋ ድምፅ ይሰማል ።

ከዚህም ሁሉ ጋር ሲሆንም በቅድሚያ ሊታሰብበት የሚገባ ደግሞ የሃይማኖቱ ነፃነት ጉዳይ ነው ። አፍሪካ የጨለማ ክፍለ-ዓለም ተብላ ትጠራ እንጅ ብዙ ታሪካውያን ሰዎች ተፈጥረውባታል ። ብዙ የሃይማኖት ሰዎችም ነበሩባት ፣ ነገር ግን ከጊዜ ብዛት ከተተኪም መጥፋት የተነሣ ታሪኳ ሰርዶ እየለበሰ ሔደ ፤ ሕዝቧም በልዩ ልዩ ቅኝ ገዦች ባህልና ሃይማኖት ስለተዋጠ ራሱን የማወቅ ችግር ገጠመው ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አህጉር አንዷ ብትሆንም በሌሎቹ አፍሪካውያን ወንድሞቿ የደረሰው ግፍ አልደረሰባትም ። ከሦስት ሺህ ዓመታት የበለጠ የነፃነት ዕድሜ ይቆጠርላታል ። በዚህም የነፃነት ጉዞዋ ከባዕድ ያልተቀላቀለ አፍሪካዊ «ኢትዮጵያዊ» ባህል አላት ፤ በሃይማኖትም በኩል በዘመነ ኦሪት ብሉይ ኪዳንን እንደ ተቀበለች ሁሉ ሐዲስ ኪዳንንም ከሁሉ አስቀድማ ተቀብላለች ። ይህም ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን መላውን የአፍሪካ ሕዝቦች የሚያኮራ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራባውያን ቅኝ ገዥዎች አፍሪቃን እንደ ቅርጫ ሥጋ የተቀ ራመቷት ወንጌልን እናስተምራለን ብለው ማለትም የበግ ለምድለ ብሰው ነው ። ለምሳሌ ፥ ደቡባዊት አፍሪካን ይዘው ወገኖቻችንን የሚያሰቃዩ ነጮች ለመጀመሪያ የአፍሪካን መሬት የረገጡት በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ—ዘመን ሲሆን ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባል ነት የተለዩ የካልቢኒስት ሚሲዮናውያን ነበሩ ። ወደ አፍሪካ ለመግባት ምክንያት ያደረጉትም ሃይማኖት ማስተማርን ነበር ። ያን ጊዜ የበግ ቆዳ ለብሶ ወደ አፍሪካ የገባው ተኩላ የብዙ አፍሪካ ውያንን ደም እየመጠጠ እስካሁን አለ ። አሁንም ቢሆን አፍሪቃን በየአቅጣጫ ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሚጥሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ብዙዎቹም አፍሪቃውያን እየተሸጡና እየተለወጡ ወደ ባዕድ አገር በመወሰድ እነሱ በባዕድ አገር እየኖሩ አገራቸው የባዕድ መኖሪያ ሁኖ ቀርቷል ። ለምሳሌ ፥ ሰሜን አፍሪቃን ብንጠቅስ አባባሉን ያጐላዋል ።

ኢትዮጵያ ነፃነቷንና አንድነትዋን አክብራ ፥ አስከብራ የቆየች ለውጭ ወራሪም አልመች ያለችው በሃይማኖቷና በታሪኳ እየተከላከ ለች ነው ። ማንኛውም የሃይማኖት ሰባኪ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ምክንያት አልነበረውም ። ርግጥ ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ አደጋ ደርሶባ ታል ። ነገር ግን የደረሰባትን ሁሉ መከራ በትዕግሥት አሳልፋ ዛሬ ካለችበት ደርሳለች ። ዛሬ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ዓለም ቢኝዝ በራሱ ስም የሚጠራ ፥ በራሱ ትውፊትና ሃይማኖት የሚመራ ስለሆነ የበላይነት እንጅ ዝቅተኛነት አይሰማውም ። ይህች አገር ከክርስትና በፊትም ሆነ በክርስትና ዕድሜዋ በሥል ጣኔና በነፃነት ይልቁንም ደግሞ በፊደልና በሥነ ጽሑፍ ከጥንታው ያን ግብጾችና ከግሪኮች የምትወዳደር ናት ። እንዲያውም በሌላ ዓለም የጠፉ መጻሕፍት የሚገኙ በኢትዮጵያ ነው ። ለምሳሌ «የሄኖክ መጽሐፍ» ፥ «ኩፋሌ» (ኢዮቤልዩ የሚሉት) ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ዋናው ምክንያት የሚከተለው ነው ። በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ለትምህርት ወደ ውጭ አገር በሔድሁበት ጊዜ ብዙ ፈረንጆች እኔንም ሆነ ጓደኛዬን የሚጠይቁን «የቅብጥ» የኮፕት ቤተ ክርስቲያን መነኰሳት ናችሁ ወይ ? እያሉ ነበር ፥ በትምህርት ገበታችንም ላይ እንዳለን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን እያሉ ሲጠሯት በመስማቴ ኀዘን አደረብኝ። በመሠረቱ «ኮፕትቅብጥ» ግብፅ ወይም ምስር ማለት ሲሆን «ሂኩፕታህ» በጥንት የግብፅ ቋንቋ «ቤት» ማለት ነው ። ከሱ የወጣ ነው ። ግሪኮች ግን «ሀ» ፊደል ስለሌላቸው ፥ «ኤጊፕቶስ» ወይም ኮፕት ይሉታል ። እንግዲህ «ኮፕት» የሀገር ወይም የነገድ ስም ነው ማለት ነው ። ስለዚህ የግብፅ ክርስቲያኖች በሀገራቸው በነገዳቸው የኮፕት ወይም የቅብጥ ክርስቲያኖችም ይባላሉ ። ዐረቦችም እል አቅባጥ ይሏቸዋል ። የቃሉ ትክክለኛ ፍች ይህ ሆኖ ሳለ ፥ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የቅብጥ ቤተክርስቲያን ብሎ መሠየም ሀገረ ትውልድን የሚያቃውስ ዜግነትን የሚደመስስ መስሎ ይታያል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትን ብዙ ወርቅ እየከፈለች እያስመጣች ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት መቆየቷን አንክድም ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ፩፻፲፩ ጳጳሳት መጥተዋል ። በዚህ የረጅም ጊዜ ግንኙነት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በእኩልነት ተዐቅበ አብረው ኑረዋል ። የሃይማኖት ቀኖናቸውና ሥርዓታቸው አንድ ነው ። በዚህ ዓይነቱ ግንኙነት የግብፅና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆኑ ከነሱ ጋር የአርመን ፥ የሶርያና የህንድ አብያተ ክርስቲያናትም አንድነት አላቸው ። እነዚህም አምስቱ አብያተ ክርስቲያናት ተጠቃለው (Oriental Churches) የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በዶግማና በቀኖና አንድ ይሁኑ እንጂ በሀገረ ስብከት የየራሳቸው ድርሻ ስላላቸው ፤ ባንዱ ስም ሌላው አይጠራበትም ። ስለ

www.ethiopianorthodox.org

ዚህ በስማችን ሌላ እንዲጠራበት አንፈልግም ፤ እኛም በሌላ ስም መጠራት አንሻም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተቻቸው ስጦታዎች ብዙ ናቸው ፤ ከነዚህም ፦

ሀ—ሙሉ ትምህርት ፤
ለ—ፍጹም ቋንቋ ከነፊደሉ ፣
ሐ—ስነ ጽሑፍ ከነጠባዩ ፣ ከነሙያው ፣
መ—ኪነ ጥበብ በየዓይነቱ ፣
ሠ—ስነ ጥበብ በየመልኩ ፣
ረ—ታሪካዊና ጥንታዊ ቅርስ ፣
ሰ—እምነት ከነፍልስፍናው ፣
ሸ—ነፃነት ከነክብሩ ፣
ቀ—አንድነት ከነጀግንነቱ ፣
በ—አገር ከነድንበሩ ፣ ከነፍቅሩ ።፤
ተ—ስም ከነምልክቱ «ከነትርጉሙ» ፣ አሁንም ቢሆን ትውልዱ ጀግንነትን ፣ አገር ወዳድነትን ለታሪክ ፣ ለባህልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ በማስተማርና በማበረታታት ቤተ ክርስቲያን የበኩሏ ድርሻ አላት ።

አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋ ።

www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በጥንት የግብፃውያን ቋንቋ ፣ ጹንጥ ፣ ቶ ፣ ኔቶር፤ ኩሽ እየተባለች ትጠራ ነበር ። ጹንጥ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን 1. ካለው ፤ ፉጥ ከሚባለው ስም ጋር ይመሳሰላል ። ቶ ፣ ኔቶር ማለትም ሀገረ እግዚአብሔር ማለት ነው ይላሉ ። ሙሴ ብሉይ ኪዳንን ሲጽፍ ይህችኑ አገር «የኩሽ ምድር» እያለ የጻፈው በግብጽ ተወልዶ ያደገ እንደመሆኑ መጠን የግብጻውያንንም ቋንቋ ያውቅ ስለነበር ነው እንጅ ኩሽ የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል አለመሆኑ ታውቋል ። ኢትዮጵያ የኩሽ ምድር ለመባል የበቃችበት ዋናው ታሪካዊ ምክንያት ፦—የካም የመጀመሪያ ልጅ የኩሽ ዘሮች ስለ ሰፈሩባት ነው ። ይህችው አገር በሌላ አጠራር ፦— « የሳባ ምድር» አንዳንድ ጊዜም «አቢሲኒያ» እየተባለች ትጠራለች፣ ምናልባት ይህ ስያሜም የተገኘው እነዚሁ የኩሽ ልጆች ሳባና አቢስ ( ሰብታ ) ስለ ሰፈሩባት በስማቸው አስጠርተዋታል ማለት ነው። 2. በሳባ የሳባ ምድር ፣ በ[illegible]ታ ( በአቢስ ) አቢሲኒያ እየተባለች ለብዙ ዓመታት ቆይታለች ። ዐረቦች ግን አቢሲኒያ የሚለውን ስያሜ «ሐበሽ» ብለው ድብልቅ ውጥንቅጥ ለማለት ይቃጣሉ ። ነገር ግን ምንጭ የለውም ። ምዕራባውያን አሁንም አቢሲኒያ እያሉ ይጠሯታል ። በ፫ሺ፯፻ ዓመተ ከጌታ ልደት በፊት በየመን ይኖሩ የነበሩ ከነገደ ሴም የተከፈሉ ነገደ ዮቅጣን 3. በባብ እልመንደብ ( የመከራ በር ማለት ነው ) በኩል ገብተው ሰፈሩባት ። በዚች አገር ከሚኖሩ የኩሽ ዘሮች ጋር እየተጋቡና እየበረከቱ ሄዱ ። በዚያን ጊዜ ይህችን አገር ምድር አግዐዚት ፣ ምድረ—አግዐዝያን ፣ ነፃ አገር ነፃነት ያላቸው ሰዎች መኖሪያ ብለው ጠሯት ። በመጨረሻ ለዚች አገር የተሰጣት ስያሜ «ኢትዮጵያ» የሚል ነው ፤ በሀገራችን እንደሚተረከው—ኩሽ ሁለት ስም ነበረው ። ሁለተኛው ስሙ ፣

1. ዘፍጥ ፲፥፮
2. ዘፍጥ ፲፥፮
3. ዘፍጥ ፲፥፳፭—፴፪

www.ethiopianorthodox.org

«ኢትዮጲስ» ይባላል ። አቅኚዎቹ ባባታቸው ስም ይችን አገር «ኢትዮጵያ» ብለዋታል ፤ እነሱም ኢትዮጵያውያን ይባላሉ እየተ ባለ ይተረካል ። አንዳንዶች እንደሚሉት ደግሞ፡— «ኢትዮጵያ» የሚለው ቃል ከግሪክኛ የተወረሰ ነው ፣ «ኤቶስ» ዋዕይ ፣ «አፕ» ሲስ»—ገጽ አርአያ ማለት ነው ። እነዚህ ሁለት ቃላት ሲጣመሩ «ኤቴአፒያ» ወይም «ኤቲአፕስ» የሚል ቃል ይወጣል ፤ ይህም እንደ መጀመሪያው «ኤቲአፒያ» ቢል የአገሪቱን ቆላነት ያመለክ ታል ። ቆላ በረሃ ፣ የዋዕይ ፣ የትኩሳት አገር ማለት ነው ። እንደ ሁለተኛው «ኤቲአፕስ» ቢል ግን የሕዝቧን ምንነት ያመለክታል በዋዕየ ጸሐይ ፊቱ የበለዘ ፣ የጠቆረ የበረሃ የቆላ ሽንቅላ ማለት ነው ። በሆሜር መጽሐፍ ደግሞ ቀዩን ወይን ኢትዮጵያ ብሎት ስለሚገኝ፡— «ኢትዮጵያሦ» ማለት ቀይ የቀይ ዳማ ቀለም፤ ያለው ሕዝብ ማለት ነው ይላሉ ።

የኢትዮጵያውያን አባት ኩሽ በሞተ በ፪ሺ፬፻፶ ዓመት ፣ በ፪፻፬ ከጌታ ልደት በፊት ፤ መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደዕ ርዕ የመለሱ ሰባው ሊቃውንት ሙሴ ፡—« ኩሽ » እያለ በዕብራ ይስጡ ብሉይ ኪዳን የጻፈውን ኢትዮጵያ በሚል ቃል ለውጠውታል ።

ቢታሪክ ሰዎችና በፈላስፎች ዘንድ ስለ ኢትዮጵያ የተነገረውን በመጠኑ ለመግለጥ ያህል፡—ሆሜር የተባለው የግሪኮች ባለ ቅኔ ገጣሚ (ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብዙ ተናግሯል ። « የኢ ትዮጵያ ሕዝብ በጉልበት ኃያላን ፣ በውበት የተደነቁና በጠባይ ጭምቶች ፣ ትሕትናን የተሞሉ ናቸው ። ከዚህም የተነሣ ከግሪክ ፲፪ አማልክት አንዱ የመጀመሪያውና ትልቁ እንደ አባት የሚቆ ጠረው ዜውስ ኃያላኑን ኢትዮጵያውያኑን ለማየት ከነሱ ጋር ለመ ብላት ወደ ውቅያኖስ አካባቢ ወረደ ብሏል ።» ከ፬፻፶ ከጌታ ልደት በፊት የነበረው ምዕራባውያን የታሪክ አባት የሚሉት ሔሮዶቶስ

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ባነሣበት መጽሐፍ 4፥ ኢትዮጵያውያን ፤ በውበት ፣ በቁመትና በኃይል ከሰዎች ሁሉ የሚበልጡ ናቸው ብሏል ።

ኢትዮጵያ በታሪክ ሰዎችና ፤ በፈላስፎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስም የታወቀች አገር ናት ፤ የሕዝቧም ማንነት በቅዱስ መጽሐፍ (በብሉይ ኪዳን) ተገልጧል ። ሙሴ የስነ ፍጥረትን አቀማመጥ በተናገረበት በመጀመሪያው መጣፍ ኢትዮጵያ በዐባይ ወንዝ የተከበበች አገር መሆኗን ተናግሯል ። 5፥ መጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያን ሕዝብና ምድር ሁልጊዜ ከግብፅ ጋር ፤ በማያያዝ ይጽፋል ። 6፥ በጂኦግራፊ አቀማመጥም ኢትዮጵያ ከግብጽ ደቡብ የምትገኝ አገር መሆኑዋ በቅዱስ መጽሐፍ ተነግሯል ። 7፥ ሱዳንና ግብጽን ሲመግቡ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወንዞች ዐባይና ተከዜ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቁ ናቸው ። 8፥ ኢትዮጵያ በማዕድን የከበረች አገር እንደመሆኗ አልማዟና ወርቋም በዓለም ተደናቂ ነበር ። 9፥ ሕዝቧም በንግድ ሥራ በዓለም የታወቁ ነበሩ ። በንግዳቸውም በልጽገውና ተደስተው ይኖሩ ነበር ፤ 10፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ድንክ አጭር ፣ እንደ አዛሔል ቀውላላ ሳይሆኑ ልከኛ መጠነኛ ናቸው ። 11፥ መልካቸውም እንደ ቁራ ያልጠቆረ ፣ እንደ ለምጻም ያልተገነባ

4. ሔሮዶቶስ ፫ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ፳—፻፲፬ ፤
5. ዘፍጥ ፤ ፪—፲፫ ፤
6. መዝ ፤ ፷፰—፴፩ ፤ ኢሳ ፤ ፲፰—፩ ፤ ፪ ፤ ፯ ፤ ሕዝቅ ፤ ፴—፬ ፭ ፤ ዳን ፤ ፲፩—፵፫ ፤ ናሆ ፤ ፫—፱ ፤
7. ሕዝቅ ፤ ፳፱—፲ ፤ ሶፎ ፤ ፫—፲ ፤
8. ኢሳ ፤ ፲፰—፩ ፤ ኤር ፤ ፫—፲ ፤
9. ኢዮ ፤ ፳፰—፲፱ ፤
10. ኢሳ ፤ ፵፫—፫ ፤
11. ኢሳ ፤ ኤር ፤ ፵፭—፲፬ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ቦገ እሳ የሚመስል ፤ ጠይም ነው ። 12፡ የኢትዮጵያ ግዛት እጅግ በጣም ሰፊ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል ። በዜና መዋዕል ካልዕ 13፡ እንደ ተተረከው ኢትዮጵያውያን ዜራህ (ዝሪ) በሚባለው ንጉሣቸው እየተመሩ ዘምተው ምድረ ይሁዳን ከያዙ በኋላ በንጉሥ አሳ ድል ሁነዋል ። ኢትዮጵያውያን ፤በኃይላቸው ተመክተው በሚሠሩት ሥራ ነቢያት ይገሥጿቸው ነበር ፤ 14፡ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ መካከል ፤ያለውን የማያቋርጥ ፍቅርና ግንኙነት ሲገልጡ ደግሞ፡— «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች » እያሉ በግልጽ ተናግረዋል ።

---

12. ኤር ፤ ፲፫—፳፫ ፤
13. ፪ኛ ዜና መዋ ፤ ፲፬—፱ ፤ —፲፭ ፤ ፲፮—፰ ፤
14. ሶፍ ፤ ፫—፲፪ ፤

www.ethiopianorthodox.org

# ኢትዮጵያ በሃይማኖት

ከመጀመሪያው እስከዚህ ባጭሩ የገለጥነው የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ሀልውና ለማስተዋወቅ ፤ ያህል ነበር ። ከዚሁ በማያያዝ ከክርስትና በፊት ስለ ነበራት ሃይማኖት በመጠኑ እናወሳለን ።—ከክርስትና በፊት ስለኢትዮጵያ ሃይማኖት ስንናገር የአቅኒዎቿን የሕይወት ታሪክ መመርመር ሊኖርብን ነው ። ከላይ እንደ ገለጥነው ኢትዮጵያን ያቀኑ ሰዎች የመምለኬ እግዚአብሔር የኖህ የልጅ ልጅ (ሳባ) እና አቢስ (ሰብታ) ስለሆኑ የእያታ ቸውን አምላክ አንድ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር ቢባል እውነት ይመስላል ። ነገር ግን እምነቱ በትምህርት የተደገፈ ስላል ሆነ እና ኑሯቸውም ከፍልስጥኤም ውጭ ስለሆነ አንዳንድ የአምልኮ ባዕድ ልማዶች ሠርገው ሳይገቡ አልቀሩም ። ለምሳሌ ፤— ከጌታ ልደት በፊት ፩ሺህ ዓመት አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለዘንዶ ይገብሩ ፤ ዘንዶ ያመልኩ እንደ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ተጽፏል ። ይኸው የኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት እንደሚለው በኢትዮጵያ ሲመለክ የኖረውን ዘንዶ የገደለው የንግሥተ ሳባ አባት አንጋቦስ የተባለው ሰው ነው ። ይኸው ታሪክ ነገሥት ታሪኩን በመቀጠል ፤—ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷንና ከሰሎሞን ምኒልክ የሚባል ልጅ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ መውለዷን ፤ ልጇም አድጎ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጎብኝቶ ሲመለስ የሙሴን ጽላትና ካህናተ ኦሪትን ፤ እንዲሁም ኦያሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከሊቃቻቸው ጋር ይዞ እንደ መጣና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ብሉይ ኪዳን ወደ ግዕዝ ቋንቋ መመለሱን ፤ ባንድ አምላክ ማመንም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን በሰፊው ይተርካል ። ሌሎች የውጭ አገር ጸሐፊዎች ግን ያን ጊዜ በኢትዮጵያ አካባቢ በየመንና በግብጽ የነበረውን የአይሁድ ኃይልና የብሉይ ኪዳን እምነት መስፋፋት

www.ethiopianorthodox.org

በታሪክ ስለሚያውቁ ምናልባት ኢትዮጵያ ከነዚህ ከጐረቤቶቿ ጋር በነበራት የንግድና የሥልጣኔ ግንኙነት የብሉይ ኪዳንንም እምነት ከዚያው ከነሱ ሸምታው ይሆናል ብለው የግምት ሐሳባቸውን በጽሑፍ ገልጠዋል ።15። ከዚህም ሌላ በ፭፻፹፮ ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን በተቃጠለች ጊዜ እሥራኤላውያን ብዙዎቹ ተማረኩ።አንዳንዶቹም ነፍሴን አውጭኝ በማለት በየበረሀው ተሰደዱ ። ከነሱም ዮሐናን በሚባለው ሰው መሪነት ወደ ግብጽ የተሰደዱ ነበሩ ፤ ወደ ግብጽ ከተሰደዱት ውስጥ ደግሞ ተከፍለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር ይባላል ።፤በዚህ ጊዜ ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን ለማስፋፋትና ለማጠናከር አመች ነበር ማለት ነው ። በኤርምያስ ፵፬ እንደ ተጻፈው ከባቢሎን ምርኮም በፊት በግብፅ በዝርወት የሚኖሩ ብዙ አይሁድ ስለነበሩ ምናልባት በየምክንያቱ ወደዚች አገር እየገቡ ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን ሳያስፋፉ አልቀሩም ። ምንጩና የጸሐፊዎቹ ግምት የተለያየ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳንን እምነትና ባህል ለመቀበሏ ፣ በሐዋ ሥራ በምዕራፍ ስምንት የተመዘገበው ታሪክ ምስክር ሊሆን ይችላል ። ይህ ሰው ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ ሊጸልይ መሆኑ ተብራርቶ ስለተተረከና ሲያነበው የነበረው ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የታላቁን የኢሳይያስን መጽሐፍ ስለ ነበር ነው ።

ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበሏ የታሪክና የጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ሲሠራባቸው የሚኖሩ አያሌ ልማዶችና ባህሎች አሉ ፤ እነዚህ የብሉይ ኪዳን ልማዶችና ባህሎች ባሁኑ ጊዜ ፣ ማለት፡ በክርስትና ሃይማኖታችን ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆኑ እንደ ልማድ ሁነው የሚጠበቁ ናቸው ። እነዚህም ፦

ሀ/ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸውን እንስሳትና አዕዋፍ ዛሬም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አይመገቧቸውም ። ይህ በወንጌል ለሚያምን ሁሉ የተከለከለ አይደለም ፣ ከላይ እንደ ገለጥነው እኛ ግን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ መሠረት ነው ።

15. Adrian Fortescue, The Lesser Eastern Churches (London 1913) P. 294

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ ግዝረት ፤ በብሉይ ኪዳን ለማመን ምልክት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ መለያ ምልክታቸው ወይም ማኅተማቸው ጥምቀት ነው ። በሀገራችን ግን ከብሉይ ኪዳን በተወረሰው ልማድ ልጅ ሲወለድ ይገረዛል ፤ ግዝረቱ ግን የሕግ ሳይሆን የፈቃድ ነው ፤ ይህም ማለት በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ግዝረት ሕግ አይደለም ፤ ምዕመናን ልጆቻቸውን ቢያስገርዙም ባያስገርዙም የራሳቸው ፈቃድ ነው ፤ ማለት ነው ።

ለምሳሌ ያህል እነዚህን ሁለቱን ጠቀስን እንጂ ጠቅላላው በሕዝቡ የኑሮ ሥርዓትና ሃይማኖታዊ ስሜት ፤ በኀዘንና በደስታ ጊዜ ያለው ሁኔታ ፤ የበዓላት አከባበር ፤ የሴቶችና የሕፃናት ጌጣጌጥ ሁሉ ፤—የብሉይ ኪዳንን ሥርዓትና የሴማውያንን ሥልጣኔ የሚያሳይ ነው ። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የማኅሌት ሥርዓት ፤ የካህናቱ ልብስ — ተክህኖ ፤ ካባው ፤ ድርቡ ፤ ጸናጽሉ ፤ ከበሮው ፤ ኩፋሩ ፤ መጠምጠሚያው ፤ የታቦቱ ክብርና ሌላውም ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን አገር እንደ ነበረች ነው ። በሌሎች ከአረማዊነት በተመለሱ አገሮች በግሪክ ፤ በላቲንና በሌሎችም ይህ ሁሉ አይታወቅም ። አንዳንድ የአረማዊነት ጠባይ ግን ይታይባቸዋል ። የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያትና ሊቃውንትም በጥንት ስብከታቸው ሃይማኖትን የሚጐዱ ልማዶችን ብቻ እንጂ የሕዝቡን ጥቃቅን ልማድ ግን ማጥፋት አስፈላጊ መስሎ ስላላገኙት ብዙ አልታገሉለትም ። ስለዚህም ፤—ከብሉይ ኪዳን የተመለሱት እንደ ኢትዮጵያ ያሉት አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ሲኖሯቸው ፤ ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ በአረማዊነት በነበሩበት ጊዜ የሚበሏቸውን ይበላሉ ፤ ግዝረትም ምን እንደ ሆነ አያውቁም ።

በሃያኛው መቶ ዘመን በጥንት ቅርሶች ጥናት (Archeology) በኢትዮጵያ ውስጥ በየሀና በአድቤደራ በሌሎችም ሥፍራዎች አየሉ

www.ethiopianorthodox.org

.ጣኦት ምስሎችና የቤተ ጣኦት መገልገያ ዕቃዎች እየተቆፈሩ ወጥተዋል ፤ የጣኦት ቤተ መቅደሶችና የፀሐይና የጨረቃ ምስል የተቀረጸባቸው የመገበያያ መሐለቆች ተገኝተዋል ። አንዳንድ ባለታሪኮችም እንደሚሉት ፦— በአኩሱም ንጉሥ የነበረው አይዛና ( ኤዛና) ( ምናልባት የአብርሃና የአጽብሐ አባት ሳይሆን አይቀርም ) ራሱ የረቂቁ የማሕሬም ልጅ ነኝ እያለ ይጠራ ነበር ብለዋል ። «ማሕሬም» ግሪኮች «አሬስ» ይሉታል ። የጦር ፥ የጦረኞች ፥ የጀግኖች የአርበኞች አምላክ ማለት ነው ። ይኸው ማሕሬም ለብዙ ዘመን ለአኩሱም ንጉሣውያን ቤተ ሰብ ውቃቢ አምላክ ሳይሆን አልቀረም ። በኋላ ግን ይኸው አይዛና ኑብያን ድል አድርጎ ከያዘ በኋላ ምንም ዓይነት የጣኦት ስም አላነሣም ፤ ያገኘውም ድል የሰማይ አምላክ ድል እንጅ የሱ እንዳልነበረ ጽፏል ። «በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው በሰማይም በምድርም ለዘለዓለም የሚገዛ» ብሎ ድል የሰጠውን አምላክ ገልጧል ። 16. በአይዛና በመጀመሪያው የግዛት ዘመኑ የተሠሩ መሐለቆች የጣኦታት ምስል ፥ የግማሽ ጨረቃን የከዋክብት ምስል ነበረባቸው ፤ በኋላ የወጡት መሐለቆች ግን መስቀል ቅርጽ ታትሞባቸው ነበር ። እዚህ ላይ ባጭሩ የተገለጠው በጥንታዊ ቅርስ መርማሪዎችና በባለ ታሪኮች የተከሠተው የአረማውያን ኅብረ አምሳል የፊተኛውን ታሪክ አይንደውም ፤ በጣዖት ማምለክና የአሕዛብን ልማድ በማደጎ መውሰድ ከከነዓን ውጭ ይቅርና በከነዓንም ምድር የተለመደ ነበር ፤ ለልዑል እግዚአብሔር መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ሰሎሞንም እንኳ ለግብፃዊት ሚስቱ መስገጃ ቤተ ጣኦት አሠርቶ ነበር ። ይህን የመሰለ አድራጐት በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተነግሯል ። ነገር ግን የእሥራኤል እምነት የሚነገረው ባንድ አምላክ ግመናቸው ነው ፤ መታወቂያቸውም ይኸው ነው ። በኢትዮጵያም እንዲሁ ነው ፤ ብዙ የተለያዩ መሪዎች እየተነሱ ላመራር እንዲመቻቸው ሲሉ ብዙ ነገሮችን ቢለውጡና ቢያዳቅሉም ፥ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ታሪክ አይለውጠውም ። ስለ ኢትዮጵያ የሃይማኖትና የምራል

16 "Littman D. A. E. ir 32-34

www.ethiopianorthodox.org

ክብር የተናገረ ሶፎንያስ፡—ኢትዮጵያ በአንድ አምላክ የምታምን አገር መሆኗን ሲገልጥ፡—«እምነ ግዕዶተ አፍላገ ኢትዮጵያ ያመጽኡ ሊተ መሥዋዕተ» ፡—«ከኢትዮጵያ ወንዝ ወዲያ ግዶ የሚሰግዱልኝ የተበተኑት ልጆቼ መባዩን ይዘው ወደኔ ይመጣሉ » ብሏል ። ይህም አነጋገር ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄዶ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ በተጠመቀ ጊዜ ተፈጽሟል ። 17።

17. የሐዋ ፤ ሥራ ፰—፳፯—፵ ፤

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፩ ፤

# ኢትዮጵያና የክርስትና ሃይማኖት

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ፣ ወይም ኢትዮጵያና የክርስትና ሃይማኖት የተዋወቁት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣—18. ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ባጠመቀው ጊዜ ነው ይህም የሆነው ከጌታ ልደት በኋላ በ፴፬ ዓ.ም. ነው ። ኢትዮጵያዊው ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ አዲሱን ፣ ሃይማኖቱን ለሀገሩ ሕዝብ አስተምሯል ። ወደፊት እንደምናየው ። መጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ሥርዓተ ክርስትናን በትምህርት ያጠናከረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በመሠረተው ነው ። ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመጀመሪያ የጻፉ ሊቃውንት ፣—፩/ ሩፊኖስ 19. ፪/ ቴዎዶሬጦስ 20. ፫/ሶቅራጥስ 21. ፬/ሶዞሜኖስ 22. እነዚህ ናቸው ። ሩፊኖስና ሶቅራጥስ 23. ማቴዎስ መጥቶ አስተምሯል ብለዋል ከ፫፻፵፯—፬፻፲፱ ዓ. ም. የነበረው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ጀሮም (ኢየሮኒሞስ) የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ እንድርያስ ነው ይላል ። 24. ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ ቶማስ ነው ይላል ። 25. የእስክንድርያው አርጌንስ ግን ወደ ኢትዮጵያ ምንም ሐዋርያ እንዳልተላከ ነገር ግን ወደ ጥቂት የአፍሪካ ሕዝብ ብቻ የወንጌል መልእክት መድረሱን ይናገራል ። 26. «የቤተ ክርስቲያን

---

18. የሐዋ ፤ ሥራ ፰—፳፮ ፤
19. Hist Eccl. i9 (p.L.xxi 478 - 80)
20. Hist Eccl. i22 (P.G.ixxxii 969 - 72)
21. Hist Eccl. i.19 (P.G. ixvii 125 - 30)
22. Hist Eccl. i.24 (ib. 995 - 1000)
23. Rufinus Eccl. Hist. x.9 and Socrates i.19
24. Cot. Script. i.262
25. Hom. 31
26. Origenis Opera Omnia, ed Lommatzsch, 1834, iv.27

www.ethiopianorthodox.org

ታሪክ አባት» የሚባለው አውሳብዮስ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ በም ዕራፍ ፰ የተጻፈውን መሠረት አድርጎ ፣—«ሕፅው ለወገኖቹ ሐዋ ርያ ሆነ ፣» የኢትዮጵያ ሐዋርያ እሱ ነው ። ይለዋል ። 27። እነዚህ ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ታሪክ ጸሐፊዎች «ኢትዮጵያ» ስለሚ ለው ቃል የተለያዩ ስሞችን ስላነሱ የነሱ አለመግናኘት ሳይሆን ምናልባት በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ በሚል ስያሜ የሚጠሩ ሌሎች አገሮች ስለ ነበሩ የየበኩላቸውን ጽፈዋል ፤ ለዚሁም ዋናው መረጃ ሔሮዶቶስ የተባለው ግሪካዊ ታሪክ ጸሐፊ ያሰፈረው ነው ። በእሱ አመለካከት ፣—ከሊብያ ደቡብ የሚገኘውን አገር ሁሉ ኢትዮጵያ በሚል ስያሜ ይጠራው ነበር ። 28። አንዳንድ ጊዜም ኑብያን ኢትዮ ጵያ ይላት ነበር ። 29። ሕንድና የዐረብ አገሮችም በዚህ ስም ያደና ግሩ ነበርና ፣—የሚሉ ባለ ታሪኮች አሉ ። እኛ ግን በዘፍጥረት ፪ ፣ ፲፫ የተጻፈውን ፣—«የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው እር ሱም የኢትዮጵያን ምድር ይከባል » የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ይዘን ግዮንም የዐባይ ወንዝ ነው ፤ ኢትዮጵያም አሁን ያለንባት አገራችን ናት ። ብዙ ሐዋርያት መጥተው ቢያስተምሩም የሐዋርያት ተልዕኳቸው ዓለምን ዞረው ለማስተማር ስለሆነ ፣ኢት ዮጵያም ከዓለም የተለየች ስላልሆነች ይልቁንም የክርስትና ሃይማ ኖት ለተወለደበት አገር በጣም ቅርብ ስለሆነች ፣ ኢትዮጵያን መጥ ተው ያስተማሩ ሐዋርያት ቁጥር በዛ ሊባል አይቻልም ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎችም ስለ ሌላ ኢትዮጵያ አልጣሩም ። ኢትዮጵያችን ክርስትናን የተቀበለችው በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ይሁን እንጅ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት በአ ራተኛው ምዕት ዓመት ነው ። ይህንን ዕድል ያገኘችበትንም ምክ ንያት ሩፊኖስ እንደሚከተለው ይተርከዋል ። እሱ እንደሚለው ሜሮጵዮስ የተባለ አንድ ነጋዴ (ፈላስፋ) ከሁለት ወጣት ዘመዶቹ ጋር ሁኖ ከጢሮስ ወደ ሕንድ አቅጣጫ በጀልባ ተጓዘ ። 30። ከነዚህ

27. Eu. Church history, 11.i,13
28. Herod iv. 197
29. Herod ii. 146
30. Historica Ecclesiastica P.L. xxi. 478 - 80

www.ethiopianorthodox.org

ሁለት ወጣቶች ትልቁ ፍሬምናጦስ ትንሹ ደግሞ ኤዴስዮስ ይባል ነበር ። የኤዴስዮስ ሁለተኛ ስሙ (ሲድራኮስ) ነው ።31፥ ሁለቱም ክርስቲያኖች ነበሩ በጉዞዋቸው ጊዜ በአፍሪካ የባሕር ጠረፍ በቀይ ባሕር ወደብ ውሀ ለመጠጣት አገር ለማየት ከጀልባቸው ወርደው ጀልባቸውንም ከወደብ አስጠግተው ሳሉ በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በጀልባዪቱና በተሳፋሪዎቹ ላይ አደጋ ጥለው ዕቃቸውን ዘረፉቸው ። ሜሮጵዮስንና የጀልባዪቱንም ቀዛፊዎች እዚያው ገደሏቸው ። እንደ አጋጣሚ ሁኖ ሁለቱ ወጣቶች ብቻ ከመገደል አምልጠው ባንድ ዛፍ ሥር ተጠግተው ሲጸልዩና መጽሐፍ ሲያነቡ ተገኙ ፤ ያገኙዋቸውም ሰዎች በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳያደርሱ በፈረስ አንገት በጦር እንደበት የተማረኩ ሰዎች አመጣንልህ ብለው ለንጉሣቸው ሰጡት ። እነዚህ ሁለት ወጣቶች እየዋሉ እያደሩ በቤተ መንግሥቱ (በአኩሱም ቤተ መንግሥት) ተወዳጅነትና ታማኝነትን አገኙ ። ንጉሡ አይዛና ፥ የአብርሃና አጽብሐ አባት ነበር ። ኤዴስዮስን ጋሻ ጃግሬ አደረገው ፤ ፍሬምናጦስን ግን በጅሮንድ አድርጐ ሾመው ፥ ንጉሡ ሊሞት በተቃረበበት ጊዜ ልጆቹ ገና አካለ መጠን አላደረሱም ነበርና መንግሥቱን በሞግዚትነት እንድትይዝ ለእቴጌዪቱ አደራ ሲል ሁለቱን ሶርያውያን ምርኮኞች ሑር ለቀቃቸው ። ነገር ግን በእቴጌዪቱ ልመና ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው ቀርቶ ልጆችዋ እስኪያድጉ ድረስ በአስተዳደር በኩል ሲመክሯት ቆዩ ። ፍሬምናጦስ በአኩሱም በነበረበት ጊዜ የቤተ መንግሥቱ አማካሪ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተሰበከው የክርስትና ሃይማኖት በሚገባ የሚስፋፋበትን መንገድ ይፈልግ ነበር ። ያን ጊዜ የነበሩት የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሃይማኖት ብቻ እንጅ ክህነት ፥ ቁርባንና የመሳሰሉትም የክርስቲያን ሥርዓቶች አልነበራቸውምና ። ልዑካኑ አካለ መጠን አድርሰው ያባታቸውን መንግሥት ሲረከቡ ፥—ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ ተመልሶ ካህን ሆነ ፥ ይህንን ታሪክ ለሩፊኖስ የነገረውም በጢሮስ ተገናኝተው መሆኑን ሩፊኖስ በታሪኩ መግቢያ ላይ አውስቶታል ። ፍሬ

---

31. A. Fortescue, the Lesser Eastern Chur ches, London, 1913. P. 295

www.ethiopianorthodox.org

ምናጦስ ግን ስለ ጵጵስና ጉዳይ በቅርብ ከምትገኘው ከእስክንድ ርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲወያይ በአኩሱም ቤተ መንግሥት ተልኮ ሄደ ። 32. ፍሬምናጦስ እስክንድርያ እንደ ደረሰ የእስክንድ ርያን ቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖች አላገኛቸውም ፤ ይህም የሆ ነበት ምክንያት እንደሚታወቀው ያን ጊዜ በኒቅያ ጉባኤ ስለ ነበሩ ነው ። 33. ፍሬምናጦስ እነሱ እስኪመለሱ ድረስ አንድ ዓመት በእ ስክንድርያ ቆይቷል ። በኒቅያ ጉባኤ እለእስክንድሮስና አትናቴዎስ አርዮስን ድል ነስተው ከተመለሱ በኋላ ጉዳዩን ለነሱ አቅርቦ በመ ጠናት ላይ እንዳለ አንድ ሁለት ዓመት ወሰዷል ። በ፫፻፳፰ ዓ. ም. ፓትሪያርክ እለእስክንድሮስ አርፎ በመንበሩ አትናቴዎስ ተተካ ፤ በዚህ ጊዜ ፍሬ ምናጦስ የተላከበትን ጉዳይ ለአትናቴዎስ አቀረበ እሱም በዚህ ተደስቶ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ቋንቋቸውንና ባህላ ቸውን የሚያውቅ ሌላ ባለመገኘቱ ራሱን ፍሬምናጦስን፡—«ኤጲስ ቆጶስ ዘአኩሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ» ብሎ በቅብዓትና በአንብሮተ እድ ሹሞ ላከው ። ፍሬምናጦስም ጵጵስናውን ተቀብሎ ከተመለሰ በኋላ በኢትዮጵያ የክርስትናን ሥርዓት አስፋፍቶ ሰበከ ። የክህነት ንና የቁርባንንም ሕግ አጠናከረ ። በኢትዮጵያ ግዛት በሙሉ የወ ንጌልን ትምህርት ለማዳረስ የሚረዱት ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት ፣ ከዕብራይስጥና ከዕርዕ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መለሰ ። የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ የለወ ጠውና አዲሱንም ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብ ዘዴ የፈጠረ እሱ ነው ። በዚህ አኳኋን በ፫፻፴ ዓ-ም- ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔ ራዊ ሃይማኖት ሆነ ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያን አገር እንደ ሆነች ታወቀች ። ሩፊኖስ ግን አሥራ ሰባቱን ዓመት ቀንሶ ፣ ፍሬ ምናጦስ ጳጳስ የሆነው በ፫፻፵፮ ዓ.ም. ነው ይላል ። 34. የናናውያን ደግሞ ፣ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ፣ የታላቁ ቆስጠን ጢኖስ እናት ዕሌኒ ወንጌልን እንዲያስተምር ልካው ነው እያሉ ይተርካሉ ። ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪ

32. ፫፻፳፭ ዓ. ም.
33. Ibid. P. 324 - 26
34. Rufinus loc. cit. i. ix

www.ethiopianorthodox.org

ያው ጳጳስ ፍሬምናጦስ ነው ፤ የሾመውም ፳ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አትናቴዎስ ነው ። ፍሬምናጦስ በኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ፦«አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን» ይባላል ። ይህም ለአንድ ሐዋርያ የሚገባ ስም ነው ። ብርሃን ወንጌልን በመላው ኢትዮጵያ እንዲዳረስ ሐዋርያዊ ተጋድሎ ያደረገ ሰላማዊ አባት ነውና ። ቆስጠንጢኖስ ከሞተ በኋላ (ከ፫፻፴፯—፫፷፩) በቍስጥንጥንያ ነግሦ የነበረው ዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ የአርዮስን ሀሳብ ተቀብሎ የኒቅያን ጉባኤ አክብረው የተቀበሉትን አርቶዶክሳውያንን ለማጥፋት ሌት ከቀን ይጥር በነበረበት ጊዜ የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስን ከመንበሩ አሳድዶት ነበር ። በዚህም ጊዜ ፤ አትናቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ ሹሞ የላከውን ፍሬምናጦስን አባረው በየመን የነበረውን አርዮሳዊ ኤጲስ ቆጶስ ቴዎፍሎስን (ትውልዱ ሕንዳዊ ነበር) እንዲቀበሉ ወደ አኩሱም ነገሥታት ወደ አብርሃና አጽብሐ መልእክት ላከ ። የመልእክቱም ሙሉ ቃል እንዲህ የሚል ነበር ።—«ቪክቶሪዮስ ኮንስታንስዮስ ማክሲሙስ አውግስጦስ ለአብርሃና አጽብሐ (አይዛናና ሳዛና) እግዚአብሔር የሰጠን ትምህርትና ማስተዋል ለሁሉም እውነትንና ጽድቅን ለሚፈልግ ሁሉ እንዲዳረስ ስመኝ በናንተና በሮማውያንም ቤተ ክርስቲያን መካከል አንድነት እንዲኖር ይገባል ፤ ከሹመቱ የተሻረው ብዙ ሺ ክስ ቀርቦበት መመለስ ያቃተው ፤ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ሹሞ ልኳልና በቶሎ ፍሬምናጦስን መልሳችሁ ለተከበረው ጳጳስ ለጊዮርጊስ በዚያም ላሉት ቀሳውስት ላኩትና የርሱን ነገር እነሱ ይጨርሱት ።

የአባ አትናቴዎስን ሥራ ግን ከናንተ በቀር አገር ሁሉ አውቆ አላስጠጋ ስላለው በናንተ ዘንድ መጠጊያ ይፈልጋል ። ፍሬምናጦስ ከልቡ ጳጳስ መሆን ከፈለገ የሕይወቱን ታሪክ ለቀሳውስቱ ገልጦ የቤተ ክህነትን ሕግና ሥርዓት በደንብ ፈጻሚ መሆኑ በነዚያ ዘንድ ከታወቀ ተመልሶ እንደገና ጳጳስ መሆን ይችላል ። ያለዚያ እንደ አትናቴዎስ እንደ ለፍላፊው ፤ ከሕግ የሚሸሽ ሆኖ ወደ አክሱም የመጣና ሹመቱን የያዘ እንደሆነ እናንተንም ቤተ ክርስቲያናችሁንም እንዳያበላሽና ሁከት እንዳይፈጥር ያስፈልጋል ። እኔ

www.ethiopianorthodox.org

ግን እንደሚመስለኝ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ተመልሶ በጣም ከከበረው ጳጳስ ከጊዮርጊስና ከፍ ካሉት ሊቃውንት ተገናኝቶ የቤተ ክህነትን ሕግና ትምህርት ከተረዳ በኋላ ወደ ጵጵስና ሥፍራው ሊመለስ ይችላል ።» የሚል ነበር ። 35. አብርሃና አጽብሐ ግን ለኒቅያ ጉባኤ ውሳኔና ለአትናቴዎስ ትምህርት ያላቸውን ድጋፍ በመግለጥ የዚህን መልእክት አሳብ አልተቀበሉትም ። ፍሬ ምናጦስም ያላንዳች ችግር ሐዋርያዊ ተልዕኮውን ሲያከናውን ቆይቶ አረፈ ። ዕረፍቱም በሐምሌ ፳፮ ቀን ነው ።!

ከሱም ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ጵጵስና ከሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር እኩል ሆነች ። ብዙ ክርስቲያኖችና መምህራንም በሌላው ዓለም ስቃይ ሲጸናባቸው ጥግ ለመሻት የሚመጡት ወደ ኢትዮጵያ ነበር ። ለምሳሌም ያህል ፤ በጉባኤ ኤፌሶን የተወገዘው ኋላም በጉባኤ ኬልቄዶን መለካውያን መልኩን በንባብ ሸፍነው የተቀበሉትን የሁለት ባሕርይ እምነት እንቀበልም በማለታቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ የጸናባቸው ዘጠኝ መነኮሳት ከሶርያና ከታናሽ እስያ ተሰደው በ፬፻፹ ዓ·ም· በመንግሥተ አልአሜዳ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል ። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝበ ክርስቲያኑም ከአባት በወረደው ደግነቱና እንግዳ ተቀባይነቱ በፍቅር ስለ ተቀበላቸው እነሱም ኢትጵያን እንደ ተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን አስፋፍተዋል ። እስከ ዛሬ ድረስ በስማቸው የሚጠሩትንና ሌሎችንም ገዳማት መሥርተዋል ። ከዚህም ሁሉ ጋር የሀገሪቱን የግዕዝ ቋንቋ ተምረው አያሌ መጻሕፍትን ከሱርስትና ከዕርዕ መልሰዋል ። በዚህ አኳኋን ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን ፈጽመው ስላረፉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች ። ስማቸው ገዳማቸውና የዕረፍት ቀናቸው እንደሚከተለው ነው ።

---

35. STORIA D'ETIOPIA, C. ROSSINI, Page 149 - 151

www.ethiopianorthodox.org

| ስም | ገዳም | የዕረፍት ቀን |
|---|---|---|
| አባ አሌፍ | ብኅዛን (አህስአ) | መጋቢት ፲፩ ቀን |
| » አረጋዊ | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት ፲፬ ቀን |
| » አፍጼ | የሃ (የሐ) | ግንቦት ፲፪ ቀን |
| » ሊቃኖስ | ደብረ ቆናጽል | ኅዳር ፳፩ ቀን |
| » ገሪማ | መደራ | ሰኔ ፲፯ ቀን |
| » ጉባ | ገርዓልታ | ግንቦት ፳፱ ቀን |
| » ይምዓታ | ገርርዓልታ | ጥቅምት ፳፫ ቀን |
| » ጰንጠሌዎን | አክሱም አጠገብ | ጥቅምት ፯ ቀን |
| » ጽሕማ | ፅ‚ዴንያ | ጥር ፲፯ ቀን |

በፊት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተሰበከችልን ፡ በኋላም በፍሬምናጦስ (አባ ከሣቴ ብርሃን) እና በእነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳን የጸናችልን ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትባላለች ። ኦርቶዶክስ ቃሉ የዕርዕ ሲሆን ፡ ጥምር ቃል ነው ። —«ኦርቶስ» ቅጽል ነው ፤ ቀ ርትዕት ፡ ቀጥ ያለ ቀጥተኛ ማለት ነው ። «ዶክስ» ደግሞ «ዶኮ» ካለው ግሥ የወጣ ሲሆን ፡ ፍቹ ማሰብ መገመት ፡ መተርጐም ማመን ማለት ነው ። «ኦርቶዶክስ» እንደ አንድ ስም ሁኖ ተጠ ቃሎ ሲፈታ ቀጥተኛ አሳብ ፡ ቀጥተኛ አስተያየት ፡ በሃይማኖ ትም ርትዕት ሃይማኖት ፡ ቀጥተኛ ሃይማኖት ፡ ማለት ነው ። ኦርቶዶክስ የሚለው ስያሜ በቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በ፫፻፳፭ ዓ.ም. በኒ ቅያ በተደረገው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ነው ። ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በኒቅያ ተሰብስበው አርዮስን ረትተው ሃይማኖታቸውን አጽንተው በጸሎተ ሃይማኖት ረቂቅ ላይ ተስማም ተው ሲለያዩ ሃይማኖታቸውን ኦርቶዶክስ ብለዋታል ። የአርዮስን አሳብ የተከተሉት ግን አርዮሳውያን ይባላሉ ። ኦርቶዶክስ ፡ ክር ስቲያኖች የመሠረቱት ቃል እንደመሆኑ መጠን የሚቀጠለውም ለክርስትና ሃይማኖት ብቻ ነው ። በምዕራቡ ዓለም ያሉ ብዙ ጸሐ ፊዎችና ተናጋሪዎች ግን ይህንን ቃል ባልሆነ መንገድ ይጠቀሙበ ታል ። ከላይ እንደ ተገለጠው ቃሉ የተፈጠረው ምንም ለውጥ

www.ethiopianorthodox.org

ወይም መሻሻል ያልተቀላቀለበትን የክርስትናን ሃይማኖት ለግመ ልከት ሲሆን ፥ ዛሬ ግን በፖለቲካም ሆነ በሃይማኖት የሚሰበከውን አጥብቆ የያዘውን ኦርቶዶክስ ይሉታል ። ለምሳሌ፥—በአይሁዳዊ ሕግ የጸናውን ኦርቶዶክስ አይሁዳዊ ይሉታል ። በእስልምናም ሃይ ማኖት ሕግና ሥነ ሥርዓት ጠብቆ የሚኖረውን ኦርቶዶክስ እስ ላም ይሉታል ። የቃሉ ፍች የሚያሳየው ግን የእምነቱን ዓይነትና ጥራት እንጅ የአማኙን ስሜት አይደለም ። «ተዋሕዶ» ለምሥጢረ ሥላሴም ፥ ለምሥጢረ ሥጋዌም የሚያገለግል ቃል ነው ። ነገር ግን ይህ ቃል በዛ ብሎ የሚታየው በምሥጢረ ሥጋዌ ነው ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይህ ቃል በርከት ብሎ የታየው ከጉባኤ ኤፌሶን (፬፻፴፩ ዓ.ም.) ውሳኔ በኋላ ነው ።.በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እን ደሚታወቀው <u>የቍስጥንጥንያ</u> ሊቀ ጳጳስ የነበረው <u>ንስጥሮስ</u> ፥— «አምላክ በሰው አደረ» (ይኸውም በቅዱሳንና በጻድቃን እንደሚያ ድር ማለት ነው) ብሎ በይፋ ባስተማረ ጊዜ ፪፻ ሊቃውንት በቅ ዱስ <u>ቄርሎስ</u> ሊቀ መንበርነት በኤፌሶን ጉባኤ አድርገው ንስጥሮ ስን ረትተው፥— «አምላክ በሰው አደረ» የሚለውን የንስጥሮስ ትም ህርት ሠርዘው ወንጌላዊው፥—«ቃል ሥጋ ኮነ» ባለው መሠረት ቃል ሥጋ ኾነ ፤ ይኸውም እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ነው ብለው ወስነዋል ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ «ተዋሕዶ» የሚለው ቃል ከምሥ ጢረ ሥላሴ ይልቅ በምሥጢረ ሥጋዌ እየበረከተ ሄዷል ። የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኒቅያ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ፥ በኤፌሶን ፪፻ ው ሊቃውንት የወሰኑትን ትምህርተ ሃይማኖት አክብራ ጠንቅቃ ስለያዘች «ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ» ትባላለች ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፱ ፤

# ከካሌብ – ዮዲት

ከፀ̄ቱ ቅዱሳን መምጣት በኋላ የአክሱም ቤተ መንግሥትና መላው የኢትዮጵያ ግዛት በክርስትና ሃይማኖት ትምህርትና ስብከት ተዳርሶ ነበር ። 36. በዚሁ ጊዜ በደቡብ የዐረብ ግዛት ሁሉ ክርስትና ተዳርሶ ስለነበር በኢትዮጵያና በዓረብ አገሮች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ነበር ፤ ነገር ግን በያትሪብ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ በክርስቲያን ዐረቦች ላይ ጥላቻ ስለነበራቸው ባላቸው ሁሉ ኃይል በመጠቀም የመንን ይዘው በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በቁ ። በየጊዜውም በሚደርስባቸው ጦርና ወረራ ከፍልስጥኤም እየፈለሱ ወደ ደቡብ ዐረብ የሚሔዱ አያሌ አይሁድ ነበሩ ፤ ይልቁንም በ፸ ዓ·ም ጥጦስ በኢየሩሳሌም የነበረውን መቅደስ ባቃጠለውና ኢየሩሳሌምንም ባጠፋት ጊዜ ብዙ አይሁድ እየሸሹ ወደ የመን ፈልሰው ገብተዋል ። በዚያም ከኖሩ ዘንድ ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን በማጠናከር ንጉሥም አንግሠው እንደነበር ይነገራል ። እነዚህ አይሁድ በአካባቢያቸው በሚኖሩ የናግራን ክርስቲያኖች ላይ የጥላቻ ስሜት ነበራቸው ። ከ፬፻፹፭—፭፻፲፭ ዓ.ም. የነበረው በየመን የአይሁድ ንጉሥ በኛ ጽሑፍ ፊንሐስ የላቲን የዐረብና የፋርስ ጽሑፍ—ድሁ ኖባስ ፥ ዱና ፥ አን—ዳምና ዱናስ ይለዋል ። በደቡብ ዐረብ በናግራን የሚገኙትን ክርስቲያኖች ብዙ ሥቃይ አጸናባቸው ። 37. ይህን የክርስቲያኖች ዕልቂት ዜና ከሞት የሸሹ የናግራን ምዕመናን ያን ጊዜ ክርስቲያኖች በበዙበት በቍስጥንጥንያ ፥ በእስክንድርያና በአክሱም ለሚገኙ የሃይማኖት ወንድሞቻቸው አሰሙ ። ይህ የዕልቂት ዜና የኢትዮጵያን ክርስቲያኖችና የአክሱምን ቤተ መንግሥት በጣም አሳዘነ ። በዘመኑ የነበሩት

---

36. P. G. lxxxviii 169

37. [illegible] ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ካሌብም ከልብ አዝነው እነዚህን ግፍ የጸና ባቸው የናግራን ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚረዱ ይገልጽላቸው ዘንድ ወደ ፈጣሪያቸው ጸሎትና ምሕላ ያዙ ፡፡ የቊስጥንጥንያው ንጉሥ ዮስጢኖስም ዕልቂቱ ያሳዘነው መሆኑን ገልጦ ለእስክንድር ያው ሊቀ ጳጳስ ለአባ ጢሞቴዎስ ላከባቸው ፡፡ አባ ጢሞቴዎስ ለአ ክሱም ቤተ መንግሥት የሃይማኖት አባት እንደመሆናቸው መጠን አክሱምም ለየመን ቅርብ ስለሆነች ወደ የመን ተሻግረው ክርስቲ ያኖቹን ከዕልቂት እንዲያድናቸው የሚል መልእክት ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት ለአጼ ካሌብ ላኩ ፤ አግሌቅን አጥፋ ብሎ ሳሙ ኤል ሳውልን እንዳዘዘው ማለት ነው ፡፡ አጼ ካሌብም በየመን የሚ ደረገውን የክርስቲያኖች ዕልቂት ቀደም ብለው ሰምተው ወደ አምላካቸውም ጥበቡን እንዲገልጥላቸው ምህላ ይዘው ስለነበር የአ ቡነ ጢሞቴዎስ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መልእክት በደረሳ ቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተረድተው በዘመናቸው በነበረው የጦር ዝግጅት ተዘጋጅተው ሠራዊታቸውን ክተት ብለው መርከቦቻቸውን ጭነው በአዱሊስ የባሕር በር ወደ የመን ተሻገሩ ፡፡

ከዚያም ግፈኛውን ፊንሐስ ከነሠራዊቱ ደምስሰው የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ጠግነው ሌሎች አዲሶችም ሠርተው ከፊን ሐስ ሰይፍ የተረፉትን ምዕመናንም አጽናንተውና አረጋግተው ከአ ሥር ሺ ሠራዊት ጋር የሚጠብቃቸው አብርሃ የሚባል ብልህ ሰው መርጠው ሾመውላቸው ፤ ወደ አክሱም ተመለሱ ፤ ከየመን ከተ መለሱ በኋላ ብዙ ጊዜ በመንግሥትነት ሥልጣን አልቆዩም ፤ መን ግሥታቸውን ለልጃቸው ለቀው መንነው ልብሰ ምንኩስና ለብ ሰው አንዲት መንቀል (የውሃ መጠጫ እና አንዲት ምንጣፍ) ይዘው ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ ሲል በሚገኘው በአባ ጰንጠሌዎን ገዳም ባለው ዋሻ ገብተው ተቀመጡ ፡፡ ቤተ መንግሥታቸውን ለቀው በመነኑበት ሰዓት ዋጋው እጅግ የሆነ የንጉሡበትን ዘውዳቸ ውን በጌታ መቃብር በጐልጐታ እንዲሰቀልላቸው ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት ፡፡ በምናኔ ለ፲፪ ዓመታት ከተጋደሉ በኋላ በ፭፻፴፮ ዓ.ም. ግንቦት ፳ ቀን አረፉ ፡፡ ዕድሜያቸውም ፸ ዓመት ነበር ፡፡ በክርስ ቲያኖች ላይ በሀገረ ናግራን የተነግሠውን ዕልቂት ለማስወገድ ዘም

www.ethiopianorthodox.org

ተው ክርስቲያኖችን ነፃ ያወጡና በምንኩስናም ሕይወት የአበውን አሠረ ጽድቅ ፈጽመው ያረፉ ደገኛ ጻድቅ ንጉሥ ስለ ነበሩ አጼ ካሌብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸው ከጻድ ቃን ነው ። የናግራንን ክርስቲያኖች ስለ ማዳናቸው ፣ ዓለምን ስለ መናቃቸውና ዘውዳቸውንም ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መላካቸው የሚ ገልጥ በኢትዮጵያዊ ሊቅ የተደረሰላቸው ዐርኬ ፦

ሰላም ለካሌብ ትእምርተ ኀድገታ ለብዕሉ ፤
እንተ ፈነወ አክሊሉ በኢየሩሳሌም ይስቅሉ ፣
ዘንቱ ኃያል ኢይትመካህ በኃይሉ ፣
እመ በእዴሁ ሠራዊተ ሳባ ተቀትሉ ፣
ዘእንበለ (ያ) ይትርፍ አሐዱ እምኔሆሙ ።

አጼ ካሌብን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታከብራቸው ሌላ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም በጥቅምት ( October ) ፳፯ ቀን በያመቱ አከብራለሁ ትላለች ። በሀገረ ናግራን ስላለቁትም ሰማዕታት በኢትዮጵያዊ ሊቅ የተደረሰ ዐርኬ ፦

ሰላም (ንብል) ለክሙ ስንዓክሙ መዓድመ ፣
ከዋክብተ ናግራን ዓበይት ዘአብራህክሙ ዓለመ ፣
ዓራቂ ኵሉን ወመስተሳልመ ፣
ቅድመ እምላከ ኮናኒ እመ ኃጢአትነ ቆመ 38 ፣
በእንተ ስሙ ዘከዓውክሙ አርእይዎ ደመ ።

ከዐጼ ካሌብ በኋላ በልጃቸው በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መን ግሥትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጪ ዓለም ጋር ግንኙ ነት ነበራት ። ይልቁንም የክርስቲያኖች መናኸሪያ ከነበሩት ከእስ ክንድርያና ከቍስጥንጥንያም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረ ። በዚ ህም የመተባበርና የወዳጅነት ግንኙነት ሳቢያ የሃይማኖት ጠላታ ቸውንም ተባብረው ለመቋቋም ይላላኩ ነበር ። በሀገር ውስጥም በሕዝቡ ዘንድ የሃይማኖት ስሜት እየጠነከረ በመሄዱ አያሌ ገዳ ማት ተቋቁመው ለመተዳደሪያ የሚሆን ርስት ጕልት የተሰጣቸው

[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዘመን ነው ፤ የቅዱስ ያሬድ መነሣትና በዓለም የታወቀው መዝሙሩ ያን ዘመን በጣም እንድናስታውሰው ያደርገናል ። አጼ ገብረ መስቀል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ጎልጎታን ለመሳለም ብዙ ጊዜ ቢመኙም አልተሳካላቸውም ። ግን ኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም ካሏት (ዛሬ ተነጥቃለች) ቅዱሳት መካናት ጥቂቶቹን ያገኘችው በርሳቸው ዘመን ነው ። በወጣትነት ዕድሜው የመነኰሰው ልጃቸው አባ ሙሴም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ ከሚኖሩ መነኮሳት እንዳንዱ ሁኖ በምንኩስና ሕይወት መኖሩ በታሪክ ታውቋል ። 39*

አፄ ገብረ መስቀል ከሞቱ በኋላ ከአባታቸው ከአጼ ካሌብ ጀምሮ ለመቶ ዓመታት የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የመን በፋርስ እጅ ወደቀ ፤ ባማረና በከበረ ዶንጊያ በኢትዮጵያውያን ተሠርተው የነበሩ የሰነዓ አብያተ ክርስቲያናት ተደመሰሱ ፡ ክርስቲያኖችም እየመነመኑ ሄዱ ፤ በኋላም በመሐመድ መነሣት 40* የመንን የእስልምና ሃይማኖት አጥለቀለቃት ። ይህ ብቻ አይደለም ፤ መሐመድ የክርስቲያን አገሮችንና መሪዎቻቸውንም ጭምር ወደ እስልምና ለመለወጥ አሳብ ስለ ነበረው ለቁስጥንጥንያው ንጉሥ ለሕርቃል እስልምናን እንዲቀበል ጽፎለታል ። በዚያ ዘመን ለነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ አርማሕ እስልምናን እንዲቀበል ጽፎለት ነበር ይባላል ። መሐመድ በተነሣበት ዘመን በቤተ ክርስቲያን በአንድ ባሕርይና በሁለት ባሕርይ ባዮች መካከል የከረረ ጠብ ስለነበር «የገባያ ግርግር ለቀጣፊ በጀው» እንደሚባለው ትምህርቱን ለማስፋፋት ብዙ ችግር አላጋጠመውም ። ይልቁንም የክርስቲያን መናኸሪያዎች የነበሩትን ቦታዎች ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር አደረጋቸው ። መሐመድ ከመካ ወደ መዲና በተሰደደበት ጊዜ 41* ከተከታዮቹ ጥቂቶቹ ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው ሲገቡ የተደረገላቸውን ሰብአዊ ርኅራሔ ሰምቶ «አበሻን አትንኩ» ብሎ መናዘዙ ይነገራል ። ይሁን

39. J.B. Coulbeaux — Histoire Politique . . .
Vol. Page 190-191

40. ፭፻፸ ዓ. ም.

41. ፮፻፲፬ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

እንጅ ተከታዮቹ ይህን ቃል ባለማክበር ግብፅን የሚያስተዳድሩት የዐረብ ሹማምንት በእስክንድርያና በሊቀ ጳጳሳቱ ላይ እጃቸውን ስለጫኑበት የአክሱምን መንግሥት በመንፈሳዊ ረገድ እንኳ የሚያጽናናው አጣ ። ጳጳስ ለማምጣት ከአክሱም ወደ እስክንድርያ በሚሄዱት ኢትዮጵያውያን ላይ ከእስክንድርያ በሚመጣው ጳጳስና በ፶ሚው ሊቀ ጳጳስ ላይ አረቦች ተጽዕና እያደረጉ ጳጳሳቱንና መልእክተኞቹንም እያሠሩ እየፈቱ ግብር እያስከፈሉ የእስክንድርያንና የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያናት አዳከሟቸው ። ከሀገረ ናግራን ጦርነትና ከአጼ ገብረ መስቀል በኋላ እስከ ዮዲት መነሣት ፫፻ ዓመት አለ ። በታሪካችን መግቢያ ላይ እንደ ገለጥነው ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ጀምረው በየጊዜው ከፍልስጥኤም እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት እሥራኤላውያን ብዙዎች ክርስትናን ሲቀበሉ ጥቂቶቹ ደግሞ አንቀበልም ብለው በሀገሪቱ ተራራማና ቆላ ቦታዎች ይኖሩ ነበር ። እነዚህም በሌላው ሕዝብ ዘንድ ፈላሾች እየተባሉ ይጠራሉ ። ስደተኞች ማለት ነው ። እነሱም ለራሳቸው የሚያስተዳድራቸው ጌዴዎን የሚባል ሹም ሹመው ነበር ። እሱም ዮዲት የምትባል ልጅ ነበረችው ፤ መልከ መልካምና ኃይለኛ ነበረች ።

በ፰፻፵፪ ዓ.ም. ገደማ በአክሱም የድግናዣን ልጅ አንበሳ ውድም የተባለ ሕፃን ነግሦ ሳለ ሕፃኑ ንጉሥ አገሩን ለማስተዳደር አለመቻሉን ሰምታ ዘመዶቿን በክተት አሰልፋ ዮዲት ወደ አክሱም ገሠገሠች ። ሕፃኑም ንጉሥ ከመኳንንቱ ጋር ሁና ወደ ሸዋ ስለ ሸሸ ፣ ዮዲት አክሱም ከተማ ገብታ ወረራዋን ቀጠለች ። በክርስቲያኖች ላይ ከአባት የወረደ ጥላቻ ስለ ነበራት የክርስቲያኖች ቅርስ የነበረውን ሁሉ አቃጠለች ። በአብርሃና አጽብሃ የተሠራችውን በኢትዮጵያ የመጀመሪያዪቱን የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አቃጠለች ። ከክርስትና በፊትም በክርስትናም ዘመን የተሠሩ ብዙ ሐውልቶችን አፈራረሰች ። መጻሕፍት ፣ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ ተደመሰሱ ፤ እያሌ ክርስቲያናችና ካህናትም ከድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጋር አብረው [illegible] ሕዝቡ በዮዲት ፈንታ

www.ethiopianorthodox.org

ጉዲት ወይም እሳቶ እያለ ይጠራታል ። የነገሠችውም ለ፵ ዓመታት ነው ፤ ከ፵ ዓመት የመከራና የስቃይ አገዛዝ በኋላ ጉዲት ሞተች ። አንበሳ ውድምም ወደ አክሱም ተመልሶ የመንግሥቱን ሥልጣን ያዘ ።

በዚህ ጊዜ በሀገሪቱ የሃይማኖት መሪ ጳጳስ ስላልነበረ የሕዝቡ ተወካዮች ወርቅና ብራቸውን ጭነው ጳጳስ ለማምጣት እንደ ተለመደው ወደ ግብጽ ሄዱ ። እንዳጋጣሚም በእስላሞቹ ትእዛዝ የሊቀ ጳጳስ መቀመጫ ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ ተዛውሮ ነበር ። ሊቀ ጳጳሱም አባ ቆዝሞስ ነበሩ ። መልእክተኞቹ ካይሮ ደርሰው ጭነው የወሰዱትን ገጸ በረከት ለከሊፋውና ለሊቀ ጳጳሱ ከአበረከቱ በኋላ ምርጫ ተደረገና አቡነ ጴጥሮስ የተባሉት የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆኑ ተመረጡ ። ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡም በእስላሞች ጭከናና በአክሱም መንግሥት ላይ በወረደው አደጋ ለብዙ ዘመን የጳጳስ መምጣት ተቋርጦ ስለ ነበር ። የአክሱም ሕዝብና ንጉሡ በሃይማኖታዊ ናፍቆት በታላቅ ክብርና ደስታ ተቀበሏቸው ። ጳጳሱም ሥራቸውን በማከናወን ብዙ ዘመን እንደቆዩ ንጉሡ ታሞ ሲያጣጥር ፤—እግዚአብሔር ይማርህ ሊሉት ወደ ቤተ መንግሥት ይሄዳሉ ። ንጉሡም እንደሚሞት ተረድቶት ከሱ በኋላ አልጋውን የሚወርሰውን ለማወቅ ፤ አባቴ እኔ መሞቴ ነው ፤ ከሁለቱ ልጆቼ መንግሥቴን ተረክቦ ሕዝቡን ሊያስተዳድር የሚችለው የትኛው ይመስልዎታል ? አላቸው ። ጳጳሱም በቅንነት መንፈስ አልጋህን ለትንሹ ልጅህ አውርስ አሉት ፤ ወዲያውም አባቱ ሞተና ትንሹ ልጅ የአባቱን አልጋ ወረሰ ። በዚህ ጊዜ የበኩር ልጁ በጳጳሱና በነገሠው ወንድሙ ላይ የበቀል ርምጃ ለመውሰድ ያስብ ነበር ። በዚህ አሳብ ላይ እንዳለ ከዚያው ከግብፅ ከአባ እንጦንስ ገዳም የመጡ አባ ሚናስና አባ ፊቅጦር የሚባሉ ሁለት መነኮሳት ስለነበሩ ፤ ኀዘኑን ለነሱ ገለጸላቸው ፤ እነሱም በተንኮል ተነሣሥተው ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከአባ ቆዝሞስ የተላከ እስመስለው የሚከተለውን ጽሑፍ አርቀው ይሰጡታል ።— «አባ ጴጥሮስ ከእስክንድርያ መንበር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያልተሾመ አታላይና ሕገወጥ ጳጳስ ነው ። ያባቱን ዙፋን ሊወርስ የሚገባው የበኩሩ ልጅ ነው» የሚል ጽሑፍ ሰጡት ።

www.ethiopianorthodox.org

እሱም ይህን ጽሑፍ ባገኘ ጊዜ ብዙ ጀሌ ሰብስቦ ወንድሙን ውጊያ ገጠመው ። በጦርነቱም ድል ስላጋጠመው ወንድሙን ከዙፋኑ አውርዶ እሱ ነገሠ ። አቡነ ጴጥሮስም ወደ ወህኒ ቤት ተላኩ ። ይህን ተንኰል ከተበተቡት አንዱ አባ ሚናስ ጳጳስ ሆኑ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአባ ሚናስና ግብረ አበሩ በነበረው በአባ ፊቅጦር መካከል ጠብ ተጀመረ ። አባ ፊቅጦር በአባ ሚናስ ቤት ያለውን ወርቅና ብር ዘርፎ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። በዚያም ሃይማኖቱን ወደ እስልምና ለውጦ ቆቡን ጥሎ ተቀመጠ ። ይህ ሁሉ የኢታላይነት ተግባር መፈጸሙ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተሰማው ዘግይቶ ነው ። እንደ ተሰማ ግን ሊቀ ጳጳሱ አባ ቆዝሞስ አባ ሚናስ በኢታላይነት ስለ ቀሰጠ ውግዘት አስተላለፉበት ። የአቡነ ጴጥሮስ ንም ሕጋዊ ጳጳስነት አረጋገጡ ። ንጉሡም የአባ ሚናስን ኢታላይ ነት በሰማ ጊዜ ወዲያው ገደለው ። አቡነ ጴጥሮስ ግን በእሥር ቤት እንዳሉ ሙተው ስለነበር መንበሩ ያለ ጳጳስ ቀረ ። ከ፱፻፲፭— ፱፻፸፩ ዓ.ም. ድረስ ከአባ ቆዝሞስ በኋላ የተነሱ አራት ሊቃነ ጳጳ ሳት ፤—አባ መቃርዮስ ፣ አባ ቴዎፋንዮስ ፣ አባ ሚናስና አባ አብ ርሃም ናቸው ። እነዚህ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ሹመው አልሰደ ዱም ።42* በእነዚህ ፹፬ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን ጳጳስ ባለማግኘቷ ስሃይማኖት በኩል ብዙ ችግር ደረሰ ። ሕዝቡም ተደናግጦና ተስፋ ቆርጦ እግዚአብሔር ቢጣላን ነው እንጂ መቅሠፍት ሁሉ ይደርስብን ነበር እያለ ኀዘኑን ጨርሶ ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ ነበር ። እግዚአብሔር ግን ይህን ሕዝብ ጨርሶ አልረሳውም ።

42. ETUDES SUR L'ANCIENNE ALEX-
ANDRIE A.M. DE SOGHIEB PAGE 245

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፫ ፤

# ከዮዲት በኋላ እስከ ዐፄ ይኩኖ አምላክ

የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ከአኩሱም ወደ ላስታ በተዛወረ ጊዜ በዮዲት ወረራ ተደናግጦ የነበረው ክርስቲያን ሕዝብ የሃይማኖት ስሜቱ እንደ ገና ተቀሰቀሰ ። የተቃጠሉትን መጻሕፍት እንደ ገና በማጻፍ የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ በማሠራት ብዙ ጥረት ተደርጓል ። የክርስቲያኖቹም ፍቅርና መተባበር ሥራውን ሁሉ እንዲቃና ረድቷል ። የነገሥታቱና የመኳንንቱ ልጆች በወጣትነት ዘመናቸው እየመነኑ ገዳም በመግባታቸው ምንኩስናዊ ሕይወት በጣም ተስፋፍቶ ነበር ። ከ፱፻፹፭ ዓ.ም. ጀምሮ የነበረው ጠጠውድም የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ በዮዲት ጊዜ የፈረሰውን (የዕንዳ ጽዮንን) የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያንና የፈራረሱትን ሐውልቶች ማሠራቱና በርሱም ዘመን የግብፅ ክርስቲያኖች ከእስላሞች ፊት እየሸሹ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ተጽፏል ። በኅዳር ፲፯ ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደሚተርከው ከ፱፻፺፭—፲፻፭ ዓ.ም. የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ <u>ጃን</u> <u>ሥዩም</u> በዘመኑ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ለነበሩት ለአባ ፊላታዎስ በኑብያው ንጉሥ በጊዮርጊስ በኩል አንድ መልእክት ላከ ፤ መልእክቱም እንዲህ የሚልነበር ። «አባቶቻችን በአቡነ ጴጥሮስ ላይ በሠሩት በደል እግዚአብሔር ተቆጥቶናል ፤ ሀገራችን በአባር በቸነፈር ፤ በጦር ብዙ ስቃይ ተቀበለች ። ምዕመናንና ካህናቱ አለቁ ፤ አብያተ ክርስቲያናቱም በጦር በወራሪ ፈረሱ ከመፍረስ የተረፉትም በካህናት መታጣት ተዘጉ ። ይህን ሁሉ ችግራችንንና መከራችንን ተገንዝበው ሀገራችንን የሚባርክልን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቀን ጳጳስ ይላኩልን

www.ethiopianorthodox.org

የሚል ነበር ። 43. ይህ መልእክት እንደደረሰ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ፈቀደ ፤ ወዲያውም ምርጫው ተከናውና ከገዳመ አስቄጥስ ከአባ መቃርስ ገዳም የተመረጡ አባ ዳንኤል የኢትዮጵያ ጳጳስ ተብለው ተሾሙ ። ኢትዮጵያ በገቡ ጊዜም ለብዙ ዘመን አዝኖና ተክዞ የነበረው ክርስቲያን የናፍቆትና የደስታ ስሜት የተቀላቀለበት እንባ እያለቀሰ ተቀበላቸው ። በዚህ ጊዜ አቡነ ፊላታዎስ አቡነ ዳንኤልን ሹመው በመላካቸው ኢትዮጵያዊው ሊቅ የሚከተለውን አርኬ ደርሰላቸዋል።

ሰላም ለከ ፊላታዎስ ሐዋርያ ፤
ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ፤
በእብሬትከ አንፈሱ ሕዝበ ኢትዮጵያ ፤
በእንተ ዘሜሙ (በ) ላዕሌሆሙ ብእሴ ጉህልያ ፤
አመ ጽእለተ ጸር ኮነ (ኑ) ወለኅር ሕብልያ ።

እሳቸውም የፈረሰውን በማሠራት ያዘነ የተከዘውን በማጽናናትና በማረጋጋት ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ሲፈጽሙ ቆዩ ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚለው የግብፅ አገረ ገዥዎች የሆኑት እስላሞች ወደ ኢትዮጵያ በሚላከው ጳጳስ ምክንያት ሊቃነ ጳጳሳቱን ግብር ከፈሉ እኛን ሳታስፈቅዱ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ አትላኩ በማለት ብዙ ጊዜ ሲያሥሯቸው ፤ ሲፈቷቸው ኑረዋል ። ግንኙነቱን ለመቆጣጠር እንዲመቻቸውም የእስላም መሪዎች ባደረጉባቸው ተጽእኖ ሊቃነ ጳጳሳቱ መንበራቸውን ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ አዛውረው ነበር ። ሲወርድ ሲዋረድ በቆየው በክርስቲያኖች ልማድ መሠረት የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት ለኑብያውና ለኢትዮጵያው ንጉሥ ያስተላልፉት የነበረን ሐዋርያዊ መልእክት 44. በአባ ዘካርያስ የሊቀ ጵጵስና ዘመን (፲፻፲፯—፲፻፴፪) የእስላሞቹ መሪ ከሊፋ እል ሐኪም እንዳይላክ ከለከለ በዚሁ የተነሣ አባ ዘካርያስም ታሠሩ ። የግብፅ ክርስቲያኖችም መከራ ስለ ጸናባቸው ወደ ሮምና ቁስጥንጥንያ እንዲሔዱ በትምህ

43. ስንክሳር ፤ ኅዳር ፲፪ ቀን ፤
44. ENCYCLICAL LETTER

www.ethiopianorthodox.org

ርተ ሃይማኖት ስለማይመስሏቸው ኑብያ በእስላሞች ስለ ተወረ ረች በቀጥታ ወደ ሃይማኖት ወንድሞቻቸው ወደ ኢትዮጵያ መጡ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብም እንደ ተለመደው የወንድምነት አቀባበል አደረገላቸው ። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ የነበሩት ጳጳስ አባ ዳንኤል አርፈው ስለ ነበር ሌላ ጳጳስ ለማስመጣት ወደ ግብፅ መልእክተኛ ተላከ ። ያን ጊዜ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አባ ክሪስቶ ዱሎስ (ገብረ ክርስቶስ) ፲፻፵፯—፲፻፸፱) ቀደም ሲል በኑብያና በኢትዮጵያ የሚገኙትን መስጊዶች ሁሉ አፈራርሱ ብለህ አባ ፊቅጦርን ወደ ኑብያ ፣ አባ ቄርሎስን ወደ ኢትዮጵያ ልከሃል ተብለው ተወንጅለው ወህኒ ቤት ገብተው ስለነበር ኢትዮጵያው ያኑ መልእክተኞች ጳጳስ አላገኙም ። በዚህ መካከል አብዱም የሚ ባል ግብጻዊ እስላም የሐሰት ደብዳቤ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አባ ቄርሎስ ነኝ አለ ። የጵጵስና አቀባበልም ተደረገለት ። የዚህ ሰው ሐሰት በግብፅ እንደ ተሰማ ፣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንና የመ ንግሥቱም ባለሥልጣኖች ወዲያው እንዲያዝ ወደ ኢትዮጵያ መል እክት ላኩ ። ቀሳጢውም ተይዞ በዳሕላቅ በኩል ወደ ግብፅ ተወሰደ ። አንገቱን በሰይፍ ተቀጣ ።

ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አባ ክሪስቶዶሎም አርፈው በምትካቸው አባ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ ። 45 አባ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳስ እንደ ሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ለመላክ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዝግጅት አደረገ ፣ ነገር ግን ያን ጊዜ ግብፅን ይገዛ በነበ ረው «በድር እል ጀማል» ተጽእኖ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ቅዱስ ሲኖዶስ የመረጣቸው ሳይሆኑ የእስላሞቹ ወዳጅ አቡነ ሳዊሮስ ነበሩ ። አቡነ ሳዊሮስ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ግርማ ሥዩምና ሕዝቡ ካህናቱም ጭምር የደስታ አቀባበል አደረ ጉላቸው ። ነገር ግን አቡኑ ከበድር እል ጀማል ጋር ባደረጉት ስም ምነት መሠረት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምንም ሥራ ከመሥ ራታቸው በፊት በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ዐረብ እስላሞች መስጊዶች እንዲሠሩ አደረጉ ። እስላሞቹም በኢትዮጵያ ላይ ሃይማኖታቸውን

45. ፲፻፹፰—፲፻፺፪ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

እንዲያስፋፉ የሐሳብ ድጋፍ ይሰጧቸው ጀመር ። እኒሁ አቡን በኢትዮጵያ ሰባት መስጊዶችን ማሠራታቸው ይነገራል ። ጳጳሱ ይህን ያደረጉበት ምክንያት ከበድር አል ጀማል ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ብቻ ሳይሆን ፤ እርሳቸው በኢትዮጵያ ይህን ሲያደርጉ በግብፅ የሚኖሩ ወገኖቻቸው አገዛዝ የቀለለላቸው መስሏቸው ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የእስላሞች መልእክተኛ ሆነው በመጡት በእኒህ አቡን ላይ ተቆጥቶ ተነሣ ። ጥላቻውም እየበረታ ሄደ በዚህ ምክንያት ጳጳሱ ወደ ግረፊያ ቤት ገቡ ። አሠርተዋቸው የነበሩ መስጊዶችም እንዲፈርሱ ተደረገ ፤ በዚህ ጊዜ ከአቡኑ ጋር አብሮ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ወንድማቸው የተደረገውን ሁሉ ለበድር አል ጀማል ነገረው ። እሱም ይህን በሰማ ጊዜ ኃይለኛ ነኝ ባይ ነበርና የሚከተለውን መልእክት ለኢትዮጵያው ንጉሥ ለግርማ ሥዩም ላከ ።—«በሀገርህ የፈረሱት መስጊዶቻችን እንደገና ካልተሠሩ እኔም በግብፅ የሚገኙትን የቅብጥ (ኮፕት) አብያተ ክርስቲያናት እንዳልነበሩ አደርጋቸዋለሁ» ብሎ የዛቻ መልእክት ላከበት ። ነገር ግን ንጉሡም በኢትዮጵያዊ ወኔ ተቀስቅሶ ዛቻውን ከምንም ሳይቆጥር የሚከተለውን መለሰለት ፦— «ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ድንጊያ ብታነሣ መካ ተሻግሬ የከአባን ድንጊያ አመድ አድርጌ ትቢያውን ካይሮ እልክልሃለሁ» የሚል መልስ ላከበት ።46* « ከመካ የመስጊዱን ድንጊያ አስመጥቼ አሠራሃለሁ » የሚል መልስ መለሰለት የሚሉም አሉ ።

በዚህ በግርማ ሥዩም ዘመነ መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ የመስቀል ጦርነት ተጀምሮ ስለነበር ግብፃውያን ፊታቸውን ወደዚያ ሲመልሱ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ዓይናቸውን በግብፅ ላይ ጥለው ነበር ። ግርማ ሥዩም አርፎ ልጁ ይምርሐነ ክርስቶስ ተተካ በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል ያለው ግንኙነት ግን አሁንም በእስላሞች ተጽእኖ የተነሣ የሻከረ ነበር ። አቡነ ሳዊሮስ በግርማ ሥዩም ዘመነ መንግሥት ከታሠሩ ጀምሮ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ አልተላከም ነበርና ይምርሐነ ክርስቶስ ወደ ግብፅ መልእክተኞችን ልኮ አባ

46. Renaudet: Op. Cit. 463-464

www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ የተባሉትን ጳጳስ አስመጣ ። ዳሩ ግን አባ ጊዮርጊስ ደግሞ ስስታምነታቸውና በንግድ ገንዘብ መሰብሰባቸው ስለ ታወቀ ወደ ግብፅ ተመልሰው ሄዱ ። ይምርሐነ ክርስቶስ በዘመኑ ከፈጸማቸው ድርጊቶች፥—የግብፅ እስላሞች በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርሱትን ግፍ በመቀበል የዐባይን ወንዝ ለመገደብ መሞከሩ ነው ። የዐባይ ውሀ በግብፅ እያነሰ በመሄዱና የግብፅ ሰዎችም በውሀ ጥም የሚ ያልቁ ሲሆን መሪዎቹ ተደናግጠው አማላጅ ሁነው የዐባይን ውሀ እንዲያስለቅቁ በዘመኑ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩ አቡነ ሚካ ኤል ተልከው ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። 47* እርሳቸውም መጥተው የዐባይ ውሀ ቢቆም በጥም የሚያልቁ ክርስቲያኖች ወንድሞቻችሁ ጭምር ናቸው እንጅ እስላሞች ብቻ አይደሉም ። አሁንም ከግብፅ ተልኬ የመጣሁት ይህንኑ ለናንተ ለልጆቼ ለመግለጥ ነው ብለው ለንጉሡ ለይምርሐነ ክርስቶስና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልመና ቸውን አቀረቡ ። በዚህም ጊዜ ውሀው ተለቀቀ ። ሊቀ ጳጳሱም ደስ ብሏቸው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

ይምርሐነ ክርስቶስ ሲያርፍ ልጅ ስላልነበረው የወንድሙ የጃን ሥዩም ልጅ ሐርቤ ነገሠ ። ስሙ በሀገራችን ሐርቤ ወይም ገብረ ማርያም ይባላል ። ዐረቦች ቀኑዳ ፤ ፈረንጆች ሲኖዳ ወይም ሸኑዳ ይሉታል ። ይህ ንጉሥ ብዙ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ሥራዎ ችን የሠራ ሲሆን ፤ ሌላው ሁሉ ጠፍቶ ኤጲስ ቆጶስ በማሾም ምክ ንያት በርሱና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአባ ገብርኤል መካ ከል የተነሳውን ጠብ ጸሐፊው ሁሉ በስሙ ይተርክለታል ። በዚህ ዘመን 48* በካይሮ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አባ ገብርኤል ሁለተኛ ናቸው ። እርሳቸውም ከቅዱስ ማርቆስ ጀምሮ ፸ኛ ሊቀ ጳጳሳት መሆናቸው ነው ። የኢትዮጵያም ጳጳስ አቡነ ሚካኤል ነበሩ ። ቅዱስ ሐርቤ እንደ ነገሠ የኢትዮጵያን ስፋት ፤ የሕዝቡን ብዛት በመመልከት በኢትዮጵያ ጠረፍ ላይ የነበረው የዐረብ እስላሞች ኃይልም እየጨመረ በመሔዱ ከግብፅ እየተሾሙ እየመጡ በቤተ

47. ፲፻፹፱—፲፻፺፫ ዓ. ም.
48. ፲፩፻፴፩—፲፩፻፵፮ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

መንግሥቱ አካባቢ የሚኖሩ ግብፃውያን ጳጳሳትም ቅስናና ዲቁና ከመስጠት በቀር ከአውራጃ ወደ አውራጃ ተዘዋውረው ክርስትናን ለመስበክ አለመቻላቸው ከልብ ስላሳዘነው፥—መላውን ኢትዮጵያን ተዘዋውረው የሚያስተምሩ ሰባት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ አቡነ ሚካኤልን ጠየቋቸው ። ጳጳሱም ሊቀ ጳጳሱን አባ ገብርኤልን ሳልጠይቅ አላደርገውም አሉ ።

በዚህ ጊዜ ከሊቃውንቱ ጋር መክሮ ይህንኑ ሹመት ከአባ ገብርኤል ለማስፈቀድ መልእክተኞቹን ወደ ግብፅ ላከ ። ሊቀ ጳጳሱ ግን ይህን ጥያቄ አልተቀበሉትም ።—በየጊዜው ጳጳስ ወደ ኢትዮ ጵያ በሚመጣበት ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታት ብዙ ወርቅና ብር ዕንቁና አልማዝ ገጸ በረከት ይላክ ስለ ነበር ከእንግዲህ ወዲህ ሐበ ሾች ራሳቸውን ከቻሉ ይህ ሁሉ መቅረቱ ነው ብለው አባ ገብር ኤል ብቻ ሳይሆኑ ከሊፋዎቹና ሡልጣኖቹም በቅዱስ ሐርቤ ጥያቄ ብዙ ተደናገጡ ። ጥቅማቸው እንዳይቀርባቸው ተመካክረው እዚ ያው እኛው የላክነው ጳጳስ በቂ ነው ፤ የኤጲስ ቆጶሳቱ ሹመት አስፈላጊ አይደለም የሚል መልስ ለቅዱስ ሐርቤ ተላከለት ። መል እክተኞቹ ይህን መልስ ይዘውለት በመጡ ጊዜ በጣም አዘነ ። ነገር ግን አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ እንደገና ከሊቃውንቱ ጋር ተመካ ክሮ አቡነ ሚካኤል በርጅና ምክንያት ተዘዋውረው ለመሥራት ስላልቻሉ ለርሳቸው ረዳት ሁኖ የሚሠራ አንድ ኢትዮጵያዊ ኤጲስ ቆጶስ እንኳ እንዲሾም ይፈቀድልን ብሎ ሁለተኛ መልእክት ላከ ። ነገር ግን የግል ጥቅም በመካከሉ ያለበት ስለሆነ ላሁኑም ጥያቄ የተ ሰጠው መልስ አይሆንም የሚል ነው ። በዚሁ ምክንያት በቅዱስ ሐርቤና በጳጳሱ በአቡነ ሚካኤል በሊቀ ጳጳሱ በአባ ገብርኤል መካ ከል ትልቅ ጠብ ተፈጠረ ። —በሚያዝያ ፲ ቀን የሚነበበው ስንክ ሳራችን ግን ይህንኑ ሲተርክ ፤ ይህን ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ስሜት ያለው ቅዱስ ንጉሥ፥—ስሙን እንኳ ሳይጠራ ኢትዮጵያውያን ፥— ኤጲስ ቆጶሳት ይሾሙልኝ ማለቱን እንደ ኃጢአት ፤ የግብጹን ሊቀ ጳጳስ አባ ገብርኤልን እንደ ገባሬ ተአምር በመቁጠር፥—ንጉሡ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ በመጠየቁ እግዚአብ ሔር ተቆጥቶ በአገሩ በኢትዮጵያ ላይ መቅሰፍት አወረደበት ይላል።

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን የተቀደሰ አሳብ ይባርካል እንጅ በዚህ አይቆጣም ። እንደ አጋጣሚ ሁኖ በዚያ ዘመን ድርቅ ወይም በሽታ ሀገሪቱ ላይ ቢወርድም ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እን ዳይሾሙ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ያመጣው ነው ማለት እውነት አይደለም ። ከአባ ገብርኤል በኋላ የተነሱት አባ ዮሐንስም የአባ ገብርኤልን እልክ ተከትለው ለኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶስነትን አልሰጥም አሉ ። 49* ያም ሆነ ይህ በቅዱስ ሐርቤ አነሳሽነት የተ ጀመረው ጥያቄ ዛሬ ተሟልቶ ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች በራሷ መሬት ላይ እስከ ፓትሪያርክነት ለመሾም ስለበቃች የቅዱስ ሐርቤ ሐሳብ ተፈጸመ ለማለት ይቻላል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ሁልጊዜ በታሪክ ስታስታውሰው ትኖራለች ። በዚያ በጨለማው ዘመን ይህን ራስ የመቻል ሐሳብ ያፈለቀ ቅዱስ ንጉሥ ነውና ። ከቅዱስ ሐርቤ በኋላ መንግሥቱን ወንድሙ ቅዱስ ላሊበላ ወረሰ። ላሊበላ በነገሠበት ዘመን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ አባ ማርቆስ አራ ተኛ ነበሩ ። 50* ቅዱስ ላሊበላ እንደ ነገሠ ገጸ በረከቱን አስጭኖ ጳጳስ ለማስመጣት መልእክተኞች ወደ ግብፅ ላከ ። ነገር ግን በዚ ያን ጊዜ የነበረው የግብፅ መሪ ሱልጣን እል አዲን አቡበከር ኢብን ኢዮብ በክርስቲያኖች ላይ ከባድ ተጽእኖ አድርጎ መነኮሳቱንም ፈጅቷቸው ስለነበር ለጵጵስና የሚመጥን መነኩሴ በመጥፋቱ መል እክተኞቹ በደጅ ጥናት በመጉላላት ሦስት ወር ያህል ቆዩ ። በመ ጨረሻም ሲሰለቻቸው ለሱልጣኑ አቤት አሉ ። እሱም የሚፈል ገው ይኸንኑ ስለነበር ወዲያው ምርጫ እንዲደረግና ጳጳስ ተሹሞ እንዲላክ ፈቀደ ። ምርጫው ተከናውኖ አቡነ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ተሾሙ ። እርሳቸውም ደብረ ሮሐ ሊገቡ ጥቂት ሲቀራቸው ከዚያ በፊት ጳጳሳት ሲመጡ እንደሚደረገው ሁሉ የንጉሡ የጭን በቅሎ በወርቅ መረሻትና በወርቅ መጣብር በሐር ግላስ ተሸልማ ለጳጳሱ ቀረበች ። በዚያች ተቀምጠው መነሳንሱ የሐር የሆነ የወ ርቅ ጭራ ይዘው የሐርና የወርቅ ድባብ ተዘርግቶላቸው ወደ ደብረ

49. RENAUDE PAGE 545

50. ፲፩፻፷፬—፲፪፻፷፯ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ሮሐ ገቡ ። ንጉሡና እቴጌዪቱ እንዲሁም መላው ሕዝብና ካህናቱም የደመቀ አቀባበል አደረጉላቸው ፤ በበነጋው ጳጳሱ ቀድሰው ሲጨርሱ እንደ አጋጣሚ ዝናም ስለ ዘነመ ጳጳሳችን የእግዚአብሔርን ረድኤት ይዘውልን መጡ ፤ ጳጳሳችን ሲመጡልን እግዚአብሔር በረድኤት ጐበኘን ብሎ ሕዝቡ በምር ደስ አለው ። ጳጳሱ በኢትዮጵያ ከአራትና ከአምስት ዓመት በላይ አልቆዩም ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የእቴጌይቱን የመስቀል ክብራን ወንድም (ዘመድ) ገብሮን የሚባለውን ኤጲስ ቆጶስነት ሹመውት እንደ ነበር ይናገራል። በኋላ ግን ሕዝቡ ስለ ወደደው ቅንዓት ሳያድርባቸው አልቀረም ። በመካከሉም በዕለት ግጭት የግል ዕቃ ቤት ጠባቂያቸው የነበረውንና ሕዝቡም እንደ ቅዱስ አባት የሚቆጥረውን ካህን ወርቅ ሠር ቆብኛል ብለው አስገደሉት ። የሚች ወገኖችም ወንድማችንን በግፍ የገደለውን ጳጳስ አንፈልግም የሚል ስሜት አደረባቸው ። በዚህ ምክንያት ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ፤ እዚያ ሲደርሱ ለምን እንደ ተመለሱ ሊቀ ጳጳሱ ቢጠይቋቸው የሚከተለውን መልስ ሰጡ እቴጌዪቱ ወንድማቸው ገብሮንን ኤጲስ ቆጶስነት እንድሾምላቸው ጠይቀውኝ ሾምሁት ፣ እሱም ሹመቱን እንዳገኘ አገሩ ነውና ሕዝቡን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን እያስተባበረ የጵጵስናውን ሥራ ጨርሶ ቀማኝ ። ከዚያም አልፎ ተርፎ ለሕይወቴ የሚያሰጋኝ ሆነ በዚህ ምክንያት ሸሽቼ ወደ ሀገሬ ተመለስሁ ብለው መልስ ሰጡ ። ሊቀ ጳጳሱም ነገሩን ለማጣራት አባ ሙሴ የሚባሉ መነኩሴ ወደ ኢትዮጵያ ላኩ ። እርሳቸውም የተላኩበትን ጉዳይ ለንጉሡና ለንግሥቲቱ አቀረቡ ። እነሱም አቡነ ሚካኤል ወደ አገራቸው የተመለሱበት ምክንያት እርሳቸው እንዳወሩት አለመሆኑን ከላይ እንደ ተጻፈው ዘርዝረው ነገሩት ። የተባለው ኤጲስ ቆጶስም የቤተ መንግሥቱ ስዕል ቤት ኃላፊ እንጅ ወደ ጵጵስናው ሥራ ጣልቃ አለመግባቱን ጨምረው ለአባ ሙሴ ነገሩአቸው ። አባ ሙሴም ይህንኑ ሲያጣሩ ለአንድ ዓመት ያህል ቆዩ ፤ በዚሁ ዓመት የተባለው ኤጲስ ቆጶስ ገብሮን አረፈ ። ዓፄ ላሊበላም ከሱ በፊት ከነበሩ ነገሥታት ለየት ባለ ሁኔታ ገጸ በረከት አስይዞ ጳጳስ ለማስመጣት ወደ ግብፅ መል[illegible]ኞች ላ[illegible] ከመልእክተኞቹ ጋር አብረው ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ግብፅ ተመልሰዋል ። በዚህ ጊዜ ከተላከው ገጸ በረከት ውስጥ ለሊቀ ጳጳሳቱ የተሰጠ ሥራው በጣም የሚያስደንቅ የወርቅ ዘውድ ፣ ለሡልጣኑ የተሰጠ አንድ ዝሆን ፣ አንድ አንበሳ ፣ አንድ ቀጭኔ ፣ አንድ የሜዳ አህያ ከነነፍሳቸው ይገኙባቸዋል ። እነዚህ ሁሉ እንደ ኤግዚቢሽን በካይሮ ለሕዝብ ሲታዩ ብዙ ቀን ሰነበቱ ። አባ ሙሴም ኢትዮጵያ በቆዩበት ጊዜ ምንም እንኳ ኤጲስ ቆጶስ ገብሮን እንደ ጳጳስ መከበሩን ቢያይም አቡነ ሚካኤል ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የበቁት በፈጸሙት የነፍስ መግደል ወንጀል እንጅ በኤጵስ ቆጶስ ገብሮን ጉዳይ አለመሆኑን ለሊቀ ጳጳሱ በጽሑፍ አቀረቡ ። ሊቀ ጳጳሱም አቡነ ሚካኤል የሚሻሩበትን በቂ ምክንያት ሕዝብ እንዲያውቀው በመዐልቃ ገዳም አያሌ የግብፅ ክርስቲያን ሰብስበው አባ ሙሴ ያመጡት መረጃ ተነበበ ። ከዚህ በኋላ አቡነ ሚካኤል የጳጳ ስነቱን ሥልጣን ተገፈፉ ። በርሳቸውም ፈንታ ምርጫ ተደርጎ ከአባ እንጦንስ ገዳም የመጡ ሁለት መነኮሳት፣— አባ ይስሐቅ የኢትዮ ጵያ ጳጳስ ፣ አባ ዮሴፍ ኤጲስ ቆጶስ ተብለው በመጋቢት ወር ፩ሺህ ፪፻፲ ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። አቀባበሉም እንደ ተለመደው የሚያስደስት ነበር ።

በላሊበላ ዘመነ መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ ሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ይካሔድ እንደ ነበር በታሪክ ይታወቃል ። የመስቀል ጦርነት ማለት ካቶሊኮች ኢየሩሳሌምንና መላዋን የፍል ስጥኤም ምድር ከእስላም አረቦች ለማስለቀቅ ያደረጉት ጦርነት ነው ። ነገር ግን የጦርነቱ ዓላማ ይኸ ይሁን እንጅ መላውን የክር ስቲያን ዓለም የሚያስተባብር ሳይሆን በሮማ ካቶሊኮች ብቻ የሚ መራ ስለሆነ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከጦርነቱ አልተሳ ተፉም ። ስለዚህ በዐረብ ዓለምና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው ሁኔታ ጋብ ያለ ነበር ። በዚህ በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት በና ዝሬትና በጥብርያዶስ መካከል የተፋፋመ ጦርነት ተደርጎ ነበር ተዋጊዎቹም ከካቶሊኮች ወገን የጀርመን ንጉሥ ፍሬደሪክ ባርባሩስ የእንግሊዝ ንጉሥ ሪቻርድ ልበ አንበሳ ፣ የፈረንሳይ ንጉሥ ፊልጶስ አጉሥት ናቸው ። በእስላሞቹ በኩል ደግሞ ሳላህ አዲን የተባለው

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን ሁሉ አሸንፎ ኢየሩሳሌምን መልሶ በቁጥጥሩ ሥር አደረገ ኒዎፊቶስ የተባለው ቆጵሮሳዊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ 51* በ፩ሺ፱፻፲፱ ዓ. ም. ሳላህ አዲን በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ኢየሩሳሌምን በያዘ ጊዜ ከክርስቲያን ቅርሶች ዋናዎቹን በጐል ጎታ በሚገኘው በቅዱስ መቃብር አጠገብ ያለውን ዕሌኒ ንግሥት ቅዱስ መስቀሉን ያስወጣችበትን ዋሻና በቤተ ልሔም ጌታ የተ ወለደበትን ጐል ለቅዱስ ላሊበላ በስጦታ ያበረከተው መሆኑን ጽፏል ። 52* የላሊበላን ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ታሪክ የሚያስታውሰበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ጻድቁ ንጉሥ በከተማው የሠራቸው አሥራ አንዱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ ናቸው ። ዝርዝራቸውም ፦

፩. ቤተ ደናግል
፪. ቤተ ማርያም
፫. ቤተ መድኃኔ ዓለም
፬. ቤተ መስቀል
፭. ቤተ ጐልጐታ
፮. ቤተ ቅዱስ ሚካኤል
፯. ቤተ ገብርኤል
፰. ቤተ አባ ሊባኖስ
፱. ቤተ መርቆሬዎስ
፲. ቤተ አማኑኤል
፲፩. ቤተ ጊዮርጊስ ናቸው ።

በላሊበላ ከቋጥኝ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በመላው ኢት ዮጵያ እስከ ፳፫ ይደርሳሉ ይባላል ። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ግን ባንድ ከተማ ያሉ ናቸው ። ከላሊበላ በኋላ የወንድሙ ልጅ ነአኩቶ ለአብ መንግሥቱን ሲወርስ ላሊበላ የጀመረውን መንፈሳዊ ተግባር ሁሉ እሱ አሟልቶ ሠራ ። ከመንገሡም በፊት ላሊበላን አስፈቅዶ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን መሥራቱ በገድሉ ተጽፏል ። በኢ ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ያየነው ።— ቤተ ክርስቲያ ኒቱ በጳጳሳት በኩል የነበረባትን ችግር ነው ። ኢትዮጵያ ጳጳሳትን

---

51. C.A.D. 1944 "Cf. Papadopoulos" (St. Petersberg 1894) ii, 409.

52. "ETHIOPI in Palestina" "Vol. 1 P. 31-32".

www.ethiopianorthodox.org

ከግብፅ ታስመጣ ስለነበር አንዱ ጳጳስ ሲያልፍ ሌላውን ለመተካት ኢትዮጵያ በመንግሥት ደረጃ የግብፅን ከሊፋዎች መለማመጥና ደጅ መጥናት ነበረባት ። ብዙ መለማመጥና እጅ መንሻ ወርቅና ብር የዝሆን ጥርስ ጌጣ ጌጥ ለግብጽ ሊቃነ ጳጳሳትና ሱልጣኖች መስጠት ነበረባት ። ከዚህ ሁሉ በኋላ የሚመጡት ጳጳሳት ደግሞ የሀገሩን ቋንቋ ስለማያውቁ የማስተማር ችግር ነበር ። ግማሾቹም በግብፅ የወገኖቻቸው ሥቃይ የተቃለለላቸው እየመሰላቸው በእስላሞች ገዥዎቻቸውም ዘንድ ተወዳጅነትንና መልካም ዝናን ለማትረፍ ከክርስትና ይልቅ እስልምናን ለማስፋፋት ይጥሩ እንደነበር ተመልክተናል ። ለዚህም ደግሞ የግብፅ ሱልጣኖች ካልፈቀዱ ስለማይመጡ ፣ ብዙ ጊዜ መምጣታቸው ይቋረጥ ነበር ። ራሳቸውን ከቻሉ ጥቅማችን ይቀራል በሚል መንፈስም ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዳይሾሙ የተደረገውን ሁሉ ታሪክ መዝግቦታል ። በዚህ ጊዜ በታላላቅ በዐላት ጳጳሳት በሌሉ ጊዜ ነገሥታቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉ ነበር ይባላል ። 53. አቡ ሚላህ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ነገሥታት ክህነትና መንግሥት አስተባብረው ይዘው ከመቅደስ እየገቡ ይቀድሱ እንደ ነበር ጽፏል ። 54. ይኸ እንኳ ከአብርሃና አጽብሃ ጀምሮ እስከ ነአኩቶ ለአብ ካሉት ውስጥ እንደሆነ እንጅ ከዚያ ወዲህ ክህነትና መንግሥት አስተባብረው የያዙ ብዙ ይገኙ አይመስልም ። የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር ለማቃለል ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ለመሾም ግብፃውያን እምቢ ቢሉም በትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) ለሚመስሉን ለኢየሩሳሌምና ለአንጾኪያ ሊቃነ ጳጳሳት፣—ኢትዮጵያ ጉዳዩን ማሰማቷ አልቀረም ። እንዲያውም በ፩ሺህ ፱፻፴፯ ዓ.ም. አባ ቶማስ የተባለ ኢትዮጵያዊ የጵጵስናን ማዕርግ ከአባ እግናጥዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት መቀበሉን አንዳንድ የታሪክ ሰዎች በጽሑፋቸው አስፍረውት ይገኛል ። ሌላውን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመልከት ።

---

53. A. Fortescue, the Lesser Eastern Churches, (London 1931) P. 300.
54. Churches and Monasteries, ed. ct. P. 286.

www.ethiopianorthodox.org

1270–1283

## ምዕራፍ ፬ ፤

# ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዘመነ መሣፍንት

በይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት 55* የመጣ ጳጳስ አልነበረም ። እንዲያውም ቀደም ብሎ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዲቁና የሰጧቸው አቡነ (ጌ) ቄርሎስ ከ፩ሺ፪፻፶፱ ዓ.ም. ገደማ ጀምሮ ከሞቱ ተቋርጦ ነበር ። ፀፄ ይኩኖ አምላክ ጳጳስ ለማስመጣት ከግብፅ ሱልጣን ከሩቅና አዲስ ባይባርር ጋር በየመኑ ሱልጣን በሐምዳኒድ በኩል ከ፩ሺ፪፻፷፬ ዓ. ም. ጀምረው ይጻጻፉ ነበር ። ነገር ግን በይፋት በኩል ያለውን የአዳል እስላሞች ንቅናቄ በመደገፍ ሱልጣኑ ጳጳስ ተሹሞ እንዲመጣ አልፈቀደም ። እንዲያውም በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል የነበረውን የፖለቲካ ግንኙነት ሳይቀር አቋረጠ ። ገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደሚለው—አቡነ ተክለ ሃይማኖት አረማውያንን አስተምረውና አጥምቀው ቀድሰው ለማቁረብ ጽላትና ሜሮን አጥተው ተቸግረው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልዩ አረማዊው ንጉሥ መተሎሜ ያረከሰውን ጽላት ባርከው እንዲቀድሱበት ከእግዚአብሔር መታዘዛቸውንና በዚሁም ቅጽበት የጵጵስናውን ሥልጣን በተአምራት ከእግዚአብሔር መቀበላቸውን ሲገልጽ፡—«በሊቃነ ጳጳሳት እንደሚሾሙ ሌሎች ጳጳሳት ሳይሆን አንተን ግን እኔው ሾምሁህ» አላቸው ይላል ። በኋላም አቡነ ዮሐንስ የሚባሉ ጳጳስ ከግብጽ መጥተው ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በግማሽ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆኑ መፍቀዳቸውን ይኸው ገድለ ተክለ ሃይማኖት ይገልጣል። ሌሎች ባለታሪኮች ደግሞ ጳጳስ እንዲላክለት ወደ ግብፅ የላከው መልእክት ባለመሳካቱ ተናዶ ፡—አፄ ይኩኖ አምላክ በኢየሩሳሌም

55. ፩ሺ፪፻፸—፩ሺ፪፻፹፫ ፤



በኩል ወደ ሶርያ ተላልኮ ከያዕቆባውያን ወገን የሚሆኑ አባ ዳዊት እግናጥዮስ የተባሉት የሶርያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኢዮብ የተባሉትን ጳጳስ ልከውላቸው ነበር ይላሉ ። በልጃቸው በያግብዓ ጽዮን ዘመነ መንግሥት 56* በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት እየተሻሻለ ስለሔደ አባ ዮሐንስ የተባሉት ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ሰላማን ሹመው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ ። በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት 57* ጳጳሱ አቡነ ያዕቆብ ይባሉ ነበር ። እርሳቸውም ፡—በገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደ ተጠቀሱት አቡነ ዮሐንስ ቀና መንፈስ ስለነበራቸው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት መንበር ለተቀመጡት ሦስተኛው እጨጌ አቡነ ፊልጶስ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ እንደ ሰጧቸው ገድለ ፊልጶስ ይተርካል ። አቡነ ፊልጶስም ተጋዳይ ሐዋርያ ስለ ነበሩ በሥልጣናቸው ብዙ ተጋድሎ ማድረጋቸውን ይኸው ገድለ ፊልጶስ ይናገራል ። ገድለ ፊልጶስና ክብረ ነገሥት እንደሚለው፡—አፄ ዓምደ ጽዮን የአባቱን ሚስት የእንጀራ እናቱን ዕቅብት አድርጎ ይዞ ስለነበር አቡነ ፊልጶስ ረድአቸው አኖሬዎስ ዘጽጋጃን አስከትለው ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው ያባትህን ሚስት ልትይዝ አይገባህም ብለው ገሰጹት ። ዮሐንስ ሔሮድስን የወንድምህን ሚስት ልትወርስ አይገባህም ብሎ እንደ ገሠጸው ፤ ንጉሡም ተናዶ ከነረድአቸው ገረፋቸው ። በዚያም ሌሊት የነዚህ ቅዱሳን ደም የፈሰሰባት ኩተማ በእሳት እንደ ወደመች እና እጨጌ ፊልጶስም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መሰደዳቸው በሰፊው ተተርኳል ።

ባለፈው እንደተመለከትነው ወደፊትም እንደምናየው ፡—የአቡነ ተክለ ሃይማኖትና የአቡነ ፊልጶስ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን በተከታታይ አልተሠራበትም ። አሁንም ቤተ ክርስቲያናችን ጳጳሳትን ለማግኘት ብዙ መቸገሯንና ከግብፅ ሱልጣኖችም ጋር መታገሏን እናያለን ። 58*

፹፩ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ማርቆስን በግብር ምክንያት ማምልክ ሱልጣን ባሠራቸው ጊዜ በዘመኑ የነበሩት የኢ

56. ፩ሺ፪፻፹፭—፺፬ ፤
57. ፩ሺ፪፻፺፰ ፤
58. ፩ሺ፫፻[illegible]—፩ሺ፫፻[illegible] ፤

www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ ንጉሥ አፄ ሰይፈ—አርዕድ የሚያስፈራራ መልእክት ስለ ላኩበትና በኢትዮጵያ በንግድ ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ እስላም ግብጻውያንን ሰብስበው ስላሠሩ ሊቀ ጳጳሱ እንዲፈቱ ተደረገ ። ታሪከ ነገሥቱ ግን አፄ ሰይፈ—አርዕድ አቡነ ማርቆስን ለማስፈታት ላዕላይ ግብፅ ድረስ ዘምተዋል ይላል ። 59*

በዚሁ በ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ጌታ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ከፋይ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ ይተረካል ። ስለ አመጣጡም ሁለት የታሪክ ምንጭ አለው ። ከነዚህም አንዱ በሀገራችን የሚተረከው ዐፄ ዳዊት ራሳቸው ግብጽ ድረስ ዘምተው ከዚያ ይዘውት መጡ ይላል ። ነገር ግን አፄ ዳዊት ግብጽ አልተሻገሩም ፤ ቢሔዱም መስቀሉ አለ የሚባለው በኢየሩሳሌም ስለሆነ ከግብፅ አመጡት ማለት ያስቸግራል ። ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ፡—የአፄ ዳዊት አያት አፄ ሰይፈ—አርዕድ የግብፅን ሱልጣኖች በኃይል ይጋፏቸው ስለነበር እነሱም ክርስቲያኖችን ያሰቃዩ ነበር ። ይህ አለመግባባት እንዲወገድና የግብጽ ክርስቲያኖችም ዕረፍት እንዲያገኙ በማሰብ በአባ ማርቆስ የሊቀ ጵጵስና ዘመን የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ መሪ ሁነው ከእስክንድርያም አባ ቄርሎስ (የአሕናስ ኤጲስ ቆጶስ) እና አባ ማዕምር የተባሉ ሊቅ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። በዚህ ጊዜ አፄ ሰይፈ—አርዕድ አርፈው የልጃቸው ልጅ አፄ ዳዊት ነግሠው ነበር ። እነዚህ መልእክተኞች በግብፅ ሱልጣኖችና በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት መካከል የነበረውን አለመግባባት አስወግደው ወደሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ አፄ ዳዊት በነበራቸው መንፈሳዊ ቅንዓት ዕሌኒ ንግሥት አስቆፍራ ካስወጣችው የጌታ ግማደ መስቀል ከፍለው እንዲልኩላቸው ለገጸ በረከት የሚሆን ብዙ ወርቅና አልማዝ አስጭነው ወደ ኢየሩሳሌም ላኩ ። ፓትሪያርኩም የመስቀሉን ከፋይ የአክሊለ ሦኩንም ሉቃስ የሣለውን ምስለ ፍቁር ወልዳ ጨምረው ላኩላቸው ። መልእክተኞቹም ይኸን ተቀብለው የስናርን በረሀ

59. ስንክሳር—ጥቅምት ፲፱ ቀን ፤



አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት አፄ ዳዊት የክብር አቀባበል ሊያደርጉላቸው ሲሔዱ የተቀመጡባት ባዝራ ጥላቻው መሞታቸውን ይተርካል ። «ወሀሉ ትእምርተ ስብረት ውስተ ግንባሩ እስከ ይእዜ በደሴተ ዳጋ» እንዲል ። ያም ሆነ ይህ የጌታ ግማደ መስቀል ከፋይ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ። መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ የገባው መስከረም አሥር ቀን ነው ። የተቀጸል ጽጌ በዓልም የተጀመረው ያን ጊዜ ነው ይባላል ። መስቀሉ አሁን የሚገኘው በወሎ ክፍለ ሀገር በግሼን አምባ (ደብረ ከርቤ) ተቀብሮ ነው ።

የቤተ ክርስቲያናችንን ስነ—ጽሑፍና ኪነ—ጥበብ ያስፋፉት፣ አምልኮ ጣኦትን ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለማጥፋት የታገሉት አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው ። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የነገሡት በ፲፬፻፳፬—፷፰ ዓ.ም. ነው ። ከዚህም ሌላ በዘመናቸው ዜና መዋዕላቸው እንደሚለው ደቂቀ እስጢፋ የሚባሉ 60* ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ መናፍቃን እንደ ተነሱ ይጽፋል። ይኸው ዜና መዋዕል እንደሚለው እነዚህን መናፍቃን ንጉሡ ባሉበት ሊቃውንቱ ተከራክረው ረቷቸው ። ከ ህ በኋላ እነ ደቂቀ እስጢፋኖስ ለፍርድ ወደ ንጉሡ ቀረቡ ። ንጉሡም ፍርዳቸውን ከምዕመናን እንዲቀበሉ የተሰበሰቡትን ምዕመናን ጠየቁ ። ሁሉም በሞት ቅጣት እንዲቀጡ በየነባቸው ። በመጨረሻም አፍንጫቸውን ተፎን ነው ምላሳቸውን ተቆርጠው ፣ በደንጊያ ተወግረው የካቲት ሁለት ቀን ሞቱ ፤ በ፴፫ኛው ቀን መጋቢት ፯ ቀን የመስቀል ዕለት በዚያ ቦታ ብርሃን ወርዶ ታየ ። ስለዚህም ይህችን ቦታ ደብረ ብርሃን ብለው ሰየሚት ። ይህ ቦታ በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የሚገኘው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሳይሆን አይቀርም ። ድርጊቱም የተፈጸመው (በ፲፬፻፵፬—፲፬፻፵፭) ገደማ ነው ።

በዚሁ ክፍለ ዘመን በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ፲፬፻፴—፲፬፻፴፩ በፍሎሬንስ 61* በተደረገው የዓለም አብያተ ክር

60. ስያሜው ከምን እንደመጣ አላውቀውም ፤

61. [illegible] ጣሊያ ከተማ ናት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ስቲያናት ጉባኤ በኢየሩሳሌም ከኢትዮጵያ ገዳማት አበ ምኔት ከአባ ኒቆዲሞስ የተላኩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወደ ጉባኤው ተልከዋል ። የጉባኤው ዓላማ፡— የቱርክ እስላሞች እየተበራቱ አይለው የክርስቲያን አገሮችን ሁሉ ስለያዙ ክርስቲያኖች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አስወግደው የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ወራሪ እስላም ለመቋቋም ነበር ። ነገር ግን በጉባኤው ላይ የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያኖች ስላልተስማሙ ጉባኤው ወደ ተጠበቀው ስምምነት ሳይደርስ ተበትኗል ። አንዳንድ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች፡—እንደነ አባ ኩልቦ ያሉ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ራሳቸው ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት ለመሩት የሮማው ፓፓ ኤውጂንዮስ ፬ኛ ጽፈውላቸው ነበር ። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አበ ምኔት አባ ኒቆዲሞስን ወደ ጉባኤው እንዲሔዱ አዘዋቸዋል ብለው ጽፈዋል ። ነገር ግን እነ አባ ኩልቦ በካቶሊካዊት እምነታቸው በሮማዊ ትውፊታቸው የሮማውን ፓፓ ክብር ለማጋነን ፡—የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይጽፉላቸው ነበር ለማለት ነው እንጅ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደብዳቤም አልጻፉ ፣ መልእክተኛም አልላኩ ። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አባ ምኔት አባ ኒቆዲሞስ ግን ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚወክሉ መነኮሳት በማኅበር አስመርጠው ልከዋል ፤ ይህም ራሳቸው ለሮማው ሊቀ ጳጳስ በጻፉት ደብዳቤ ይታወቃል ። አባ ኒቆዲሞስ ለሮማው ፓፓ የጻፉት እንዲህ የሚል ነበር ። «እኔ እንዳልመጣ በእስላሞቹ ዘንድ ይታወቃል ብየ ስለ ፈራሁ በጥቅምት ፲፬ ቀን ደብዳቤ አስይዤ ልጆቼን ልኬያቸዋለሁና ለፋሲካ ተመልሰው ወደኔ እንዲመጡልኝ ፣ ከመጡም በኋላ ሁኔታውን ሁሉ እንዲነግሩ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ይሔዳሉ ። የክርስቶስን በጎች ለመጠበቅ በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ስለ ተቀመጥህ የጀመርኸውን አሳብ ፈጽመው ፤ ክርስቲያን ሁሉ አንድ ከሆነ እግዚአብሔር እስላሞቹን ከኢየሩሳሌም ከተቀደሰችዋ ምድር አውጥቶ ይበትናቸዋል ። ፈረንጅ ወደ ሀገራችን ለመሔድና ለመመለስ በጣም አደገኛ ይሆን በታል ። እኛን ግን በትንሽ ጦር ብዙውን በሚያሸንፈው በንጉሣችን ብርታት ምንም ያህል አያስቸግሩንም ። ወዳንተ መልእክተኛ መላኪያን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳችንና እስላሞቹ አያውቁም ።» 62*



በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመው ማንኛውም ድርጊት እንደ ሌሎቹ ነገሥታት በዜና መዋዕላቸው ተመዝግቧል ። እዚህ ላይ ደግሞ ተንትኖ ለማቅረብ ቦታው ስላልሆነ ቤተ ክርስቲያን ነክ የሆነውን ብቻ ተመልከተናል ።

ከዚህ ሁሉ ጉዞዋ በኋላ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ብዙ የለዋወጠው በአጼ ልብነድንግል ዘመነ መንግሥት የተፈጸመው የ፲፭ ዓመት የግራኝ ወረራ ነው። 63* ሙሉ ታሪኩ በኢትዮጵያ ታሪክ በየቦታውና በየቋንቋው ተጽፎ ይገኛል ። ያንን መመልከት በቂ ነው ። ለመግቢያ ያህል ግን በዚያ ዘመን አካባቢ ከኢትዮጵያ ውጭ የነበረውን ሁኔታ እንመለከታለን ።

ቁስጥንጥንያ በሞንጎልያና በቱርክ እስላሞች ከተያዘችበትና 64* የመላዋ ታናሽ እስያ ክርስቲያኖች በእስላሞች ቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ የሞንጎልያና የቱርክ እስላሞች ከሃይማኖት ወንድሞቻቸው ከዐረብ እስላሞች ጋር ኃይላቸውን አስተባበሩ ። የወረራው ተግባርም እየተስፋፋ ሔደ ። መላዋ ሰሜን አፍሪቃ እና የአውሮፓ ደቡብ ግሪክ ፣ ስፔይን ፣ አልባንያ ፣ ቡልጋሪያ ፣ ሩማንያና ፣ ዩጎዝላቢያ እነዚህ ሁሉ የቱርክ ግዛቶች ሆኑ ። ይህ ሁሉ ሲሆን የክርስቲያን አገር የሆነችው ኢትዮጵያ አልተደፈረችም ነበር ። ይህም የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያ ተራራማ አገር ስለሆነች ለውጭ ወራሪ ስለማትመች ነው ። ነገር ግን እዚሁ በኢትዮጵያ ወሰን ላይ የተወለደው ግራኝ መሐመድ ፡—በስመ እስላም ከቱርክ ባለ ሥልጣኖች ጋር እየተላላከ የኢትዮጵያን ክርስቲያን ሕዝብ ለመደምሰስና ሀገሪቱንም ለቱርክ ለማስረከብ ተነሣሣ ። ይህ አድማ በቤተ መን

62. ሄኒሪክ ቼሩሊ. ገጽ ፻፺፫—፻፺፬ ፤
63. ፲፭፳፯—፭፵፫
64. ፲፬፶፫

www.ethiopianorthodox.org

ግሥት እንደ ተሰማ ባለ ሥልጣኖቹ ወደ ክርስቲያን አገሮች ርዳታ ለመጠየቅ ሳይልኩ አልቀሩም ። ነገር ግን ርዳታውን የተጠየቁት አገሮች ካቶሊኮች ስለሆኑና ፥— ኢትዮጵያም የሮማ ካቶሊክን እምነትና ሥርዓት ስላልተቀበለች ርዳታው ዘገየ ። በመካከሉም ግራኝ መሐመድ ከቱርክ እየተላላከ ያመጣውን መሣሪያና በድብቅ ያሠለጠነውን ወታደር አሰልፎ ኢትዮጵያን መውረር ጀመረ ። ፲፭ ዓመት ሙሉ ባለማቋረጥ በኢትዮጵያ ላይ የቱርክ ጥይት ነደደ ። ከዮዲት ወረራ ተርፈው የቀሩትና ክርሷም በኋላ የተተከሉት የክርስቲያን ቅርሶች በግራኝ ወረራ ጨርሰው ወደሙ ። በወርቅ በብር የተሠሩ ገዳማት በእሳት ተለበለቡ ፤ ለምሳሌ ፥—የወረኢሉ መካነ ሥላሴ ገዳም ፥ በደብረ ሊባኖስ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምና ሌሎችም በሺህ የሚቆጠሩ ገዳማትና አድባራት እንዳልነበሩ ሆኑ ። ካህናቱና መነኮሳቱም ገዳማቸው ሲቃጠል ሲያዩ በደም ፍላት እሳቱ ውስጥ እየገቡ አረው አለቁ ። የሃይማኖት መጻሕፍትና የታሪክ ሰነዶች የእሳት ራት ሆኑ ። ከሞት የተረፉ ምዕመናንም በሰይፍ እየተገደዱ የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ ተደረጉ ።

ከላይ እንደገለጥነው የግራኝ ወረራ በብዙ መጻሕፍት ስለ ተጻፈ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ያንን ማንበብ ይገባዋል ። እዚህ ላይ ግን የግራኝ ወረራ በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ሕይወት ላይ ያደረሰውን ጉድለት እንመልከት ።—

ሀ. የቤተ ክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ ማለት ፤
ለ. ያለ ካህን ፈቃድ ማግባት ( ዕቁባት ማስቀመጥ ) ፤
ሐ. በሆነ ባልሆነው ሚስት ከባሏ ፤ ባል ከሚስቱ መፋታት
መ. ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች መውለድ ፤

ባጠቃላይም ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመውን ምሥጢራዊ ተሳትፎ ፥— ማለት ንስሐንና ቁርባንን ተክሊልን እየረሱት መሔዳቸው ግራኝ መሐመድ ጥሎት በሔደው እስላማዊ ልምድ ተስበው ነው ። ብዙ የክርስቲያን ቦታዎችም ከግራኝ ወረራ በኋላ ስማቸው ተፋልሶ ቀርቷል ። ለምሳሌ ፥— በባሌ በአቡነ አኖሬዎስ



የተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር ስም ይጠራ የነበረው ቦታ ዛሬ « ኑራ ሁሴን » እየተባለ ይጠራል ። ምንም እንኳ በክርስትና እምነት የሚከለከል ባይኖር በኢትዮጵያ ርጥብ ሥጋ መብላት የተጀመረው ከግራኝ በኋላ ነው ። ይህም የሆነበት ምክንያት ምዕመናኑ በጧያኔነት በዱር በገደል ሲንከራተቱ በነበሩበት ጊዜ ብዙ እህል ስለማያገኙ ቀለባቸው አውሬ እያደኑ ብቻ ነበር ። የአውሬውን ሥጋ ለመጥበስ ደግሞ ጠላት ጢሱንና ሽታውን እየተከተለ መጥቶ እንዳይመታቸው ጥሬውን ይበሉት ነበር ። የእስላም ዜና መዋዕል በመዘገበው ፥ — በግራኝ ወረራ መላው ክርስቲያኖች ሰልመው ነበር ይላል ። የኢትዮጵያ ክብረ ነገሥት ደግሞ ፥— በወረራው ጊዜ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው የኖሩ ኢትዮጵያውያን ከአሥር አንድ ብቻ ነበሩ ይላል ። 65* ነገር ግን በተከታታይ እንደምናየው ከግራኝ ወረራ በማከታተል የተደረገውን የላቲኖች የተንኰል መልእክተኞች 66* ሙከራ በመቃወም በዝተው የተነሱ የምዕመናንና ሊቃውንት ብዛት ክብረ ነገሥቱም ሆነ የእስላሙ ዜና መዋዕል ያቀረቡትን ያስተባብላል ። የወረራው ኃይል ተሸንፎ በተወገደ ጊዜ የጠፉባትን ምዕመናን ፈልጋ ለማግኘትና ወደ ሕጽኗም ለመመለስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ደክማለች ድካሟም በከንቱ አልቀረም ። ብዙዎቹ ተመልሰዋል ። የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ እንባቆም ፈርቶ ወደ እስልምና የገባውን ክርስቲያን ሁሉ መጽሐፈ ቄድር እየተደገመ ጸበል እንዲረጭና ወደ ሃይማኖቱ እንዲመለስ አድርገው ብዙው ተመልሷል ። መጽሐፈ ቄድርን የጻፉም ራሳቸው ናቸው ። የግራኝ ወረራ በተፈጸመበት ጊዜ የነበሩት የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ልብነ ድንግል በስደት እንዳሉ ድባሩአ በሚባለው ቦታ አረፉ ። ልጃቸው አፄ ገላውዴዎስ ነገሡ በርሳቸው ዘመነ መንግሥት የካቲት ፳፩ ቀን (፲፭፻፴፭) ዓ. ም. ግራኝ ተገደለ ። ግራኝ ከሞተ በኋላ በኢትጵያና በፖርቱጋል መካከል ይላላክ የነበ

6. J. Spencer Trimingham, Islam in Ethiopia, (Oxford 1952) P.88.
66 ኢየሱሳውያን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ረው ቤርሙዴዝ ለአፄ ገላውዴዎስ ጥያቄ አቀረበ ። ግራኝን ለመ ውጋት ከፖርቱጋል መንግሥት ርዳታ በተጠየቀ ጊዜ አባትዎ — ከአገራቸው ቆርሰው ለፖርቱጋል ሊሰጡ ከግብፅ ጳጳስ ማስመጣታችሁም ቀርቶ ከሮማ ለማስመጣት ፤ በመላዋ ኢትዮጵያ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት ብሔራዊ እንዲሆን ቃል ገብተውልኝ ነበርና ይህ መፈጸም አለበት ። እኔም የመጀመሪያው አቡን ልሁን አላቸው ። እርሳቸው ግን ለፖርቱጋል መንግሥትም ሆነ ለሮማ የሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች አባታቸው የገቡት ቃል ኪዳን ምን ዓይነት እንደ ሆነ አላወቁም ። ስለዚህም ለተደረገልን ርዳታ የገንዘብ ስጦታ እና ደርጋለን እንጅ ኢትዮጵያን ቆርሰን አንሰጥም ። የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ይሁን ብለን አናውጅም አሉ ። ቤርሙዴዝ በዚህ ጊዜ ተናደደ ፤ ከንጉሡም ተጣላ ፤ ክርክሩና ጠቡ በሁለቱ መካከል ብቻ አልቀረም ያን ጊዜ በጣም የታወቁት ሊቃውንት እነ አባ ዝክሬና እነ አባ ጳውሊ አዲስ ከእስክንድርያ ተሹመው የመጡት ጳጳስ አቡነ ዮሴፍም በወንድማማችነት የተደረገ ርዳታ ስለሆነ ፤ ንጉሡ እንዳሉት ወርቅና ብር እንጅ ኢትዮጵያ ተቆርሳ ለፖርቱጋል አትሰጥም ፤ ሃይማኖታችንንም አንለውጥም ብለው ከቤርሙዴዝ ጋር ተከራከሩ ። ቤርሙዴዝም በንዴት ወደ ሀገሩ ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ለፖርቱጋል ቤተ መንግሥትና ለባቲካን ቤተ ክህነት አቀረበ ።

የሮማው ፓፓ ጳውሎስ ፫ኛ እና የፖርቱጋሉ ንጉሥ ቤርሙዴዝ ባቀረበው መግለጫ ላይ ተወያይተው እንደገና ሌሎች ሚሲዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ተስማሙ ። ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት ከሚላኩት ሚሲዮናውያን የኢትዮጵያን ባህልና ቋንቋ ለማስተማር « የኢትዮጵያ ኰሌጅ » የሚባል ትምህርት ቤት በባቲካን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ተከፈተ ። በዚህ ት/ቤት ለመጀመሪያ የሠለጠኑት ዣን ኦኔዝ ባሬቶ ፤ አንድሬ ኦቢዮዶ ፤ ሚልኪዎሪ ካርኔሮ ናቸው ። እነዚህም ከሌሎች አሥር ሚሲዮናች ጋር ሁነው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የካቶሊክን ሃይማኖት (ዶግማ) እንዲያስፋፉ ተላኩ እነዚህም ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክብር እንደ ጦር ወታደር ሁነው የሚያገለግሉ ኢየሱሳውያን



የሚባሉት ክፍሎች ናቸው ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ፤ ሌሎች ደግሞ ኤጲስ ቆጶሳት ተብለው ነበር ። ነገር ግን ፓትሪያርክ የተባለው ሕንድ አገር ሲደርስ ሞተና በምትኩ አንድርያ ኦቢያዶ ፓትሪያርክ ተባለ ።

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከጳጳሳቸው ከአቡነ ዮሴፍ ጋር ሁነው ከሚሲዮናውያኑ ጋር ክርክር ገጠሙ ፤ ሚሲዮናቹም ለጊዜው የተሸነፉ መስለው ከክርክሩ ሸንጎ ዘወር አሉ ። ዐፄ ገላውዴዎስ ከሞቱ በኋላ በወንድማቸው በዐፄ ሚናስ ዘመነ መንግሥት እነዚሁ ሚሲዮናውያን ክርክራቸውን ቀጠሉ ። ሕዝቡና ካህናቱም ያለ ማቋረጥ ተቃውሞውን ያቀርብ ነበር ። ንጉሡ ኦቢያዶን አስ ጠርተው ሁለተኛ የሮማን ባህልና ሃይማኖት እንዳይሰብክ ከለከሉት። እሱም በዚህ የተነሣ በዐፄ ሚናስ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሒድ ጀመር ። እንዲያውም ከእስላሞች ጋር በምስጢር እየተገናኘ ዐፄ ሚናስ የሚገደሉበትንና የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የሚያዙበት የተንኰል ወጥመድ ሲያጠምድ ይውል ነበር ። 67. በዚህ ስለ ተነሣበት ከግብር አበሮቹ ጋር በግዞት ቤት እንዲቆይ ተደረገ ። ከዚያም አምልጠው በኢትዮጵያ ዙሪያ ሰፍረው ከነበሩ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ከቱርኮች ጋር ተቀላቀሉ ። ንጉሡ ይህን ሲሰሙ ከቱርክ ጋር ተዋግተው ሚሲዮናውያኑን ለመማረክ ዘመቱ ፤ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ስላልቻሉ ተመለሱ ።

ሚሲዮናቹ ግን አሁንም ኢትዮጵያን ወደ ሮማዊ ሥርዓት ለማስገባት ተስፋ አልቆረጡም ። ይህንንም ወደፊት እንመለከተዋለን።

ዐፄ ሚናስ ከሞቱ በኋላ በዐፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት 68. ይኸው አንድርያ ለፖርቱጋል መንግሥት ሌላ አሳብ አቀረበ ፤ ይህም እንደሚከተለው ነበር ። የፖርቱጋል ጦር ኃይል እንዲመጣና የኢትዮጵያን የባሕር በር እንዲይዝ ይህ አድራጐት የፖርቱጋልን መንግሥትና ሕዝብ ከመጥቀሙም በላይ ኢትዮጵያውያን የላቲንን ባህል

67. Archdole A. King, The rites of Eastern Christiandom,
6. [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል የሚል ነበር ። ነገር ግን የፖርቱጋል መንግሥት የእንድርያስ ምክር የማያዋጣው መሆኑን ስለ ተረዳው ሀሳቡን አልተቀበለውም ። ይልቁንም ክርስቲያኑን ሕዝብ እርስ በርሱ ከማጫረስ የክርስቶስን ስም ወዳልሰሙ አሕዛብ ወደ ጃፓንና ቻይና ሔዶ ቢያስተምር የሚጠቅም መሆኑን ለእንድርያስ ተነገረው።

በዐፄ ዘድንግል ዘመነ መንግሥት 69* በአማራ በኩል (ሳይንት) እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚል ሐሳዊ መሲሕ ተነሥቶ ነበር ። የዚህ ሰው እናቱ መርዓተ ወንጌል ትባላለች ። አባቱ ግን አይታወቅም ። ጌታ ክርስቶስ ያደረገውን በማስመሰል ፲፪ የሐሰት ሐዋርያት ፸፪ የሐሰት አርድዕት ፤ ፴፮ የሐሰት ቅዱሳት አንስት ( ሴቶች) መርጦ ትምህርቱን ያሰራጭ ጀመር ። ንጉሡ ይህን ሰምተው ወታደር ልከው አስያዙት ፤ በዚህ ጊዜ ጭፍሮቹ ሁሉ ተበታተኑ፤እሱም ወደ ንጉሡ ፊት ቀርቦ ቢጠየቅ አዎ ፤ እኔ ክርስቶስ ነኝ ፤ ከድንግል ማርያም ተወልጄ ሞቼ ተነሥቼ ወደ ሰማይም ዐርጌ ነበር ። ከቤተ እሥራ ኤል በመወለዴ እሥራኤል ያልሆኑት ሁሉ ባዕድ አደረገን እንዳ ይሉኝ አሁን ደግሞ ከቤተ አሕዛብ ከምትሆን ከመርዐተ ወንጌል ተወለድኩ አላቸው ። እርሳቸውም ፦ « ሰይጣን በሰው እያደረ እንዴት ይጫወትብናል » ብለው በመገረም በሰይፍ እንዲቀጣ አደረጉ ።

በኒሁ በዐፄ ዘድንግል ዘመነ መንግሥት 70* በአባ ጴጥሮስ ፖኤዝ (Poez) የሚመሩ ሌሎች ላቲኖች መጡ ። ወዲያው እንደመጣ ወደ ቤተ መንግሥት ገባ ወጣ ስላበዛ ዐፄ ዘድንግል ወደ ካቶሊክነት ገብተዋል እየተባሉ በሕዝቡና በካህናቱ ዘንድ ይታሙ ነበር ። ሐሜት ብቻ ሳይሆን ካቶሊኮቹና ኦርቶዶክሶቹ እርሳቸው ባሉበት ግራና ቀኝ ሲከራከሩ ለካቶሊኮቹ ያደሉ ነበር ይሏቸዋል ። በሚሲዮኖቹ አግባቢነት ከሮማው ፓፓ ቀሌምንጦስ ፰ኛ እና ከእስፓኙ ንጉሥ ከፊልጶስ ፫ኛ ጋር የወዳጅነት መስመር ዘረጉ ። የካህናቱ እና የምዕመናኑ

69. ፲፭፻፺፮—፲፭፻፺፯
70. ፲፭፻፺፯



የተቃውሞ ድምፅ እየበረከተ ስለሔደ ለዘድንግል እንዳትገዙ ሲሉ ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስ አወገዙ ይባላል ። በዚሁ ምክንያት ዐፄ ዘድንግል ከገዛ መኳንንቶቻቸው ጋር ተዋግተው ሞቱ ።

ኢየሱሳውያን የሚባሉት ካቶሊኮች ተንኰል ውስጥ ውስጡን ሲሔድ ቆይቶ ፤ በይፋ የተከሠተው በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ነው ። 71* ጴጥሮስ ፓኤዝ እንደ አንድርያ አቢያዶ ግትር ሳይሆን በጣም ፈሊጠኛ ነበር ። የሀገሪቱን የአምልኮት ማቅረቢያ ቋንቋ ግዕዝ ተምሮ ይሰብክ ፤ ይቀድስ ነበር ። ወደ ንጉሡም እየቀረበ የሮማ ካቶሊክን እምነት ቢቀበሉ የፖርቱጋል መንግሥት የጦር መሣሪያ ያስታጥቀዎታል እያለ ይሰብካቸው ነበር ። በዚህ ጓጉተው ካቶሊኮች ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚሠሩበት ቦታ ሰጧቸው ። በዚሁ በጴጥሮስ ፓኤዝ እጅ ለእስፓኝና ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዶን ፊልጵስና ለሮማው ፓፓ ለጳውሎስ ፭ኛ ደብዳቤ ላኩ ። ደብዳቤው የጦር መሣሪያ መጠየቂያ ሲሆን በውስጡ የሮማ ካቶሊክን ሃይማኖት ( ዶግማ ) መደገፋቸውን የሚገልጥ ሳይሆን አይቀርም ።

ዐፄ ሱስንዮስ የሮማ ካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን እንደደገፉና ወደነሱም እንደ ተሳቡ ስላወቁ የሱሳውያን የተባሉት የሮማ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን በዋና ዋና መናኸሪያቸው በፍሬምና ( ትግሬ) በጐርጐራ (ደምቢያ) በየቤቱ በየገበያውና በየልቅሶው እየዞሩ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ይጥሩ ነበር ። ምንም እንኳ የሮማ ካቶሊክን ደጋፊ እየተባሉ ቢታሙ ለሰባት ዓመታት ያህል በይፋ አልተጠመቁም ። በ፲፮፻፲፭ ዓ.ም. በጴጥሮስ ፓኤዝ እጅ ከነቤተሰቦቻቸው በሮማ ካቶሊክ ሥርዓት ተጠምቀው ካቶሊክነታቸውን አስታወቁ ። በዚህ ዓመት ጴጥሮስ ፓሬኤዝ ጐራጐራ ላይ ሞተ ። በዚህ ጊዜ አልፎንሱ ሜንዴዝ የተባለው የእስፓኝ ተወላጅ በሮማው ፓፓ በጎርጎርዮስ ፲፭ኛ እጅ 72* በሊዝቦን ተቀብቶ በየካቲት ወር ፲፮፻፲፮

71. ፲፭፻፺፯—፲፮፻፳፬
72. ፲፮፻፲፮—፳፫

www.ethiopianorthodox.org

ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ተብሎ ተሰየመ ። ረዳት የሚሆኑት ሁለት ኤጲስ ቆጶሳትም አብረውት ተሾሙ ። አንዱ ኢትዮጵያ ሳይገባ በሕንድ የፖርቱጋል ቅኝ ግዛት ወደ ነበረችው ወደ ጐዋ (GOA) ሔዶ ሞተ። አልፎንሱና ሌላው ኤጲስ ቆጶስ ፲፳ ቀሳውስት አስከትለው ትግሬ ውስጥ ፍሬሞና ወደምትባለው ቦታ ሰኔ ፳፩ቀን ፲፮፻፳፭ ዓ.ም. ደረሱ ። 73 * በ፩፮፻፳፮ ዓ.ም. ንጉሡ ዐፄ ሱስንዮስ ለሮማው ፓፓ ለኡርባን ፰ኛ ለሮማ መንበር ታማኝ መሆናቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ ላኩ ። በዚሁ ዓመተ ምሕረት የካቲት ፲፩ ቀን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሮም ሥር እንድትተዳደር የሚል አዋጅ ከሱስንዮስ ቤተ መንግሥት ታወጀ ። አዲሱ ፓትሪያርክም ከረዳት ኤጲስ ቆጶሱና ከ፲፰ቱ ካህናት ጋር ሁኖ የኢትዮጵያውያንን ባህልና ሥርዓት በማጣጣልና በማቋሸሽ የሮማውያንን ግን በማጋነንና በማከባበር አዲስ የፕሮፓጋንዳ ለውጥ አወጁ ።

ሱስንዮስና አልፎንሱ በመተባበር ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እንደገና እንዲጠመቁ ፤ ካህናቱ እንደገና እንዲካኑ ፤ አብያተ ክርስቲያናቱም እንደገና በሮማውያን እንዲባረኩ ፤ በውስጣቸውም ያለው በምሥራቃውያን ሥርዓት የተሣለው የቀለም ሥዕል ቀርቶ በሮማውያን ከደንጊያ የተጠረበ (የተቀረጸ ምስል) እንዲቆም የሮማውያን የቅዳሴ ሥርዓትና የቀን መቁጠሪያ ( የጐርጐርዮስ ባሕረ ሀሳብ) በኢትዮጵያ እንዲሠራበት ፤ አርብና ረቡዕ መጾሙ ቀርቶ ቅዳሜ እንዲጾም የቅዳሜም ሰንበትነት እንዲሻር ፤ የሚል ሕግ አወጡ ። ወደ ካቶሊክ እምነት ያልገባና ይህንንም ሕግ ያላከበረ የአካል ቅጣት ይፈጸምበታል የሚል አዋጅ እንዲታወጅ አልፎንሱ ለንጉሡ አቀረበ ። ንጉሡም በዚሁ ተስማሙ ። አልፎንሱና ንጉሡ ከመሰሎቻቸው ጋር የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ሲጥሩ ጳጳሱ አቡነ ስምዖን ደግሞ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተቆርቋሪ የሆኑትን ይዘው ከንጉሡ ጋር ጦርነት ከፈቱ ጦር፤ ነቱንም ለማጠንከር የአባቶቻችንን ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ንጉሡ ለውጠዋልና እርሳቸውን የተከተለ

73. ፍሬሞና ማይጉዓዕ፤



ውጉዝ ከመ አርዮስ ብለው አወገዙ ፤ በጦርነቱም ከጳጳሱ ጋር ሁነው አዝማች የነበሩት ዮልዮስና አባ ዲዮስቆሮስ ከብዙ ካህናት ጋር በጥይት ተመትተው ወደቁ ። አቡነ ስምዖን በዚህ ጊዜ መስቀላቸውን ጨብጠው በጀግንነት የሃይማኖት ልጆቻቸውን በማደፋፈር ላይ እንዳሉ በጦር ተወግተው ሞቱ ። በጦርነቱ ላይ ግን ድሉ የዐፄ ሱስንዮስ ሆነ ።

ከዚያም በኋላ በንዴት ፥— የኢትዮጵያ ትዱሳን አፅም ከረፈበት እየወጣ ይቃጠል ጀመር ። ብዙ ካህናት መነኩሳትና ምዕመናን ልጅ ጋዋቂ ሳይባል የተዋሕዶ ሃይማኖት ልጅ የሆነ ሁሉ እየተመረመሩና እየተጠየቁ ብዙ ሥቃይ ተፈጸመባቸው ።

ከጐጃም ፤ ከቤጌምድር ፤ ከትግሬና ከላስታ ሰማዕትነት እያምለጥሁ እያሉ መጥተው በሱስንዮስ አደባባይ ከ፰ ሺህ በላይ ሕዝብ ረገፈ ። በዚህም የተነሣ ለሰባት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጦርነት ተደረገ ። ንጉሡም በኃይል ጦርነቱን ለማቆም ሽቅብ ቁልቁል በማለት ደከሙ ። ልጃቸው አቤቶ ፋሲልም ምንም እንኳ በጦርነቱ ከአባታቸው ጐን መሠለፋቸው ባያጠራጥርም የርስ በርስ መተላለቁ ሁኔታ እያሳዘናቸው ነገሩን እንዲያበርዱት አባታቸውን ከመምከር አልቦዘኑም ።

ዐፄ ሱስንዮስ በነገሡ በ፳፯ኛው ዓመት ታመው እንደቤታቸው ተዘጋ ፤ በዚህ ጊዜ ልጃቸው አቤቶ ፋሲል ደንግጠው —፤ እግዚአብሔር ይህን ደዌ በአባቴ ላይ ያመጣባቸው የክርስቲያኖችን ደም በከንቱ ስላፈሰሱ ተቀይሞ ነው በማለት ፤ አባቴ እንደቤታቸው ተዘግተ ከፉኛ ታመዋልና አትርሱኝ እኔም ያዘዛችሁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ብለው ወደየገዳማቱና አድባራቱ መልእክት አስተላለፉ ። ያን ጊዜ በጣም ዝነኛ የነበሩት ባሕታዊ የማኅበረ ሥላሴው አባ ዓምደ ሥላሴ ነበሩ ። የገዳማቸውን መነኮሳት አስከትለው ዐፄ ሱስንዮስ ታመው ወደ ነበሩበት ወደ ደንቀዝ መጡ ። ሦስት ሱባኤ በጸሎት በምሕላ ቆይተው ጸበል አጠመቋቸው በዚህ ጊዜ የተዘጋ እንደቤታቸው ተፈታ ። በዚህ ጊዜ ለልጃቸው ለአቤቶ ፋሲል « የእስክንድርያ ሃይማኖት ትመለስ ፤ የሮም ሃይማኖት ትርከስ ፤ ፋሲል ይን

www.ethiopianorthodox.org

ገሥ ብለህ አዋጅ አናገር » አሏቸው ። አዋጁ ታወጀ ፤ ሕዝቡም ተደሰተ ። የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት የደስታ ደወል ድምፅ አሰሙ ፤ በየዋሻው በየበረሃው አልፎንሱ ያሳደደው መምህራንና መነኩሳት መጽሐፎቻቸውን ፤ ታቦቶቻቸውን እየያዙ ወደየቦታቸው ተመለሱ ። በኢየሱሳውያን ካቶሊኮች ተታለው ከቤተ ክርስቲያና ቸው የተለዩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ንስሐ እየገቡ ወደ ቤተ ክርስ ቲያናቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው ።

ዐፄ ሱስንዮስም ብዙ አልቆዩም በነገሡ በ፳፰ኛው ዓመታቸው ሞቱ ፤ ልጃቸው ዐፄ ፋሲል በመንገሣቸው ሕዝቡ የተደሰተውን ያህል በሱስንዮስም መሞት ደስታው የበለጠ ሆነ ። ይህ ሁሉ ሲሆን የደም ሰው አልፎንሱ ግን አሁንም ደንቀዝ ተቀምጧል ።

የፋሲል መንግሥት ሲደላደል በእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መሪ ነት ከአልፎንሱ ሜንዴዝ ጋር ለመከራከር ሊቃውንቱ ፈቃድ ጠየቁ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በጐንደር ጉባኤ ተደረገ ። የተዋሕዶዎቹ አፈ ጉባኤ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ነበሩ ። አልፎንሱ ሜንዴዝም ከወ ገኖቹ ጋር ሁኖ ለክርክር ቀረቡ ። ጥያቄውን የጀመረው ራሱ አል ፎንሱ ሜንዴዝ ነው ። የመጀመሪያው ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር ።

<u>ጥያቄ</u> ፦ አልፎንሱ ሜንዴዝ ፤

« የአብ የባሕርይ ልጁ ሞተ የሚለው ገጸ ንባብ ከምን ይገኛል

<u>መልስ</u> ፦ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ፤

«ጠላቶቹ ስንሆን እግዚአብሔር በልጁ ሞት አዳነን» ይልብሀል ጳውሎስ ሮሜ ፭ ቁ. ፲ መልሱ ትክክለኛ ስለሆነ አላከራከረም ፤

<u>ሁለተኛ ጥያቄ</u> ፦ አልፎንሱ ሜንዴዝ ፤

የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው ፤

<u>መልስ</u> ፦ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ፤

በዚህ ጊዜ መብራት አስበርተው በጉባኤው መካከል አድ ርገው ፦ የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው ? ብለው ጠየቁት ይባ



ላል ። እሱ ግን መልስ አልሰጠም ። መልሱን ራሳቸው መለሱ ፤ የዚህ መብራት ገጽ በዚህ በኩል ብቻ ነው እንደማይባል የእግዚ አብሔርም ፊት በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው አሉት ። ይልቁንም የእ ግዚአብሔር ፊት በክፉ አድራጊዎች ዘንድ ነው የሚለውን የዳዊት መዝሙር በመጥቀስ አልፎንሱ በጓደኞቻቸው ላይ ያደረሰው ግፍ እናዶአቸው ስለ ነበር ፊቱን በጥፊ አሉት ይባላል ። በዚህ ጊዜ የጎንደር ሊቅ ፦

ረከብናሁ ለበትር ዘያደክማ ለሮሜ ፤
ጽሩበ በንባብ ወቅሩጸ በትርጓሜ ።

ብሎ ደስታውን በቅኔ ገለጠ ይባላል ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ፋሲል አል ፎንሱ ከሀገር ለማስወጣት ስለ ፈለጉ የፈጸማቸውን ድርጊቶች ሁሉ በፖርቱጋል ለካቶሊኮች ፓትረያርክ ምክንያቱን ሁሉ ገልጠው ጻፉ ። «የመጡት ሰዎች የሃይማኖት ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ምንም የረዱን ነገር የለም ፤ ያደረጉት ነገር ቢኖር በአባቴ ዘመነ መንግሥት እንዳልተጠመቅን ቆጥረውን እንደገና እናጥምቃችሁ አሉን ፤ ካህና ቶቻችንን ዲያቆናቶቻችንን እንደገና እንካን አሉ ፤ በቤተ መቅደሳችን በእንጨት የተሠራውን የእኛን መንበር አቃጥለው የራሳቸውን የደ ንጊያ መንበር አቆሙ ፤ በእኛ ቀሳውስት የተባረከውን እንዳልተባ ረከ በመቁጠር እንደ ርኩስ ዕቃ በእሳት አቃጠሏቸው ።

የተደረገውን ሁሉ በይቅርታ ለማለፍ የማይቻል ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ የሚደረገው ውይይት ፍሬ የሌለው ነው ። ሕዝበ ክርስቲያኑ ብዙ ሥቃይ ተፈጽሞበታልና ። ከዚህ በኋላ አልፎንሱ ሜንዴዝን ይህ ሁሉ ደም የፈሰሰ በናንተ ምክንያት ነውና ከነተከታዮችህ ከሀ ገሬ ውጡልኝ አሉት ። እነሱም ከጎንደር ወጥተው በትግሬ ፍሬ ሞና በምትባል ቦታ ተደብቀው ሰነበቱ ። በፍሬሞና መደበቃቸውን ዐፄ ፋሲል ሰምተው ባስቸኳይ በምጥዋ በኩል ከኢትዮጵያ እንዲ ያስወጡት ወታደሮችን ላኩ እነሱም ከፍሬሞና መጥተው በምጥዋ

---

74. (Job Luodlphus, Op. cit., p. 364) (J. Spencer, Islam in Ethiopia, [illegible] 99).

www.ethiopianorthodox.org

በኩል ከኢትዮጵያ ለመውጣት መረብን ተሻግረው ከባሕር ነጋሽ ዮሐንስ አካን ዘንድ ሰነበቱ ። ክብረ ነገሥታችን እንደሚለው አልፎንስ አሞኛል ብሎ እዚያ ተኝቶ ከጐንደር ተከትለውት መጥተው ለነበሩት ሁለት ኢትዮጵያውያን የቅብዐትንና የጸጋን እምነት አስተማራቸው ። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ ሁለት እሾህ ተከየባታለሁ አለ ይባላል ። ቅባዐትና ጸጋ ከሮማ ካቶሊክ ባህል ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ ወደፊት እንገልጣለን ።

አልፎንስ ሜንዴዝ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ያን ጊዜ የፖርቱጋል ግዛት ወደ ነበረችው ወደ ሕንድ ሔደ ሕንድ በደረሰ ጊዜም በዘመኑ የካቶሊክ ኃያል መንግሥት ወደ ነበረው ወደ እስፓኝ ንጉሥ መልእክት ላከ።«ኢትዮጵያን ወደ ላቲን ባህል ለመለወጥ አስቀድሞ ሀገሪቱን በጦር ኃይል መያዝ ያስፈልጋል ፤ አለዚያ ግን ድካማችን ሁሉ ፍሬ አላስገኘም» ብሎ የተደረገውን ሉሉ ዘርዝር ጻፈለት ።75.

ነገር ግን የእስፓኝ መንግሥት ኢትዮጵያን በጦር ኃይል ለመውረር ባይታጣም ፤ ጉዳዩ እንዲጠና ወደ ቫቲካን ተላለፈ ። በቫቲካን ተጠንቶ እንደገና የፈረንሣይ ካፑቺኖችን ለመላክ ምልመላ ተጀመረ። ይህንንም ዐፄ ፋሲል ሰምተው ያለኔ ፈቃድ ማንንም የውጭ አገር ሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳታሳልፉብኝ ሲሉ በምጥዋ ዙሪያ ሰፍረው ከነበሩ የቱአኪን ፓሻዎች ጋር ስምምነት አደረጉ ። ስለዚህም ለጥቂት ጊዜ የካቶሊኮች ጉዞ ጥቂት ጋብ አለ ።

ዐፄ ፋሲል በሃይማኖት አሳብቦ የሚመጣ ማንኛውንም ኃይል ከቤተ ክርስቲያን ጐን ሁነው የተከላከሉት ስለ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው ። አንደኛ በተዋሕዶ ሃይማኖት የሚያምኑ የቤተ ክርስቲያን አባል እንደመሆናቸው መጠን ሃይማኖታቸው ስለሚያስገድዳቸው ነው ። ሁለተኛው ግን ከርሳቸው በፊት የነበሩ አባታቸው ወደ ባዕድ ሃይማኖት በመግባታቸው ሕዝቡን እስከ መከፋፈል ደረጃ አድርሶት ስለ ነበር ፤ ሕዝብ እንዳይከፈል ሀገር እንዳ

75. cf. C. Beuari R.A.S.O., Vol. XIII (1913) letters nos. 13 and 23 to the king of Spain; Job Ludoiphus, Op. cit. (p. 265).



ይቆረስ በነበራቸው ብሔራዊ ስሜት ነው ።76. ኢትዮጵያ ያን ጊዜ እንደ ፋሲል ያለ ፤ እንደ ገላውዴዎስ ያለ መሪ ባይኖራት ፤ እንደ ዛሬ ሮዴሺያና ደቡብ አፍሪካ ሁና ትቀር ነበር ።

አልፎንሱ በሐማሴን አሞኛል ብሎ ተኝቶ በድብቅ የቅብዐትና የጸጋን ሃይማኖት ያስተማራቸው ሰዎች ኤዎስጣቴዎስ ዘሳንኪ ጊዮርጊስ (ጐጃም) ፤ ቁረንጭ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖት (ዘሸዋ) ናቸው ። የቅበዐትን ባህል ያስተማረው ለኤዎስጣቴዎስ ነው ። የጸጋን ባህል ለተክለ ሃይማኖት ነው ። ቅብዐትና ጸጋ በንባብ እንጂ በምሥጢር አንድ ናቸው ። የሮማ ካቶሊክ ሁለት ባሕርይ ዘውግ ናቸው ። የያንዳንዳቸውን ዶግማ በቦታው እንገልጸዋለን ። በተዋሕዶዎች እና በሮማ ካቶሊኮች መካከል በተደረገው ጦርነት ፣— የተዋሕዶዎች የጦር አበጋዝ ሁነው የዋሉት ብፁዕ አቡነ ስምዖን በጦር ተወግተው ከሞቱ በኋላ አንድ ቀሳጢ ግብጻዊ ጳጳስ ነኝ ብሎ መጥቶ ሲቀስጥ ቆይቶ በኋላ ጓደኛው ቀሳጢነቱን ነግሮበት በደቅ ታሥሮ ይኖር ነበር ። ኋላ ግን ዐፄ ፋሲል ወደ ግብፅ ተላልከው አቡነ ማርቆስ የተባሉትን ጳጳስ አስመጡ ። የቅበዐትና የጸጋ ሃይማኖትም እንደ ሰደድ እሳት ውስጥ ውስጡን ተያይዞ ስለ ነበረ ፤ አዲሱ ጳጳስ እንደ መጡ ቅብዐቶች ከተዋሕዶዎች ጋር እንከራከር ቀን ይቀጠርልን ብለው አመለከቱ ። በዚህ ጊዜ የአልፎንሱ ንግር ደረሰ በሃይማኖት የርስ በርስ መለያየት ተጀመረ ። ንጉሡና ጳጳሱ በተገኙበት እንዲከራከሩ ተፈቀደ ። በተወሰነው ቀን የቅብዐቶች ተወካይ ዘኢየሱስ የተባለ ሰውና የተዋሕዶዎች ተወካይ አዳም ዘእምፍራዝ ክርክር ገጠሙ ። በመጨረሻም የተዋሕዶዎች ተወካይ አዳም ዘእምፍራዝ አሸነፈና ጉባኤው አበቃ ። ነገር ግን የሚሲዮናች አሳብ ርስ በርስ አለያይተው ዘወር ለማለትና ኋላም እነሱ የዘሩት ልዩነት ወንድማማች ሲጋደሉ ለመሣቅ ከተመቸም አስታራቂ መስለው ገብተው አገርን ለመያዝ ስለሆነ ፤ ከገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ባንድነት ሁነው ከውጭ የመጣ የሃይማኖትም ሆነ የሀገር

76. J. Spencer Islam in Ethiopia, Oxford 1952 (p. 100).

www.ethiopianorthodox.org

ጠላታቸውን ድል ሲያደርጉ የኖሩ ኢትዮጵያውያን እዚህ ላይ በአልፎንሱ ተንኰል በተመረዙ ሁለት ሰዎች ስብከት መለያየታቸውና ርስ በርስ ደም መፋሰሳቸው ያሳዝናል ። በቤተ መንግሥትም በየጊዜው የሚነግሡ ነገሥታት አንዱን አንዱ ሲደግፍ አንዱን አንዱ ሲነቅፍ ከባድ ችግር ተፈጥሮ ነበር ፤ ለምሳሌ በዐፄ ዮሐንስ ቀዳማዊ (አዕላፍ ሰገድ) ዘመነ መንግሥት በቅባቶችና በተዋሕዶዎች መካከል ተነሥቶ በነበረው ክርክር ንጉሡን ወዳንድ ወገን አደሉ በመባል አሳምፀቻቸው ነበር ።

ዐፄ ዮሐንስ ቀዳማዊ ወዲያው እንደ ነገሡ ቅብዐቶችና ጸጐች አንድ ወገን ሁነው ከተዋሕዶዎች ጋር እንድንከራከር ይፈቀድልን ብለው ጠየቁ ። ጉባኤው ተፈቀደ ፤ ጉባኤው በተደረገበት ዕለት የጥያቄው ቅድሚያ ለተዋሕዶዎች ተሰጠ ። የተዋሕዶዎቹ ተወካይ ቅብዐቶችና ጸጎች አንድ ወገን ሁነው እንደ መጡበት አውቆ አስ ቸጋሪ ጥያቄ ጠየቃቸው ።—

ጥያቄ ፦ የተዋሕዶዎች ተወካይ ፤ ሃይማኖት አንዲት ናት ወይስ ሁለት ?

የቅባቶችና የጸጐች ተወካይ ግን ሁለት ብል ጳውሎስ ሃይማኖት አንዲት ናት ብሏልና ያስረታኛል ፤ አንዲት ናት ብል ቅብዐትና ጸጋ ተባብረናልና የናንተ ሃይማኖት ሁለት ነው ብሎ ይረታኛል ብሎ ደንግጦ ዝም አለ ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ጣልቃ ገብተው ይህን ተውና ሌላ ጥያቄ ጠይቅ አሉት እሱም ንጉሡ እንዳደሉበት ተሰምቶት ቀን ይሰጠኝ አለ ። ስምንት ቀን ተሰጠው እነዚያም ንጉሡ ያደረጉላቸውን ድጋፍ በመግለጥ በየመንገዱ ዳር ፦ « ዛሬ ንጉሡ ለኛ ባያደሉ ተረትተን ነበር » እያሉ በደስታ ወደየቤታቸው ሔዱ የተዋሕዶዎቹ ተወካይ ግን ዳኛ በማጣቱ ተናዶ ተማሪዎቹን ሰብስቦ አገሩ አክሱም ነበር ፤ ወደ አክሱም ሔደ ይባላል ። በዚያ ጊዜ የነበሩ ሊቃውንት ሃይማኖታቸውን የሚመሠክሩት በቅኔያቸው ነበር መናፍቃንንም በቅኔ ይገሥጿቸው ነበር ። ለምሳሌ የሮማን የሁለት ባህርይ እምነት ሲነቅፉ ፦ ሊቃውንት ከተቀኟቸው ፤



ቃለ እምነ ሥጋ
በአፍአ ፈለጡ ውሉደ ሮሜ
ዘንተኒ ልማደ ዘአፍአ (ዘሮሜ) ከመ ኢንግበር ልማደ
ዋሕድና ክልኤቱ በታቦር ተግህደ
ዘሰገደኒ ሊቃል እንዘ ይሬሲ አሐደ
ለሥጋ ሰገደ ኀበ ሰገደ
ባዕደ አብ እስመ ኢወለደ
ወድንግል ኢወለደት ባዕደ ።

በዚሁ ዓይነት የሮማ ሃይማኖት ቅርንጫፍ የሆኑትን ቅብዐቶችንም ይገሥጿቸው ነበር ።

የተዋሕዶ ሊቅ ቅብዐቶችን ሲነቅፍ የተቀኘው ፦

መንበረ ኪሩባዌ
እመ በቅብዐት ወረሰ ፍሬ ከርሥኪ ዕጹብ
ዘወርቀ ድንጋሌ ማርያም መሶብ
እስመ ከማሁ ኩልነ ሱቱፉነ ቅብዓት ሕዝብ
እስፍንተ ያገምር መንበሩ ለአብ
ወእስፍንተ ይጸውር ኪሩብ ። ይህንና ይህን የመሳሰለ ቅኔ ይቀኙ ነበር ። የቅብዐቶችና የጸጐች አዲስ ትምህርት ሆነ ተብሎ ለማለያየት የተተከለ እሾህ ስለሆነ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ካህናትን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ከመንግሥት ፤ መንግሥትንም ከሕዝቡ ማለያየቱን ቀጠለ ።

ኤዎስጣቴዎስ በሀገሩ በጐጃም ቅብዐትን አስፋፍቶ ስለነበር የጐጃም ባላባቶችና ከሊቃውንቱም ብዙዎቹ ቅብዐቶች ነበሩ ። በጐንደርና በሸዋም ቁረንጭ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖት የጸጋን እምነት ስላስተማረ ሊቃውንቱ ሁሉ ይተማሙ ነበር ።

ከላይ እንዳየነው በቀዳማዊ ዮሐንስ ጊዜ ተሰሚነት የነበራቸው ቅባቶች ነበሩ ። በልጃቸው በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ግን ወደ ቤተ መንግሥት መግቢያ አላገኙም ። የሃይማኖት ክርክርም አልተነሣም ። ከአድያም ሰገድ ኢያሱ በኋላ በዐፄ ተክለ ሃይ

www.ethiopianorthodox.org

ማኖት ዘመነ መንግሥት እንደገና ጉባኤ እንዲደረግ ተወሰነና ንጉሡና ጳጳሱ በተገኙበት ጉባኤ ተደረገ ። በዚህ ጉባኤ ላይ ተዋሕዶዎቹ ረቱ ፤ ጳጳሱ አቡነ ማርቆስም ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስን በቅብዐት የባሕርይ ልጅ የሚለውን ሁሉ አወግዛለሁ አሉ ፤ ቅባቶች በብዛት ተስፋፍተው የነበሩ በጐጃም ስለ ነበር ለዚህ ጉባኤ ከጐጃም ወደ ጐንደር መጥተው የነበሩት ሁሉ ታሠሩ ። ከአፄ ተክለ ሃይማኖት በኋላ የነገሡት ዐፄ ቴዎፍሎስ ግን የጐጃሞችን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ እንደአባቶቻቸው ጉባኤ ሠርተው ክርክር ሳይሰሙ እንኳ « ክርስቶስ በቅብዓት የባሕርይ ልጅ ነው » የሚል አዋጅ አወጁ ። በዚህ ጊዜ የተዋሕዶዎች ክፍሎች ቀርበው ምነው ንጉሥ ሆይ እንደአባቶችዎ ዘመን በይፋ በጉባኤ ሳንከራከር እንዲህ ያለ አዋጅ አወጁብን ብለው ቢጠይቋቸው ጐጃሞችን ስለምወድ ነው የሚል መልስ ሰጧቸው ይባላል ። በዚህም ጊዜ ተዋሕዶዎቹ አዝነው ተመለሱ ። ከዚህ በኋላ የውስጥ ለውስጥ ትርምስና በንጉሡም ላይ ጥላቻ ተፈጠረ ።

በውስጥ ያለው ብጥብጥ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ በ፩ሺ፮፻፲፩ ዓ.ም. ላይ የነገሡት ዐፄ ዮስጦስ የጦር መማሪያ እንዲያቀብሏቸው ሦስት የካቶሊክ ሚሲዮናችን በወልቃይት ዐይነ እግዚእ በሚባል ቦታ በድብቅ አስቀምጠው ይማከሩ ኑሮ ፤ እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ምሥጢር ተገለጠ ። ሰዎቹ የመጡት አንዱ ከኦስትሪያ ፤ ሁለቱ ከሮም ነው ። ስማቸውም ሚካኤል — ሳሙኤል — ዳዊት ይባላሉ ። ዐፄ ዳዊት አብራክ ሰገድ በሺ፮፻፲፮ ዓ.ም. ሲነግሡ እነ አባ መዝሙር የተባሉ በነዚህ ሚሲዮናችና በሟቹ በዐፄ ዮስጦስ መካከል ስለ ነበረው የውስጥ ግንኙነት የተደበቀውን ምሥጢር አውጥተው የተደበቁት ሚሲዮናች ይቅረቡልን ብለው አቤት አሉ ። ጉዳዩን ለመስማት ጉባኤ ተሰበሰበ ፤ እነሱም ወደ ጉባኤው ቀርበው ሃይማኖታቸውን ቢጠየቁ ካቶሊኮች ነን አሉ ። በዚህ ጊዜ የተሰበሰቡት ሊቃውንትና የሃይማኖት ሰዎች እነዚህማ በሱስንዮስ ዘመን ብዙ ደም ያፋሰሱ አይደሉም ወይ ብለው ይሙት በቃ ፈረዱባቸው ። ወዲያው የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸው ።



እነዚህ ሚሲዮናች ከተገደሉ በኋላ ቅባቶች ከተዋሕዶዎች ጋር ለመከራከር ጉባኤ እንዲደረግላቸው ንጉሡን ዐፄ ዳዊትን ጠየቋቸው የንጉሡ ቢትወደድ ዘጊዮርጊስ ራሱ ቅባት ስለ ነበር እሱ እንደሚረዳቸውና እንደሚያሸንፉም ተስፋ አድርገው ነው ። ንጉሡም ጉባኤው እንዲደረግ ፈቀዱ ፤ ነገር ግን በጉባኤው ላይ ለመገኘት ስለአልፈቀዱ ቢትወደዳቸው ዘጊዮርጊስ በጉባኤው እንዲገኝ አዘዙ ። በዚህ ጊዜ የተዋሕዶዎቹ ክፍሎች ይህ ሰው ቅባት መሆኑን ስለሚያውቁ የሱን ውክልና አልተቀበሉትም ። በመካከሉ ንጉሡ ራሳቸውን ከሐሜት ለማዳን ሲሉ ጉዳዩ ሃይማኖትን እንጂ አስተዳደር የሚመለከት ስላልሆነ ወደ ንጉሥ መቅረብ የለበትም ። በጳጳሱ በአቡነ ክሪስቶዶሉ ( ገብረ ክርስቶስ ) መታየት አለበት ብለው ወደ ጳጳሱ መሩት ። ጳጳሱ ግን እንደነ አቡነ ስምዖን ያይደሉ ፍርሀትና አድር ባይነት ያጠቃቸው ሰው ስለ ነበሩ ፤ የንጉሡንና የቢትወደድ ዘጊዮርጊስን ዝንባሌ ተመልክተው ፡— « ሃይማኖትዎ ምንድነው ? » ተብለው ቢጠየቁ « ሃይማኖቴ ተዋሕዶ ነው » በማለት ፈንታ «ሃይማኖቴ ከኔ በፊት እንደነበሩት እንደ አባ ማርቆስና እንደአባ ሲኖዳ ነው » ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ የቅባት ወገኖች የሆኑት በቢትወደድ ዘጊዮርጊስ አቅራቢነት ወደ ንጉሡ ቀርበው ጳጳሱ የተናገሩትን ነገሯቸው ፤ ንጉሡም የአባ ማርቆስና የአባ ሲኖዳ ሃይማኖት ምን ነበር አሏቸው ። እነሱም ቅባት ነዋ ! ብለው በድፍረት ተናገሩ ንጉሡም እንግዲያውማ « በተዋሕዶ የባሕርይ ልጅ የሚሉት ተረቱ ፤ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ሆነ የሚሉት ረቱ » ብላችሁ አዋጅ ንገሩ አሉ ፤ አዋጅ ተነገረ ። የተዋሕዶዎቹ ክፍሎች በጳጳሱ መልስና በንጉሡ አዋጅ አዝነው ጳጳሱን እንደገና ሒደው ቢጠይቋቸው ብቻቸውን ስለ ነበሩ « ሃይማኖቴ ተዋሕዶ ነው » አሏቸው ።

በዚህ መልስ ደስ ብሏቸው ወደ እጨጌው መኖሪያ ቤት አዘዞ ተሰብስበው ሒደው ንሴብሖ እያሉ ሲዘምሩ ንጉሡና ቢትወደዳቸው ጐንደር ወሬው ደረሳቸው ። በዚህ ጊዜ አዋጃችንን ጥሰዋል ብለው በጣም ተናደዱ ንዴታቸውንም ለመወጣት በጐንደር አካ

www.ethiopianorthodox.org

ባቢ የሚኖሩ ጃዊ የሚባሉትን የእስላምና የአረማውያን ክፍሎች አስታጥቀው በእጨጌው ቤት የተሰበሰቡትን ሁሉ አንድ እንኳ ሳያተርፉ ፈጅዋቸው ። በዘመኑ የነበሩት እጨጌ ተክለ ሃይማኖትንም እግራቸውን ከከብት ጭራ ጋር አሥረው መሬት ለመሬት ራቁታቸውን እየጐተቱ አውለው ገደሏቸው ። በዚያ ጊዜ በተዋሕዶዎቹ ላይ የተፈጸመው ግፍ በአልፎንሱና በሱስንዮስ ጊዜ ከተፈጸመው የማያንስ ነው ። ጳጳሱም ከላይ እንደተገለጠው እንደ አባቶቻቸው ያይደሉ ፈሪና መስሎ አዳሪ ስለነበሩ በንጉሥና በቢትወደዱ ትእዛዝ እንደገና «በቅብአተ መንፈስ ቅዱስ የባህርይ አምላክ ሆነ» ብለው አወጁ ። በተዋሕዶዎቹ ሥቃይ ቅባቶቹ ከልክ ያለፈ ተደሰቱ ። ይህም የርስ በርስ ደም መፋሰስ የአልፎንሱ ሜንዴዝንና በጠቅላላውም የውጭ ሚሲዮናችን ተንኮል ሲያስታውስ የሚኖር ነው ።

ያን ጊዜ በተፈጸመው ዕልቂት ከተደሰቱት ክፍሎች አንዱ የተቀኘው ፤

ሰላም እብል ለሰብለ አዘዞ ፀረ ቅባት
ወእጨጌሆሙኒ እጨጌነት ከሚስት
ሶበ እንቢ ለግዜር ይቤሉ ወእንቢ ለንጉሥ ዳዊት
ጃዊ ቀደደ ሆድ ሆዶሙ ወሰለቦሙ እስከ ጎንበርት
ወበእንተዝ ይቤሉ በ፺ ዓመት ግዝረት ።

የቅባቶችና የተዋሕዶዎች ክርክርና ጠብ በዚሁ ብቻ የተፈጸመ አይደለም አሁንም ወደፊት እናየዋለን ።

1769-1855 — 1995

## ምዕራፍ ፰ ፤

# ከዘመነ መሣፍንት እስከ አሁን

ከ፲፯፻፷፱—፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ድረስ ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ እንደ ቅርጫ ሥጋ ተከፋፈለች ። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንም እየተዳከመች ሔደች ። የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያሁኑን ይዞታዋን ለማወቅ በየጊዜው የደረሰባትን ወረራ ስናውቅ ብቻ ነው ። በዚህ በዘመነ መሳፍንት ነገሥታቱን ለምስል ብቻ እንግሠው እያስቀመጡ አገሪቱን የሚመሩት እምባ ገነን መሳፍንትና መኳንንት ስለ ነበሩ ዘመናቸውም ዘመነ መሳፍንት ተብሏል ። እነዚሁ መሳፍንት እርስ በርሳቸው ስለማይስማሙ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ከውጭ አገር መሣሪያ ለማስገባት በሚሲዮኖቹ አማካይነት ወደ የመንግሥታቱ ይላላኩ ነበር ። በዚህ አጋጣሚ ሚሲዮኖቹ ሃይማኖታቸውን ለማሠራጨት አመች ጊዜ ሆነላቸው ። በየመኳንንቱ ቤት እየተቀመጡ አማካሪዎች ሆኑ ። በተለይ በሰሜኑ ክፍል ኤርትራን ለምሳሌ ብንወስድ ከኤርትራ ክፍል ብዙዎቹ [illegible] እስልምና የሔዱት በዚሁ በዘመነ መሳፍንት ነው ። በዚህ ክፍለ ሀገር ቆለኞቹ ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት ካህናትና የሃይማኖት መምህራን አይተው ስለማያውቁ የእስላም ወራሪ በመጣባቸው ጊዜ የቤተ ክርስቲያናቸውን ንዋያተ ቅዱሳት ተሸክመው በረሀ ለበረሀ በመዞር የሃይማኖታቸው መጠበቂያ አድርገውት እንደኖሩ ቤታሪክ ይታወቃል ። ኋላ ግን ካህን የማጣቱ ችግር እየቀጠለ ስለሔደ አባቶች አልፈው ልጆች ሲተኩ የሃይማኖታቸው ምልክት የነበሩት ንዋያተ ቅዱሳትም በየዋሻው ምስጥ እየበላቸው ተበጣጥሰው ሲያልቁ ወደ እስልምና ሃይማኖት ተሳቡ ። የራሳቸውን ባህል ስላጡት የቱርኮችንና የዓረቦችን ባህል ተሸከሙ ። «በኒ አሚር» የሚባሉት መሠረተ ክርስቲያኖች የመሐመድ ተከታዮች ለመሆን የበቁት «በፋካራ ፋንጅ» ተስበው« በመሐመድ አትማን

www.ethiopianorthodox.org

እልሚርጋኒ» ተሰብከው ነው ። ይህ ሰው ብዙዎቹን ክርስቲያኖች ወደ እስልምና መልሷል ። የላከውም «አህመድ ኢብን አድሪስ» የገብዕ መሪ የነበረው ነው ። 77. ማሪያና ቤት አሰገደ የሚባሉት ደግሞ 78. «አድ ሻይኽ» በሚባሉ የእስላም ሚሲዮኖች ተሰበው እስላሞች ሆኑ ቢለን ~~ቀቀ~~ባሉት ባላባቶችም ግብጻውያን ቀይ ባሕርን በያዙ ጊዜ እንደሌሎቹ ዘመዶቻቸው ከቤተ ክርስቲያናቸው ተለዩ በዚህ ምክንያት በመጀመሪያ ጠንካራ የክርስቲያን ይዞታዎች የነበሩ ሁሉ የእስላም ይዞታዎች ሆኑ ብዙ የሰውና የቦታም ስሞች ሳይቀሩ በክርስቲያኖች ታሪክ መሠረት ተሠይመው ከነበሩበት ቀለ ውጠው በዓረብ ስም መጠራት ጀመሩ ። 79. በሰሜኑ ክፍል ይህ ጉዳት የደረሰባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በደቡብና በምዕራቡ ክፍል ተመሳሳይ ጉዳት ደርሶበታል ። በደቡብና በምዕራብ የነበረው የክርስትና ታሪክ በሰሜን ከነበረው የማያንስ ነበረ ። አሁን ግን ሁሉንም አረም ውጦት ተገኘ ።

ስለ ደቡብ ክፍል የክርስትና ታሪክ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ሐዋርያዊ ጉዞ እንኳ ብንጠቅስ አጭር አይደለም ። እርሳቸው የነበሩ በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ። የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጉዞአቸውንም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አድርገው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ማሳነጻቸውን ብዙ ገዳማትንም መመሥረታቸውን ገድላቸው ይነግረናል ። ተልዕኳቸውን ፈጽመው በደብረ ሊባኖስ ገዳማቸው በተወሰኑበት ጊዜም በመላ ኢትዮጵያ ፲፪ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ሲያሰማሩ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያም ዕጣ የደረሳቸው ብዙ ገዳማትን ሠርተዋል ። የክርስቲያኖችን ሕይወትም በክርስቲያናዊ ትምህርት መሥርተዋል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምንም እንኳ አልፎ አልፎ ከጐረቤት አገሮች የሚመጡ የዓረብ ሚሲ

77. ፩ሺህ፰፻፲፪ ።
78. ፩ሺህ፰፻፲፰ ።
79. J. Spencer, Islam in Ethiopia (Oxford, 1952) p. 113.



ዮኖች መኖራቸው ባይካድም ክርስትና በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ የጠነከረ ኃይል ነበረው ።

ከላይ እንደ ተናገርነው ኢትዮጵያ በመሳፍንት በተከፋፈለች ጊዜ ግን የደቡብና የምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ብዙውን ወደ እስልምና እና ወደ አረማዊነት ተለወጠ ። በክርስትናቸው የጸኑትም እስከ አራት ትውልድ ድረስ ካህን አይተው አያውቁም ነበር ። ሃይማኖታቸውንም የሚያውቁት ካባቶቻቸው ባገኙት ልማድ ብቻ ነበር ። ለምሳሌ በሊሙ 'እናርያ) አጠገብ ኖና በሚባለው አገርና በአካባቢውም ጥንት ሳይለወጥ የመጣውና የአባቶቻቸውን የክርስትና ሃይማኖት ጠብቀው የኖሩ ክርስቲያኖች ነበሩ ። አጽዋማት በአላትን ሳይቀር ባህረ ሐሳብ ሳይኖራቸው ራሳቸው በልማድ ያወጧቸው ነበር ። በአካባቢዋ ላሉት የክርስቲያን አውራጃዎችና መንደሮች መሪ ብርሃን የነበረችው ኖና ለመቶ ዓመታት ያህል ካህን አይታ አይታወቅም ነበር ። በቄስ ማጣት ምክንያት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች እምነት እንጂ ጥምቀት አልነበራቸውም ።

ከኖና ቀጥሎ ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን የሚኖርበት አገር ሞቻ የተባለው ነው ። በሞቻ ግራኝ እንኳ ያላፈረሳቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ ። የዚህ አገር ክርስቲያኖች በየሳምንቱ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሰበሰቡበት ጊዜ ቀድሶ የሚያቆርብ ቄስ ስላልነበራቸው ልጆቻቸውን አዝለው ቤተ ክርስቲያኑን እየዞሩ «ንስእለኪ ማርያም» እያሉ ልመናቸውንና ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር አሰምተው ይመለሱ ነበር ። 80. ይህ ዓይነቱ የክርስቲያኖች ችግር በጣም እየባሰበት ሔደ ። የዚህ ክፍል ባላባቶችና ታላላቅ ሰዎችም ከሱዳንና ከአረብ አገሮች የሚመጡ ሽቱና ልዩ ልዩ የጌጥ ዕቃዎችን ለማግኘት ሲሉ ከዓረብ ነጋዴዎች ጋር ወዳጅነት አበጁ በዚህ ሳቢያ አረቦች ሃይማኖታቸውንም ቀስ በቀስ አስጠኗቸው ። የእስልምናን ሃይማኖት ያለምንም ችግር ተቀበሉ ። አሊታው ከተ

80. "Annales de la Porop de la Foi XVII 279.

www.ethiopianorthodox.org

ያዘ የጭፍራው ኃይል አይመከትምና ሕዝቡም እነሱን እያዩ ተገልብጠው ሰለሙ ። ብሔራዊና ክርስቲያናዊ ስማቸውንም ትተው በአረብ ስም መጠራት ጀመሩ ። በወንጌል ፈንታም ትምህርቱ ቁርዓን ሆነ በጠቅላላ ጥንተ ክርስቲያን የነበሩት ክፍሎች ለምሳሌ በከፋ ክፍለ ሀገር ብቻ እንኳ ጌራ ፤ ጉማ ፤ ሊሙ ፤ (እናርያ) የሚባሉት ሁሉ ባንድ ጊዜ ወደ እስልምና ተለወጡ ።

በዚህ የጨለማ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታደርገውን አጥታው ስትቸገር በመከራዋ ላይ መከራ ለመጨመር በመሀል አገር ያለውን ክርስቲያን ደግሞ ለመከፋፈል 81. የሮማ ፓፓ የነበረው ጎርጎርዮስ ፲፭ኛ በ፩ሺ፮፻፴፱ ዓ.ም. የላቲን ሚሲዮኖችን በብዛት ላከባት ። በኋላም ፩ሺ፮፻፵፮ ዓ. ም. 82. ጉግልዬልሞ ሞሳላ የተባለው ሚሲዮናዊ (ካቶሊክ) በከፋና ባንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ግዛቶች እየተዘዋወሩ በክርስቲያኑ ሕዝብ መካከል የሚለያይ ትምህርት ያስተምር ጀመር ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ልቡና እንዳሰበው ልል ሁኖ አላገኘውም ። የሕዝበ ክርስቲያኑ ጠንካራነት መከራውን ሳይሰቀቅ ታግሎ እምነቱን ቢያቆይም ፤ ቤተ ክርስቲያናችን በዘመነ መሳፍንት ብዙ ቅርሶቿን አጥታለች ።

በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም ከነበሩን አያሌ ቦታዎች ብዙዎቹን የተነጠቅነው በዚሁ በዘመነ መሳፍንት ነው ። የውስጥ ብጥብጥ ስለ ነበረ በየዓመቱ ለትንሣኤ ወደ ኢየሩሳሌም ይደረግ የነበረው ጉዞ ተቋረጠ ። እዚያ ይኖሩ የነበሩትም መነኮሳት በችግርና በሕመም አለቁ ። በዚህ ጊዜ በየምክንያቱ ባለቤት የሌለው የጠፍ ንብረት ሁኖ በአርመኖችና በግሪኮች ብዙ ንብረት ተወሰደ ። ለምሳሌ ጥንት በጎልጎታ ውስጥ የታሪክ ቦታዎች ያሏቸው ግሪክ ፤ አርመን ፤ ኢትዮጵያ ፤ ሶርያና ግብፅ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ከነዚህ ተለይታለች ። ሌሎቹ ግን እስካሁን ድረስ ርስታቸውን እንደያዙ ናቸው ።

81. ፩ሺ፰፻፴፩—፵፯
82. Guglielmo Mossala.



በዘመነ መሳፍንት መጀመሪያ ላይ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ 83. ከሞቱ ወዲህ በኢትዮጵያ ጳጳስ ስላልነበረ ፤ የትግሬ ፤ የስሜንና የላስታ መስፍን የነበሩት ደጃዝማች ውቤ ለመንግሥ አስበው ጳጳስ እንዲላክላቸው አለቃ ሀብተ ሥላሴ የተባሉ ባለሟላቸውን መልእክት አስይዘው ወደ እስክንድርያ ላኩ ። ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ የሲኖዶስ ስብሰባ አድርገው በምንኩስና ስማቸው አባ እንድርያስ ይባሉ የነበሩትን የ፳፭ ዓመት ወጣት መነኩሴ አባ ሰላማ ሣልሳይ ብለው ቀብተው ወደ ኢትዮጵያ ላኳቸው ። 84. አቡነ ሰላማ ከመምጣታቸው ቀደም ብሎ በሸዋ የይፋቱ ባላባት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሁለት ልደት (ተዋሕዶ ማለት ነው) የምትል ሁሉ ሀገሬን ልቀቅልኝ ብለው አዋጅ ነግረው ስለ ነበር ብዙ የተዋሕዶ ሊቃውንት እነ አለቃ ወልደ ኪዳን ከሸዋ ተባረው በጎንደር ይኖሩ ነበር።

አቡነ ሰላማ «በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ የባሕርይ ወይም የጸጋ ልጅነትን አገኘ» የሚሉትን የቅብዐትና የጸጋ ክፍሎች እያወገዙ የተዋሕዶን እምነት ሲያስተምሩ ብዙ ጭቅጭቅና ብጥብጥ ተነሣ። ቅብዐት ፤ ጸጋና ካቶሊክ የሆኑት ተባብረው በአቡነ ሰላማና በተዋሕዶዎቹ ላይ ያድሙ ጀመር ። በዚህም ምክንያት በጐጃም ፤ በበገና በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ ቅብዐትና ጸጋ የሆኑ ሁሉ መልእክተኞቻቸውን ወደ ጳጳሱ እየላኩ ብዙ ብጥብጥ አስነሱ ። በዚህ ጊዜ አቡነ ሰላማ የተዋሕዶዎቹን ሊቃውንት አስከትለው ወደ ትግሬ ተሰደዱ ። ቅብዐትና ጸጐቹም አሸነፍን ብለው እየተደሰቱ ወደ የሀገራቸው ተመለሱ ። ከሸዋ ለመጡት መልእክተኞች መሪ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤት የሚኖር ደብተራ አሥራት የሚባል ሰው ነበር ። እሱ ከነተከታዮቹ ወደ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤት ሲገባ የድል አድራጊ አቀባበል ተደረገለት ። አዝማሪም እንዲህ ብሎ ገጠመ ይባላል ።

83. ፩ሺ፰፻፳፩
84. ፩ሺ፰፻፴፪ ኅዳር ፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደ አሥራት ማን አለ የሚያውቀው ድኅውን ፥
ትግሬ መርቶት መጣ ያን ረጅም አቡን ።

ያን ጊዜ ትግሬን የሚገዙትና አቡነ ሰላማንም ያስመጧቸው ደጃዝማች ውቤ በጸጋንት ይታሙ ስለ ነበር ጳጳሱ አሁንም የመንፈስ ዕረፍት አላገኙም ። ስለዚህም ደጃዝማች ካሣ (ቴዎድሮስ) በሃይማኖት ፍጹም ተዋሕዶ መሆናቸውን ሰምተው አብረዋቸው የነበሩትን ሊቃውንት አስከትለው ወደ ደጃዝማች ካሣ መጡ ። እርሳቸውም በክብር ተቀብለው የክብር ቦታ ሰጧቸው ። በዚያ ሁነው ለደጃዝማች ካሣ ጠቃሚ ምክር ይመክሩአቸው ነበር ። ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ የሚቻለው አንድ ሃይማኖት ብቻ ሲኖር መሆኑን ጧት ማታ ይነግሩአቸው ነበር ። ደጃዝማች ካሣም በምክራቸው ደስ ስላላቸው የመንበረ ማርቆስን ምሥጢረ ሃይማኖት (ዶግማ) በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ አቡነ ሰላማን ጠየቋቸው ። እርሳቸውም የተዋሕዶን እምነት አብራርተው በመግለጥ «በቅብዓት የባሕርይ ወይም የጸጋ ልጅ ሆነ» የሚለውን በመንቀፍ ጽሑፍ አዘጋጅተው 85. በአዋጅ እንዲነገር አደረጉ ። ደጃዝማች ካሣም ይህን የአቡኑን እምነት ያልተቀበለ ከፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቀጣል ብለው አዋጁን በአዋጅ አጸደቁ ። በዚህ አዋጅ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲደሰት አንዳንድ ካቶሊኮችና የቅብዓትና የጸጋ እምነት ያላቸው እንደገና ሁከት ፈጠሩ ።

በዚህ ጊዜ በአካለ ጉዛይና በምጥዋ የካቶሊክን ሚሲዮን ሲመራ የነበረ አባ ያዕቆብ የተባለ ኢጣልያዊ 86. በዚህ አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያን ምድር ለቆ እንዲወጣ ተደረገ ። ከርሱ ጋር በእምነት የተሳሰሩ ጥንተ ቅብዓትነት የነበራቸው አባ ጉብረ ሚካኤል የሚባሉ የመርጡለ ማርያም መነኩሴ ነበሩ ። የሀገር ተወላጅ በመሆናቸው ከሀገር እንዲወጡ አልተደረገም ፤ ወደ

85. ሐምሌ ፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በኢትዮጵያ አቆጣጠር ፤
86. ነጮች ቢስኮቦ ጀውስቲኖ ዴ.ጃኮቢስ ይሉታል ።



ባዕድ ሃይማኖት በመግባታቸው የሞት ቅጣት እንዲፈጸምባቸው ታስቦ ነበር ። ኋላ ግን በአሥራት ተሻሽሎላቸው በእሥር ቤት እንዳሉ ሞቱ ። 87.

በ፲፮፻፵፯ ዓ.ም. በኢት/ አቆጣጠር የካቲት ፭ ቀን ደጃዝማች ካሣ በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ ። በነገሡ በ፭ ዓመት በ፲፰፻፶፪ ዓ.ም በጥቅምት ወር የእስክንድርያው ፓትሪያርክ አባ ቄርሎስ አራተኛ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። ይኸውም ፓትሪያርካዊ ጉብኝት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ነው ። የመጡበትም ምክንያት ስለ ሦስት ነገር ነው ይባላል ።

፩ኛ. ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ የሚሔዱት ኢትዮጵያውያን እባክዎ አገራችንን ይዩልን እያሉ ይለምኗቸው ስለ ነበረ ኢትዮጵያን ለማየት ፤

፪ኛ. ዓፄ ቴዎድሮስ ከቱርኮች ጋር ተጣልተው ስለነበር ይታረቁ ለማለት ፤

፫ኛ. ካይሮ ያለውን የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን (ካቴድራል) ለማሳደስ አስበው ነበርና የገንዘብ ርዳታ ለመጠየቅ ነው ይባላል ።

ፓትሪያርኩ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ታላቅ አቀባበል ተደረገላቸው በውይይታቸውም ወቅት ሌላውን ጥያቄ ሁሉ በደስታ ሲቀበሉት ፥ ከቱርክ ጋር ዕርቅ ያድርጉ የሚለውን የፓትሪያርኩን ጥያቄ ዐፄ ቴዎድሮስ አልተቀበሉትም ። እንዲያውም የሃይማኖት አባቴ ሁነው እንዴት ለቱርክ አማላጅ ሆኑ በማለት በፓትሪያርኩ ላይ ጥርጣሬ ስላደረባቸው አሠሩአቸው ፥ በኋላ ግን ሊቃውንቱና መኳንንቱ መክረው ምንም ያል ሆነ ጥያቄ ቢጠይቁ ፓትሪያርካችንን ማሠር የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ያጐድፋልና ይፈቱልን ሲሉ ፥ ዓፄ ቴዎድሮስን ጠየቁ ። ከእ

87. አሁን ካቶሊኮች ብፁዕ ጉብረ ሚካኤል ይሏቸዋል ፤ ወደፊትም ቅዱስ ሲሏቸው ይዘጋጃሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሥራት ተፈተው ለቤተ ክርስቲያኑ ማሠሪያ የሚሆን ብዙ ወርቅ ብር የዝሆን ጥርስ ጭነው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

ዓፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት ፤ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ መሪ ነበሩ ። 88. በዘመናቸው በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ሰብስበው ፦ ኢትዮጵያ የራሷ የወንጌል መምህራን አሏት ፤ ይልቁንስ እናንት የሠለጠናችሁበትን ለእኛም የሚያስፈልገንን ብረት ማቀለጥና መቀጥቀጥ (ቴክኖሎጂ) አስተምሩን ብለዋቸው ነበር ይባላል ። ነገር ግን ንጉሡ ለኢትዮጵያም ለቤተ ክርስቲያንም ያሰቡት አሳብ ከግቡ እንዳይደርስ በጐጃምና በሰሜን የነበሩ እንደነ ደጃች ንጉሤ ያሉ ጠላቶቻቸው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ከሆነው ኢትዮጵያዊ ከሚባለው ሕዝብ ጋር ከኢጣሊያና 89. ከፈረንሳይ መንግሥት ወኪሎች 90. ጋር እየተመሳጠሩ ትግላቸው ፍጻሜ እንዳያገኝ ያውኳቸው ነበር 91. ምንም እንኳ ሐሳባቸው ከግቡ ሳይደርስ ቢሞቱ ዓፄ ቴዎድሮስ የቱርክን እስላም ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት የማያወላውል ሐሳብ ነበራቸው ። ስለዚህ ነው አዝማሪአቸው እንዲህ ብሎ የገጠመው ።

ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም ፤
ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም ።
አንተም ጌታ አይደለህ እኔም የአንተ ሎሌ
የየሩሳሌም ሰው ካልሜን በርሜሌ

በተለይም በ፩ሺ፰፻፷፫ ዓ.ም. በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ይዞታ የነበሩትን ሁሉ የቱርክ መንግሥት ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በመስጠቱ ተናደው ስለነበር ፤ የጦር መሣሪያ ከእንግሊዝ መንግሥት ጠይቀው በቱርክ ላይ ለመዝመት ቁርጥ ሐሳብ ነበራ

88. "To him (Theodore) Christianity and Abyssinia were Synonymous" J. Spencer Islam in Ethiopia, Oxford, 1952, p. 118.
89. fr. de Jecobis.
90. M. Belliord.
91. Religion in the Middle East, Vol. 1 (Cambrige, 1969) p.463.



ቸው ይህንንም ሐሳባቸውን ለመፈጸም በዘመናቸው የእንግሊዝ ንግሥት ለነበረችው ለቪክቶሪያ መልእክት ልከው ነበር ። 92. ነገር ግን ዓፄ ቴዎድሮስ የክርስቲያን ንግሥት ስለሆነች ትረዳኛለች ብለው ለቢክቶሪያ ቢጽፉላትም የእንግሊዝ መንግሥት ከቱርክ ጋር የጦር ቃል ኪዳን ስለ ነበራቸው ጥያቄአቸው መልስ አላገኘም ። በዚህም የተነሣ ዓፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ተጣሉ ። በኢትዮጵያ ታሪክ እንደምናውቀው ከሞትም ያደረሳቸው የዚሁ ጠንቅ ነው ።

ዓፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ አባ በዝብዝ ካሣ የተባሉት በአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው ዮሐንስ አራተኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ ። እርሳቸውም እንደ አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በሃይማኖት አንድ ለማድረግ ይመኙ ስለነበር ከውጭ በሚመጡ ሚሲዮናች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጉ ነበር ። ወንጌልን በስፊው ለማስተማር እንዲያመችና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ልጆች እንድትመራ ከርሳቸው በፊት በሐርቤይ ዘመነ መንግሥት ተጠይቆ ሳይሳካ የቀረውን ጥያቄ እንደገና በማንሳት ዓፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ጠይቀው ነበር ። ነገር ግን ለጥያቄያቸው መልስ ስላላገኙ ወደ ቁስጥንጥንያ (ቂልቅያ) ከአርመን ፓትርያርክ ጋር ስለዚሁ ጉዳይ ተጻጽፈው ነበር ። 93. ኋላ ግን ሕዝቡ ያልለመደው በመሆኑ ቅር እንዳይለው ተገንዝበው አራት ጳጳሳት ሾመው እንዲልኩላቸው የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት ጠየቁ ። ፓትርያርኩም አቡነ ዮሐንስን ፤ አቡነ ጴጥሮስን ፤ አቡነ ሉቃስንና አቡነ ማቴዎስን ሾመው ላኩላቸው ። ከነዚህም አቡነ ዮሐንስንና አቡነ ጴጥሮስን በትግሬ አስቀርተው አቡነ ሉቃስን ወደ ጐጃም አቡነ ማቴዎስን ወደ ሸዋ ላኳቸው ።

92. Otto Meinardus, The Copts in Jerusalem, (Gairo, 1960).
93. H.M. Hyatt, The Church of Abyssinia, London, 1928, p. 46.

www.ethiopianorthodox.org

ዓፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው ለኢትዮጵያ ካደረጓቸ ውለታዎች አንዱ ሀገሪቱ በሚሲዮናውያን ስብከት እንዳትከፋፈል ያደረጉት ጥረት ነው ። ከዕለታት አንድ ቀን ሚሲዮናውያንን ሰብስበው እነ አባ (ካርዲናል) ማስያስንም ጭምር ከሸዋ አስመጥተው ምን ልታደርጉ ወደ ኢትዮጵያ መጣችሁ ብለው ጠየቋቸው ፤ እነሱም ወንጌል ልንሰብክ ነው ብለው መለሱ ። ንጉሡም ፦ ወንጌል አንድ ነው ፤ እግዚአብሔርም አንድ ነው ። እኔም ሕዝቤን ለመስበክ የሚበቁ ጳጳሳትና ቀሳውስት አሉኝ ። ለማን ለመስበክ ትፈልጋላችሁ ? አሏቸው ፤ እነሱም በዚህ አገር ለሚኖሩ ይሁዲዎችና እስላሞች ብለው መለሱላቸው ። ንጉሡም ወደ ኢትዮጵያ ስትመጡ የአይሁድን አገር ኢየሩሳሌምን የእስላሙን አገር ግብፅን ሊቢያን ሳውዲ ዓረቢያንና የመንን እንደምን አልፋችሁ መጣችሁ ። አሁንም እኔ የሀገሬን ሕዝብ የእጅ ሥራና ጥበብ የሚያስተምሩ ሥጋጃ ሠሪዎች ፤ አናጢዎችና ነጋዴዎች ብረት ሠሪዎች የሆኑትን እቀበላለሁ እንጂ እናንተን አልፈልግምና አገሬን ልቀቁልኝ ብለው ገሚሶቹን በምጥዋ ገሚሶቹን በመተማ በኩል አስወጧቸው ። ዓፄ ዮሐንስ በመተማ ከማሕዲስቶች ተዋግተው እስኪሞቱ ድረስ በግራኝ ወረራ ብዙ ገዳማት እንዲሠሩ አድርገዋል ። ለምሳሌ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ከግራኝ ወረራ በኋላ የተሠራው በ፬ኛ ዓፄ ዮሐንስ ነው ዓፄ ዮሐንስ ያሠሩት ይህ ቤተ ክርስቲያን ባለ ፲፰ ቋንጮ ነበር ይባላል ። በኋላ ዓፄ ምኒልክ (ዳግማዊ) በዘመነ መንግሥታቸው ለማሠራት ሲሉ ፤ ባለ ፲፰ቱ ቋንጮ ቤተ ክርስቲያን በሦስት ወር ፈረሰ ይባላል ። በኢየሩሳሌምም ካሉን አብያተ ክርስቲያናት በውበቷ የቱሪስቶችን ዓይን የምትማርከው የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት (ዘውድ ቅርፅ) ቤተ ክርስቲያን የተሠራችው ያን ጊዜ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አበ ምኔት መምህር ወልደ ሰማዕት አሳሳቢነት ዓፄ ዮሐንስ ከቱርክ የማረኩትን ወርቅ ልከው ነው ። ከዚህም ጋር እንደ አንድ ሐዋርያ በግራኝ ጨርሶ ጠፍቶ የነበረውን የኢትዮጵያ ሰሜን ምሥራቅ እስሰው የወሎውን ባላባት መሐ



መድ ዓሊን ሚካኤል በሚል ስያሜ ራሳቸው የክርስትና አባት ሁነው አጥምቀዋቸዋል ። አባ ዋጠው የሚባሉትንም ንጉሥ ምኒልክ የክርስትና አባት እንዲሆኗቸው አዝዘው ኃይለ ሥላሴ በሚል የክርስትና ስም እንዲጠመቁ አድርገዋል ። ፺፬ የሚያስተምሯቸውም ኢትዮጵያዊውን ሊቅ መምህር አካለ ወልድን ሰጥተዋቸዋል ። ዓፄ ዮሐንስ ፍጹም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ስለነበሩ ፤ « በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ወይም የጸጋ ልጅ ሆነ» የሚሉ መናፍቃን ኃይላቸው የተዳከመው በርሳቸው ዘመነ መንግሥት ነው ። በመጀመሪያ አክሱም ላይ ተዋሕዶዎችና ቅብዐቶች ባደረጉት ክርክር የተዋሕዶ ክፍሎች «የተቀብዐ» ትርጓሜው ሥጋን ተዋሐደ ፤ ሰው ሆነ ማለት እንጂ ሌላ ቅብዕ ሌላ ክብር አለመሆኑን ገልጠው አመስጥረው ስላቀረቡ ቅብዐቶችን ረቷቸው ። ከዚህ በኋላ ከቅብዐቶች ጋር የነበረው ክርክር ጋብ አለ ፤ ነገር ግን ጸጋ የሚባሉት ክፍሎች ደግሞ በታላላቅ አድባራት ትምህርታቸውን አስፋፍተው ተዋሕዶዎቹን አስቸግረው ስለነበር በ፩ሺ፰፻፸፰ ዓ.ም. በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ ላይ ጉባኤ ተደርጐ ጸጎች ስለ ተረቱ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የጸጎች ሃይማኖት እየተዳከመ ሔደ ።

የዚህን የቦሩ ሜዳ ክርክር (ጉባኤ) ጉዳይ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ፦ «ዝክረ ሊቃውንት» በሚባለው መጽሐፋቸው የጻፉትን በሙሉ እናቀርባለን ። መልአከ ብርሃን አድማሱ እንዳቀረቡት በጉባኤው የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ፤ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፤ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል (የራስ መኰንን አባት) ከቤተ መንግሥት ሲሆኑ ከቤተ ክህነት እጨጌ ቴዎፍሎስ ነበሩ ። ባለ ሥልጣን የነበሩትን ብቻ ለማስታወስ እንጂ ሌሎችም ብዙ ሊቃውንት እንደ ነበሩበት የታወቀ ነው ።

94. መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ፦ ዝክረ ሊቃውንት ፲፱፻፶፱ — አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ገጽ ፪፻፬—፪፻፮

www.ethiopianorthodox.org

ከተከራካሪዎቹም ወገን የተዋሕዶዎቹ አፈ ጉባኤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ሲሆኑ ፤ ለርሳቸው ባለቀረኝ (ረዳት) የነበሩት አለቃ ተክለ ሥላሴና መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ናቸው ።

የጸጋዎቹ (የሦስት ልደት ባዮቹ) አፈ ጉባኤ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስና ባለቀረኝ (ረዳት) የነበሩት አለቃ ሀብተ ወልድ ፤ አለቃ ውቤና አለቃ ቤተ ሌዊ ናቸው ። ከዚህ በኋላ ክርክሩ ይቀጥላል ።

የመጀመሪያው ጥያቄ የተሰጠው ለሁለት ልደቶች ነበረ ።

አፈ ጉባኤው አለቃ ኪዳነ ወልድ ተጠየቅ ልጠይቅህ ።

፩ኛ ጥያቄ ፤ ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው ? ሲሉ ጠየቁ ።

መልስ ፤ (አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ) አዎን ሥላሴ በአካል ሦስት ናቸው ሲሉ መለሱ ።

፪ኛ ጥያቄ ፤ ሥላሴ በክብር ዕሩያን ናቸው አይበላለጡም ? አሉ ። አዎን ሥላሴ በክብር ዕሩያን ናቸው አይበላለጡም ሲሉ መለሱ ።

፫ኛ ጥያቄ፡— ሥላሴ በከዊን ህልውና ከመገናዘብ በቀር አንዱ አካል በአንዱ አካል አያድርም አሉ ።

መልስ፡— አዎ በከዊን ህልውና ከመገናዘብ በቀር አንዱ አካል በአንዱ አካል አያድርም ።

፬ኛ ጥያቄ፡—አንተ በራስህ አንቅተህ ከሦስቱ አንዱ አካል ቃል ሥጋ በሆነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አደረበት መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የጸጋ ልጅ ሆነ እያልክ ታስተምራለህ? ሲሉ ጠየቁ ።

አለቃ ሥነ ጊዮርጊስም መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ ። ዋልድቤ እንግዳ ፥ ዙርአንቤ እንግዳ የተባሉ መነኰሳት አብረዋቸው ቁመው ነበርና ሁለቱም ባንድ ቃል፡— አዎን ወልደ ሥላሴ እንለዋለን ብለው በድፍረት ተናገሩ ። በዚህ ጊዜ ዓፄ ዮሐንስ አራት አምላክ



ማለታችሁ ነውን ብለው ተቆጡ ። ዕጨጌ ቴዎፍሎስ ጃንሆይ ዳኛ ነት መስማት ነው እንጂ መቆጣት የለብዎትም ሲሉ ተናገሩ ።

ሁለተኛ ጥያቄ፡— (አለቃ ኪዳነ ወልድ ባለቀረኝ)

አለቃ ተክለ ሥላሴ ቀረኝ ብለው፡—ሃይማኖት በብሉይ በሐዲስ ተነግሯል ተጽፏል ብለው ጠየቁ መልስ— አዎን ተነግሯል ተጽፏል አሉ ። ጥያቄ፡— በብሉይ ወልድየ አንተ ተብሎ ቀዳማዊ ልደቱ ወእነ ዮም ወለድኩከ ተብሎ ደኃራዊ ልደቱ ተነግሯል አሉ ። መልስ፡— አዎ ተነግሯል አሉ ። ጥያቄ፡— በሐዲስም ፈነወ ወልዶ ተብሎ ቀዳማዊ ልደቱ ወተወልደ እምብእሲት ተብሎ ደኃራዊ ልደቱ ተነግሯል መላሽ፡—አዎን ተነግሯል አሉ።ጥያቄ፡—ቅድመ ዓለም ከአብ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን መወለዱን ካመንሽኝ ሁለት ልደት ማለት ይህ ነዋ ብለው አሳዩ። ምሥጢሩ ጥልቅ ሆኖ ለሰሚ የማይረዳ ስለሆነ ሁሉም ዝም አሉ ።

ሦስተኛ ጥያቄ፡— (የአለቃ ኪዳነ ወልድ ባለቀረኝ) መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ቀረኝ ብለው ጠየቁ ።

ጥያቄ፡— የንጉሥ ገንዘብ ተሰፍሮ ተቆጥሮ በመዝገብ ይጻፋል? መልስ፡— አዎ ተቆጥሮ በመዝገብ ይጻፋል ። ጥያቄ፡—በመዝገብ ከተ ጻፈው ያጎደለም ያተረፈም ይቀጣል ?

መልስ፡—ያተረፈም ያጎደለም ይቀጣል አዎን ጥያቄ፡— የሥ ላሴ ገንዘባቸው ሃይማኖት ተሰፍሮ ተቆጥሮ በመጽሐፍ ተጽፏል? መልስ፡— አዎን የሥላሴ ገንዘብ ሃይማኖት ተሰፍሮ ተቆጥሮ ተጽ ፏል ። ጥያቄ፡— ከመጻሕፍት ቃል ያተረፈም ያጎደለም ይቀጣል ? መልስ፡— አዎን ያተረፈም ያጎደለም ይቀጣል ። ጥያቄ፡— መጽሐፍ ነአምን ክልኤተ ልደታተ ብሎ በእንዝ ወስና ነገሮናል ? መልስ፡— አዎን መጽሐፍ ነአምን ክልኤተ [illegible]ታተ ይላል ። በዚህ ጊዜ ጠያ ቂው ከመጻሕፍት ቃል ያተረፈም ያጎደለም የሚቀጣ ከሆነ መጽሐፍ ጠንቅቆ፡— ነአምን ክልኤተ ልደታተ ብሎ ወስና ከተናገረ አንተ

www.ethiopianorthodox.org

ከዚሀ አልፈሀ ተርፈሀ ሦስት ልደት እያልክ ስታስተምር ከተገኘሀ ትቀጣለኛለሀ ሲሉ ውርድ ነዙ ።

አለቃ ሥነ ጊዮርጊስም መልሰው ተጠየቅ አሉ ። ዓፄ ዮሐንስ ልታሳስቱኝ ነው ተጠየቁ ይቅርና ርሱ በእኅዝ ነአምን ክልኤተ ልደታተ ብሎ ቆጥሮ እንዳስረዳ አንተም ሦስት ልደት የሚል ንባብ አምጣ ብለው ተናገሩ ። በዚህ ጊዜ የልዑል ራስ መኰንን አባት ደጃች ወልደ ሚካኤል ብድግ ብለው ተነሥተው ጃንሆይ፥— እነዚህኞቹ እየተፈራረቁ ሲጠይቁ ቆይተዋል እነዚህን ጥያቄ ብንከለክላቸውማ ዳኝነት ይጎድልብን የለምን ብለው አመለከቱ። ። ዓፄ ዮሐንስም የደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን ቃል ተቀብለው ደግ ነው ይጠይቅ አሉ ። ከዚህ በኋላ አለቃ ሥነ— ጊዮርጊስ ተጠየቅ አሉና እናትና ልጁን ልደት እንጂ ያገናኛችዋል ሲሉ ጠየቁ ። አለቃ ስነ ጊዮርጊስ እንዲህ ብለው መጠየቃቸው፥— እመቤታችን አዳም ወስዶት የነበረውን የጸጋ ልደት እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ተወልዳለች። ልጅዋንም እንደሷ የጸጋ ልደት ተወለደ ባይ ናቸውና ይህ ልደት ያገናኛቸዋል ለማለት ነበረ ። መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ግን ካፉቸው ጠለፍ አድርገው ሁሉ ወደሚያውቀው ወደ ግዙፉ ወደ ልደተ ሥጋ ለውጠው ።— አባዬ አባዬ ያራዳ መምህር የርሷ ልደት በዘር በሩካቤ የርሱ እንበለ ዘርዕ ምን አገናኛቸው ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ በአደባባይ ያለው ሁሉ ሳቀ አደነቀ ። ዓፄ ዮሐንስም ነገሩ እንዳላማረ አዩትና ተጠየቁ ቀርቶ ወልደ ዮሐንስ ሁለት ልደት የሚል ምስክር ከመጽሐፍ እንዳመጣ አንተም ሦስት ልደት የሚል ደረቅ ንባብ አምጣ አሏቸው ። አለቃ ስነ ጊዮርጊስም በደብረ ብርሃን ተአምረ ማርያም ተጽፏል አሉ ። ከምታስተምረው ከዐራቱ ጉባኤ አጣህና ስለ ሃይማኖት ተአምረ ማርያም ትጠቅሳለህን? ቢሏቸው ከጉባኤው መጽሐፍስ የለም አሉ ። በዚህ ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ነገሩ ይደርና እንመካከርበት አሉ ።

ዓፄ ዮሐንስም ደግ ነው ይደር ብለው ፈቀዱ ። መምሬ ወልደየስ የተባለ የወግዳ ቄስ አብሮ ቄሞ ነበርና ወልደ ዮሐንስ የደላከው

www.ethiopianorthodox.org



ጋላ ሳትሰልበው አመለጠልህ ብሎ ጮኾ ተናገረ ። መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ነገሩ ገባቸውና ጃንሆይ ቄስ አሐዱ አብ ቅዱስ ብሎ ከባረከው በኋላ መስዋዕት እንደማያድር ንጉሥም ካከራከረና ካመሳከረ በኋላ ፍርድ ሊያድር አይገባውምና በቆስጠንጢኖስ ዳኝነት ይገፍዎታለሁ ይህ ፍርድ አይደርብኝ ሲሉ አመለከቱ ። ዓፄ ዮሐንስም ደግ ነው ይፋረዱ አስፈርድ ሲሉ አዘዙ ። ባደባባይ የተቀመጠ ሁሉ ባንድ ቃል ከመጽሐፍ ያላገኛችሁትን በማስመሰል ሰውን ሁሉ ስታስክዱ ኑራችኋልና ትቀጣለችሁ እያለ በነአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ፈረደባቸው ። ባለ ፍትሐ ነገሥቱ ሊቄ መርዓዊም አራት አካል ካላችሁ ትቀጣላችሁ ሲሉ ፈርደውባቸዋል ። ዓፄ ዮሐንስ በፈጣሪዩ ላይ በድፍረት ያልሆነ ቃል ተናግረዋልና የአካል ቅጣት ይቀጡ ቢሉ አለቃ ኪዳነ ወልድ ጃንሆይ ይህማ መቼ ይሆናል ከነዚህ ይልቅ የባሰ ክህደት አርዮስ ተናግሮ ነበር ተጋዘ፤ ተሰደደ እንጂ የአካል ቅጣት ተፈረደበት? ከእነዚህም እንመለሳለን የሚሉት እየተገዘቱ ይመለሱ አንመለስም ያሉት ቦታ ተወስኖባቸው በግዞት ይቀመጡ እንጅ የአካል ቅጣትስ አይገባቸውም ሲሉ አመለከቱ ። ዓፄ ዮሐንስም ዋልድቤ እንግዳንና ዙርአንቤ እንግዳን በድፍረት ወልደ ሥላሴ እንለዋለን ብለው ተናግረዋልና አልምራቸውም ብለው እጅ እግራቸውንና ምላሳቸውን አስቆረጧቸው ። ዋልድቤ እንግዳ ወዲያው ሞተዋል ዙርአንቤ እንግዳ ግን በዕድሜ ቆይተው ንስሐ ገብተው ሞተዋል ። እነአለቃ ሥነ ጊዮርጊስም ሁለት ልደት እንላለን እያሉ እየተገዘቱ ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

ከዚህ በኋላ ቀስ በቀስ ቅብዓትና ጸጋ የሚባለው ባዕድ ትምህርት ጨርሶ ጠፍቷል ። ዓፄ ዮሐንስ የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው ምዕመናንን ሲያሰቃዩና አብያተ ክርስቲያናትን ሲያፈርሱ ከነበሩ የሱዳን ማኅዲስቶች ጋር ተዋግተው አረፉ።ርሳቸው ከአረፉ በኋላም በዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥትም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሥራ ተሠርቷል።አያሌ አብያተ ክርስቲያናት የመተዳደሪያ ርስት ተተክለዋል ካህናትም ሰፋፊ ርስት ተተክለው ነበር ። በመሣፍንት ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያ አንድ ለማድረግ የቴዎድሮስንና የዮሐንስን

ዓላማ በመከተል የደቡብ ኢትዮጵያን ግዛት ሲያስሱ ከግራኝ ወረራ ጀምሮ ጠፍተው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን እንዲ ታደሱ አድርገዋል ።

ከዚህም ሌላ በኢየሩሳሌም የዴር ሡልጣን ገዳማችን ከግብጾች ጋር በነበረን ክርክር የኢትዮጵያ መነኮሳት መውጫ መግቢያ በር ተነ ፍጓቸው ሲቸገሩ ዓፄ ምኒልክ ወደ ቱርክ መንግሥት ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ የተባሉትን ሰው ልከው የዴር ሡልጣን በር እንዲ ከፈት አድርገዋል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከውጭ ወደ ሀገራችን በሚገቡ ሚሲዮናች ላይ ግን የሚያረግ ቁጥጥር ስላልነበረ በዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የተባረሩት ሚሲዮኖች እነ አባ ማስያስ ሁሉ እየተመለሱ መጡ ።

ከ፲፱፻፱ ዓ.ም. ጀምሮ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መልኩ ትንሽ ዘመናዊነትን ያዘ ። በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም. መስከረም ፩ ቀን የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ተመሠረተ ። በፊት ቅዱስ ሐርቤ በኋላም ዓፄ ዮሐንስ ጀምረውት የነበረው፤—« ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች ጳጳስ መሾም አለ ባት » የሚለው ጥያቄ ፍጻሜውን ያገኘው በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መን ግሥት ነው።

ግብጻዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ከሞቱ በኋላ የኢ ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ ልጆች ጳጳስ መሾም አለባት የሚል ጥያቄ ወደ ኮፕቶች ቀርቦ በኢትዮጵያና በኮፕት ቤተ ክርስቲያን መካ ከል ለሦስት ዓመታት ያህል ውይይት ከተደረገ በኋላ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ ተሾሙ ። እነሱም፤—

፩. አቡነ አብርሃም የፊት ስማቸው መምህር ደስታ ፤
፪. አቡነ ይስሐቅ የፊት ስማቸው መምህር ወልደ ኪዳን
፫. አቡነ ጴጥሮስ የፊት ስማቸው መምህር ኃይለ ማርያም
፬. አቡነ ሚካኤል የፊት ስማቸው መምህር ሐዴስ ናቸው

ከነዚህም ጋር አቡነ ቄርሎስ የተባሉ አንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ አብረው ተሹመው መጥተዋል ። ርሳቸውም ከፍሬ ምናጦስ ጀምሮ



፻፲ኛው ሊቀ ጳጳስ ናቸው ። በዓመቱ በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም. የእስክንድርያ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ ፲፱ኛ ኢትዮጵያን በመጐብኘት ላይ እንዳሉ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበሩትን ገብረ መንፈስ ቅዱስን ጥር አንድ ቀን አቡነ ሳዊሮስ ብለው ሾሟቸው ።

በ፳ኛው ምዕት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመ ጀመሪያ ጊዜ አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተሾሙ ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጵጵስና ደረጃ እንድትተዳደር የተፈቀደው ፍሬ ምናጦስ የመጀመሪያው ጳጳስ ሲሾም ነው ። 95 ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለ፩ሺህ፮፻ ዓመታት ያህል ወደ ኢትዮጵያ እየተሾሙ የሚመጡት የግብጽ ጳጳሳት ነበሩ ።

ኢትዮጵያ ከግብፅ ጳጳሳት ስታስመጣ መቆየቷ በሚከተለው ምክንያት ነው ። በሠለስቱ ምዕት ስም በጉባኤ ኒቅያ ቀኖና አን ቀጽ ፵፪ በስርዋጽ የገባ ፤— «ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ» የሚል ትእዛዝ ነበር ። ይህ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጨመረ ነው ። ይኸው ሕግ በሰማኒያኛው ቀኖናው ኢት ዮጵያውያን ጳጳስ እንዳይሾሙ ይከለክላል ። 96 ግብፃውያን ይህን ምክንያት አድርገው ኢትዮጵያውያን ጳጳስ መሆን አይገባቸውም እያሉ ሲከራከሩ ከላይ የተጠቀሰው ረጅም ዘመን አልፏል ። እርግጥ ሠለስቱ ምዕት ይህን የግብጾችን ጥቅስ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን መለያየት እንዳይፈጠር በማሰብ በኒቅያው ቀኖና በስድስተኛው አን ቀጽ «የግብፅ ፤ የሊቢያንና የፔንዳፖሊስ መንበሮች ክርስትናን ከእ ስክንድርያ መንበር ስለ ተቀበሉ ለመሪያቸው ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ እንዲታዘዙ ሕግ ሠርተዋል ። ቀኖና ወስነዋል ። የሮምና የአ ንጾኪያ ሊቃነ ጳጳሳትም በየሀገረ ስብከታቸው ተመሳሳይ ሥልጣን ነበራቸው በዚህ ሳቢያ ኢትዮጵያም ከእስክንድርያ ሀገረ ስብከት ክፍል ስለ ነበረች ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መታዘዝ ነበረባት የሚል የኮፕቶች እምነት ብዙ ጊዜ ሲሠራበት ኖሬ ።

95 ፫፻፴ ዓ.ም.
96. "Canones Arabici XVII 36".

www.ethiopianorthodox.org

እውነቱን ለመናገር ከሆነ ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው ከግብፅ ሐዋርያ ተልኮላት አልነበረም ። በመጀመሪያ እንደ ተገለጸው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሐዋርያት ዘመን ነው ። የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ጳጳስ ግን ከኢትዮጵያ ተልኮ ጵጵስናን የተቀበለው ከግብፅ ነው ። ዘሩም ሶርያዊ ነው ። ጵጵስናን ከእስክንድርያ ማምጣት ደግሞ ክርስትናን ማምጣት ማለት አይደለም ። ሐዋርያም የሚባለው ሐዶ ያስተማረ ነው ። ኢትዮጵያ ክርስትናን ከግብፅ ተቀበለች ቢባልም እንኳ ብዙ ምዕመናን ለጵጵስና ማዕረግ የሚበቁ ልጆች ካሏት ልጆቿን ለመሾም ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይፈቅድላታል ። የቤተ ክርስቲያን ክህነት እንደ ምኩራብ ክህነት በዘር የሚወርድ አይደለምና ። ለምሳሌ ቆጵሮስ ክርስትናን የተቀበለችው ከአንጾኪያ ስለነበር ፤ በሠለስቱ ምዕት ትእዛዝ መሠረት የአንጾኪያ ክፍል ሁና ስትኖር ብዙ ምዕመናንና ለጵጵስና የበቁ የነቁ ልጆች ባፈራች ጊዜ እስከ ፬፻፴፩ በአንጾኪያ ሥር ስትተዳደር ቆይታ በ፬፻፴፩ በኤፌሶን በተደረገው ሦስተኛው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ራሷን በራሷ ለማስተዳደር እንድትችልና የራሷን ልጆች ጳጳሳት እንድትሾም ተወስኖላታል ።97። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን «ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳሳት አይሹሙ» በሚለው ሰው ሠራሽ ሐረግ ታሥራ ከላይ የጠቀስናቸውን እያሌ ዓመታት በትዕግሥት አሳለፈች ፤ በነዚህ እያሌ ዓመታት ውስጥ ለመላው ኢትዮጵያ የሚላከው አንድ ጳጳስ ብቻ ነበር ፤ እሱውም የሕዝቡን ቋንቋ ስለማያውቅ ለማስተማርም ሆነ ለማስተዳደር በስም በለው ነበር ። የሚቀመጠውም ንጉሡ ባለበት ቦታ በከተማ ብቻ ስለነበር ፤ በገጠሩ የሚኖረው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያኑ እንዳይዘጋበት ሕፃናቱን በጀርባው አዝሎ በትከሻው ተሸክሞ ጳጳሱ ወዳለበት የወር የሁለት ወር ጉዳና ተጉዞ ይመጣል ። ከዚያም ገንዘቡን ከፍሎ ካኑልኝ ሲል ጳጳሱ ገንዘቡን ተቀብሎ ከሥርዓተ ቤተ

፺፯. የጉባኤ ኤፌሶን ቀኖና አንቀጽ ፰



ክርስቲያን ውጭ ዕድሜው ለክህነት ሳይደርስ ፤ ለክህነት የሚያበቃ ሙያ ሳይኖረው እየካነ ይልከዋል ። ልጁም ተክና በቂ ትምህርት ሳያገኝ በቤተ ክርስቲያን በድምጫ የሰማውን ብቻ ይዞ በዲቁና ሲያገለግል ይቆይና በዕድሜው ከፍ ሲል ፤ አሁንም ያለበቂ ሙያ ቄስ ይሆናል ፤ በዚሁም ላይ ደግሞ አንዱ ጳጳስ ሙቶ ሌላው እስኪተካ ብዙ ዓመታት ያልፋሉ ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የቄስና የዲያቆን ችግር ይደርስባታል ።

ይልቁንም ደግሞ ጳጳሳትን የምትልክልን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በፋርስ (፮፻፲፬) ፤ በእስላም ዓረቦች (፮፻፴፱) እና ኋላም በቱርክ (፩ሺ፱፻፶፪) ስለተያዘች ፤ እንደልብ ጳጳስ ልትልክልን አትችልም ነበር ። በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ላይ በነበረው የእስላሞች ተፅዕኖ ምክንያት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ፤ ማለት የግብፅና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በቀጥታ ለመነጋገር ስለማይችሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት ወደ ግብፅ መሪዎች ጳጳስ እንዲመጣላቸው ዘወትር አማላጅና የእጅ መንሻም ይልኩ እንደነበር ባለፈው ገልጠናል ። ምልጃው አልሆን ሲል ደግሞ በማስፈራራትና በዛቻ ጳጳሳት እንዲላኩላቸው ያደርጉ ነበር ፤ አልፎ አልፎም እንደነ ቅዱስ ሐርቤና እንደነ ዓፄ ዮሐንስ አራተኛ ያሉ ነገሥታት የግብጽን ሡልጣኖች ከመለማመጥ ራሳችንን መቻል አለብን በሚል መንፈስ ተነሣሥተው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ነፃ ለማውጣት ቢሞክሩም እግዚአብሔር የፈቀደው እስኪደርስ በዘመናቸው አልተፈጸመም ።

አሁን በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከላይ ስማቸው የተገለጸውን አምስት ኤጲስ ቆጶሳት ከራሷ ልጆች አገኘች ። ሊቀ ጳጳሳት ሁኖ የሚመራው ግን የግብጹ ሊቀ ጳጳስ ነው ።

እነሱ በተሾሙ በስምንተኛው ዓመት ኢትዮጵያ በግፈኛው ፋሺስት ተወረረች ። ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ለመግዛት ባደረገው ዘመቻ በ፲፱፻፳፰ (፲፱፻፴፮) በሊቢያ ዋና ከተማ በትሪፖሊ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማፈራረስና ክርስቲያኖችንም ለመ

www.ethiopianorthodox.org

ፍጅት መነሳቱን የሚገልጥ አዋጅ ነገረ ። አዋጁም የሚከተለው ነበር ። «የፋሺስት ጣሊያን በሊቢያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ እስላሞች የሰላም ዋስትና ለመስጠት አስቧል ። ትክክለኛ ፍትሕና ብልጽግናም ለእስላሞች ያደርጋል ። የነቢዩ መሐመድንም ሕግ ያከብራል ፤ ከዚህም በላይ ለመላው ዓለም እስላሞች ያለውን ቅንና መልካም አስተሳሰብ ሊገልጥ ይወዳል ። 98*

ከዚህ ቀደም ብሎ በ፲፱፻፳፰ (፲፱፻፳፰) ዓ.ም. የሙሶሎኒ ጦር ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የኢትዮጵያን ምዕመናን ወደ ላቲንነት ጐትራ ለማስገባት ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ የአዝመራ ጊዜ የሆነላት መስሏት ነበር ። ስለዚህ የኢጣሊያ ጳጳሳት ካርዲናሎችና ፓፓውም ለሙሶሎኒ ብዙ የጦር መሣሪያ ርዳታ አድርገዋል ። ምዕመናኑም በየቤተ ክርስቲያኑ ለሙሶሎኒ የጦር መሣሪያ መግዣ የሚውል ገንዘብ ወደ ሙዳየ ምጽዋት እንዲያስገቡ በየሰበካው ቄስ ይታዘዙ ነበር ።

ሙሶሎኒ አዋጁን በሥራ ለማዋል ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተደረገለት ርዳታ የራያንና የሶማሊያን እስላሞች አስነስቶ የብዙ ክርስቲያኖች ደም አስፈሰሰ ። በቤት ፤ በሕፃንና በሽማግሌም ሳይቀር የኦርቶዶክስ ክርስቲያን በሆነ ሁሉ ላይ ግፍ ተፈጸመ ። ብዙ ገዳማትንና አድባራትን አፈራረሰ ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ጠላት እየተከላከለች ያቆየቻቸውን የታሪክና የሃይማኖት ቅርሶቿን ዘርፎ ወስዶ ለቫቲካን አስረከበ ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስታቲስቲክ ክፍል እንደተመዘገበው ፪ሺህ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል ። በአርበኝነት ለሃይማኖታቸውና ለአገራቸው ክብር ሲሉ ከኢጣሊያ ጋር ፊት ለፊት ተዋግተው የሞቱቱትን ክርስቲያኖች ሳይጨምር በአድባራቱና በገዳማቱ ፡— በደብረ ሊባኖስ ፤ በላሊበላ ፤ በአክሱም ፤ በጐ

98. A Bertola Regime dei culti nell Africa Italiana "Bologna, 1939," p. 162.



ንደርና በዝቋላ ብዙ ባሕታውያንና መነኮሳት ካህናት ፤ ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው መሥዋዕት ሁነዋል ። ከጳጳሳቱም ታሪካቸው ለኢትዮጵያ ክርስቲያን መመኪያ የሆነው አቡነ ጴጥሮስ (ቀዳማዊ) ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያና አቡነ ሚካኤል ጳጳስ ዘጐሬ በግፈኛው ፋሽስት ተገድለዋል ።

ከዚህ ላይ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስከፊና አሳፋሪ ሁኖ የሚታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመደምሰስ ቫቲካን ከሙሶሎኒ ጋር መተባበሩ ነው ። እንዲያውም ከሙሶሎኒ ጐን ተሠልፈው ምክር ይሰጡ የነበሩና ብዙ ካህናትንም ያስፈጁ የወታደር ልብስ ለብሰው የመጡ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች ናቸው ይባላል ። ፓፓውም የተቀደሰ ዘመቻ ነው ብለው መድፉንና ታንኩን ባርከዋል ። በዚሁ ሁሉ ድርጊታቸውም በዓለም ክርስቲያኖች ዘንድ ተነቅፈውበታል ።

ከብዙዎቹም መካከል ኤሊክ ሲንድሩም የሚባሉት የስዊድን ጋዜጠኛ ፓፓውን እንዴት እንደወቀሷቸው (ሲሞን ረስቲን የተረጐመውን) ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን ።

«ቅዱስ ሆይ ፤ እኔ በሰሜን አገር የተወለድሁ አንድ ፕሮቴስታንት ነኝ ። ባገራችንም በስዊድን በግንባራችን የምንደፋው በእልፍኞችን ሁነን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ጋር ስንናገር ነው እንጂ ከሰው ጋራ ብንናገር ቁመን እንነጋገራለንና በእግርዎ ላይ ወድቄ ጫማዎን ስለማልስምዎ አይቆጡብኝ ። ቅዱስ ሆይ ፤ እኔ አንድ ምስኪን ኃጢአተኛ ፤ እርስዎ ግን የመድኃኒታችን ምትክ ነዎት የማይሳሳቱም ነዎት ፤ ይሁን እንጂ እኔ እነቅፍዎታለሁ ። እርስዎ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ነዎት ፤ ካቶሊካዊት ማለትም የሁሉ ማለት ነው ። ዛሬ እንግዲህ የርስዎ ቤተ ክርስቲያን በውነት የሁሉ ቤተ ክርስቲያን ናት? እርስዎ ከሙሶሎኒ ጋር ሁነው ከሌላው ዓለም ጋር በጠብ አሉ ። እርስዎና ከርስዎ በታች ያሉት ሌሎችም ጳጳሳት ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ቅኝ አገር እንድትሆን የሚገባ ነው ብለው ተናገሩ ርስዎ መቼም የሐዋርያው የጴጥሮስ ተከታይ ነዎትና አይሳሳቱም ። እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ ቃልዎን

www.ethiopianorthodox.org

ሳይሰማ በኢጣሊያ ላይ «ሳንክሲዮን» ቢያደርግ መሳሳቱ ነው ? ቅዱስ ሆይ ፤ ኢጣሊያ የፍርድ ሥራ ትሠራለች ብለው ሰብከዋል ። የመሲና ፤ የቢሪንዲቢም ጳጳሳት ወርቃቸውን ሁሉ ለጦርነቱ ከሳራ እንደሰጡ ሰማን ። እናንተ ጳጳሳት ይህንን ስታደርጉ እግዚአብሔር ከኢጣሊያ ጋር ነው የማለት ያህል ይመስለኛል ። እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ የኢጣሊያን ሥራ ቢቃወም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቃወም ይሆን ? ኢትዮጵያውያንስ አገራቸውን ሲጠብቁ በእግዚአብሔር ላይ ተነሥተው ይኸንን ርስዎ እንዳሉ ኢጣሊያ የጽድቅ ውጊያ የምትዋጋ ከሆነ ሌላውም ዓለም ይህንን የጽድቅ ጦርነት ቢቃወም መቼም ከናንተ በቀር ሌላው ዓለም ሁሉ እግዚአብሔርን የካደ ይመስላል ። እንግዲህ ርስዎ እንደሚሉት እግዚአብሔር አምላካችን የኢጣሊያ መንግሥት ቃሉን ሊያፈርስ መሐላውንም ሊሰብር ፈቅዷል ። ርስዎ እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን ለመጠበቅ ቢሰበሰቡ ፤ የኢጣሊያ አይሮፕላን ጥርግ አድርጉ ቢያጠፋቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ነው ። ሴቶችንና ሕፃናትን በቦምብ ሲያጠፉ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ ይህንን ሁሉ ካሁን በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ አላገኘነውም ነበርና ርስዎ አሁን ስላስተማሩን ትልቅ ነገር ነው ። ይህንን ሁሉ የምታስተምረን ቅድስቲቱ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ። በዱሮ ዘመን ግን ቤተ ክርስቲያን ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል ብላ ታስተምር ነበር ። ቅዱስ ሆይ ፤ የርስዎ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አይደለችም የሁሉም አይደለችም ፤ እግዚአብሔር መሐላን ማፍረስ ይወዳል ብለው ቢያስተምሩን ውሸትዎ ነው ብለን እንመልስልዎታለን ። ርስዎም የዓለም ሁሉ አባት ነኝ ሲሉ ሳሉ የሙሶሎኒ ባሪያ ሁነዋል ። በኢጣሊያ ላይ ሥጋዊ «ሳንክሲዮን» እንደ ተደረገ ፤ እንደዚሁም በርስዎ ላይ መንፈሳዊ « ሳንክሲዮ » ማድረግ የግድ ነው ። ርስዎ የሚያመልኩት አምላክ ጣዖት ነው እንጂ አምላክ አይደለም። ኢትዮጵያ ፤ ርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም ። ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ ርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም ። ርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውዬው ለሙሶሎኒ የሚታዘዙ ሁነዋልና ። ርስዎ መናገር በተገባዎ ጊዜ ዝም አሉ ፤ ዝም ማለትም በተገባዎ ጊዜ ተናገሩ ። አሁንም ከሌሎች ጳጳሳት ጋራ የሙሶሎኒን ሚና ስመዋል ። የዓለምን ሰላም የሚያውከውን ወንበዴውን ቢያወግዙት ኖሮ ለቤተ ክርስቲያንዎ እንዴት ያለ ጥቅም በሆነ ነበር ። ምናልባት ርስዎም በታሠሩ ነበር ፤ ምናልባትም እንደ ዱር ዘመን ክርስቲያኖች ወደ ሰማዕትነት ሞት በደረሱ ነበር ። ዓለምም ሁሉ ከርስዎ ጋር በሆነ ነበር ። ክርስቲያን ቢሆን አረመኔም ቢሆን ሰው ሁሉ ርስዎ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆኑ በተረዳ ነበር ።



አሁንም በቅርብ የገና በዓል ነው ። ለግፍ ጦርነት ወርቃቸውን የሰጡ ጳጳሳትም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር ላይ ሰላም ይሁን ለሰውም በጐ ፈቃድ ይሁን ብለው ሊዘምሩ ናቸው።ይኸንንም ሲዘምሩ በደረታቸው የወርቅ መስቀል ሳያደርጉ አይቀርም ነገር ግን በጀርባቸው ላይ የእንጨት መስቀል ቢሸከሙ ይሻል ነበር ። ቅዱስ ሆይ ፤ በዓሉን ያሳምርልዎ ብዬ ምኞቴን እገልጻለሁ።» ይህ የጭካኔ ድርጊት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደ ትልቅ ገደል ሁኖ ይኖራል ።

ኢጣሊያ ወደ ሀገራችን ገብቶ ወረራውን እንደ ቀጠለ ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሹመት ለመካሰስ ወደ ሮማ ሔዱ ። የጠየቁት ስላልተሳካላቸው ተቆጥተው ወደ ኢትዮጵያ ሳይመለሱ ወደ ሀገራቸው ገቡ ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተሰብስበው ከአምስቱ ኤጲስ ቆጶሳት አንዱን አቡነ አብርሃምን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አሏቸው ። በዚህ ጊዜ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አድራጐቱ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው ስትል አቡነ አብርሃምንና በርሳቸው የተሾሙትን ሁሉ አወገዘች ። ድርጊቱ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንኳ ነውር የለበትም ብቻ እውነት ይሁን ውሸት ፦ የግብፅ ቤተ ክስበቲያን የምትለው በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. አራቱ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትና አምስተኛ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ ሲሾሙ ውል አለን ነው ። ውሉም ፦ የግብፅ ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ሳታውቀው ሊቀ ጳጳስ መሾም ቀርቶ ኤጲስ ቆጶስ እንኳ እን ዳይሾሙ የፈረሙ መሆናቸውንና አሁን ግን ያንን አፍርሰው መሾማ ቸውን ጠቅሳለች ። አቡነ ቄርሎስም ወደ ግብፅ የተመለሱት በግብፃውያን አባባል ፦ ኢትዮጵያውያኑ ኤጲስ ቆጶሳት ተጨማሪ ኤጲስ ቆጶስ ለመሾም ቢጠይቋቸው አይሆንም ውል አላፈርስም አሉ በዚህም ምክንያት ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ነው የሚሉት ። የግብፃውያንን ግዝት ከምንም ሳትቆጥር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ሥራዋን ቀጠለች ። እያሌ ኤጲስ ቆጶሳትን እየሾመች ለሐዋ ርያዊ ተልዕኮ አሰማራች ።

አቡነ አብርሃም ካረፉ በኋላ (፲፱፻፴፩) መንበረ ሊቀ ጵጵስ ናው ለንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት (ሐዲስ ተክሌ) ተላለፈ ።(በ፲፱፻ ፴፪) ዓ. ም. አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው ተሾሙ የኢጣሊያ ፋሺስት ኃይል ተደምስሶ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ በ፲፱፻፴፯ ዓ. ም. በመጋቢት ወር መጨረሻ ስለ ቤተ ክርስቲያ ናችን ጉዳይ በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ንግግር ተጀመረ ። ወዲያው የግብፅ ፓትርያርክ መልእክተኞች ከጳጳሱ ከአቡነ ቴርሎ ስና ከቤተ መንግሥቱ ሹማምንት ጋራ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሰኔ ወር ውይይት ተደረገ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበችው ሐሳብ ለግብፅ መል እክተኞች በሰኔ ፲፩ ቀን ተሰጥቷቸው ሲሔዱ ገና ከመድረሳቸው በፊት ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ በድንገት ማረፋቸው በሰኔ ፲፰ ቀን ተሰማ ። በመንበራቸውም የሚተኩት አዲሱ ፓትርያርክ እስ ኪመረጡና እስኪሾሙ ድረስ ፲፱ ወሮች ያህል ስለ ፈጀ ነገሩ ፍጻሜ ሳያገኝ ዘገየ ።

በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. በየካቲት ወር መጀመሪያ አቡነ መቃርዮስ የእ ስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኑ ። እርሳቸው ከተሾሙ በኋላ ንግግሩን ለመቀጠል የግብፅ መልእክተኞች በግንቦት ወር ወደ አዲስ አበባ መጡ ። እነዚህ መልእክተኞች ስለፊተኛው ጥያቄ መልስ ይዘው ይሆናል ተብለው ሲጠበቁ አንዳችም መልስ አለመያዛቸውንና ለን



ግገር ብቻ የመጡ መሆናቸውን አስረዱ ። ከብዙ ውይይት በኋላም የኢትዮጵያ ሊቃውንት መክረው ያቀረቡት ሐሳብ በሰኔ ፳፩ ቀን ተሰ ጥቷቸው ተመለሱ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበችው ጥያቄ ፍሬ ነገሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት በስድስት ክፍሎች ተገልጿል ።

፩ኛ/ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤተ ክህነት ክፍል አድገው በሃ ይማኖት ጸንተው ከሚኖሩት መንፈሳውያን አባቶች ለሊቀ ጳጳስ ነት የሚገባው ሰው ተመርጦ በእስክንድርያው አባታችን ተባ ርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት ፥

፪ኛ/ የእስክንድርያው ሲኖዶስ በሚመርጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለጵጵስናና ለኤጲስ ቆጶስነት የሚገቡትን መንፈሳው ያን አባቶች እንዲመርጥና በእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመ ጣው ሊቀ ጳጳስ ባርኮ እንዲሾመው ፥

፫ኛ/ በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆንና መልእክተኞቿ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ ፥

፬ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖ ዶስ ውስጥ መንበር እንዲኖራትና ሲኖዶሱ በተሰበሰበ ቁጥር መልእክተኞቿ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው እንዲገኙ ፥

፭ኛ/ ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋር እንዳትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸው ጳጳሳት ከግ ዝቱ እንዲፈቱላት ፥

፮ኛ/ በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው መንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የእናትነትና የልጅነትም መሠረት የጠነከረ ሁኖ እንዲኖር የገዳም ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እንዲከፈት ፥ ስለዚሁም ት/ቤት አቋቋምና [illegible] ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ቡራኬያቸውን እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ሰጡን ፤ በዚህ ትምህርት ቤት ተመርቀው ለጵጵስና ወይም ለቁ ምስና የታጩት መምህሮች ወደ ምስር ገዳማት እየሔዱ ከወንድ ሞቻቸው ጋር በመንፈስ ተባብረው እንዲመለሱ እንደዚሁም ከም ስር የሚመጡት ወንድሞቻችን ወደ ኢትዮጵያ ገዳም ሲመጡ በመንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ የሚል ነው ።

የጥያቄውም መልስ ከአምስት ወር የሚበልጥ ስለዘገየ ፤ የኢትዮ ጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. እንደገና በደብ ዳቤ ያስታውስ ዘንድ ግድ ሆነበት ፤ ከብዙ ጉትጐታም በኋላ የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. የግብፅ ቤተ ክርስቲያን መልስ ሰጠች ። ነገር ግን የተጻፈው ደብዳቤ ለጊዜ ማርዘሚያ ያህል እንጂ ለሌላ የማይጠ ቅም መሆኑ ስለታወቀ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ቀጥተኛው መልስ በቶሎ እንዲሰጣት እንደገና ሌላ የልመና ደብዳቤ በመጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ተጻፈላቸው ። ከዚህ በኋላ ከግብጻውያን ጉባኤ የስምምነትን መንፈስ የማይደግፍና የሚያሳዝን መልስ በሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተጻፈላት ። በዚህ መልስ ውስጥ ከሠፈሩት ዓይነተኛ ጉዳዮች የኢትዮጵያ ተወላጅ ባገሩ ላይ የሊቀ ጳጳስነት ማዕርግ እንዲያገኝ ተብሎ በ፩ኛና በ፪ኛ ተራ ቁጥር የተጠየቀውን በፍጹም እንደማይቀበሉት በመግለጥ ፤—በኢትዮጵያ ሊሾም የሚገባው ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ ብቻ መሆኑን አረጋገጡ ። ሌሉ ቹን ጥያቄዎች ግን ለምሳሌ፤—በጉባኤ እንዲገኝ በተባለውና ስለ ትም ህርት ቤቱ መቋቋም ፈቃደኞች መሆናቸውን ገልጠዋል ።

ከግብፅ የመጣው ይህ መልስ በሐምሌ ፯ ቀን ወደ ኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀርቦ ከተነበበ በኋላ በኢትዮጵያ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ እንጅ ኢትዮጵያዊ ሊሾም እንደማይችል ግብፃውያን ከወሰኑ ፤ ይህ አስተያየት ዘራችንን የሚያሳንስ የነፃነት ክብራችንንም የሚቀንስ ነውና ኢትዮጵያ ራሷን ችላ መኖር ይገባታል ሲል የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ለመንግሥት አመለከተ ። በኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ከመላው የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ ከሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሊቃውንት



አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ አድርገው ፳፪ ሊቃውንትና ፳፬ መምህ ራን በጉዳዩ እንዲነጋገሩ ተመረጡ ። እነዚህም የተመረጡት ፶፮ ሰዎች በመጀመሪያ ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ፤ ሁለተኛ ኅዳር ፲፫ ቀን ፤ ሦስተ ኛም ኅዳር ፲፮ ቀን በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ተሰብስበው ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርሰው ከተወያዩ በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ አሳለፉ ።

፩ኛ/ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳትም ጳጳስም የሚሾመው ከኢትዮጵያ መም ህራንና መነኮሳት ውስጥ ብቻ እንዲሆን ብሎ መንፈሳዊ ጉባኤ ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ያቀረበው ዋና ጥያቄ የሚገባ መሆ ኑን ተስማምቶበታል ።

፪ኛ/ የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ይህን ጥያቄ ያልተቀበሉት በበቂ ምክንያት አለመሆኑን መላው ጉባኤ ተረድቶታል ።

፫ኛ/ መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ እንዲመረጡ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል ። ይኸውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለሆነ መንግ ታችን መልእክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ጋር ተወያይቶ በሰላም እንዲጨርስልን ነገር ግን መን ግሥት መልእክተኞቹን ልኮ ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ተጠ ባባቂ ወይም ከጉባኤው ከተወያየ በኋላ ፍሬ ያለው መልስ ካል ተገኘ ፤ አሁን ዓቢይ ጉባኤያችን በተስማማበት ውሳኔ ወደፊት እንገፋበታለን።ይህንን ውሳኔያቸውን ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፊርማ ወደ መንግሥት አስተላለፉ ።

ከዚህ በኋላ መንግሥት በቀጥታ ጉዳዩን መከታተል ጀመረ ። ከብዙ ውይይትና መጻጻፍ በኋላ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖ ዶስ አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ ፈቀደ ። አምስት ቆሞሳት ተመርጠው ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም. ወደ ካይሮ ሔዱ። የቆሞሳቱም ስም የሚከተለው ነው ።—፩ኛ/ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፪ኛ/ [illegible] ፫ኛ/ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ፬ኛ/ መምህር ዘሪሁን

www.ethiopianorthodox.org

ብርሃን ፤ ፭ኛ/ መምህር ጌታሁን ናቸው ። ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም. ሥርዓት ሲመተ ጵጵስና ተፈጸመላቸው ። በዚህ ጊዜ ሀ/አመጋ ኅብረ ጊዮርጊስ ፤—አቡነ ባስልዮስ ፤ ለ/መምህር ገሪማ ፤—አቡነ ሚካኤል ፤ ሐ/ሊቀ ሥልጣናት መልአከቱ ፤—አቡነ ቴዎፍሎስ መምህር ዘሩፈ ብርሃን አቡነ ያዕቆብ ፤ ሠ/ መምህር ጌታሁን ፤—አቡነ ጢሞቴዎስ ተባሉ ። እነዚህ ጳጳሳት ይሾሙ እንጂ «ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በራሳቸው ሊቀ ጳጳስ መሾም አለባቸው » የሚለው የኢትዮጵያ ጥያቄ አሁንም አልተመለሰም» የበላይ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ነበሩ ። (ግብፃዊው) አቡነ ቄርሎስ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. አረፉ ። ከሦስት ወር በኋላ የሊቀ ጵጵስና ምርጫ በአዲስ አበባ ተከናውና ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ለመሆን የድምፅ ብልጫ አግኝተው ተመረጡ። ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ፪ኛ ተሾሙ ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትሪያርክነት መንበር ከፍ አለች ። ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ሆኑ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ከ፲፰ ሚሊዮን ያላነሱ ምዕመናን ተከታዮች አሏት ። የካህናት ቁጥር ፤

ሀ/ ቄስ ፸፫ሺህ፭፻፷፫ (ሰባ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ሦስት ፤ )

ለ/ ዲያቆን ፶፪ሺ፭፻፶፪ (አምሳ ሁለትሺ አምስት መቶ አምሳ ሁለት

ሐ/ ደብተራ ፴፱ሺ፵ (ሠላሳ ዘጠኝሺ አርባ) ድምር ፩፻፷፭ሺ፩፻፶፭ ቀሳውስት ፤ ዲያቆናትና ደባትር አሏት።በየጊዜው ከሚሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ሌላ በሀገር ውስጥ ብቻ ፲፫ሺ፴፪ አሥራ ሦስት ሺ ሠላሳ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሏት ። ከነዚህም ፩ሺ፴፪ የገጠር ሲሆኑ ፲፪ሺ የደብርና የታላላቅ ከተማዎች አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።



በውጭ አገርም ፤ በኢየሩሳሌም አምስት ፤ በካርቱም አንድ ፤ በእንግሊዝ አገር አንድ ፤ በአሜሪካና በዌስት ኢንደስ አገሮችም አያሌ አብያተ ክርስቲያናት አሏት ። በኢትዮጵያ ውስጥ ከ፰፻፴፭ በላይ ገዳማት ይገኛሉ ። የመነኮሳቱና የባሕታውያኑም ቁጥር ከ፲ሺ በላይ ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ሕግ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በሲኖዶስ አባላት ተጠንቶና ተረቆ የተጻፈ ሕግ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፳ ሀገረ—ስብከቶች አሏት ። ይህም ማለት ከፓትሪያርኩ ጋር ፳ የሲኖዶስ አባላት ጳጳሳትና ሊቃነ—ጳጳሳት አሉ ማለት ነው ። ይህ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ያሉት የሲኖዶስ አባሎች ከነሀገረ ስብከታቸው እዚህ ላይ እንገልጻለን ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የርእሰ ከተማዪቱ የአዲስ አበባን ሀገረ ስብከት ይዘው ሊቀ ጳጳስና የመላዋ ኢትዮጵያ ፓትርያርክ የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ፤

፩/ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሐረር ሊቀ ጳጳስ ፤
፪ኛ/ » » መርቆሬዎስ የጐንደር ሊቀ ጳጳስ ፤
፫ኛ/ » » ኤፍሬም የአርሲ ሊቀ ጳጳስ ፤
፬ኛ/ » » መቃርዮስ የጐጃም ሊቀ ጳጳስ ፤
፭ኛ/ » » ዜና ማርቆስ የወለጋ ሊቀ ጳጳስ ፤
፮ኛ/ » » በርተሎሜዎስ የሲዳሞ ሊቀ ጳጳስ ፤
፯ኛ/ » » ናትናኤል የትግራይ ሊቀ ጳጳስ ፤
፰ኛ/ » » ዘካርያስ የጋሞ ጐፋ ሊቀ ጳጳስ
፱ኛ/ » » መርሐ ክርስቶስ በሐረር የሰሜንና የምዕራብ አውራጃዎች ሊቀ ጳጳስ ፤
፲ኛ/ » » ኤልሳዕ የከፋ ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፩ኛ/ » » ሰላማ የባሌ ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፪ኛ/ » » ታዴዎስ የኢሉባቦር ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፫ኛ/ » » ይስሐቅ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፬ኛ/ » » ሳሙኤል የወሎ ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፭ኛ/ » » በርናባስ የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯ኛ/ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ ፤
፲፰/ » » ጢሞቴዎስ የከፋ የማጅና የጊሚራ ሊቀ ጳጳስ
፲፱ » » ገብርኤል የኤርትራ ሊቀ ጳጳስ ።
፳ » » ኤልያስ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ጳጳስ
፳፩ » » ገሪማ በሱዳን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ
፳፪ » ጳውሎስ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ኃላፊና የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ናቸው ።

ምዕራባውያን በተሳሳተ ግምት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ የቤተ ክርስቲያኒቱም የበላይ ራስ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ ። ነገር ግን ከላይ እንደ ገለጥነው የቤተ ክርስቲያኒቱ ራስ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ። የምትመራውም በሲኖዶስ ሕግ ነው ። እጨጌ የሚለው ቃል ከአቡነ ተክለ—ሃይማኖት ጀምሮ የደብረ ሊባኖስ አበ ምኔቶች የማዕርግ ስም ነው ። አቡነ ባስልዮስ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እየተባሉ ጵጵስና ሲቀበሉ ፤ «አበነ ባስልዮስ እጨጌ ወጳጳስ» ተባሉ ። የሊቀ ጵጵስናውንና የፓትርያርክነቱንም ሥልጣን ሲደርቡ እጨጌነቱን አልለቀቁም ። በዚሁ ሳቢያ ወራሾቻቸው ሁሉ የእጨጌነቱንም ሥልጣን እንደያዙ ቀሩ ። በመላዋ ኢትዮጵያ ከ፩፪፻ የማይበልጡ በበጀት ተቀጥረው የሚያስተምሩ የወንጌል መልዕክተኞች አሉ ። በከፍል የሚያስተምሩ ከ፩ሺ የማያንሱ መምህራንና ፳፪፻፴፱ የመጀመሪያ ደረጃ ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትሪያርክ ሥር ይተዳደራሉ ። ነገር ግን ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስነው የወንጌል መልእክተኞች የመምህራንና የትምህርት ቤቶች ቁጥር ቤተ ክርስቲያኗ በትምህርት በኩል ያለባትን ችግር ለማቃለል በቂ አይደለም ።

ቤተ ክርስቲያንን እንደገና ሊያንቀሳቅሳትና ሊያራምዳት የሚችለው የጥንት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና የዩኒቨርሲቲ (መንፈሳዊ ኮሌጅ) ተማሪዎች አንድ ላይ ሁነው ቀሳውስቱን በመንፈሳዊ ትምህርት በማሠልጠን ለምዕመናኑ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ዘመኑ በሚፈቅደው መሠረት በመስጠት ቢተባበሩ በየገዳማቱ የመነኮሳት መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያገግም ምሁራኑ ገዳማዊ ሕይወትን ቢመሠርቱና ቢያስፋፉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያኗትን አጽንቷ ለመጠበቅ ሌሎቹንም ለማቅረብ ትችላለች ።

www.ethiopianorthodox.org

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

## ምዕራፍ ፯

### ክፍል ፩

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት (ዶግማ)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ከዚህም ጋር ከሐዋርያት ጀምሮ ባፍ በመጣፍ በቤተ ክርስቲያን ሊታወንት ትምህርትና ትውፊት (tradition) ላይ የተመሠረተ ነው ። (ሃይማኖት ርትዕት እንተ ሐዋርያት ትውፊት) «ቄርሎስ» እነዚህንም ሁለት የእምነታችን መሠረቶች እንደሚከተለው እንገልጸቸዋለን ፤ ሀ/ በቅዱሳት መጻሕፍት ስማዕ እሥራኤል አሐዱ ውእቱ አምላክከ 101። ባለው መሠረት ባንድ አምላክ ማመንን ታስተምራለች ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን (Monotheistic) «ባለ አንድ አምላክ ናት» ። 102። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን (ሞኖቴይስቲክ) ባለ አንድ አምላክ ብትሆንም እንደ ብሉይ ኪዳን እምነት አንድ ገጽ ማለት አይደለም ። እንደ አዲስ ኪዳን ትምህርትና አማናዊ ምስክርነት «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» 103። ባለው አምላካዊ ትምህርት መሠረት በሦስት አካላት (በሥላሴ) በአንድ መለኮት ታምናለች ።

ለ/ ከሐዋርያት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ሊታወንት ስለ አንድነትና ሦስትነት የተሰጠውን አርቶዶክሳዊ ምስክርነት ተቀብላ

---

100. J. Spencer Trimingbom, The Christian Church in Ethiopia, (World Dimination Press, 1950) p. 17

101. ዘዳግም ፮ ፣ ፬ ።

102. ቀዳ. ቆሮ. ፰ ፣ ፮ ፤ ኤፌ. ፬ ፣ ፫—6 ፤ ቀዳ. ቆሮ. ፲፪ ፣ 6 ፤ ቀዳ. ቆሮ. ፰ ፣ ፮ ፤ ሚልክ. ፪ ፣ ፲ ፤ ማር. ፲፪ ፣ ፳፱ ።

103. ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

እነሱ ስለ ቅድስት ሥላሴ የሰጡትን ትምህርት ታስተምራለች ። ቅድስት ሥላሴ ፤ አብ ፤ ወልድ ፤ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ ። የአብ ግብሩ መውለድ ፤ የወልድ ግብሩ መወለድ ፤ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረጽ ነው ። አብ ቢወልድ ቢያሠርፅ እንጂ እንደወልድ አይወለድም ፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠርጽም ፤ ወልድም ቢወለድ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርጽም ፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠርጽም ፤ መንፈስ ቅዱስም ቢሠርጽ እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርጽም ፤ እንደ ወልድ አይወለድም ። ለአብ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው ። ለወልድም ፍጹም አካል ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ አለው ፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው ። እነዚህም ኩነታት ይባላሉ ። ኩነት ማለት ቅርጽ ማለት ነው ( በዓረብኛ ከወነ ብሎ ቅርጽ አወጣ ይላል ።) ሊቃውንት ስለ ሦስትነት ባጭሩ ከዚህ በላይ እንደ ገለጥነው ሲያስተምሩ ለትምህርታቸው ምሳሌ ከሥነ ፍጥረት ጠቅሰዋል ።

ለምሳሌ ፤ ለፀሐይ ሦስትነት አለው ፤ ሀ/ ክበቡ ፤ ለ/ ብርሃኑ ፤ ሐ/ ሙቀቱ ፤ በክበቡ አብ ፤ በብርሃኑ ወልድ ፤ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል ፤ ነገር ግን አንድ ፀሐይ ይባላል እንጂ ሦስት ፀሐይ እንደማይባል ሥላሴም በስም በግብር በአካል ሦስት ቢባሉ ፤ አንድ አምላክ ናቸው እንጅ ሦስት አማልክት አይባሉም ። ሥላሴ በዘመን አይቀዳደሙም ፤ በክብር አይበላለጡም ። ሥላሴን በዘመን አቀዳድሞ ፤ በክብር አበላልጦ የሰበከ አርዮስ (ወልድ ፍጡር በመለኮቱ) በኒቅያ ጉባኤ (፫፻፳፭ ) ተረትቷል ። መንፈስ ቅዱስን ሕጹጽ ያለ መቅዶንዮስም በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ( ፫፻፹፩ ) ተረትቷል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢረ ሥላሴን ሊያፋልሱ ተነሥተው የነበሩ እነዚህን መናፍቃን ስታወግዝ ትኖራለች ። መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ ሠረጸ የሚሉትንም ታወግዛለች ።

ሐ/ በምሥጢረ ሥጋዌም ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ በፍጹም ባሕርያዊ ተዋሕዶ ከቅድስት ድንግል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ እኛን ለማዳን መወለዱን ጥምቀቱን ፤ በጲላጦስ ዘመን መሰቀሉን ፤ መሞቱንና መነሣቱን ወደ አባቱ ማረጉን ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን መላኩንና ኋላም ለፍርድ መምጣቱን ታስ



ተምራለች ። ወዶ ባደረገው አትሕቶ ርዕስ (በቄርሎስ አነጋገር) በዚህ ድንቅ በሆነ ምሥጢር ከቅድስት ድንግል የተወለደው እሱ ከሁለት አካል አንድ አካል ፤ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ነው ። ተዋሕዶውም እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ነው ። በዚህም እምነቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኤፌሶን ጉባኤና (፬፻፴፩ ዓ. ም. ) ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር በመተባበር ሥጋን ከመለኮት ነጥሎ አካልና ባሕርይን ከፋፍሎ የሰበከ ንስጥሮስንና ተከታዮቹን ስታወግዝ ትኖራለች ። ሥጋን ከመለኮት ጋር ቀላቅሎና አጣፍቶ የተወገዘውን የአውጣኪን ትምህርት አትቀበልም ። በ፬፻፶፩ ዓ. ም. በመርቅያን በብርከልያና (ሉልክሪያ) በሮማው ፓፓ በልዮን ቀዳማዊ አነሳሽነት ተረፈ ንስጥሮቄውያን መለካውያን በጉባኤ ኬልቄዶን የወሰኑትን የምንታዌ ትምህርት (dualism) ታወግዛለች ።

በዚሁ በምሥጢረ ሥጋዌ «ርጉም ንስጥሮስ» ቅድስት ድንግል ማርያምን "ወላዲተ አምላክ" አትባልም ብሎ ስለነበር ቅድስት ማርያም "ወላዲተ አምላክ" መሆኗን ትመሰክራለች ። ከንስጥሮስ በፊትም ሆነ ከሱ በኋላ የተነሱ (አንዲ ዲኮማርያቶስ) «አንጢንድቆ ማርያጦስ» ፀረ ማርያም ማለት ነው ። ድንግልናዋን ለማጉደፍ የሚናገሩትን ሁሉ ትቃወማለች ። እነሱ እንደሚሉት ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቶስን የወለደችው በዘርዓ ብእሲ ነው ይላሉ ። ይህም እሷን ብቻ ሳይሆን የተሳደቡት ልጅዋንም ነው ። እሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ነው ማለት ነውና ። ይህም ዘለፋቸው የቅዱስ መጽሐፍን ምስክርነት እንዳልተቀበሉ ያስረዳል ። 104. እሱን ከወለደችውም በኋላ ሌሎች ልጆች ወልዳለች የሚሉም አሉ ።የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህንም ታወግዛለች ። ድንግል ማርያም (ቅድመ ጸኒስ ፤ ጊዜ ጸኒስ ፤ ድኅረ ጸኒስ ፤ ቅድመ ወሊድ ፤ ጊዜ ወሊድ ፤ ድኅረ ወሊድ ፤) ድንግል ናትና ። ከዚህም ጋር ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደ ጻፈው ጌታ በመልዕልተ መስቀል ላይ እንዳለ እናቱን እንዲጠብቅለት ራሱ ወንጌላዊው ዮሐንስ አደራ መቀበሉን ተናግሯል ። ሌላ ልጅ ቢኖራትማ ለተማሪው አደራ የናቱን ነገር ይለው ነበርን ምሥ

104. ማቴ. ፩ ፡ ፲፰ ፤ ሉቃ. ፩ ፡ ፴፩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ጢሩ ሥጋዌን እንደ መሰላቸው አድርገው ለማቅረብ የሞከሩ መናፍቃን እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸውን የጠራነው መናፍቃን ብቻ አይደሉም ። ባለፈው ብዙዎች ነበሩ ፤ ወደፊትም መልካቸውን እየለዋወጡ ይነሳሉ ። ከሆነ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለመናፍቃን እጅዋን ሳትሰጥ መኖሯን ባለፈው ተመልክተናል ። ብዙ የውጭ አገር ሰዎች የወንጌል መልዕክተኞች ነን እያሉ ተመላልሰውባታል ።

የካቶሊኮች መምጣት ከፖርቱጋሎች ጋር መሆኑን ባለፈው ገልጠናል ። የፀረ ማርያም (ፕሮቴስታንት) የተባለው ቡድን መምጣት የጀመረው በ፲፮፻፴፬ ዓ.ም. ጀምሮ ነው ። መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ጀርመናዊው ጴጥሮስ (Hefling) ነው።ጀምስ ብሩስ የተባለው እንግሊዛዊም የመጣው 105 ።የኢትዮጵያን የሃይማኖት ይዞታ ለመሰለል ነው ። በ፲፰፻፳፪ ዓ. ም. የፕሮቴስታንት ሚሲዮን ሳሙኤል ጐባት (Samuel Gobat) እና (Christian Kuglar) ክርስቲያን ኩግለር የተባሉ ሁለት ሚሽዮኖች መጥተው ነበር ። ከነሱም በኋላ (C.W.Isenberg) እና (Ludwing Kraft) የተባሉ ሚሲዮናች መጥተው ነበር ። ፲፰፻፵፰ ዓ. ም. ከስዊዘርላንድ እየተነሱ ብዙ ሚሲዮኖች መጥተዋል ። በየጊዜውም ከስዊድን ፣ ከኖርዌይ ፣ ከሆላንድና ከጀርመን ብዙ የፕሮቴስታንት መልእክተኞች መጥተዋል ። እነ ዚህም የሚመጡት ሕዝቡን በሃይማኖት ከፋፍለው ሀገሪቱን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ነው ። ለምሳሌ እነ ሊዎፖልድ ትራቤሊ እነ አን ጀሎ ቬንኪ ፣ እነ ጁሴፔ ሳፔቶ ፣ እነ ጉሊዮልም ግሳያ እነሱንም የመሳሰሉ የፖለቲካ ሰዎች ሁሉ እንደ እስላም ኢማማ እየጠመጠሙና ግልድም እየታጠቁ ጦር እየያዙ አባ ዱላ በሉን እያሉ በእስላሞቹ ቤት እየዞሩ በሃይማኖት ስም የፖለቲካ ጉዳያቸውን ያካሒዱ ነበር ። 106 ። በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት አልፎንሱ ሜንዴዝ በሁለት ኢትዮጵያውያን በቁረንጭ መናፍቅ ኤዎስጣቴዎስና በር

105. ከ፲፮፻፳፰—፲፮፻፴፪ ዓ. ም.

106. ሊምፔር ኩሉኔያል ፋሽስታ የተባለውን መጽሐፍ መመልከት ለዚህ ታሪክ አገላለጥ ደጋፊ ይሆነዋል ።



ጉም ተክለ ሃይማኖት ላይ የዘራው የቅብዐትና የጸጋ እምነት የሀገሬቱን ሊቃውንትና መሪዎችም ጭምር ከፋፍሏቸው እንደነበር ያለፈውን ማስታወስ ይበቃል ። የቅብዐት ልጅ የሚባሉት ፦« ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ» ተዋሕዶ ሁለትነትን እንጂ ንዴትን ከሥጋ አላራቀም ፤ ንዴት ከሥጋ የራቀው ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ በማኅፀን በተቀባ ጊዜ ነው ይላሉ ። እነሱም በሦስት ይከፈላሉ ።

ሀ/ መጀመሪያ በዓፄ ፋሲል ዘመን የነበሩት እነ ዕውር ዘኢየሱስ መጽሐፍ እንደየ ርእሶ ይላልና 107 ። ቃል በተዋሕዶ ጊዜ ዜገ ከሥጋ ጋር ሲዋሐድ የባሕርይ ክብሩን አጣ ለቀቀ ፤ ሲቀባ ወደ ጥንተ ክብሩ ተመልሶ በሰውነቱም ባምላክነቱም አንድ ወገን የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል ። ተቀቢው ቃልም ሥጋም ነው ። ምሥጢሩ እንደ በትረ ሙሴ ማለት ነው ። ሚጠትንና ውላጤን ባንድነት ያሳያል ።

ለ/ በቀዳማዊ ዮሐንስ ጊዜ የነበሩት (ጻድቁ ዮሐንስ) እነ አካለ ክርስቶስ ደግሞ ዜገ ማለትን ነቅፈው አጸይፈው «መጽሐፍ» እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ» ይላልና ሥጋ በተዋህዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነት ክብር አላገኘም ሲቀባ ግን ክብር ተላልፎለት ተፈጥሮ ተጉብሮ ጠፍቶለት በቅብዓት የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ብለዋል ። ምሥጢሩ መቀባትንና መለወጥን ለሥጋ ብቻ መስጠት ነው ።

ሐ/ በዓፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የነበሩት እነ አለቃ ጐሹ (አራት ዓይን) በቅብዐት ብቻ ማለትን ነቅፈው መጽሐፍ በሁለቱም ሁሉ በተዋሕዶ ከበረ በቅብዐት ከበረ ይላልና ቅብዓት ያለ ተዋሕዶ ተዋሕዶም ያለ ቅብዓት ብቻ ብቻውን አያከብርም ፣ በተዋሕዶና በቅብዓት ባንድነት የአምላክነት ክብር ከብሮ የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል ፤ ምስጢሩ ሁሉ ፍጹም ውላጤ ነው ። 108 ። ቅብዓቶች ፦«አብ

107. ካልዕ ቆር. ፰ ፣ ፱ ፤

108. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ « ቀብዐ » የሚለውን ግሥ ተመልከት

www.ethiopianorthodox.org

ቀባኢ ፣ ወልድ ተቀባኢ ፣ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ፣ ነው በማለት ሁሉም አንድ ናቸው ። ይህም ማለት ሦስቱን አካላት በሀብት ከፋፍለው አብን ሰጪ ፣ ወልድን ተቀባይ ፣ መንፈስ ቅዱስን ስጦታ ማድረጋቸው ነው ።

መ፡—ምንም እንኳ በምሥጢር ከቅባቶች ጋር አንድ ቢሆኑ በንባብ የተለያዩ ስም ስላላቸው የጸጋ ልጅ የሚባሉት ደግሞ ይህን የመሰለ አስተሳሰብ ነበራቸው ፤ ጸጐች የሚሉት ፡—አዳም በተፈጥሮ ያገኘውን ንጽሐ ጠባይዕ በፈጣሪው ላይ ባመጠ ጊዜ ጨርሶ አጣው ፤ ቃል አዳምን ወደ ነበረበት ለመመለስ ክብሩን ለማደስ ሰው በሆነ ጊዜ አዳምን ወደ ነበረበት ሀገሩ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ የሚያስችለውን ሥልጣን ከአብ ዘንድ ተቀበለ ። ይኸውም በፈለገ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ሲያርፍበት ነው ። በዚህ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ቃል ሦስተኛ ተወለደ ።—ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት አንድ ልደት ፣ ድህረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ ሁለት ልደት ፣ ኋላም በዮርዳኖስ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ልደት ፣ የሚሉት እንደዚህ አድርገው ነው ። እነሱ እንደሚሉት ተቀብዐ አንቀጹ የቃል ስለሆነ ሥጋን አይመለከትም ፣ በእነሱ እምነት መሠረት ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ፣ ሥጋ የቃል ክብር ፤ ተላልፎለት ከብሯል ፣ ቃል ግን ወልደ አዳም ፣ ወልደ አብርሃም ፣ «ወልደ ዳዊት ፣ ወልደ ማርያም ለመባል የበቃው በተዋሕዶ ሳይሆን በሦስተኛው ጊዜ መወለድ ነው ፤ በዚህ በሦስተኛው ልደት ደቂቀ አዳም ከወልድ ጋር ተዘምዶ አላቸው ልደት ያገኛቸዋልና ይላሉ። «ወበዛልሳይ ልደት እምአቡሁ ፣ ሀለወነ ተዘምዶ ምስሌሁ።») የጸጐች ቅኔ»፡— ሐሳባቸውን ባጭሩ ለማገለጥ ያህል የቃል ከሥጋ መዋሐድ ሥጋን ሲያከብር፣ቃልን ፍጹም ሰው ለመባል ያበቃው ቅብዓት መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



ርስቲያን ይህንን ትምህርት በመቃወም ፡—«እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ፣ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል በተዋሕዶ» በተዋሕዶ የቃል የሆነው ሁሉ ለሥጋ ሆነ፣ የሥጋ የሆነው ሁሉ ለቃል ሆነ፤ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት መወለዱ አንድ ልደት ፣ ድህረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ ሁለት ልደት ፣ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ እያለች ትናገራለች ።

ጸጐች ከቅብዐቶች የሚለዩበትን እንደሚከተለው እናቀርባለን ።

| ጸጐች | ቅብዐቶች |
| --- | --- |
| ቅብዓት የጸጋ (የማደጎ ልጅ ሆነ) ተቀብዐ፡አንቀጹ ለቃል ብቻ ነው፤ | በቅብዐት የባሕርይ ልጅ ሆነ ተቀብዐ ፣ አንቀጹ ለቃልም ለሥጋም ነው ። |

የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበለው በዮርዳኖስ ፣ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበለው በማኅጸን ፣

የጸጐችና የቅብዓቶች ትምህርት በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የግኖስቲኮችና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱ የነጳውሎስ ሳምሳጢን የጸጋ ትምህርት ይመስላል ። አዶፕሺኒዝም (Adoptinism) ልዩነቱ እነ ጳውሎስ ሳምሳጢ ፡—ቃል ቅድመ ሥጋዌ የነበረውን አካላዊ ህላዌ (ኩነት) ሲክዱ ፣ እነዚህ ግን ይህን የሚሉ አይመስለኝም ። በዚሁ እምነታቸው በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ብዙ ጊዜ ብጥብጥ ሲፈጥሩ እንደ ኖሩ ያለፈውን ታሪክ ማስተዋል ይጠቅማል ።

ከጸጐችና ከቅብዓቶች ሌላ ፣ በምሥጢረ ሥጋዌ የወልድን አምላክነት የጠበቅን መስሏቸው «መለኮት በአካል ሦስት ነው» ወላዲ፣ መለኮት ፣ ተወላዲ መለኮት ፣ ሠራፂ መለኮት ፣ የሚሉ፣ እንደነበሩ የሚታወስ ነው ። በመሠረቱ ወላዲ ፣ ተወላዲ ፣ ሠራፂ

www.ethiopianorthodox.org

የሚለው ቃል ለሥላሴ የአካል ግብር ይባላል ። መለኮት ግን የሦስቱም አንድነት የሚነገርበት ቃል ነው ። የሥላሴን አንድነት የሚያመለክተውን፡—«መለኮትን» ለአካል ግብር ቅጽል አድርጎ ማቅረብ ሦስቱንም ወላድያን ፤ ሦስቱንም ተወላድያን ፤ ሦስቱንም ሠራጽያን ፤ ማለት ነው ። ግብርንና ስምን ያፋልሳል ፤ አንድነት ሦስትነትን ያጣፋል ፤ ያደናግራል ። «ኢይፈልስ ስመ አብ እምከዊነ ስመ አብ ኀበ ከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፤ ወስመ ወልድኒ ኢይፈልስ እምከዊነ ስመ ወልድ ኀበ ከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወስመ መንፈስ ቅዱስኒ ኢይፈልስ እምከዊነ ስመ መንፈስ ቅዱስ ኀበከዊነ ስመ አብ ወወልድ» የሚለውን ጎባብ ያልተመለከተ አስተሳሰብ ነው ። ይህ አስተሳሰብ ቀድሞ በዮሐንስ ተዓቃቢ ብቅ ብሎ የጠፋ ነው ። ወደ ሀገራችን ግን ማን እንዳመጣው አይታወቅም ብዙ ጊዜ ገዳማቱን ሲያፋጅ ኑሯል ። አሁንም በዋልድባ ርዝራዡ አለ ይባላል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምሥጢረ ሥላሴም ሆነ በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርቷን በቅዱሳት መጻሕፍትና በሊቃውንት ትርጓሜ ላይ መሥርታ ከመናፍቃን የሚሠነዘረውን ሁሉ በመከላከል ከፍተኛ ተጋድሎ ስታደርግ ኑራለች ፤ ትኖራለችም ።

ሐሳባችንን ለማጠቃለል፡—በምሥጢረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያናችን በሦስት አካላት በአንድ መለኮት ታምናለች ። በምሥጢረ ሥጋዌም፡—ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ታምናለች ። ታስተምራለች ። ተዋሕዶውም ባሕርያዊ ነው ። ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት መወለዱ አንድ ልደት ድህረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ ሁለት ልደት ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ።—የ ቤተ ክርስቲያናችን እምነት ይህ ነው ።



ክፍል ፯ ።

የታቦት ፤ የሥዕልና የመስቀል ክብር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

# ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ሀ/ ታቦት ፡— ከብሉይ ኪዳንና ከእሥራኤል የነፃነት ሕይወት ጋር የተያያዘ ታሪክና የት መጣ አለው ፤ ታሪኩና የትመጣው የታወቀ ቢሆንም ለመግቢያ ያህል በመጠኑ ከዚህም እናነሣለን ።— እሥራኤል በግብፅ ፬፻፴ ዓመታት ያህል በባርነት ቀንበር ሲገዙ ከኖሩ በኋላ በሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር ተአምራት ከግብፃውያን የአገዛዝ ቀንበር ነፃ ወጡ ። ወደ አገራቸውም ለመመለስ አርባ ዓመት ሙሉ በቃዴስ በረሀ ሲኳትኑ ኖሩ ። በግዞት ሳሉም ሆነ አሁን በጉዟቸው ከአባቶቻቸው የወረሱትን ሃይማኖት አልረሱም ። «የአብርሃም ፤ የይስሐቅ ፤ የያዕቆብ ፤ አምላክ » አዶናን ፤ ፍረድልን ከማለት አቋርጠው አያውቁም ነበር ። ይህን ጽኑ እምነታቸውንና በስሙ ስለ ተጠሩ የሚደርስባቸውን ሥቃይና ግፍ ተመልክቶ ነፃ አወጣቸው ። ነፃ ካወጣቸውም በኋላ በድብቅ በግዞት ያቀርቡ የነበረውን አምልኮት ነፃ ሕዝብ ሁነው በነፃ እንዲያመልኩት ራሱ ስለፈለገ በዚያው ሲጓዙበት በነበረው በረሀ ውስጥ በምትገኝ በሲና ኮረብታ ላይ ለመሪያቸው ለሙሴ ተገልጦ የውለባ የቃል ኪዳንና መታዘዝ ምልክት የሚሆኑ አሥር ሕግጋትና ትእዛዛት የተጻፈባቸው ሁለት የዕብነ በረድ ገቢታዎችን (ሠሌዳዎችን) ሰጠው ለእሱም ማስቀመጫ ታቦትና እንደ መቅደስም የምታገለግል የምስክር ድንኳን እንዲሠራ ሙሴን አዘዘው ። 109. ታቦት የጽላቱ ማደሪያ ነው ። 110. ምናልባትም በግዕዙ አወጣጥ ቤተ «አደረ» ከሚለው

109. ዘፀአ. ፳፭ ፡ ፲፱ ፤ ፲፭ ፡ ፲፰ ፤ ፳፭ ፤ ፲ ፡ ፳፱ ፤
110. ዘፀአ. ፳፭ ፡ ፳፪ ፤ ዘሌዋ. ፲፮ ፡ ፲፪

www.ethiopianorthodox.org

ግሥ የወጣ ሳይሆን አይቀርም ። የታቦት ትርጓሜው ማደሪያ መሠወሪያ ማለት ብቻ ሳይሆን መታያ መገለጫም ነው ። ንጉሥ በዙፋኑ እንዲገኝ ፥ እንዲገለጥ ታቦት ለእሥራኤል የአምላክ መገለጫ ነውና ። እሥራኤል በጉዟቸው ሁሉ ታቦት ይዘው ሲጓዙ የኖሩ እነ ሰሎሞን ለታቦቱ የሚሆን ቤተ መቅደስን በከፍተኛ ወጭ ያሠሩትና ለታቦት ይሰገዱ ይንበረከኩ የነበሩት በታቦቱ ውስጥ በነበረው በጽላቱ ዐሠርቱ ቃላት ስለተጻፉ ብቻ አልነበረም ። ግን እሥራኤል ኃጢአት ሠርተው አምላካቸውን ባስቀየሙት ጊዜ በአባር ፥ በቸነፈር ፥ በምርኮ—በጦር ይቀጣቸዋል ። ንስሐ ሲገቡና ሲለምኑት ደግሞ አባት ለልጁ እንደሚራራ ራርቶ ይምራቸው ነበር የእግዚአብሔር ምህረት እንደ መጣላቸው የሚያውቁትም በታቦቱ ላይ ብርህት ደመና መጥታ ስታርፍ ነበር ። ይህንንም ዕብራውያን «ሸኪናሐ» ይሉታል ፥ ለምሕረት መገለጥ ለምሕረት መምጣት ማለት ነው ።

ባጠቃላይ አነጋገር ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለምሕረት ለሕዝቡ በሚገለጥበት ጊዜ ዙፋኑ ነው ማለት ነው ። 111* ወደ ዋናው ሐሳባችን እንመለስና ታቦት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በልማድ ያለ አይደለም ፥ ወይም አንዳንድ የዋሆች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ኦሪትን ከሥርዓተ ወንጌል ጋር በባላንጣነት የምታታግል አይደለችም ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጀመሪያ ላይ እንዳነሣነው ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን አገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ጠቃሚ ነገሮች በክርስትና መንፈስ እየተረጐመች ትጠቀምባቸዋለች ። ከብ

111. ዘፀአ. ፲፫ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ። ፲፱ ፥ ፲፮ ፥ ፲፰ ። ፳፬ ፥ ፲፮ ፥ ፲፯ ። ፴፫ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ፥ ፵ ፥ ፴፬ ፥ ፴፰ ። ፳፰ ፥ ፳፩ ፥ ፳፪ ። ፲፮ ፥ ፯ ። ዘዳግ ፥ ፩ ፥ ፴ ። ዘኍል. ፱ ፥ ፲፭—፲፮ ። ፯ ፥ ፳—፱ ። ፴፳ ። ፳፳ ፥ ፳፪ ። ፲፮ ፥ ፯ ። ዘሌዋ ፥ ፲፮ ፥ ፪ ። ፱ ፥ ፮ ፥ ፳፫ ። ዘኍል. ፲፬ ፥ ፲ ። ፲፮ ፥ ፲፱ ፥ ፴፬ ። ፳ ፥ ፮ ። ነገሥ. ቀዳ. ፰ ፥ ፲ ፥ ፲፩ ። ዮሐ. ፩ ፥ ፲፬ ። ሐጌ. ፬ ፥ ፱ ።



ሉይ ኪዳን ከወሰደቻቸው አንዱ ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ነው ። አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሠራበት ጊዜ ከዕፀ ወይም ከዕብነ በረድ ተቀርጾ በላዩ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ስም (ኅቡዕ ስም) «አልፋና ኦሜጋ» የመጀመሪያውና የመጨረሻው ማለት ነው ። ይህ ቃል ከተጻፈበት በኋላ በኤጲስ ቆጶሱ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል ። በቅዳሴም ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ወደ መሆን የሚለወጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው ። የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእሥራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጥበት ዙፋን ነበር ይህ ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ፥ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ እያለ ያመኑትን ሁሉ የሚጠራበት የምሕረት ምስዋዕ ነው ። ክብርና ስግደትም የሚደረግለት ስለዚህ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ታቦት ያላት ትምህርታዊ መመሪያ ያልገባቸው አንዳንዶች እንደመሰላቸው ቢተረጉሙት ቤተ ክርስቲያናችን በሙሴና በክርስቶስ ፥ በብሉይና በሐዲስ ወይም በጣኦትና በእውነት፥በምሳሌና በአማናዊ ያለውን ልዩነት ስለምታውቅ ለሚጠይቋት ሁሉ ይህንን እምነቷን ከማስረዳት ተቆጥባ አታውቅም።

ከኢትዮጵያም ሌላ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (Oriental Churches) ታቦት የተለመደ ሕግ ነው ። ሥጋውን ደሙን የሚፈትቱት በታቦቱ ላይ ነው ። ለምሳሌ ግብፃውያን ታቦቱን ፥— «ሉሕ»ይሉታል ፥ ጽላት ሠሌዳ ማለት ነው ። ያለሱ ሥጋውና ደሙን አይፈትቱም ። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተብለው የሚጠሩ ፥— «የግሪክ ፥ የሩሲያ ፥ የሩማንያና » ሌሎችም ወደ ክርስትና የተመለሱት ከአረማዊነት ስለሆነ የታቦትን ምሥጢር አያውቁትም በታቦቱ ፈንታ ከመንበር የማይነሳ እንደ ታቦት የሚከበር የጌታ የስቅለቱ ወይም የግንዘቱ ሥዕል ያለበት የነጭ ሐር መጐ

www.ethiopianorthodox.org

ናጽሬያ አላቸው ። ያለሱ ሥጋውና ደሙን አይፈትቱም ። ይህንንም በዕርዕ ፦ «እንዲሚንሲዮን» ይሉታል ። «ህየንተ ታቦት» ማለት ነው ። የሮማ ካቶሊኮች ፦ «ሜንሳ » MENSA ይሉታል ፥ ጠረ ጴዛ ማለት ነው ። ከዚህም ጋር እነሱ ከአምስቱ የምሥራቅ አብ ያተ ክርስቲያናት በቀር አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚሠየምበት ጊዜ በመንበሩ ላይ የዐፅመ ቅዱሳን ሽራፊ እንዲቀመጥበት ቀኖናቸው ያዝዛል ።

እንግዲህ በኛ በኩል ስለ ታቦት ክብር ለሚጠይቁን ሁሉ መጽ ሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ መረጃችን (Tradition Proof) በመ ጠኑ ይህ ነው ።

ለ/ ሥዕል ፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ከክርስትና በፊት ሥዕል በቤተ አሕዛብም ሆነ በቤተ አይሁድ የታወቀና ከአምልኮት ጋር የተያያዘ ነበር ። በቤተ አሕዛብ እን ጨት ጠርቦ ደንጊያ አለዝቦ ማምለክ የተለመደ ነበር ። እንዲያ ውም የሮማ ነገሥታት አማልክት ተብለው ከመመለካቸው በላይ ከሞቱ በኋላ ሥዕላቸው በደንጊያና በእንጨት እየተቀረጸ ሲመለኩ መኖራቸው በታሪክ ይታወቃል ። ክርስትና በመጣ ጊዜም ከክርስ ትና ጋር ያጣላቸው ይኸው ልማዳቸው ነው ። በክርስትና ትምህ ርት ይህ አምልኮ ጣዖት ነውና ፤ በቤተ አይሁድም እንደ አሕዛብ ሳይሆን በታቦተ ሕጉ በጽላተ ኪዳኑ ላይ ሥዕል ኪሩብን እንዲስል ራሱ እግዚአብሔር ሙሴን አዝዞት ነበር ። 112. እነዚህ የኪሩቤል ሥዕሎች ከታቦቱ አይለዩም ። ምክንያቱም ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ ዙፋን ስለሆነ የመንበረ ፀባዖት አምሳል ነው ። ሥዕለ ኪሩ ቤልም የጸወርተ መንበር ኪሩቤል አምሳል ናቸውና የሚሳሉትም እንደሚናተፍ አውራ ዶሮ ሁነው ነው ። የንጉሥ አንጋች ንጉሡ በተቀመጠበት በዙፋኑ ፊት ነቃ ፥ ቆጣ ፥ ብሎ እንደሚቆም ።

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን የተጀመረበት ግን ከዚህ የተለየ ታሪ ካዊ ምክንያት አለው ። በጥንታውያን ክርስቲያኖች ዘንድ የሥዕል

112. ዘፀአ. ፳፭ ፥ ፲፱ ። ነገሥ. ቀዳ. ፮ ፥ ፳፫ ። ሕዝቅ. ፱ ፥ ፫ ። ፲ ፥ ፫ ። ፲ ፥ ፩ ፥ ፪ ። ሔኖ. ፲፭ ፥ ፲፩ ፥ ዘፀአ. ፳፭ ፥ ፭ ። ዘፍ. ፫ ፥ ፳፬ ።

www.ethiopianorthodox.org



ክብር እንዴት ተጀመረ ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ተገለ ጠው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፍርኩታ ውስጥ ነው ። ካታ ኮምብ (ገበበ ምድር) ይሉታል ፥ በዚህ ዋሻ ውስጥ የሰማዕታትን አፅም እየሰበሰቡ ጸሎት ይጸልዩ ትምህርት ያስተምሩ ነበር ። በዚሁ ውስጥ ብዙ አማኞች እየመጡ የማኅበራቸው አባል መሆን ጀመሩ በዚህ ጊዜ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍቶ ለመስጠት በ፤ መጻ ሕፍት አልነበሩም ። እንደልብ ወጥቶ ለመፈለግና ለማ ጋጀት ነፃነት ስላልነበራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌ ዎችን በሥዕል እያሠፈሩ ማስተማር ጀመሩ ። በዚህ ሁኔታ ሥዕል ማስተማሪያ ሁኖ ቆይቷል ። ሥዕሎችም የሚሳሉት በምሳሌነት «ሲምቦል» ሲሆን የሚሳሉትም በአመድና በከሰል በዋሻው ዙሪያ ነው ። በዋሻው ፊት ለፊት ላይ (በአፈ ጽዮን) የሚስሉት እረኛው በጉን እንደ ተሸከመ አድርገው ነው ። «ክርስቶስ ያመኑበትን ሁሉ በሱም አምነው የሞቱትን ሁሉ የሚያድናቸው ቸርና ታማኝ ጠባቂ መሆኑን ለማስረዳት» ሌላውን ሥዕላቸውን የሚጀምሩት በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነው ። ለምሳሌ የቀደሙ ሰዎች አዳምና ሔዋን እን ዴት እንደ ተሳሳቱና ያሳታቸውንም እባብ በመካከላቸው እንዳለ አድርገው ይስሏቸው ነበር ። 113. በምህላና በጸሎት ላይ ያለች የም ዕመንን ነፍስ በመርከብ ውስጥ ያለውን ኖኅን አስመስለው ይስ ሏት ነበር ። 114. የአቤልን መሥዋዕት የክርስቶስ መሥዋዕትነት ምሳሌ 115. በውሃ ተጠምቆ መዳንን ወይም መዳን በጥምቀት መሆ ኑን ሲገልጡ ሙሴ በበትሩ ደንጊያውን መትቶ ለተጠሙ እሥራ ኤል ውሃ ማፍለቁን 116. የሰማዕታትና የምዕመናን መከራና ትዕ ግሥት የኢዮብ መከራና ትዕግሥት ምሳሌ 117. «የምዕመናን በዚህ

113. ዘፍ. ፫ ፥ ፩—፯ ፤
114. ዘፍ. ፯ ፥ ፩—፳፬ ፤
115. ዘፍ. ፬ ፥ ፬ ፤
116. ዘፀአ. ፲፯ ፥ ፮ ፤
117. [illegible]

ዓለም መኖር የእሥራኤል ጉዞ በሐቅለ ሲና» «የሙሴ ደብረ ሲና መውጣት እምላኩንም ማየት ፤ የምዕመናን ክብርና ልዕልና ። «ሠለስቱ ደቂቅ በእሳት ውስጥ ከገብርኤል ጋር ምዕመናን በዚህ ዓለም በመከራ ቢሰቃዩም ታዳጊ መልአክ የማይለያቸው ለመሆና ቸው ምሳሌ » «ኤልያስ ሐሜለቱን ለኤልሳዕ ጥሎ ሲያርግ ክር ስቶስ በረከቱን ለምዕመናን ሰጥቶ ማረጉ ፤ ምዕመናን በሱ አምነው ገነት መንግሥተ ሰማያት መግባታቸው» «ዳንኤል በግበ አናብስት ሰማዕታት በዐላውያን ሸንጎ» ጦቢት ከዓሣው ጋር ምዕመኑ ከአዳኙ ከክርስቶስ ጋር «በጥንት ግሪኮች ዓሣ ሲሉ ፡— «ኢኽቲስ » ይላሉ ። የዚህ ፊደል እያንዳንዱ ምህጻረ ቃልነት አለው ። ኢ— ኢየሱስ ፤ ኽ—ኽርስቶስ ፤ ቴ—ቴው ኢዮስ ፤ (የእግዚአብሔር ልጅ) ስ—ሶቴር ፤ («መድኅን») አዳኝ ፤ በተገናኝ ፡— «ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መድኅን» ማለት ነው ። «ሶስና ከሁለት ዳኞች ጋር ፤ ሰማዕታት በዐላውያን ነገሥታት ፊት» «ዮናስ ወደ ባሕር ሲጣል ፤ አንበሪ ዮናስን በየብስ ሲተፋው የነበረባት ጐጆ በዱባ ቅጠል ተሸፍና ዮናስም በጣም ተደስቶ በኋላም በደረቀችበት ጊዜ በጣም አዝኖ ፡— ይህም ሁሉ አንድ ላይ ሁኖ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ፤ ከዚያም የሙታንን ትንሣኤ ያስረዳል ። »

የሐዲስ ኪዳንንም ታሪክ እንደዚሁ በግበበ ምድር ውስጥ ይስ ሉት ነበር ። «የገብርኤል ብሥራት የጌታ በቤተ ልሔም ዘይሁዳ መወለድ ፤ የሰብአ ሰገል ስግደትና አምኃ ሕፃኑን ለታቀፈችው ለድ ንግል ማርያም አምኃውን ሲያስረክቡ ፤ የምድረ ግብፅ ስደት ፤ ዮሴፍና ሰሎሜ ጓዛቸውን ተሸከመው አብረው ሲሰደዱ ፤ የጌታ ጥም ቀትና የሦስቱ ዓመት ትምህርት ከተአምራት ጋር ፤ የቃና ሠርግ ፤ የዕውሩ ዓይን ፤ የመጻጉዕ መዳን ፤ ልብሱን ስትዳስስ ደሟ የደረቀ ላት ሴት (እንተ ደም ይውኃዛ) የአምስቱ እንጀራና የሁለቱ ዓሣ ቡራኬ ፤ ለአምስት ሺ ሰው መመገብና አሥራ ሁለት ቅርጫት ማትረፍ ፤ ሳምራዊት ማድጋዋን ተሸክማ ወይም ውሃውን ከዐዘ ቅቱ በሸንከሎዋ ስትስብ ፤ ጌታ ሳምራዊትን ሲያነጋግር ፤ የሰነፎቹና የብልሆቹ ደናግል ሁኔታ ፤ የጴጥሮስ ክህደትና ጸጸት ፤ የይሁዳ



ክህደትና መምህሩን አሳልፎ መስጠት በመጨረሻም ሞቱና ትን ሣኤው ፤ ማርያም መግደላዊትና የተነሳው ክርስቶስ እመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ በግራዋ በኩል ኢሳይያስ ወደሷ እያመለከተ ፡— «ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ብዬ የተናገርሁላት ይቺ ናት እንደማለት ነው ።» ይህንና ይህን የመሳሰሉ ሌሎችም ሥዕ ሎች በጥንት የክርስቲያኖች መሸሸጊያ ዋሻዎች በከሰልና ባመድ ተስለው ተገኝተዋል ። ይህን ሁሉ ያደርጉ የነበር በፊት እንደ ተባ ለው የሃይማኖታቸውን ታሪክ ለማስተማር ነው ።

ከዚህ ሌላ የምዕመናንን ልቡና ለማጽናናት በሰማዕትነት የሞ ቱት ወንድሞቻቸው ዐፅም ባረፈበት አኳያ አሟሟታቸውንም በሥ ዕል ይገልጹት ነበር ። በዚህ አኳኋን የሥዕል ክብር በቤተ ክርስ ቲያን እንደ ተጠበቀ እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀ መሪያ ድረስ ከቆየ በኋላ ፤ በሥዕል ምክንያት በሮምና በቢዛንታ ይን ግዛት በሚኖሩ ምዕመናን ዘንድ አለመግባባት ተፈጠረ ። ለዚ ህም አለመግባባት ዋናው ምክንያት አንዳንድ ክርስቲያኖች ሥዕል ከመውደዳቸው የተነሳ ሥዕሎችን አማልክት ናቸው እስከማለት ደር ሰው ነበር ። (ኢኮኖላትሪያ)፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ሌላ ጐን በማጋ ደል ሥዕሎችን ጨርሰን ማጥፋት አለብን ብለው የከረረ የተቃ ውሞ በር ከፈቱ (ኢኮኖማኺያ) በመካከሉ ደግሞ እንደነዚያም ሳያ መልኩ ፤ እንደነዚህም በጥላቻ ሳይመነችኩ ፡— የጥንቱን ትምህ ርት ተከትለው ሥዕሎችን የሚወዱና የሚያከብሩ ምዕመናን ነበሩ ነገር ግን በዘመኑ የነበሩት ገዥዎች ሥዕል ማጥፋት አለብን የሚ ለውን ክፍል ስለ ደገፉ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመን ያቆየቻቸው ቅርሶቿ የቤተ ክርስቲያንን ጥንታዊ ኪነ ጥበብ የሚያሳዩ ሥዕ ሎች ሁሉ በእሳት ጋዩ ። ብዙ ምዕመናንም በዚሁ ምክንያት አለቁ። የሥዕሎቹ መጥፋት ጉዳይ በባለ ሥልጣኖች ቢደገፍም ሥዕሎቻችን አይቃጠሉብን የሚለው ክፍል እያየለ ድምጹም እየተሰማ ሄደ ፤ እንዲያውም ጠቡ እየተባባሰ ሄዶ የሮምንና የቢዛንታይንን መንግ ሥት የሚያናጋው ሆነ ።

ይህን በክርስቲያኖች መካከል የተነሣ ብጥብጥ በጉልበት ሳይ ሆን ሁለቱንም ክፍሎች በሚያግባባ የጋራ ሐሳብ ላይ ለመድረስ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ጠው በተነሳበት አካባቢ የነበሩ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በ፯፻፹፯ ዓ.ም. ጉባኤ አድርገው እንደ ሁለቱም ሳይሆን ማለት እንደ ሥዕል አምላኪዎችና እንደ ሥዕል አጥፊዎች ሳይሆን ስለ ሥዕል ክብርና ስግደት የሚገባውን ቀኖና ሁ፡ተዋል ። ከዚህም ጉባኤ በኋላ በማከታተል የተነሱ የሮማና የቢዛንታይን (መለካውያን ሊቃውንት) ስለ ሥዕል ክብርና የት መጣ አያሌ መጻሕፍትን ጽፈዋል ። ለምሳሌ በዚያው ዘመን በዚያው አካባቢ የነበረው ስመ ጥር ሊቅ ዮሐንስ ዘደማስቆ ፤ ስለ ሥዕል ብዙ ቀዋሚ ጠቃሚ የሆኑ መጻሕፍት ጽፏል ። ዮሐንስ ዘደማስቆ እንደሚለው ፦ ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት ጥቅም አለው ፤ ከነዚህም አንዱ በዋሻው እንደነበሩት ክርስቲያኖች ተአምራት ነክ የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪኮች ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሃይማኖቱን ሳይፈር ሳያፍር መስክሮ በሰማዕትነት የሞተ ወይም ስለ ዓለምና ስለ ራሱ በመጸለይ መላ ሕይወቱን ከፍትወታት ፤ ከእኩያት ፤ ከአጋንንት ጋር በመጋደል ያሳለፈውን ሰማዕት ወይም ጻድቅ በሥዕል ለማስታወስ በሥዕሉም አማካይነት እያንዳንዱ ምዕመን ለሥዕሉ ባለቤት ያለውን ክብርና ፍቅር ለመግለጥ ነው ።

በሥዕል ፊት ቁሞ መጸለይ ከባለ ሥዕሉ ረድኤት በረከት ምልጃ መለመን መማጠን ነው ። ለሥዕል መስገድ ሥዕልን መሳም ደግሞ በፊት የሥዕል ተዋጊዎች ወይም ፀረ ሥዕሎች (ኢኮኖ ማኺ) እንደሚሉት ዛሬም ብዙ ፀረ ማርያሞች እንደሚያጥላሉት ለጣኦት መስገድ ጣዖት መሳም አይደለም ። ከላይ እንደገለጥነው በሥዕሉ አማካይነት ለሥዕሉ ባለቤት ክብርንና ፍቅርን ለመግለጽ ነው ። ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ጥንታዊ ትውፊት (Tradition) ነው ። በእምነትና በፍቅር የሆነ ነገር ደግሞ ያንጻል እንጂ አይንድም ። የእግዚአብሔር መንግሥት የሚወረሰው በፍጹም እምነት ቅንነት በተሞላበት ፍቅርና ትሕትና እንጂ በተጥባበ ነገር (Rationalism) አይደለምና ።

በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት መሠረት ሥዕል የሚሳለው በቀለም ነው ። ላቲኖች ግን ቅርጽ ይቀርጻሉ ። ስለ ሥዕል ክብር በቤተ ክርስቲያን ስለተጀመረበትም ምክንያት በመጠኑ ገልጠናል ። አሁን ደግሞ ስለ ሥዕል ከተነሳ ዘንድ አከራካሪ ስለሆነው የጌታና የእመቤታችን ሥዕል የትመጣ እንደዚሁ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መሠረት በማድረግ በመጠኑ እንገልጣለን ።

www.ethiopianorthodox.org



ስለ ጌታ ስዕል ብዙ ታሪኮችና ትውፊታዊ ትምህርቶች ይነገራሉ ፤ በዚሁ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ሥዕል የሳለው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ይባላል ። ታሪኩም ከሞላ ጐደል እንደሚከተለው ነው ። ከ፲፬—፴፯ ዓ.ም. ሮምን ይገዛ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር ነው ። በሱ ዘመነ መንግሥት ነው ጌታ የተሰቀለው ፤ ይኸው ጢባርዮስ ቄሣር የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው ። እሱው ሞተበት ጢባርዮስ በልጁ መሞት በጣም አዝኖ ሬሳውን ሳያስቀብር ሰነበተ ከጥቂት ቀንም በኋላ ጌታ በኢየሩሳሌም ያደርገው የነበረውን ታምራት ያውቅ ስለነበር ፦«ከጢባርዮስ ቄሣር ምድራዊ ንጉሥ የተላከች ጦማር (መልእክት) ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ትድረስ» ብሎ ልጁን እንዲያስነሣለት የምልጃ የልመና ጽሑፍ ጽፎ ይህችን መልእክትና የልጁን ሬሣ ወስደው ጐልጐታ (የጌታ መቃብር) ላይ እንዲያኖሩለት ባለወጐቹን ላከ ። እነሱም ሔደው ደብዳቤዪቱንና ሬሣውን በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ሬሳው አፈፍ ብሎ ተነሥቷል ። ጢባርዮስም ከደስታው ብዛት የተነሣ የጌታን ውለታ ለመክፈል የዚህንስ ሰው እናቱን አምጡልኝ እኔ ቋሚ ለኀሚ ፣ ሚስቴ ገረድ ደንገጠር ሁነን እናገለግላታለን ብሎ እንደገና ሰው ቢልክ ፣ የድንግል ማርያም ክብር ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላልሆነ ተሰውራባቸው አላገኟትም ። ጢባርዮስ ግን ተስፋ እንዳይቆርጥ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ እንዳየው አድርጐ ከለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ስሎለታል ። ስለ ስዕሉ እውነተኛነትም ለማረጋገጥ ዮሐንስ የሳለው ይህ ስዕል «አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደ ሰቀሉኝ አንተ ደግሞ ሁለተኛ ሰቀልከኝ ? » የሚል ድምፅ አሰምቷል ። ስሎ ሲጨርስ ዮሐንስ -ቢስመው ከንፈሩ ከሥዕሉ ጋር ተጣብቆ ቆይቷል ። ይህ ሁሉ ከሥዕሉ የታየው ተአምራት ነው ። « አይሁድ የሰቀሉት ራቁቱን ነበር ከለሜዳ አስታጥቆ መሳል የተጀመረው ከዚያ ወዲህ ነው» እያሉ የሀገራችን ሊቃውንት ይተርካሉ ።

ስለ ጌታ ሥዕል ሁለተኛው ምንጭ (መነሻ) ጲላጦስ ለጢባርዮስ ቄሣር ስለ ጌታና ስለእናቱ እመቤታችን የላከው ሥዕላዊ መግለጫም አለ ።—ጲላጦስ በቅዱስ መጽሐፍ እንደሚታወቀው በፍልስጥኤም የሮማ መንግሥት እንደራሴ የነበረና በጌታም ሞት የፈረደ ነው ። ወደ ጢባርዮስ ቄሣር የላከው መልእክት እንደሚከተለው ነው ።—«ለጢባርዮስ ቄሣር ፤ ሰላም ላንተ ይሁን ፣ ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው ግርማዊነትህ ለማወቅ የጠየቀውን ለማሟላት ከዚህ የሚከተለውን እጽፍልሃለሁ ።—በዚህ እኔን እንደራሴህ አድርገህ በሾምኸኝ በፍልስጥኤም ምድር ፣ እጅግ በጣም የተለየ መልክና ሥልጣን ያለው አንድ ሰው ተነሥቷል ። ታላቅ መምህርና ነቢይም ነው ይሉታል ። ደቀ መዛሙርቱ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይላሉ። ስሙ ኢየሱስ ይባላል ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ቄሣር ሆይ ይህ ኢየሱስ የተባለ ክርስቶስ በየጊዜው ድንቅ ድንቅ ተአምራት ያደርጋል ሙታንን ያስነሣል ፣ ድውያንን ከማናቸውም ደዌና ሕመም ይፈውሳል ። ከዚህም ጋር ጥልቅና መንፈሳዊ በሆነ ትምህርቱ መላዋን ኢየሩሳሌምን አስደንቋታል ። አቋሙ አካሉ ግርማ ያለውና መልኩም አንጸባራቂ ጸጋ የተሞላበት በመሆኑ ማናቸውም የሚያየው ሁሉ ይወደዋል ፣ ይፈራዋልም ። አንዳንድ ጊዜ ቀላ ያለው መልኩና መሐል ለመሐል ተከፍሎ የሚታየው ጽሕሙ የሚሰጠው ውበት ፍጹም ግምት የሌለው ነው ። የፊቱ ቅርጽ መልአካውያን አይኖቹና የጥቁር ወርቃማ ጠጉሮቹም አወራረድ በሚሰጡት የተንጸባረቀ ውበት ማንም ሰው ቢሆን ለረጅም ጊዜ አተኩሮ ሊመለከተው አይችልም ። የሚመስለው እናቱን ነው ። እሷም ደግሞ በዚህ ክፍለ ሀገር በማንም ላይ ያልታየ ውበትና የትሕትና መልክ ያላት ናት ። ቆራጥ ከባድና የሚያከራክሩ ንግግሮቹም በውስጣቸው የሚገኘው ፍጹም የሆነ የመንፈስ ልዕልናና የዕውቀት መጠናቸው ከታላላቅ አዋቂዎች ተብለው ከሚገመቱት ሰዎች እጅግ አድርጎ የራቀ የጠለቀ ምሥጢር አላቸው ። በተግሣጽና በእዝናት ጊዜም በጣም ኃይለኛ ነው ። በማስተማርና በማበረታታት ጊዜ ደግሞ ትሑት ተወዳጅና ልብ የሚመስጥ ነው ። ራሱን ሳይከናንብና መጫሚያ ሳይጫማ በእግሩ ይሔዳል ። በሩቅ የሚያዩት አንዳንዶች ይስቁበታል ፤ ነገር ግን ወደፊቱ ሲቆሙና ሲቀርቡ በመንቀጥቀጥ ያደንቁታል ። ማንም ቢሆን ሲስቅ አየሁት የሚል የለም። ነገር ግን ብዙዎች ሲያለቅስ አይተውታል ። የቀረቡት ሁሉ ብዙ ሥራና ፈውስ ማግኘታቸውን ይናገራሉ ። ነገር ግን ገዥና ተገዥ ሁሉም (ባባቴ ፊት) በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው ። ምንም ልዩነት የላቸውም ብሎ ስለሚያስተምር የግርማዊነትህ አጥፊ ሳይሆን አይቀርም በማለት ብዙ ሰዎች እየመጡ ይነግሩኛል ። ስለዚህ ጉዳይ ብታዝዘኝ ወዲያውኑ ትእዛዝህ የሚፈጸም ይሆናል ። ጤና ሁን ፣ ፒ ሌንቱሌ »



በቤተ ክርስቲያን አባቶች የታሪክ መዝገብ ደግሞ ስለ ጌታ ስዕል በተአምራታዊ አገላለጥ የተጻፉ ብዙ አስተያየቶች አሉ ። ከነዚህም ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ እንደጻፈው 118. አብጋር የተባለው የዑር ንጉሥ ከደዌው የተፈወሰው የጌታን ስዕል ባየ ጊዜ ነው ይላል ። ሙሉው ታሪክ እንደሚከተለው ነው ። «አብጋር» ስመ መንግሥት ነው ። ዓፄ ጃንሆይ እንደ ማለት «አባጋር» እንዲሉ ዛር አንጋሹን ። ዑር በእመስጰጦምያ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ናት ። ጽርዓውያን «ኤዴሣ» ይሏታል ። በኛም «ሮሐ» ትባላለች ። አብጋሮች በዑር መንገሥ የጀመሩት ከጌታ ልደት በፊት ከ፩፻፴፪—፪፻፲፯ ከጌታ ልደት በኋላ ነው ። በጌታ ጊዜ የነበረው አብጋር ዮካማ (ዑካማ) ይባል ነበር ። አምስተኛው ወይም ሰባተኛው አብጋር ነው ። ይህ አብጋር ዮካማ ከጌታ ጋር ይጻጻፍ እንደ ነበር አውሳብዮስ ይተርካል ። አውሳብዮስ ታሪኩን ሰፋ በማድረግ ሲያብራራ እንዲህ ይላል።—በማይድን በሽታ ተይዞ የሚሠቃይ በኤፍራጥስ ወንዝ በላይ የነገሠ አብጋር ንጉሥ ነበር ። በዘመኑ ለነበረው ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት (ጦማር) ጽፎ የግል ታማኙ ለነበረው ለግምጃ ቤቱ ሹም ሰጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው ። ይህ ሰው በአብጋር ቤተ መንግሥት ስዕል በመሳል የታወቀ ነበር ። ደብዳቤው እንዲህ የሚል ነው ።—

118. አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን I, xiii, P.G. xx ፩፻፷ ታሪክ
(The doctrine o fAddai the apostle — Thadaios London 1876)

www.ethiopianorthodox.org

«ስለ አንተና ስለምታደርገውም ተአምራት እሰማለሁ ፤ ያንተ
ማዳን እንደሌሎቹ ዐቀበተ ሥራይ ስር ምስህ ፤ ቅጠል በጥሰህ አይ
ደለም ። አንተ ያዳንኸው ተረፈ ደዌ የለበትም ። እንደሰማሁት
ዕውራን እንዲያዩ ታደርጋለህ ፤ መጻጉዓን ጉልበታቸው ቀንቶላ
ቸው እንዲራመዱ ታደርጋለህ ፤ ልሙጻንን ታነጻለህ ፤ ርኩሳን መና
ፍስትን ታሳድዳለህ ፤ በማይድን በሽታ የተያዙትንም በምሕረትህ
ትፈውሳቸዋለህ ፤ ሙታንን ታነሣለህ ። ስለዚህ ወደኔ እንድትመ
ጣና ከዚህ ከሚያሰቃየኝ ደዌዬ እንድትገላግለኝ ፤ ለእኔም ምህረት
እንዲደርሰኝ ይህችን የልመና ደብዳቤ ጻፍሁልህ ። አይሁድ ባንተ
ላይ ክፉ ነገር እንዳሰቡና ክፉ ሊያደርጉብህም እንደከጀሉ እሰማ
ለሁ ። ከተማዬ በጣም ትንሽ ናት ፤ ትነስ እንጂ በጣም ውብ ናት
ለሁለታችን ትበቃናለች ፤ እባክህ ና ።» የሚል ደብዳቤ ጽፎ ለጌታ
ላከለት ። ጌታም የሚከተለውን መለሰለት ።—«አብጋር ሆይ ፤ ሳታ
የኝ ስላመንህብኝ ብፁዕ ክቡር ነህ ፤ ስለእኔ ተጽፎልና የሚያዩኝ
እንዲንቁኝ ፤ የማያዩኝ ግን እንዲያምኑብኝ ። በኔ ያመኑ ሕያዋን
ሁነው ይኖራሉ ። እኔም አስቀድሜ የመጣሁበትን ሥራ መፈጸም
አለብኝ ፤ ከፈጸምሁም በኋላ ወደላከኝ እሔዳለሁ ። ከሔድሁ በኋላ
ከደዌህ እንዲፈውስህና ላንተና ለቤተ ሰዎችህም የሕይወትን ቃል
እንዲያስተምራችሁ ከደቀ መዛሙርቴ አንዱን እልክልሃለሁ ። ከተ
ማህም የተባረከች ትሆናለች ፤ ጠላቶች አይገዟትም ። » ብሎ
መልስ ላከለት ። ጌታ ካረገ በኋላ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ
ቶማስ (ዕፃው በእስያ ስለነበር) ከሰብአ አርድእት አንዱን ታዴዎ
ስን ወደ ዑር ላከው ፤ ታዴዎስም እዚያ እንደ ደረሰ ለጊዜው ያረ
ፈው ጦንት በፍልስጥኤም በሚያውቀው በአንድ አይሁዳዊ ቤት
ነበር ። ከዚያ ሁና በማስተማርና ተአምራት በማድረግ ጥቂት እን
ደቆየ በቤተ መንግሥትም ዜናው ተሰማ ። ወዲያውም ተጠርቶ
ወደ ቤተ ምንግሥት ሔደ ። ታዴዎስ ገና ሲገባ ንጉሡ አብጋር
አስደናቂ ግርማ በታዴዎስ ገጽ ላይ አየ ። በቤተ መንግሥቱ የነ
በሩት ባለሟሎቹና የወንድ መኳንንት የቤት ወይዛዝርት ግን ምንም
እንኳ ለአብጋር የተገለጸው ባይገለጽላቸው ፤ ታዴዎስ እዚያ በመ



ገኘቱ አንክሮና ተመስጦ ሳያድርባቸው አልቀረም ። ንጉሡና ታዴ
ዎስ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ታዴዎስ፡— በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም እጄን እጭንብሃለሁ ብሎ እጁን ጫነበት ፤ በዚህ
ጊዜ አብጋር ከነበረበት ሁሉ ደዌ ተፈወሰ ። ታዴዎስም የሕይወ
ትን ቃል እያስተማረ በዚያች ቦታ ብዙ ቆየ ። የከተማዪቱም ነዋሪ
ዎች ክርስቲያኖች ሆኑ ፤ አውሳብዮስ ታሪኩን እዚሁ ላይ ያበቃል ።

ሌሎች የኋላ አባቶች ግን ይህን ታሪክ ሳይለውጡ ፤ አብጋር
ወደ ጌታ የላከው ሰው ሠዓሊ ስለነበር ፤ ወዲያው ጌታን ሲያይ ልቡ
ስለተመሰጠ ሥዕሉን በንድፍ ለማስቀረት ፈለገ ። ጌታን በሚያነጋግ
ርበት ጊዜ ዓይኑን ጣል እያደረገ የጌታን ገጽ በወረቀት ነድፎት
ነበር ። ወደ ሀገሩ ሲመለስ ያንን ለአብጋር አሳየው ፤ እሱም ባየው
ጊዜ በፍጹም እምነት ከመሬት ወድቆ ሰገደ ያን ጊዜም ከደዌው
ተፈወሰ ይላሉ ። ከዚህ በማያያዝ ይህ ስዕል ግባሬ ተአምር ስለሆነ
ሁሉ ሊሰግድለት ይገባል ብሎ በሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ ከፍ
ያለ ቦታ አበጅቶ እዚያ ላይ እንዲሰቀል አዘዘ ። «በአብጋርና በልጁ
ዘመነ መንግሥት ሁሉም እየመጣ ለዚህ ስዕል ሲሰግድ ኑሯል ። »

አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ስለጌታ ሥስዕል ሌላ ምንጭ ያመለክተ
ናል ፤ እሱ እንደሚለው ፤ «በወንጌል የታወቀችው እንተ ደም ይው
ኅዛ ውለታ ለመክፈል ስትል የቅርጽ ሐውልት አሠርታለት ነበር»
ይላል ። የቤሮኒኪም ታሪክ ለጌታ ስዕል ጥሩ መነሻ ነው ። ጌታ
በዕለተ ዐርብ ደሙን እያንጠፈጠፈ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጐል
ጐታ በሚወጣበት ጊዜ መስቀሉ ከብዶት ደሙ ዓይኑን ጋርዶት
አይታ ልቧ በሐዘን ስለተነካ ከተከተሉት አንዷ ቤሮኒኪ ሻሿን አው
ልቃ ፊቱን እንዲያድፍበት ወረወረችለት ፤ አድሮ ሲመልስላት ገጹ
ከሻሿ ላይ ታትሞበት ቀረ ይባላል ። ስለ ጌታ ስዕል መነሻ ታሪካ
ዊና ተአምራታዊ ምንጮች ብዙ አሉ ።

ዮሐንስ ወንጌላዊና ጴጥሮስ በባዶው መቃብር ውስጥ ገብተው
ያዩት ጌታ ተገንዝቦት የነበረው ከፈንና (ሰበን) መጠምጠሚያ ላይ
የጌታ አካል ታትሞበት ነበር ። የሚል የቤተ ክርስቲያን ትውፊት
አለ ። ስለ ጌታ ስዕል የት መጣ ከሚሉ በከፊሉ ይህ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለ እመቤታችን ሥዕል ደግሞ መጀመሪያ የሣላት ሉቃስ ነው ይባላል ። 119። በኛም በቤተ ክርስቲያን ያሉት የመዝሙርና የጸሎት መጻሕፍት የእመቤታችንን ሥዕል ሉቃስ መሳሉን ይናገራሉ ።
«ሰላም ለስዕልኪ እንተ ሰዐላ በእዴሁ ፤
ሉቃስ ጠቢብ እምወንጌላውያን አሐዱ 120።

ሐ መስቀል ፡—ሥዕል ብቻ ሳይሆን መስቀልም በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ክብር አለው ። ከጌታ በፊት መስቀል የመቅጫ መሣሪያ ነበር ። ሰውን በመስቀል መስቀል የተጀመረው በፋርስ ነው ። በፋርስ ሰዎች አምልኮት የመሬት አምላክ (Ormuzd) ይባላል ። ወንጀለኛ በሀገራቸው ሲገኝ ቅጣቱን በመሬት የተቀበለ እንደሆነ አምላካቸው እንዳይረክስ ወንጀለኛውን ሁሉ በመስቀል ይሰቅሉት ነበር ። ይህ አድራጐት እንደ ልማድ ሆኖ በሮማ ግዛት ሁሉ የተለመደ ሕግ ሆነ ። 121። በአሪትም ሥርዓት በመስቀል ፤ በስቅላት የሚቀጡ ሁሉ ርጉማን ውጉዛን ነበሩ ። ከጌታ በኋላ ግን የነፃነታችን ዓዋጅ የተነገረበት ሰላማዊ ዙፋን ስለ ሆነ ለክርስቲያኖች ሁሉ የነፃነት ፤ የድል ምልክት ነው ። «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» ክርስቶስ ሰላምን ፤ እኩልነትን በመስቀሉ አድርጓልና ። እነ ቆስጠንጢኖስ በብርሃን ቅርጽ ያዩት ይሀ መስቀል የድል ምልክት ሁኖ ይኖራል ። ይሀ የመስቀል አማናዊና ምሥጢራዊ ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ላመኑ ነው እንጂ ላላመኑ አልደረሳቸውም ። እንዲያውም መስቀልን ኃይለ እግዚአብሔር ነው። ማለቱ ዋዛ ይመስላቸዋል ። መስቀልን በመቅጫነቱ የሚመለከቱት ብዙ ናቸው ። እርግጥ መስቀል ለሞት ፤ ለአጋንንት መቅጫ ሆኗል ።

መስቀል በብሉይ ኪዳን ብዙ ምሳሌ አለው ፤ የኖኅ መርከብ የተሠራችበት እንጨት ፤ ሙሴ የፈርኦንን መሰግላን ድል ያደረገበት በትር የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው ። ምዕመናን በክርስቶስ አምነው በመስቀል አማትበው ከማየ ሥራዌ ከማየ ድምሳሴ ከኃጢአት ከአምልኮ ጣኦት ድነዋል ። በመስቀል አጋንንትን ፤ መናፍ

119. የያዕቆብ ወንጌል ተመልከት ፤
120. መልክአ ሥዕል ፤
121. (ORTHODOXY = A Creed for today, "Plain talks on the orthodox faith based on the Nicene Creed," ANTHONY M. CONIARIS) 1972, p. 128



ቃንን ፍትወታት እኩያትን ድል ሲያደርጉ ይኖራሉና ። ከዚህ የተነሣ የክርስቲያኖች ኪነ ጥበብ ሁሉ ምልክቱ መስቀል ሆነ ፤ በልብሳቸው ፤ በመጽሐፋቸው ፤ በቤት ዕቃቸው ሁሉ የመስቀል ምልክት አለበት ። በብዙ አገሮች ይልቁንም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ክርስቲያን መሆናቸው የሚታወቀው በክንዳቸው ፤ በመዳፋቸው በሚጠቀሩት የመስቀል ቅርጽ ነው ። ባልታወቀ ቦታ ሔደው ክርስቲያን ነን ለማለት ሲፈልጉ ያንን ብቅ አድርገው ያሳያሉ ።

በሀገራችንም ጥልፉ ዝምዝሙ ፤ ጌጣ ጌጡ ሌላው ቀርቶ ሴቶቹ በግንባራቸውና በሌላውም አካላቸው በመስቀል ቅርጽ ይጠቆራሉ። በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ መስቀል ከምእመናን አይለይም ። አጽማቸው በሚያርፍበት በመቃብራቸው ላይ ሁሉ የመስቀል ቅርጽ ከዕፅ ወይም ከደንጊያ ይሠራል ። በመቃብራቸው ላይ መደረጉ ፤ መስቀል የሞትና የመከራ ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ የትንሣኤና የሕይወት ምልክት (ሲምቦል) መሆኑን ለመግለጥ ነው ።

ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ፡—ታቦት ፤ ሥዕልና መስቀል በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ክብር ስላላቸው ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በራሷ ኪነ ጥበብ በራሷ ሊቃውንት የተዘጋጁትን ታቦት ፤ ሥዕልና መስቀል በቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ስታገለግልባቸው ትኖራለች ።

በሥዕል በኩል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። በራሳችን ሠዓሊዎች የተሣሉና የራሳችንን ኪነ ጥበብ የሚመሰክሩ ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን በብዛት አይታዩም ፤ በተለይ በከተማ ሕዝቡ እየገዛ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውና በግሉም በቤቱ የሚይዘው የላቲንንና የግሪክን ኪነ ጥበብ የሚያሳዩ የሚመሰክሩ ሥዕሎችን ነው ፡ ይህ በኢትዮጵያ ትውፊታዊ ኪነ ጥበብ እንዲለወጥ ካህናት ለራሳቸው ተረድተው ምዕመናንንም ማስረዳት አለባቸው ። ሥዕሎችም በተቻለ መጠን ደበስ ባለ ቀለም መሳል አለባቸው ። ጥቁርን በክፉ ፤ ነጭን በደጎና ነገር መስሎ ማቅረብ ከነጮች የተወረሰ ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፯

# የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖና

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አወዛጋቢና አከራካሪ የሆነው በቤተ ክርስቲያንም በኩል ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት አስቸጋሪ መስሎ የሚታየው የበዓላትና የአጽዋማት ጉዳይ ነው ። ስለዚህ ስለ በዓላትና አጽዋማት ባጭሩ እንገልጣለን ።

ሀ. በዓላት ፡— በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይም ቁጭ ብሎ መዋልን የለመደ የወደደ ሰነፍ የፈጠራቸው አይደሉም ፤ ምንጫቸው ወይም የት መጣቸው ሃይማኖት ነው ። በብሉይ ኪዳን በዙ በዓላት ነበሩ ፤ ከእነዚህም ቀዳሚዪቱ «ቀዳም ሰንበት» ናት ። የዚች ዕለት ክብር ከአሠርቱ ቃላት አራት በአንዱ ታዟል ። —«የእግዚአብሔር አምላክህን ሰንበት አክብር» ተብሎ አይሁድ ዕለተ ሰንበትን እንዲያከብሩ የታዘዙት ፤ እግዚአብሔር ከእሑድ እስከ ዓርብ ሲፈጥር ሰንብቶ በዚህች ዕለት ስላረፈ (ሥራ) ስላልሠራባት ነው ። ስለ ቀዳም ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ ዓይነት አተረጓጐም ነበራቸው ። «አክብር» የሚለውንም ቃል ለእግዚአብሔር እንደሚስማማ አድርገው ለመተርጐም ያላዩት መዝገበ ቃላት የለም ። ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ በዚህች በዕለተ ሰንበት ሥር መማስ ፤ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘረጉትንም አያጥፉም ፤ ያጠፉትንም አይዘረጉም ፤ የዘጉትን አይከፍቱም ፤ የከፈቱትን አይዘጉም ነበር ። ዜና አይሁድን የጻፈው ራሱም አይሁዳዊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ፡— «አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳ አይሔዱም ነበር» ይላል ። ከዚህም ጋር ቤት ቢቃጠል ፤ ሰው ቢሞት ፤ ጦር ቢመጣ ፤ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው ። ለምሳሌ በመቃብያን ታሪክ እንደሚታወቀው ፩፻ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት በዚህች በዕለተ ሰንበት ነበር ። ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. (በፈረንጆች በ፲፱፻፸፫) የም ኪፑር)



የዳስ በዓል ማለት ነው) ግብፃውያን ያጠቁቸው በበዓሉ ምክንያት ተዘልለው ሳሉ ነው ። አይሁድ ብዙ በዓላት አሏቸው ። የበዓላቸውም ሕግ ማንኛውንም ሥራ ከመሥራት መወገድ ነው ። በሌላው ዓለም ያሉ አረማውያን ደግሞ የራሳቸው በዓላትና የአከባበር ሥርዓቶች አሏቸው ። አማልክቶቻቸው ብዙ እንደመሆናቸው መጠን ብዙ በዓላትና የተለያዩ የአከባበር ሥርዓቶች አሏቸው ። ለምሳሌ፦ ፲፪ አማልክት የነበሯቸው ፅርዓውያን በነዚያው ልክ በዓላት ነበሯቸው ። አከባበራቸውም እንደ አምልኮታቸው ከፍርሃት የመነጨ እንጂ መጽሐፋዊ ወይም ምሥጢራዊ ስላልሆነ ስለ ሥርዓቱ ብዙ አያስቡበትም ። በሚኖሩበት አካባቢ አንድ ለውጥ ሲያዩ ብቻ ቶሎ ብሎ መስዋዕት ያቀርቡ ነበር ። «ነፋስ ሲነፍስ ፤ የነፋስ አምላክ (ኤዎሉስ) ተቆጥቶ ነው ። የፀሐይ ሙቀት ሲያይል የፀሐይ አምላክ (አጵሎስ) ተቆጥቶ ነው ። ባሕር ስትታወክ የባሕር አምላክ ፓሲደን ተቆጥቶ ነው በማለት ካህናተ ጣዖቱ በዓል ያዘጋጁ መስዋዕት ይሰዉ ነበር ። የበዓል አከባበራቸው ሥራ የማይከለክል ነበር የቆመውን ቢቆርጡ የተጋደመውን ቢፈልጡ በዓል እንደሻሩ አይቆጥሩትም ነበር ። እነዚህ ፡—ማለት አይሁድና አረማውያን ወደ ክርስትና በገቡ ጊዜ የቆየውን ልማዳቸውን ለመተው አስቸጋሪ ነገር ገጥሟቸው ነበር ።

የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያት ይህ ልማድ መሰናክል እንዳይሆን ሁሉንም እንዳመሉ ተቀበሏቸው ። ከአይሁድ ወደ ክርስትና የተመለሱት የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ በባህላቸው ያደርጉት የነበረውን ከማድረግ አልተከለከሉም ። ለምሳሌ ፡—በአይሁድነት ሳሉ ቅዳሜን ብቻ ያከብሩ ነበር ፤ ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ግን ቅዳሜንም ፤ እሑድንም ያከብራሉ ። ግዝረትና የመሳሰለውም የብሉይ ኪዳን ትውፊት ከቤተ አይሁድ በተመለሱት ክርስቲያኖች ዘንድ እስከ አሁን ይሠራበታል ። ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ እንደዚሁ የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ልማደ አረማውያንን አልተውም ። የቅዳሜን በዓልነት አያውቁም ፤ ግዝ

ሊቃውንቱና መምህራኑ የሕዝቡን የረጅም ዘመን ፍቅረ ጣዖት ለማስተው ስላቃታቸው በጣዖታቱ ተሰይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳን ስም እየለወጡ ያከብሩታል ። ለምሳሌ ፦— በጣኦታዊት በነበሩበት ጊዜ « ፖሲዶን » የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነበር ፤ በክርስትና ዘመናቸው ግን ሊቃውንቱ «ኒኮላዎስ» የሚባለውን ቅዱስ የባሕር ጠባቂ ብለው በያመቱ ያከብሩታል ። የመርከበኞች በዓል ነው ። «አሬስ» ወይም «ማርስ» የጦር አምላክ ተብሎ ሲመለክ የኖረ ጣኦት ነው ። በሱ ምትክ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በያመቱ ያከብራሉ ።

በጠቅላላው አረማውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት (ፍጥረት) አምላክ መድበውለት ስለነበር ፤ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሰይመዋል ። በአረማውያን የበዓል አከባበር « ኢታንሥእ እደዊከ ወእገሪከ » የሚል ትእዛዝ ስላልነበረ አሁንም ከአረማዊነት የተመለሱት ክርስቲያኖች በዓል የሚያከብሩት ሥራ ፈትቶ ተቀምጦ በመዋል አይደለም ። ለምሳሌ ፦—በዓሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ እንደሆነ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቅዳሴ ይቀደሳል ፤ የሰበካው ሕዝብ ይልቁንም በስሙ የተሰየሙት ምዕመናን ያስቀድሳሉ ፤ ቅዱስ ቁርባንም ይቀበላሉ ፤ ከጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ በጊዮርጊስ ስም የተሰየሙ ሁሉ ከቤታቸው ተቀምጠው ወዳጅ ዘመድ የሆነ ሁሉ «የከርሞ ሰው» ይበልህ እያለ የሚያመጣላቸውን ስጦታ በያይነቱ ሲቀበሉ ይውላሉ ።

የመንግሥት በዓላት «ብሔራዊና ሃይማኖታዊ» በዓላት ፤ እንደ ልደት ፤ ጥምቀት ፤ ትንሣኤና ፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት በሚከበሩበት ጊዜ ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመዘጋታቸው በቀር እያንዳንዱ ግለሰብ በየቤቱ የግል ሥራውን ቢሠራ ለራሱ ካልደከመው በቀር ከጐረቤትም ሐሜት አያስከትልበትም ። እሱም ለራሱ በዓል እንደሻረ አድርጐ አይቆጥረውም ። እንደ አርእስት ስለ በዓላት አጀማመርና የተለያዩ ሥርዓቶች አንሥተናል ። የሀገራችንስ የበዓል አከባበር እንዴት ነው ?



በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና የራሱ የሆነ መልክ አለው ። ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜንና እሑድን እንደ አንድ ቀን አድርጋ ( አስተካክላ ) ታከብራለች ። የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን ፤ እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣባት «የጌታ ቀን» ተብላ በሐዲስ ኪዳን የከበረችናትና (ራእ. ፩፤ ቁጥር ፲ ።)

በእነዚህ በሁለት ቀኖች ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያናችን የክርስቲያኖች አከባበር እንደ አይሁድ በውን የሚጫን እንዳይሆን ብታስተምርም « ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያፅርኡ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ ፤ አላ ይትገበሩ ከመ ክርስቲያን ፤ ወኢትትአቀቡ ሰንበተ ከመአይሁድ » (ፍ. ነ. ፲፱) «ወዕረፍትሰ አኮ በሰኪብ ከመ ዘሐመ በደዌ ፤ አላ በትጋሀ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ንኩን ፍቁራኒሃ ለዛቲ ዕለት» (ቅዳ. አትና.) ሕዝቡ ከብሉይ ኪዳን በወረሰው ትውፊት መሠረት በዕለተ ሰንበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት ማናቸውንም ሥራ ቢሆን አይሠራም ። ሌላው ቀርቶ ቅዳሜና እሑድ የተቀዳ ውሀ ፤ የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ ፤ ወንዝ የማይሻገሩ ክርስቲያኖች አሉ ። በሌሎቹም በዓላት እንደ ሰንበት አይጸናም እንጂ ፤ ሥር መማስ ፤ ቅጠል መበጠስ ፤ መጽሐፍ መጻፍ ፤ መደጐስ ፤ ልብስ ማጠብ ሁሉ በዓል እንደመሻር ይቆጠራል ። ይህ ሁሉ ከሕዝቡ ልማድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተደነገገ አይደለም ፤ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጌታ በዓላት ዘጠኝ ናቸው ። እነዚህም «ዓበይት በዓላት» (ታላቅ በዓላት) ይባላሉ ።

__፩ኛ. ብሥራት__ ፦—መጋቢት ፳፱ ቀን ነው ፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም የአምላክን ከርሷ መወለድ ያበሠረበት ቀን ነው ። በመንጸፈ ደይን ወድቆ ለነበረው የሰው ዘር ታላቅ የምሥራች ነውና የምሥራች ቀን (ብሥራት) ተብሏል ።

__፪ኛ. ልደት__ ፦—በትንቢተ ነቢያት የተነገረለት የሰወን ልጆች ( የንተ ተፈጥሮ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ አሁን ደግሞ በሐዳ ፤ ተፈጥሮ ለመፍጠር ማለት ፦—ዕውን ለማዳን ሰው ሆኖ የተወ

www.ethiopianorthodox.org

ለደበት ዕለት ነው ። ልደት በየዓመቱ የሚከበረው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው ። በዘመነ ዮሐንስ ግን (የሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ስለሆነች) ልደት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይሆናል ። ይህም የተጀመረው በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል ። 122* የልደት በዓል ከጾም ጋር የተያያዘ ስለሆነ ገሃድ የለውም ፤ የማይጾሙ ሰዎች ግን ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ብለው ይጾሙታል ። በዘመነ ዮሐንስ ልደት ሐሙስ በ፳፰ ቀን ቢውል ፳፱ ዓርብ ይጾማል ። ልደት በ፳፰ ማክሰኞ ቢውል ፳፱ ረቡዕ ይጾማል ። ሁለቱንም ቀን ልደት ማለት ግን ጥሩ አይደለም ። ከዚያስ ያንኑ ፳፱ኙን መያዙ ይሻላል ። በዚህ የቀን ስሌት ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሲጣሉ በት ኑረዋል ። ለወደፊቱም ይህን ለማስተካከል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሙሉ መብት አለው ።

፫ኛ/ ጥምቀት፡—ክርስቶስ በተወለደ በ፴ አመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሯል ። ጌታ የተጠመቀው በፈለገ ዮርዳኖስ ነው ፤ ያጠመቀውም ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ነው ። በተጠመቀም ጊዜ አብ በደመና ሁኖ የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮለታል ፤ መንፈስ ቅዱስም በፀዓዳ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል ። ይህ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዋዜማው ታቦታቱ በየቤተ ክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር (በሰው ሠራሽ የውሀ ግድብም ቢሆን) በዳስ ፥ በድንኳን ያድራሉ ። ሌሊት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ አድሮ ሥርዓተ ቅዳሴውም ይፈጸማል ። ሲነጋ በወንዙ ዳር (በግድቡ) ጸሎተ አኰቴት ተደርሶ አራቱም ወንጌላት ከተነበቡ በኋላ ውሀው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል ። የጠበሉን መረጨት አይተው በቀድሞ ዘመን ወደ ሀገራችን መጥተው የነበሩ ኢየሱሳውያን ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ታጠምቃለች ብለው አጥላልተው ጽፈዋል ።» ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን ለኛ ብሎ ያሳየውን ትሕትና ለመመስከር ፥ ለምዕመናን የጌታን በረከት ጥምቀት ለማሳተፍ እንጅ የተጠመቁትን ምዕመናን

122. ፩ሺህ፱፻፺፰ ዓ. ም.



እየመላለሰች በያመቱ አታጠምቅም ። ጥምቀት አሐቲ መሆኗን ታውቃለችና ። እርግጥ ያልተጠመቁ አረማውያንና ሌሎችም የጥምቀት በዐል በሚከበርበት ጊዜ እየመጡ በክርስቶስ አምነው ይጠመቃሉ ። ጥምቀት የሚከበረው በያመቱ ጥር ፲፩ ቀን ነው ። ጥምቀት ረቡዕ ቢውል ገሀዱ ማክሰኞ ፥ ዓርብ ቢውል ገሃዱ ሐሙስ ለውጥ ሁኖ ይጦማል ። ጥምቀት የሚውልባቸው ዐርብና ረቡዕ አይጦሙምና ። በበዓለ ጥምቀት የታቦታቱ ወደ ወንዝ መውረድ ጌታ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሔዱ ምሳሌ ነው ።

፬ኛ/ ደብረ ታቦር፡—ጌታ በማስተማር በነበረበት ጊዜ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን ክብረ መንግሥቱን የገለጠበት ዕለት ነው ። 123* ይህ በዐል በያመቱ ነሐሴ ፲፫ ቀን ይከበራል ። ይህ በዐል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በምዕመናን ዘንድ የተለየ ስም አለው ፤ በምዕመናኑ ዘንድ፡—ቡሄ ይባላል ። ቡሄ ማለት (መላጣ ገላጣ) ማለት ነው ። በሀገራችን ክረምቱ አፈናው ተዋግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታየው በዚሁ በዐል አካባቢ ስለሆነ «ቡሄ» ያሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ። «ድርጊቱ በተፈጸመበት በፍልስጥኤም ግን የደመና መልክ የማይታይበት ፍጹም የበጋ ወራት ነው ።» በሀገራችን ሕፃናቱ ይህ በዐል ከመድረሱ በፊት ቀደም አድርገው ጅራፍ ሲገምዱና ሲያጮሁ (ሲያኖጉ) ይሰነብታሉ ፤ እናቶችም ለዚህ በዐል የሚሆን ዳቦ ለመጋገር (የሚከበረው በዳቦ ነውና) ስንዴያቸውን ሲያጥቡ ሲፈትጉ ይሰነብታሉ ። በዐሉ እንደ ነገ ሊሆን እንደ ዛሬ በዋዜማው (ነሐሴ ፲፪) የሰፈር ሕፃናት በየቤቱ እየዞሩ ቡሄ ቡሄ እያሉ ይጨፍራሉ ፤ የሚገጥሙትም ግጥም አላቸው ።— «ቡሄ ና ፥ ቡሄ በሉ ፤ ቡሄ መጣ ፥ ያ መላጣ ፥ ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ ።» እዚህ ላይ ቡሄ ያሉት ዳቦውን ነው ። በዚህ ጊዜ እናቶች ካዘጋጁት ዳቦ እያነሱ ይሰጧቸዋል ። ሔደው ዳቧቸውን እየገመጡ ሲጋረፉ ይውላሉ ። ለግርፊያው ተምሳሌት ባይገኝለትም ፥ የጅራፉ መጮህ የድምፀ መለኮት ፥ ጅራፉ ሲጮህ ማስ

12,. ማቴ. ፲፯ ፥ ፩—፱

www.ethiopianorthodox.org

ደንገጡ የሐዋርያትን (የጴጥሮስን ፥ የያዕቆብንና የዮሐንስን) በድምጸ መለኮት መደንገጣቸውንና መውደቃቸውን ያስታውሳል ። ባንዳንድ ቀበሌዎች የቡሄ ዕለት ማታ ችቦ ያበራሉ ። በደብረ ታቦር ለታየው ብርሃን መለኮት ምሳሌ ነው ። በዚያውም ላይ በኢትዮጵያችን የፀዓተ ክረምት ዋዜማ ስለሆነ ፥ ቡሄን ብርሃን ቢሉት ይስማማዋል ። «ቡሄ ከዋለ የለ ክረምት ፥ ዶሮ ከጮኸ የለ ሌሊት » እንዲሉ ። የቡሄ ዕለት ለዘመድ ላዝማድ ለእያንዳንዱ ቤት ሰብ በልጆቹ ልክ ዳቦ ይሰጣል ። በተጨማሪም ለክርስትና ልጅ ፥ ለጡት ልጅ ፥ ለአማች ፥ ለምራት ፤ የቅርብ ዕውቂያ ላለውም ሁሉ የቡሄ ዳቦ ይሰጣል ። በተማሪ ቤት ደግሞ ደብረ ታቦር የተማሪዎች በዓል ነው ። ተማሪዎች ቀድም አድርገው (ስለ ደብረ ታቦር) እያሉ እህሉን ጌሾውን ብቅሉን ይለምናሉ ፤ ሕዝቡም ባህሉን ስለሚያውቅ በገፍ ይሰጣቸዋል ። የደብረ ታቦር ዕለት ጠላውን ጠምቀው ቆሎውን ቆልተው ፥ ዳቦውን ጋግረው ሊያስቀድሱ የመጡትን ምዕመናን ሁሉ ከቅዳሴ በኋላ ይጋብዛሉ ። ይህ እስካሁን በትምህርት ቤቶች የሚሠራበት ነባር ትውፊት ነው ።

፭ኛ/ ሆሣዕና፤—ከትንሣኤ አንድ ሳምንት ቀድሞ በሚውለው እሑድ የሚከበር ነው ። ታሪኩ በወንጌል ተመዝግቧል ። 124. በዐሉን በዚህ ዕለት እንዲሆን የወሰኑት ግን ሊቃውንት ናቸው ። ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው ። በዚያች ዕለት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሆሣዕና እያሉ ስላመሰገኑት ፥ ዕለቱ በጌታ ስም ተጠርቷል ። አንዳንዶች ክርስቲያኖች ደግሞ ሆሣዕናም ይላሉ ። « የፀበርት እሑድም ይሉታል» ጸበርት እየተባረከ ለሕዝብ ይታደላል ሕዝቡም ጸበርቱን እየተቀበለ እንደ መስቀል አድርጎ እየሠራ በየቤቱ ይሰቅለዋል ። አንዳንዱም እንደ ጣት ቀለበት አድርጎ እየሠራ በጣቱ ይሰካዋል ። ከቅዳሴ በኋላ በቤተ ክርስቲያን በአራቱም ማዕዘናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ ። ከሠርክ ሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ያሉት ዕለታት የዓመተ ፍዳ መታሰቢያ (ሰሙነ ሕማ

124. ማቴ. ፳፩፡ ፩—፲፩



ማት) ስለሆኑ ፥ ጸሎተ ፍትሐት ፥ ጸሎተ አስተሥርዮ አይፈጸምም ። ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተሥርዮ የሚደረግ በዚሁ የሆሣዕና በዐል ዕለት ነው ። በአክሱምና በሌሎችም አንዳንድ ቦታዎች ታሪኩን እንዳለ ለመግለጥ አህያ ጭነው በዚያ ላይ ሰው እያስቀመጡ ሥርዓተ ዑደት ይፈጽማል ።

፮ኛ/ ስቅለት፤— የስቅለት በዓል ለዓለም ቤዛ ሊሆን መድኃኔ ዓለም የተሰቀለበት ዕለት ነው ። የስቅለት በዐል ብዙ ዘርፍ አለው ከላይ እንደ ተገለጠው ከሠርክ ሆሣዕና ጀምረው ያሉት ዕለታት የዐመተ ፍዳ መታሰቢያ ናቸው ። በነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማደ መባልዕት አይበሉም ። ስግደት ይስገዳል ፥ የጌታን መከራ ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከድርሳናት ሲነበቡ ይሰነብታሉ ። ሐሙስ ጸሎተ ሐሙስ ይባላል ። ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበት ፥ ከሐዋርያት ጋር ግብር ያገባበትና ምሥጢረ ቁርባንን ያሳየበት ዕለት ነው ። በዚህ ዕለት ቄሱ ውሀውን በብርት አድርጐ በጌታ አምሳል የምዕመናንን እግር ያጥባል ። ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ምዕመናኑ ወደየቤታቸው ሔደው ዳቦና ጉልባን ይበላሉ ። ለትንሣኤ የቱ ዘጋጀው ጠላ የሚቀመሰውም የዚያ ዕለት ነው ። በበነጋው የስቅለት ዐርብ የስቅለቱ መታሰቢያ አጎበር ተሠርቶ ለስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡና ሲሰገድ ይዋላል ፥ ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕመን ወደ ቄሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ የሠራውንም ኃጢአት ይናዘዛል ፤ ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ቀን ሲሰግደው ከዋለው ሌላ ስግደት ይሰጠዋል ። ጥብጣቤው የተገሳጽ ምሳሌ ነው ። አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል ። በቤተ ክርስቲያናችን ልማድ እመቤታችን ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውሀ አንቀምስም ብለው እስከ ትንሣኤ ቆይተዋል ይባላል ። በሀገራችንም ዛሬ እንኳ እንጅ ብዙ ሰዎች ሐሙስ ማታ የቀመሱ እሑድ የትንሣኤ ዕለት ብቻ ነው እህል ውሀ የሚሉት ። ያልተቻላቸው ግን ዓርብ ማታ ትንሽ ቀምሰው እስከ ትንሣኤ ይሰነብታሉ ። የሁለት ቀን ማክፈሉ እንኳ ቢከ

www.ethiopianorthodox.org

ብድ ቅዳሜን ማክፈል ጥሩ ልማድ ነው ። ቅዳሴው በመንፈቀ
ሌሊት ስለሆነ በልቶ ማስቀደስ ፥ በልቶ መቁረብ እንዳይሆን ።

፮ኛ/ ትንሣኤ ፦ የትንሣኤ በዓል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ ተቀ
በረ ፤በሦስተኛውም ቀን መግነዝ ፤ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ፤ሳይል
ከሙታን ተለይቶ የተነሳበት ዕለት ፤ ትንሣኤ ትባላለች ። ትንሣኤ
ለክርስቲያኖች የድል ቀን ፤ የነፃነት ቀን ናት ። የትንሣኤ በዓል
በቤተ ክስበቲያናችን ከሌሎች በዓላት ሁሉ በጣም ፤ በደመቀ አኳ
ኋን ይከበራል ፤ መንፈሳዊ ተመስጦም አለበት ። ከአምሳ አራት
ቀን የጾም ጉዞ በኋላ የምትመጣ ስለሆነች ትንሣኤን ሁሉም ይና
ፍቃታል ። ይልቁንም በአክፍሎት የሰነበቱ ሁሉ ዕረፍተ ሥጋን
ለማግኘት ትንሣኤን ፤በናፍቆት ይጠባበቋታል ። ቅዳሜ ማታ ለእ
ሑድ አጥቢያ ሕፃኑ ፤ ሽማግሌው ፤ ወጣቱ ፤ ባልቴቱ ፤ በየሰበካ
ቤተ ክርስቲያንቸው ይሰበሰባሉ ። ሥርዓተ ጸሎት ይጀመራል ።
ለትንሣኤ በዓል፤በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተመዘገበው ፤ ጸዋትው ከተ
ፍጸመ በኋላ በመንፈቀ ሌሊት ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል ። ከሌሊቱ
ዘጠኝ፤ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል ። የትንሣኤ ማዕድ፦
ባዕድ ፤ ዘመድ ፤ ወዳጅ ፤ ጠላት የማይለይበት የጋራ ማዕድ ነው
የትንሣኤ ዕለት ምንም ቢሆን ያለው በልቶ ያጣው ጦም እያድ
ርም ፤ በከተማ እንጃ እንጂ በባላገር እያንዳንዱ ምዕመን የተቻላ
ቸውን ያህል ተማሪ እየወሰደ የትንሣኤን ማዕድ አብሮ ይመገባል ።
በትንሣኤ ሳምንት በደብዳቤም በስልክም የሚሰጠው ሰላምታ ፤
« እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ » ነው ። መላሹም
«እንኳን አብሮ አደረሰን» ይላል ። (ጽርዓውያን ከትንሣኤ እስከ ዕር
ገት ፤ ዓርባውን ቀን ሰላምታ የሚሰጣጡት ፦ «ክርስቶስ ተነሣ »
ሲል አንዱ ፤ መላሹ ፦ «በዕውነት ተነሣ» ይላል ። ከእሑድ ጀምሮ
እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ዕለታት እንደ አንድ ቀን ነው የሚ
ጠሩት ፤ መዝሙሩም ጸሎቱም አይለወጥም ። ምዕራባውያን ከት
ንሣኤ ይልቅ ልደትን በደመቀ አኳኋን ያከብራሉ ። ይኸውም ስለ



ሁለት ምክንያት ነው ። አንዱ ያው እንደ ክርስቲያኖች ሁሉ ክር
ስቶስ የተወለደበትን ዕለት ለማክበር ነው ። ሌላው ምክንያት ደግሞ
አሮጌውን ዓመት ሸኝተው አዲሱን ዓመት የሚቀበሉት በልደት
ሳምንት ስለሆነ ተደራራቢ በዓል አድርገው ነው ። በምሥራቅ አብ
ያተ ክርስቲያናት ግን የበዓላት ሁሉ ርዕሰ ትንሣኤ እንደ መሆኑ
መጠን በጣም ይከበራል ። በምሥጢርም ቢሆን የክርስቶስ አምላ
ክነት በይበልጥ የጐላው በትንሣኤው ስለሆነ ከልደት አብልጠው
ያከብሩታል ።

፯ኛ/ ዕርገት ፦ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ዓርባ
ቀን ለሐዋርያት እየተገለጠ ታይቷቸዋል ። ትምህርትም አስተምሯ
ቸዋል ። በተነሣ ባርባኛው ቀን ቀደም አድርጎ እንደነገራቸው ለሐዋ
ርያት እሁንም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ነግሮ ወደ ሰማይ
የወጣበት ቀን ነው ። ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያን በጸሎት ፤ በማ
ኅሌት ይከበራል ። በሕዝቡ ዘንድ ግን ልዩ መሰናዶ የለውም ።

፰ኛ/ ጰራቅሊጦስ ፦ ጌታ ባረገ ባሥረኛው ፤ በተነሳ ባምሳ
ኛው ቀን ለሐዋርያት በነገራቸው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ
ቅዱስን ላከላቸው ። በዓለ ጰራቅሊጦስ ባለው «ጰንጠቆስጤ» የሚል
ይገኛል ። ጰንጠቆስጤ ቃሉ የግሪክ ነው ። « ፔንዲኮንዳ » «ፔንዲ
ኮስቲ» አምሳ አምሳኛ ማለት ነው ። በብሉያትና በሐዲሳት በሌሎች
መጻሕፍት ሁሉ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ ሳይለወጡ የገቡ ብዙ ጥሬ
ቃላት አሉ ። « ለምሳሌ ፦ ኬፋ ፤ ፋሲካ ፤ ኤሎሄ ፤ ላማ ፤ ሰበ
ቅታኒ ፤» —ከዕብራይስጥ ፤ «ጰንጠቆስጤ ፤ ጰራቅሊጦስ ፤ ጴጥሮስ ፤
ክርስቶስ ፤ ንብቲራ ፤ » —ከፅርዕ የተወረሱ ጥሬ ቃላት ናቸው ።
ጰራቅሊጦስ ማለት በጐን የሚቆም ፤ የሚረዳ ፤ የሚያጽናና ማለት
ነው ። ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን የእሸት በዓል ነበር ( በዓለ ሰዊት )
እሥራኤል የነፃነት በዓላቸውን ከሚያከብሩበት ከበዓለ ፋሲካ (በዓለ
ፍሥሕ) ጀምረው አምሳውን ቀን በዓል አድርገው ይሰነብታሉ ።
በአምሳኛዪቱ ቀን በዓለ ሰዊትን ( የእሸት በዓላቸውን ) ያከብ
ራሉ ። በሀገራቸው ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው ወቅት በሀገራ

www.ethiopianorthodox.org

ችን ከመስከረም እስከ ኅዳር እንዳለው የእሸት ወራት (የፀደይ ወራት) ነውና ። የእሸት በዓላቸውን የሚያከብሩት በኦሪት ዘሌዋውያን በምዕራፍ ፳፫፡፲—፲፯ በታዘዙት መሠረት ማንኛውም እሥራኤላዊ ገበሬ ከዘራው ሁሉ በያይነቱ እሸቱን ቀርጦ ተሸክሞ ወደ ምኩራቡ ይመጣል ፤በቤተ መቅደስ የሚያገለግለው ካህን ተቀብሎ ባርኮ ጸልዮ ፤ የሚጠበሰው እየተጠበሰ የሚታሸው እየታሸ በማኅበር አንድነት ይበላል ። ይህም «ቀዳምያት ይባላል ።» የመጀመሪያው ማለት ነው ። ከማንኛውም በረከት የመጀመሪያው እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ለእግዚአብሔር መሰጠት እንዳለበት ታዟልና ። በዓለ ፋሲካን ለማክበር ከዞርወት ተሰብስበው የሰነበቱ አይሁድ ሁሉ ወደየመጡበት የሚመለሱት ይህን በዓለ ሰዊትን ካከበሩ በኋላ ነው ። ይህን ሁሉ የገለጥነው በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በተሰጠበት ዕለት የነበረው ለታሪካችን መገናኛ እንዲሆን ነው ። ከዞርወት የተሰበሰቡና በዚያውም የሚኖሩ አይሁድ አብዛኛውን ጊዜ በዓል የሚያከብሩ በደብረ ጽዮን ነው ። ደብረ ጽዮን ጥንትም የዳዊት ከተማ ነበረች ፤ የዳዊት መቃብርም በደብረ ጽዮን ነው ፤ ይመጣል ብለው የሚጠብቁት መሲሕም በደብረ ጽዮን ይነግሣል ነው የሚሉት ። እንግዲህ በዚች በደብረ ጽዮን በዓለ ሰዊትን ለማክበር ተሰብስበው እንዳሉ ሐዋርያት ደግሞ በዚሁ በደብረ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር ። 125 *

ጌታ ባረገ ባሥረኛው ቀን ጧት መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጠ ። ጌታ የነገራቸው የተስፋ ቃል ሁሉ ተፈጸመ ። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የሞቱና የትንሣኤው ምስክሮች ሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በነሱ ላይ ሲያድር ለቤተ ክርስቲያን ጉዞ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ ። ሊቁ ዮሐንስ አወፈርቅ እንዳለው ፤— «መንፈስ ቅዱስ ባይወርድላት ኑሮ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ኮስምኖ ቀጭጮ ይቀር ነበር ፤ ስለዚህም በሚገባ እነጋገር ይህች ዕለት

125. Epiphanius, de Mens. et Pond. 14; Cyrial Jerus — Catech. 16.
(ይህን ቤት ቲቶ ኢየሩሳሌምን ሲያጠፋ አላፈረሰውም ይባላል ።)

www.ethiopianorthodox.org



የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ትባላለች» ይላል ። ብዙ ሊቃውንት ይህችን ዕለት የበዓላት ሁሉ እመቤት ይሏታል ። የጰራቅሊጦስ በዓል በክርስቲያን ዓለም ሁሉ ከትንሣኤው ባምሳኛው ቀን ይከበራል ። በሀገራችንም እንደዚሁ ነው ። የትንሣኤው ቀለም (በቤተ ክርስቲያን) የሚፈጸመው የጰራቅሊጦስ ዕለት ነው ።

ዘጠኙ ዐበይት በዓላትና የተ መጣቸው እንዲሁም የአከባበራቸው ሥነ ሥርዓት ከዚህ በላይ እንዳየነው ነው ። ከነዚህ ውስጥ ሆሣዕና ፥ ስቅለት ፥ ትንሣኤ ፥ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ በዓላት አዋድያት ስለሆኑ በቀን አቆጣጠር መባቻ ሐመርን ተከትለው ወደ ላይ ወደ ታች ይላሉ ። ዕለታቸው ግን አይፋለስም ። ሆሣዕና ፥ ትንሣኤ ፥ ጰራቅሊጦስ እሑድን ፥ ስቅለት ዐርብን ፥ ዕርገት ሐሙስን አይለቅም ። ሌሎቹ ጽንስ ፥ ልደት ፥ ደብረ ታቦር ፥ ጥምቀት ፥ ግን ዐዋድያት አይደሉም ፥ ዕለታቸው ግን የተፋለሰ ነው ።

ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት ሌላ ዘጠኝ ንዑሳት በዓላት አሉ ። እነሱም ፤— ፩. መስቀል ፥ ፪. ስብከት ፥ ፫. ብርሃን ፥ ፬. ኖላዊ ፭. ኅዝረት ፥ ፮. ልደተ ስምዖን ፥ ፯. ቃና ዘገሊላ ፥ ፰. ደብረ ዘይት ፱. የመጋቢት መስቀል (መጋቢት ፲) ።

ሀ/ የመስቀል በዐል የሚከበረው መስከረም ፲፯ ቀን ነው ። ይህም በዓል በክርስቲያን ዓለም ሁሉ ይከበራል ። ታሪኩም በመጠኑ እነሆ ጌታ በመስቀል ላይ ሙቶ ከተነሣ በኋላ ሕሙማን መስቀሉን እየዳሰሱ በመስቀሉ እየታሹ ይፈወሱ ነበር ። በዚህም ተአምራት እየተሳቡ ብዙዎች ክርስቲያን ሆኑ ። ይህንን ያዩ አይሁድ መስቀሉን ባንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት ። በየቀኑ የአካባቢው ፍሬ ሁሉ ቆሻሻ ስለሚጥልበት ያ ቦታ እንደ ጉብታ ሆነ ። ምንም እንኳ ለማውጣት ባይችሉ ክርስቲያኖቹ ያን ቦታ ያውቁት ነበር ። በኋላ ግን በጥጦስ ወረራ ክርስቲያኖቹ ኢየሩሳሌምን ጨርሰው ለቀው ስለ ወጡ የከተማዋም መልክ ፈጽሞ ስለተለወጠ መስቀሉ የተደፈነበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም ። በዚህም ምክንያት ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ተዳፍኖ ቆይቷል ። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (፫፻፳፯) የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት

ዕሌኒ ይህን ታሪክ ትሰማ ነበርና አስቆፍራ ለማስወጣት ጉዞዋን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለች ። እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን አላገኘችውም ፤ ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅላት አላገኘችም ። በመጨረሻ ግን የመስቀሉ መውጣት የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነበርና ፥ አንድ አረጋዊ ስሙ ኪርያኮስ የሚባል (ኪራኮስ—ድጓ) የዕሌኒን መቸገር አይቶ እንደሚከተለው ይመክራታል ። «አንቺም በከንቱ አትድከሚ ሰውም በከንቱ አታድክሚ እንጨት አሰብስበሽ ከምረሽ ዕጣን አፍሺበት ፥ በእሳትም አያይዘው የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍሪው ፥ በዚህ ምልክት ታገኝዋለሽ አላት ፥ እሷም ያላትን ሁሉ አደረገች ። « ዘዕጣን አንጸረ ሰገደ ጢስ ድጓ » የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል አሳየ ፥ ያን ምልክት ይዛ አውጥታዋለች ። «በጐልጐታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል» (ድጓ) ይህን በዓል በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ያከብሩታል ። በሀገራችንም እንደ አጋጣሚ ሁኖ የመስቀል በዓል ከጥቢ ወራት መግቢያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተለየ ድምቀት አለው ።

በመስከረም ፲፮ ባላገሩ ፥ በቀበሌው ፥ የከተማው ሕዝብ ማዘጋጃ ቤት ባዘጋጀለት ቦታ ከየቤቱ ችቦውን እንጨቱን እያመጣ ይደምራል ። ካህናቱም በደመራው ፊት ለፊት ጸሎት አድርሰው «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ» እያሉ ደመራውን ይዞራሉ ። ቀጥሎም ሕዝቡ፦— «ኢዮሀ አበባዬ ፥ መስከረም ጠባዬ» እያሉ በደመራው ዙሪያ ይጨፍራሉ ። ግጥሙ የወራቱ እንጅ የመስቀል ባይሆንም ፥ ቁም ነገሩ የመስቀልን ክብር አይለቅም ። ማታ ሕዝቡ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ ያመሻል ። በአሥራ ሰባት ጧት ደመራው ይለኮሳል ። አመድ እስኪሆን ድረስ ይቃጠላል ። ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ አመዱንና ትርኳሹን እየተሻማ ወደየቤቱ ይዞ ይሔዳል ። ለሰውም ሆነ ለከብት መድኃኒት ነው ።

በአዲስ አበባና በአካባቢው ግን ደመራውን የሚያቃጥሉት ወዲያው ጸሎቱ እንዳበቃ ነው ። ከላይ

www.ethiopianorthodox.org



በሀገራችን በጥቢ ወራት ማለት አበቦች በሚፈነዱበት ወራት ስለሆነ ባንዳንድ አነጋገር የዕንቁጣጣሽ በዓል ይባላል ። እዚህ ላይ እንቁጣጣሽ የሚሉት ሕፃናቱ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን አበቦች ለቅመው አንድ ላይ በሰርዶ አሥረው ከደመራው ዕለት ጀምረው ለጐረቤቶቻቸውና ላገኙት ሁሉ ይሰጣሉ ። ሰዎችም የሀገር ትውፊት ነውና አበባውን እየተቀበሉ ገንዘብ ይሰጧቸዋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በየቤቱ እየዞሩ ወንዶችም ሴቶችም ለየራሳቸው የሀገር ባህል ግጥም እየገጠሙ ይጨፍራሉ ። ባለቤቶችም እንደ ሽልማት እያደረጉ ገንዘብና ሌላም ነገር ይሰጧቸዋል ። አንድ ላይ አጠራቅመው ድግስ ደግሰው ይመገባሉ ። በግራኝ ወረራ ብዙ ባህሎች ሲደመሰሱ የመስቀል በዓል ግን እንኳን በክርስቲያኖቹ ተገደው በሰለሙት ኢትዮጵያውያን ዘንድ አልተረሳም ። ለምሳሌ፦—በሀገራችን ብዙ እስላሞች የመስቀልን በዐል ከክርስቲያኑ ጋር እንደ ክርስቲያኑ አድርገው ያከብራሉ ። እንግዲህ ከቀን በኋላ በወራሪ ኃይል ተገደው እስልምናን ቢቀበሉም ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ክርስቲያናዊ ባህል ሳያውቁ ያከበሩታል ማለት ነው ። ባህል የሰውን ምንጭ ፥ የሰውን የትመጣ ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ መጽሔት ነውና ። ከዚህም ጋር ብዙዎቹ እስላሞች ባንገታቸው መስቀል ያሥራሉ ። መስቀል የክርስቲያኖች ምልክት መሆኑን አያውቁትም ። ይህም መሠረታቸው ክርስቲያን መሆኑን ያሳያል ።

ለ/ ስብከት ፥ ሐ/ብርሃን ፥ መ/ ኖላዊ፦— እነዚህ ሦስት በዓላት ከልደት በፊት የሚውሉ ሦስት እሑዶች ናቸው ። ነቢያት ይወርዳል ፥ ይወለዳል ብለው በትንቢት ይጠባበቁት የነበረው መሲሕ የዓለም ብርሃን ፥ የነፍሳት ጠባቂ ነው ለማለት በቤተ ክርስቲያናችን የመዝሙርና የጸሎት ሥርዓት ከልደቱ ቀደም ብሎ ያሉት ሦስት እሑዶች ስብከት ፥ ብርሃን ፥ ኖላዊ ተብለው ተሰይመዋል ። አከባበራቸውም በቤተ ክስበቲያን ቀለም እንጂ ልዩ ሥርዓት የላ

ሠ/ ግዝረት ፡—ይህ በዓል የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ 126* ሕፃን ሲወለድ በስምንት ቀኑ ይገረዛል ። ይህን የሙሴን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታ በተወለደ በስምንት ቀኑ ተገርዟል ። የተወለደው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ሲሆን ስምንተኛው ቀን የሚውለው በጥር ስድስት ቀን ነው ። ይህ ቀን ከዚ ጊዜ ጀምሮ ሲከበር ይኖራል ።

ረ/ ልደተ ስምዖን፡—ይህም በዓል ጌታ በተወለደ በአርባ ቀኑ የሚከበር ነው ። ጌታ ሥርዓተ ኦሪትን ፣ ትንቢተ ነቢያትን ሊፈጽም እንጅ ሊያፈርስ ስላልመጣ ፣ ሕገ ኦሪትን ፈጽሟል ። ለሙሴ ሕግን የሰጠ ሲሆን የሙሴን ሕግ ፈጽሟል ። ከላይ እንዳየነው በስምንት ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቷል ፣ አሁን ደግሞ በተጻፈው መሠረት 127* የሙሴን ሕግ ለመፈጸም ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወሰዱት ። በዚያም የእሥራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረ ስምዖን የሚባል ሰው ነበር ። እሱም መሲሕን ሳያይ እንደማይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶት ነበር ።

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ መሠረት ይህ ስምዖን በ፪፻፹፪ ከጌታ ልደት በፊት በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት መጻሕፍተ ብሉያት ከዕብራይስጥ ወደ ፅርዕ በተመለሱ ጊዜ ከመላሾቹ ከሰባው ሊቃውንት አንዱ እሱ ነበር ። እንደ አጋጣሚም ለሱ የደረሰው ኢሳይያስ መጽሐፍ ነበር ። «ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ» ከሚለው ሲደርስ ድንግል ትወልዳለች ብሎ መተርጐሙ ተቀባይ የማያገኝ አሳፋሪ ነገር መስሎት «ድንግል ትወልዳለች » የሚለውን ንባብ «ወለት ትጸንሳለች» ብሎ መለሰው ። ተመልሶ እንደ ገና ቢያይ «ድንግል ትወልዳለች» የሚል ተጽፎ አገኘ ፣ ሁለተኛም ፍቆ «ወለት ትወልዳለች» ብሎ ጻፈ ። እንደ ገና ቢያይ

126. ዘሌዋ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ።
127. ዘፀአት ፡ ፲፫ ፡ ፪ ። ዘሌዋ ፲፪ ።



«ድንግል ትወልዳለች» የሚል ንባብ አየ ። በሦስተኛው እፍቃለሁ ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ ተገልጦ ተው አትፋቀው ፣ ይህን የተጠራጠርከውን ሳታየው አትሞትም አለው ፡—ጌታ በእናቱ እቅፍ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ እሱም በእግዚአብሔር ፈቃድ መጥቶ እዚያ ተቀምጦ ነበር ። ጌታን ከእመቤታችን ተቀብሎ ታቅፎ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ሁለት ከቁጥር ፳፱—፴፪ ያለውን ጸለየ ። ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በስምዖን ዕቅፍ የታየበት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል ስምዖን ጌታን በታቀፈ ጊዜ ከእርጅናው መታደሱ ስለሚነገር በዓሉ የጌታ ሁኖ ሳለ ልደተ ስምዖን እያልን እንጠራዋለን ። ሌሎቹ ፡—«የጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ» ይሉታል ።

ሰ/ ቃና ዘገሊላ ፡— ቃና በገሊላ ክፍል የምትገኝ ቀበሌ ና፦ በዚች ቀበሌ ውስጥ ጌታ ከሠርግ በዐል ላይ ተገኝቶ ነበር ። 128* ታሪኩን ከላይ በተጠቀሰው የወንጌል ምንባብ ውስጥ ይመለከቷል። የጌታ የመጀመሪያው ተአምር የተገለጠበት ሥርጊት ስለሆነ እናከብረዋለን ። ይህ በዓል የሚውለው በየካቲት ፳፫ ቀን ነበር ፣ ጌታ ዕለቱን ተጠምቆ ዕለቱን ወደ ገዳመ ራሐ ሔዷል ። ከተመለሰ በኋላ ሀሦስተኛው ቀን ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ በየካቲት ፳፫ ውሀውን የወይን ጠጅ በማድረግ የመጀመሪያውን ተአምር አሳይቷል ። አሁን ግን በዐልና በዐልን ለማገናኘት ሲባል ጥር ፲፪ ቀን የጥምቀት በዐል በዋለ በነጋው እናከብረዋለን ።

ሸ/ ደብረ ዘይት ፡—ደብረ ዘይት ወይራ የሞላበት ተራራ ማለት ነው ። የሚገኘውም በኢየሩሲሌም በስተምሥራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ነው ። ጌታ ቀን በቤተ መቅደስ ሲያስተምር 129* ደቀ መዛሙርቱ የምጽአቱን ጉዳይ እንሥተው ጠይቀውት ምልክቱን ገልጦ ነግሩአቸዋል ። የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅ/ ያሬድም

128. ዮሐ. ፪ ፣ ፩—፲፪ ።
129. ማቴ. ፳፬ ።

www.ethiopianorthodox.org

የዓቢይ ጾምን እኩሌታ እሑድ የጌታ ዳግም ምጽዓት መታሰቢያ እድርጕ መዝሙሩን በዳግም ምጽአት ጽፏል ። ዕለቱም ደብረ ዘይት ይባላል ። በዚህ ዕለት ሕዝበ ክርስቲያኑ ያለውም የሌለውም እንጀራ ጋግሮ ጥሬ ቆልቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስድና ለነዳያን ይሰጣል ። ለምን ይህን እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ የሚከተለው ነው ። « የሞቱ ነፍሳት በዛሬው ዕለት ይሰበሰባሉ ዘመዳቸው የሆነ ጥሬ ወይም እንጀራ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መጥቶ ለነዳያን የሰጠ እንደሆነ አይተው ደስ ብሏቸው ይመለሳሉ የሞተ ዘመድ እያለው አንድ ሰው በዚህ ዕለት የሚበላ ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ካልመጸወተ የዘመዱ ነፍስ መጥታ የኔስ ወገኖች አልቀዋል ብላ ትመለሳለች» እያሉ ይተርካሉ ። የአባባሉ ምሥጢር የዳግም ምጽአትን ነገር ይመለከታል ።

<u>ቀ/ የመጋቢት መስቀል</u> ፦ ይህ በዐል የሚከበረው መጋቢት አሥር ቀን ነው ። ባንዳንድ የሀገራችን ሰዎች ዘንድ ዕሌኒ በመስከረም ማስቆፈር ጀምራ መስቀሉ የወጣው መጋቢት አሥር ቀን ነው ይላሉ ። ነገር ግን ይህን አተራረክ ለመቀበል በቂ ምስክር የለም በዓለምም ዙሪያ መስቀሉ የወጣበት ዕለት የሚከበረው መስከረም ፲፯ ብቻ ነው ። ያም ሆነ ይህ መጋቢት አሥር ቀን ከንዑሳት በዓላት ዘጠነኛው ነው ። ዘጠኙን ዐበይት በዐላትና ዘጠኙን ንዑሳት ዐላት ከዚህ በላይ በመጠኑ በተገለጠው ለመረዳት ይቻላል ።

ከነዚህ ሌላ የእመቤታችን በዐላት፦ልደታ ፥ በዐታ ፥ ፍልሰታና እስተርእዮ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሲከበሩ የኖሩ ናቸው። ሌሎቹ በመቅድመ ተአምር የተጨመሩት ፴፫ቱ በዓላተ - ማርያምና በየወሩ በ፳፩ የሚከበረው የእመቤታችን በዐል ፥ በ፳፱ የሚከበረው በዐለ እግዚእ ፥ በ፲፪ የሚከበረው የሚካኤል ሌሎችም በዐላት የተጨመሩት በ፺፪ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው ። ይባላል ። ከዚያም አያይዞ ሕዝቡ የቅዱሳንንና የመላእክትን በዐላት በየወሩ ማክበር ጀመረ ። ለምሳሌ ፦ ቅዱሳን መላእክት ፥ ቅዱሳን ሰማዕታት ጻድቃንም በዓመት አንድ ጊዜ እንዲከበሩ በዓለም ዙሪያ



ሁሉ ያለ ነው ። በእኛ ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ባለበት ሰበካ በት ውልድ የመጣ ልማድ ሁኖ በቤተ ሰቡ ሁሉ ይከበራል ። እያት ቅድመ አያቱ የጊዮርጊስን በዐል ያከብር እንደሆነ ልጁ የልጅ ልጁ ያያቴ ታቦት ነው እያለ በየወሩ ተቀምጦ ይውላል ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ ሰፍራ ቀጥራ ያስተማረችው የጌታ የእመቤታችን ፤ የሐዋርያት ፤ የመላእክትና የቅዱሳን በዐላት የተወሰኑ ሁነው ሳለ ፤ ሕዝቡ በገዛ ፈቃዱ ምክንያት እየፈጠረ ዛሬም በዐል ነው ነገም በዓል ነው ብሎ ተቀምጦ ቢውል ቤተ ክርስቲያንን አያስወቅስም ። እንደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስታያንም የዓመት ስንክሳር አላት ። ይኸውም በየዓመቱ የሚከበረውን « ቅዱስ ጻድቅ» የሕይወት ታሪክና አሟሟት በዝርዝር የያዘ መዝገብ ነው ። በዚሁ በስንክሳሩ መሠረት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም በዓላትን ያከብራሉ ። አሁን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት በዓላትን መቀነስ ወይም ጨርሶመሠረዝ ሳይሆን ፤ የአከባበሩን ዓይነት ማስ[illegible] ነው ። ወይም በግልጥ እንጋገር የበዐል ሥራ መፍጠር አለባት ሥራ ፈትቶ መዋል በዐል ማክበር አለመሆኑን ቀስ በቀስ ለምእ[illegible]ናኗ ማስረዳት አለባት፤ ምዕመናን በዓሉንም አክብረው ሥራቸውንም ሠርተው ለመዋል ይችላሉና ። የነበረውን በአዋጅ መለወጥ ግን ትምህርቷን ያዛባዋል ። በዐል ማክበር እንደ በሽተኛ ተኝቶ በመዋል አለመሆኑንም የቤተ ክርስቲያን አባቶች አስረድተዋል ። 130፡ « ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያዕርዑ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ ፤ አላ ይትገበሩ ከመ ክርስቲያን ወኢትትዐቀቡ ሰንበት ከመ አይሁድ ። 131፡

የዓመት በዐላት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚከበሩት በውዳት ነው ። ለበዐሉ የተዘጋጀው መዝሙር እየተዘመረ ታቦቱ ከመ

---

130. የአትናቴዎስ ቅዳሴ ፤
131. ፍትሐ ነገሥት ፲፱ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ንበሩ ትንስቶ ቤት ክርስቲያኑን ሶስት ጊዜ ከዞረ በኋላ ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል ። ይህ የሚሆነው ጧት በሚቀደስባቸው ዕለታት ነው ። ውሎ ቅዳሴ ከሆነ ግን ታቦቱ ከዑደት ሲመለስ ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል ፤ ጸሎተ ቅዳሴ ው ሲፈጸም ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል ።

ከነዚህ ከጠቀስናቸው በዐላት ሌላ በክርስቲያኑ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበር በዐል ቅዱስ ዮሐንስ (የዘመን መለወጫ) ነው ። በኢትዮጵያችን ሁልጊዜ አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው ። የጥንት ሮማውያን አዲስ ዓመት የሚያከብሩ በመጋቢት ወር ነበር ። መስከረም ለመጋቢት ሰባተኛ ወር ነው ። «ሴፕቴምበር» ይሉታል» « ሴፕቴም (Septem) »ሰባት ከሚለው ቃል የተወረሰ ነው ። ከጢባርዮስ ቄሣር በኋላ የተነሡ አያሌ የሮም ነገሥታት በዚህ ወር ተሠይመውበታል ። ይህንኑ ወር የእንድቅትዮን ወር ይሉታል ። (Indico) ከሚለው የላቲን ቃል የወጣ ነው ። (Indicto-Onis) አዋጅ መንገሪያ ትእዛዝ ማስተላለፊያ ውሳኔ መወሰኛ ማለት ነው ። «የበጀት ዓመት» እንዲሉ ለነገሥታት የሚሰጠው ግብር ፤ ለሃይማኖት አባቶች የሚቀርበው ገጸ በረከት ተሰብስቦ መፈጸም ያለበት በዚህ ወር ነው ። በሀገራቸው የቢጋው ወራት ፍጻሜ የክረምቱ ተጋባት በመስከረምነውና ፤ « እንደ ሀገራችን ግንቦትና ሰኔ » ይህንኑ ወር በየእሥራ አምስት ዓመት የእንድቅትዮን በዓል እያሉ ያከብሩት ነበር ።

ሕገ መንግሥት የሚታደስበት ፤ ውል የሚፈርስበት የሚታደስበት በዓል ነው ። በብሉይ ኪዳን ግን እሥራኤል ነፃ ከወጡበት ከመጋቢት ወር ጀምረው ቆጥረው በሰባተኛ ወር አዲስ ዓመት እንዲያከብሩ ከፈጣሪያቸው ታዘዋል ። 132. አዲሱን ዓመታቸውን በዚህ ወር የሚያከብሩ ከእግዚአብሔር ታዘው ስለሆነ ይህ ዐውደ ዓመት ለእሥራኤል ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊም ስሜት አለው። ስለዚህ በዚህ ዓውደ ዓመት ብዙ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች ይፈጸሙበታል ።

132. ዘሌዋ. ፳፫ ፡ ፳፬ ። ዘኁልቊ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ።



ሊቀ ካህናቱ ኤፉዱን ለብሶ የሐር መነሳነሱን ይዞ የዓመቱን በዐላትና አጽዋማት ለሕዝቡ የሚአውጀው በዚህ ቀን ነው ። በክርስትና ዓለም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ ተቀብላ አዲስ ዓመት በመስከረም ወር መጀመሪያ እያከበረች ብዙ ዘመን ኑራለች ። በኋላ ግን ከ፲፭፻፸፪—፲፭፻፹፭ የነበረው የሮማ ፓፓ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ከልደት እንዲያያዝ ለማድረግ በጥር ወር ይሁን ብሎ ወሰነ ። በዚህም ውሳኔ የካቶሊክ ግዛት የነበረው ምእራቡ ዓለም በሙሉ ሲስማማ ምሥራቁ የክርስቲያን ዓለም ግን መስከረምን አለቀቀም ። በፖለቲካና በንግድ ተጽእኖ ምክንያት መንግሥታት በአቆጣጠር ወደ ምዕራቡ ዓለም ቢሳቡም በምሥራቅ ያለች ቤተ ክርስቲያን አዲሱን ዓመት የምታከብረው አሁንም በመስከረም ነው ። ለምሳሌ ፡ « ሩሲያ ፤ ግሪክ ፤ ሩማንያ» ሌሎችም ። ይህንም የቤተ ክርስቲያን አዲስ ዓመት ይሉታል ።

በሀገራችን ግን ከጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነቅጥ ሳይለወጥ የመንግሥቱም የቤተ ክርስቲያንም አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው ። ይኸውም ለኢትዮጵያ ክብር ነው ። ሁሉ በየጊዜው ባህሉን እየለዋወጠ ምንጩን አጥቶት ሲቸገር እሷ ለምስክርነት መገኘቷ ያስመሰግናልና ። «መስከረም» ማለት ድኅረ ክረምት እንደ ማለት ነው ። በሀገራችን የክረምቱ የጨለማው ወራት ተፈጽሞ የበጋው የጥቢው ብርሃን የሚፈነጥቅበት ወር ነው ። ስለዚህ በሀገራችን አዲሱ ዓመት ሁለት ዓይነት የአከባበር ጠባይ አለው ። ( ብሔራዊና ሃይማኖታዊ) ። ነገር ግን አንዱ ከሌላው የተራቀቀ አይደለም ። ብሔራዊ ያልነው ሕዝቡ ክርስቲያንም ሆነ ሌላው በብሔራዊ ስሜቱ የሐገር ልብስ ለብሶ ብሔራዊ ዘፈን ፤ እየዘፈነ አርዶ ጠምቆ ሲበላ ፤ ሲጠጣ ፤ ሲገባበዝ ፤ ሲጠያየቅ ይውላል። በሃይማኖታዊ ትውፊቱ ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየሄደ ለዚህ የደረስኸኝ አምላኬ ተመስገን ፤ የከርሞ ሰው በለኝ ፤ ተርፎ ለሚቀ

www.ethiopianorthodox.org

ረው ዕድሜ አትንፈገኝ ፤ ብሎ ፈጣሪውን ይለምናል ። ካህናቱም በቤተ ክርስቲያን ለበዓሉ የሚገባውን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ፤ ኋላም መምህሩ ወይም መሪጌታው ካፓ ላንቃ ለብሶ መስቀሉን ይዞ በዓመቱ የሚውሉትን አጽዋማትና በዓላት ያውጃል ፤ ባሕረ ሀሳብ ያወጣል ። ቀጥሎም ፍሬያተ ምድር — ዕጣኑ ፤ ጧፉ ፤ ዘቢቡ፤ ስንዴው ፤ በመሶብ ወርቅ እየቀረበ ይባረካል ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እያንዳንዱ ወንጌላዊ፣— (ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ ) አንዳንድ የመጠሪያ ዓመት አለው ይህም በየአራተኛው ዓመት መጨረሻ ለመጀመሪያው ይደርሰዋል። (Patron) ይሉታል ፈረንጆች ጠባቂ ማለት ነው ። በኛም ይኸኑ ይመስላል ። «በዮሐንስ እረስ በማቴዎስ እፈስ» እንዲሉ ። የሕፃናቱ የአከባበር ትውፊት እንደ መስቀል ነው ። ያንን ይመለከቷል ።

ከዚህ ሌላ ሕዝቡ ከጳጉሜን ጀምሮ እስከ መስከረም አንድ የወንዝ ውሃ ወዳለበት እየሄደ ጸበል ነው እያለ በሌሊት ይታጠባል ። ይህም የቆየ ባህል ነው ። አንዳንድ ሰዎች የአምልኮ ባዕድ ጠባይ ያለበት እየመሰላቸው ድርጊቱን ይነቅፋሉ ። ነገር ግን የአምልኮ ባዕድ መርዝ እንዳይቀላቀልበት ሕዝቡን ማስተማር እንጂ በውሃ መጠመቁ ነውር አይደለም ። ቤተ ክርስቲያን የምዕመናንን ሕይወት ዘወትር በትምህርት ካልቃኘችው ማንኛውም መንፈሳዊ ተግባር በአምልኮ ባዕድ መበረዙ አይቀርምና ። በመስቀልና በዘመን መለወጫ በዓል ዕለት ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ዶሮዎች ፍየሎችና በጐች ለውቃቢ እየተባሉ ይታረዳሉ ። ይህ ድርጊት ኢ ክርስቲያናዊ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ትቃወማለች ። እያንዳንዱ ሰው በራሱና በቤተ ሰቡ ልማድ የሚፈጽመው እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተገኘ አይደለም ። 133. ስለ በዓላት በመጠኑ ይህ ነው ፤ ከዚህ በማያያዝ ስለ አጽዋማትም በመጠኑ እንናገራለን ።

ጾም (ጦም) ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል ፤ መወሰን ማለት ነው ። ወይም ለሰውነት የሚያምረውን

133. አይሁድ በዓለ መጥቅዕን ማለት አዲሱን ዓመታቸውን ሲያከብሩ ዶሮ እያረዱ መታናቸውን ይረጫሉ ፤ ውቃቢ ግን አይደለም ።



የሚያስጐመዠውን ነገር መተው ማለት ነው ። ጾም ከሃይማኖት ጋር ዘለዓለማዊ ዝምድና ስላለው ፤ ሃይማኖት ባለበት ቦታ ሁሉ ጾም አለ ። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው ። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውሃ ባፋቸው አይገባም ነበር ። 134. በኃጢአት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር ። 135.

በሐዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራ መጀመሪያ አድርጐ የሠራው ሕግ ነው ። 136. ይህ ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር መንፈስ ርኩስ ሰይጣን እንኳ በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኃኒታችን ተናግሯል ። 137. ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እንዳሉ ነበር ። 138. ለስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነበር ። 139. እነ ቆርኔሌዎ ያላሰቡትን ያዩና ያገኙ በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው ። 140. የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ ከኃጢአት ቁራኛ መላቀቂያ መጣሪያ ስለሆነ በጾም ወራት ላምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆነ ሥጋዊ ፍትወትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦችን ፤ ሥጋንና ቅቤን ፤ ወተትና የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦችን ፤ ሥጋንና ቅቤን ፤ ወተትና እንቁላልን ማራቅ ታዟል ። ከመባልዕቱና ከሌላው ደስታ ጋር ባልና ሚስት በምንጣፍ በአልጋ አይገናኙም ። 141. ጾም በትምህርተ ሐዋር

134. ዘፀ. ፴፬ ፡ ፳፰ ፤
135. ዮናስ ፫ ፡ ፮—፲ ፤
136. ማቴ. ፬ ፡ ፪ ። ሉቃ. ፡ ፬ ፡ ፪ ፤
137. ማቴ. ፲፯ ፡ ፳፩ ። ማር. ፱ ፡ ፪ ፤
138. የሐዋ. ሥራ ፲፫ ፡ ፪ ፤
139. የሐዋ. ሥራ ፲፫ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፳፫ ፤
40. የሐዋ. ሥራ ፲ ፡ ፴ ፤
1. ቆላ. ቆሮ. ፯ ፡ ፭ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ያትና በሊቃውንትም ዘንድ ሲሰበክ ኑሯል ። «ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ንዑድ ነው ፣ ክቡር ነው» እንደ ተባለ ፣ ጦመኛው ለም ሳው ወይም ለራቱ ያለውን ወጭ ነዳያንን እንዲረዳበት ለድኩማን ድርጅት ወይም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን መስ ጠት ጦሙን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደርገዋል ።

ጾም የታሪክ ድርጊቶችን እያስታወሱ ከኃጢአት ለመንጻት ፣ ስለራስ የታሰበውን ለነዳያን በመስጠት የሚጾም መሆኑን ተረድተ ናል ። ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሎሌችም ፣ ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጾማል ። « ለሚያሳድዱህ ጹምላቸው » እንደ ተባለ 142. በደዌ ዳኛ ፣ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን ፣ በስደትና በምርኮ ያሉ ትንም በጾም ወራት ማስታወስ መጸለይ ይገባል ። በጾም ወራት ከመባልዕት መወሰን ብቻ ሳይሆን ዓይን ክፉ ከማየት ፣ አንደበት ክፉ ከመናገር ፣ የተቆጠበ እንደሆነ ጾሙን ክርስቲያናዊ ያደርገ ዋል ። 143.

በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ባህልና ትውፊት ውስጥ ያሉ የምዕራብም ሆኑ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከሐዋርያት የወ ረሱት የጾም ሕግና ሥርዓት አላቸው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያንም ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ስለሆነች ፣ ይህ የጾም ሕግና ሥርዓት አላት ። በሕጓም መሠረት ሰባት የጾም ወራት አሉ ።

፩ኛ/ ዓቢይ ጾም
፪ኛ/ ጾመ ሐዋርያት
፫ኛ/ የፍልሰታ ጾም
፬ኛ/ የነቢያት ጾም
፭ኛ/ ገሃድ
፮ኛ/ የነነዌ ጾም
፯ኛ/ ዓርብና ረቡዕ ናቸው ።

ሀ/ የመጀመሪያው ጾም ፣ ዓቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ ፣ ጌታ ከተጠመቀ በኋላ የጦመው የዓርባ ቀን ጦም ነው ። 144. ምዕመናን

142. ዲድ. ፩ ፣ ፫ ፣
143. ይጹም ዓይን ፣ ይጹም ልሳን ፣ እዝንኒ ይጹም እምሰሚዓ ሕሡም በተፋ ቅሮ— « ያሬድ ድጓ »
144. ማቴ. ፬ ፣ ፩ ፣



ጌታቸው ያደረገውን ምሳሌ ተከትለው ይጾሙታል ። ዓቢይ ጾም ስምንት ሳምንታት ፶፭ ቀናት አሉት ። ከነዚህም ቀናት ውስጥ ስምንት ቅዳሜ ፣ ስምንት እሑድ ይገኛሉ ፣ አሥራ አምስት ቀን ግለት ሰባት ቀን ነው ። ከጥሉላት እንጂ ከእህል ውሃ ስለማይጦሙ የጦሙ ወራት ፵ ቀን ብቻ ነው ። ይህም በጥንታዊቷ (Primitive Church) የነበረ ሥር ዓት ነው ። ለምሳሌ በ፫፻፹፬ ገደማ ከእስፓኝ ወደ ኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ረጅም ጉዞ የሄደችው (Egeria) ኤጌሪያ የተባለችው ሴት የተሳላሚ ጉዞ በሚለው መጽሐፏ (Peregrinatio ed loca Sancta) እንደጐበኘችና የጥንት ክርስቲያኖችንም በዚህ አቆጣጠር ሲጦ ሙ ማየቷን ጽፋለች ። የቄጽርሱ ኤጲስ ቆጶስ ኤጲፋንዮስም በዚህ አቆጣጠር ይቆጥር ነበር ። 145. ሌሎች ደግሞ የመጀመሪያ ውንና የመጨረሻውን ሳምንት ለይተው ይቆጥራሉ ። ለምሳሌ የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል ይባላል ። ሕርቃል (ኢራቅ ሊዮስ) የቢዛንታይን ንጉሥ ነበር ። 146 ይህ ሳምንት በስሙ የተ ጠራበትም ምክንያት እንደሚከተለው ነው ። በዘመኑ ፋርሶች ኢየ ሩሳሌምን ወርረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር ። እሱ ወደ ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ከነሱ ነጥቆ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመ ልሷል ። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች ተደስተው ለስሙ መታሰ ቢያ ይሆን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገቡለት እየተባለ ይነገራል ። ግሪኮች ግን ጾመ ሕርቃል የሚባለውን ነገር አያውቁም ። በዚህ ሳምንት ከእንቁላልና ከአይብ ከዓሣ በቀር ሥጋ አይበ ሉም ። ጾም መሆኑንም ይናገራሉ ፣ ከላይ የተጠቀሱ ትን መባልዕት መብላታቸውም በተድላ በደስታ የሰነበተ ሰውነት ጥንታቄ ነው በሽታ እንዳያመጣባቸው ለጥንቃቄ ነው ወዲያው በጾም ሲደርቅ ይላሉ ። የሳምንቱንም ስም «የአይብ ሳምንት ፣ ወይም ነጭ ጾም» ይሉታል ።

የመጨረሻው ሳምንት ሕማማት ነው ፣ ሐዋርያት የጌታችንን መከራ ሞት እያሰቡ የጦሙት ነው ይላሉ ። ያም ሆነ ይህ

145. ፒ. ፲. ፶፪፻፴፰፻፳፭ ፣
146. ፮፻፲፱ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉም ከዐቢይ ጾም ጋር እንደ መርገፍና እንደ እጀታ ስለ ተያያዘ ከዐቢይ ጾም ይቆጠራል ። ዐቢይ ጾም መባሉ ፣ የጌታ ጾም ስለሆነ ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች (አርእስተ ኃጣውእ) ድል የተነሱበት ድል የሚነሱበት ጾም ስለሆነ ነው ። በሕዝቡም ዘንድ ሁዳዴ ይባላል ። ሁዳድ ማለት የመንግሥት መሬት የመንግሥት ርስት ማለት ነው ። የመንግሥት ሁዳድ በሚታረስበት ጊዜ አዝመራው በሚሰበሰብበት ጊዜ ልጅ አዋቂ ሳይባል የመንግሥቱ ዜጋ ሁሉ ለሥራ ታጥቆ እንደሚነሣ ፣ ይህንንም የጌታ ጾም ፣ የጌታ ሁዳድ ፣ የክርስቶስ ዜጎች የሆኑ ምዕመናን ሁሉ ይጾሙታልና ። የቤተ ክርስቲያናችንን መዝሙር ንባቡን ከዜማው አስማምቶ አጠናቅሮ የተናገረው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓው በሁዳዴ ለሚገኙት እሑዶች ሁሉ የተለየ መዝሙር ስለ ሠራላቸው እያንዳንዱ እሑድ በመዝሙሩ ስም ይጠራል ።

የመጀመሪያው እሑድ፤—ዘወረደ ይባላል ። በመጽሐፉ መጀመሪያ አምላክ ከሰማይ መውረዱን ሰው መሆኑንና መሰቀሉን ስለሚያወሳ ነው ። ሙሴኒም ይሉታል ።«ምናልባት ስለ ሙሴ ሕግና ጾመ ሙሴን ስለሚያነሣ ይሆናል ።»

ሁለተኛው እሑድ ፤—ቅድስት ይባላል ። በተለይ ስለ እለት ሰንበት ቅድስና ስለሚያወሳ ነው ።

ሦስተኛው እሑድ ፤—ምኩራብ ነው ። በዚህ ሰንበት ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ በምኩራብ ገብቶ ማስተማሩ ይነገራል ።

አራተኛው እሑድ፤—መጻጉዕ ነው ። ድውያንን መፈወሱን ዕውራንን ማብራቱን የሚያነሣ መዝሙር ይዘመርበታል ።

አምስተኛው እሑድ ፤—ደብረ ዘይት ይባላል ። በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሁኖ ያስተማረው የዳግም ምጽአትን ነገር የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመራል ።



ስድስተኛው እሑድ፤—ገብር ሔር ነው ። የጌታውን ብር ተቀብሎ ያተረፈበት ፣ በጌታወም ፊት ምስጋናን ያገኘው ሰው ታሪክ ይዘመርበታል ።

ሰባተኛው እሑድ፤— ኒቆዲሞስ ነው ።—በሌሊት ወደጌታ እየመጣ ይማር የነበረው የኒቆዲሞስን ታሪክ የሚያስተውስ መዝሙር ይዘመርበታል ።

ስምንተኛው ሳምንት ፤—ሆሣዕና ነው ፤ ጌታ በአህያ ውርንጭላ ሁኖ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበት ዕለት መታሰቢያ ነው ። ከሠርክ ሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰባት ቀን ሕማማት ይባላል በነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማደ መባልእት አይበሉም ። ስግደት ይሰገዳል ። የጌታን መከራና ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከድርሳናት ተውጣጥተው በግብረ ሕማማት ይነበባሉ ። አዳም ከፈጣሪው ተጣልቶ የኖረውን የጨለማና የመከራ ዘመን በማስታወስ መንበረ ታቦቱ በጥቁር ልብስ ይሸፈናል ። ልብሰ ተክህናውም ጥቋቁር ነው ።

ሐሙስ፤—ጸሎተ ሐሙስ ይባላል ። ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበትና ከነሱም ጋር ግብር ያገባበት ምሥጢረ ቁርባንን ያሳየበት ዕለት ነው ። ( ፈረንጆች ) ዕለቱን (Monday Thursday) ወይም (The Last Supper) ይሉታል ። በዚህ ዕለት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የግብረ ሕማማቱ መጽሐፍ እንደሚያዘው ቅዳሴ ይቀደሳል ። ከቅዳሴው ቀደም ብሎ ቄሱ ውሀውን በብርት አድርጎ በጌታ አምሳል የምዕመናንን እግር ያጥባል ። ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ምዕመናኑ ወደየቤታቸው ሔደው ለበዓሉ የተዘጋጀውን ዳቦና ጉልባን ይበላሉ ። ለትንሣኤ የተዘጋጀው ጠላ የሚቀመሰውም የዚያ ዕለት ነው ። «ስለ ሕጽበተ እግር ካነሳን ዘንድ በሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናት የሚታጠቡት በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አምሳል አሥራ ሁለት ሰዎች ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

በኛ ግን በቤተ ክርስቲያናት ያሉት ሁሉ ሴትም ሆነ ወንድ ይታጠባሉ ። ነገር ግን አሠራራችን ምሳሌ ስለሚያጥረው እኛም እንደ ነሱ አሥራ ሁለት ሰዎችን ብናጥብ የሐዋርያት ምሳሌ ነው ። »

ከጸሎተ ሐሙስ በበነጋው ዐርብ የስቅለቱ መታሰቢያ ዕለት አኀበር ተሠርቶ ለስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡ ይዋላል ። ስግደቱም ከሰሞኑ ሁሉ የበለጠ ነው ። ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕመን ወደ ቄሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል ። ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ስግደት ይሰጠዋል ። በአሥራ ሁለት ሰዓት ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል ። ሁለት ቀን የሚያክፍሉ እህል ውሀ ሳይቀምሱ ያድራሉ ። የማያክፍሉ ግን ከሐሙስ የተረፈውን ጉልባንና ዳቦ ይላኩታል ።

ቅዳሜ ጧት ምዕመናኑና ካህናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ ፤ የጧቱ ጸሎት ሲፈጸም «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ ፥ ሰላምን ፈጠረ ፥ የምሥራች እየተባለ በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰበው ሁሉ ቄጠማ ይሰጣል ። የምሥራች ምልክት ነው ። ምዕመናኑም እየሰነጠቁ በራሳቸው ያሥሩታል ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ላልመጡትም ካህናት በየሰበካቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ቃጭል ይዘው ቄጠማውን የምሥራች እያሉን ያድላሉ ። ምዕመናኑም ቄጠማውን ተቀብለው ገንዘብ ያለው ገንዘብ ይሰጣል ፥ ገንዘብ የሌለው ደግሞ ለጧፍ የሚሆን (ማግ) ልቃቂት ይሰጣሉ ፤ «አንዳንዶቹ ደግሞ ከግዕዶት እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉትን ዕለታት ተከፋፍለው ይዘው ለሰበካቸው ካህናት ምግብ እያዘጋጁ ያመጣሉ ። በጐንደርና በላስታ ሁሉም ባንድ ላይ በደጀ ሰላም ይመገባሉ ። ወይንም ምዕመኑ ካህናቱን በቤቱ ይጋብዛል ። በአዲስ አበባ ግን ወደየንስሐ አባታቸው ቤት ምግብ እያዘጋጁ ይወስዳሉ ( ያከፋይ ) ይሉታል ። በዚያ ግን ገብረ ሰላመ ነው የሚባለው» ። ይህች ቅዳሜ «ሰንበት አባይ» ትባላለች ። የፊተኛዪቱ ቅዳሜ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከሥራው ያረፈበት ዕለት እንደሆነች ይህች ደግሞ የሦስት ዓመት ከሦስት ወር የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጽሞ በከርሠ መቃብር አርፎ የዋለበት ዕለት ናት ። ሁለቱኛም ይህች ዕለት «ስዑር ቅዳሜ ትባላለች ። ስዑር መባሏ ባመት አንድ ቀን ስለምትጾም ነው ። በባላገር ግን «ስዑር» ያለውን ይዘው ሰሞኑን ምንም ሳይሠሩ ስንብተው በዚህ ዕለት ይሠራሉ ። «ቅዳሜ ሹር» እንዲሉ ፥ ቄጠማው የምሥራች ምልክት መሆኑ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ዓለም በንፍር ውሀ በተጥለቀለቀ ጊዜ የኖህ መርከብ ማረፊያ አጥታ ስትንሳፈፍ የውሀውን ሁኔታ ለመረዳት ኖህ ርግብን በመርከቡ መስኮት አሾልኮ ይለቃታል ። እሷም ቄጠማ ባፏ ይዛለት ትመለሳለች ። ኖህ በዚህ ቄጠማ የውሀውን መድረቅ ተረድቶ ተደሰተ ። መርከቡንም ለማሳረፍ ተዘጋጀ ፤ «ቄጠማ ለጥፋት ውሀ መድረቅ የምሥራች መንገሪያ እንደሆነ ፥ አሁንም በክርስቶስ ሞት ማየ ሥራዌ ማየ ድምሳሴ ፥ ኃጢአት ሞተ ነፍስ ከሰው ልጆች ተወገደ ፥ የምሥራች ሲባባሉ ምዕመናን ቄጠማ ይዘው ቄጠማ አሥረው ይታያሉ ። በዚህች ዕለት ባንዳንድ ቦታ ቅዳሴ ይቀደሳል ። ባንዳንድ ቦታ አይቀደስም ። የሚቀድሱት የሚሰጡት መልስ ካሣ የተፈጸመው ዐርብ ነው ። ቅዳሴ መኖሩን የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጻፈው የዕለቱ «ክብር ይእቲ» ለማወቅ ይቻላል ይላሉ ። አይቀደስም የሚሉት ደግሞ ምንም እንኳ የምንቀበለው ሥጋ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ቢሆንም በትንሣኤ ድል ማድረጉን ከማየታችን በፊት መስዋዕት አንሰዋም ፤ ያሬድ የሠራው «ክብር ይእቲ» ቀድሱ የሚል ትእዛዝ የለውም ቅኔ ነው ይላሉ ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ቢሆን በሃይማኖት ሥርዓት ልዩነትን ስለማያመጣ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ጉራማይሌ እንዳይሆን አንድ ውሳኔ መወሰን የቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነት ነው ።



ለ/ ከዓቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም የሐዋርያት ጾም ነው ። የሰኔ ጾም ይባላል ። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስ

www.ethiopianorthodox.org

ብከተ ወንጌል ከመሔዳቸው በፊት የጾሙት ነው ። ምዕመናንም እነሱን ምሳሌ አድርገው ከጲራቅሊጦስ በበነጋው ጀምረው ይጾሙታል። ይህ ጾም በሕዝቡ ዘንድ የወታደር ጾም ይባላል ። ለስብከተ ወንጌል «ዘመቻ የተዘጋጁ ሐዋርያት በጾሙት ተምሳሊት ፤ በድሮ ዘመን ወታደሮች ለዘመቻ ሲነሱ ወይም ከዘመቻ ሲመለሱ በተሳተ በተገደፈ ይቅርበለን ለማለት በቀኖና ይጾሙት ነበር ማለት ነው።ይህ ጾም በመባጃ ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል የተወሰነ ቀን የለውም አንዳንድ ጊዜ ካርባ ይበልጣል ፤ አንዳንድ ጊዜ ከሰላሳም ያንሳል ።

ሐ/ ሦስተኛው ጾም የፍልሰታ ጾም ነው (ጾመ ማርያም ይባላል) ። የፍልሰታ ጾም ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፭ ያለው ነው ። በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚተረከው እመቤታችን ያረፈችው በጥር ፳፩ ቀን ነው (በግምት በ፶ ዓ. ም. ገደማ) ። ሐዋርያት በድኗን ሊቀብሩ ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲሔዱ አይሁድ በታተኗቸው ። በዚህ ጊዜ መላእክት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በገነት አኑረውታል ። በስምንተኛው ወር በነሐሴ አስከሬኗን እንደ ገና ከጌታ ተቀብለው በጸሎትና በምሕላ ቀበሯት ። በዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አልነበረም ። በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደልጅዋ ትንሣኤ ተነሥታ ስታርግ ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ያገኛታል ፤ በዚህ ጊዜ ትንሣኤዋን ሌሎች ሐዋርያት አይተው ለእሱ የቀረበት መስሎት ተናዶ (ፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ) በፊት የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ አሁን ደግሞ ያንችን ትንሣኤ ሳላይ ቀርቼ ነው ብሎ ከደመናው ሊወረወር ቃጣው ። በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቶማስን አጽናናችው ከርሱ በቀር ትንሣኤዋን ሌላ እንዳላየ ነገረችው ። ለምስክር እንዲሆነውም ሰበኗን ሰጥታው አረገች ። ቶማስ ሐዋርያት ወዳሉበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችንን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት ። እሱም አውቆ ምሥጢሩን ደብቆ አይደረግም «ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር? » አላቸው ። ለማሳየት መቃብር ሲከፍቱ አጧት ። በዚህ ጊዜ እሱ እመቤታችን ተነስታ አርጋለች ብሎ ሁኔታውን ተረከላቸው ። ለምስክር ይሁንህ ብላ የሰጠችውን ሰበኗንም አሳያቸው ። ሰበኗን ለበረከት ቆራርጠው ተከፋፍለው ወደየሀገረ ስብከታቸው



ተበታትነዋል ። ባመቱ ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እንዴት እኛ ይቅርብን ብለው ከነሐሴ አንድ ጀምረው ሱባኤ ገቡ ። በነሐሴ ፲፬ ቀን ትኩስ በድን አድርጎ አምጥቶ ሰጥቷቸው ከቀበሯት በኋላ በ፲፮ ተነስታለች ። በዚህ ቀን ጌታ ቀድሶ እመቤታችንም በልጇዋ እጅ ቆርባለች ። (ወተቈረበት በዕደ ወልዳ) ። (ሙሉውን ታሪክ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ይመለከቷል) ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን በረከት ለማግኘት ትጾማለች ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጾም በተለይ ሕፃናቱ ያከብሩታል ። በዚህ የአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የማይጾምና የማይቆርብ ሕፃን የለም። ብዙ ሰዎች ቤታቸውን እየዘጉ በመቃብር ቤት ሱባኤ ገብተው በጾምና በጸሎት ይሰነብታሉ ። በፍልስታ ጾም ጊዜ በጠቅላላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው ሁኔታ ሕዝቡ ልጅ አዋቂ ሳይል የሚያሳየው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የፍቅር አገሯ መሆኗን ይመሰክራል ። (በሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ጾሙ የተከበረ ነው ፤ ታሪኩ ግን የእመቤታችን ዕረፍቷም ትንሣኤዋም በነሐሴ ወር ነው ይላሉ ። )

መ/ አራተኛው ጾም ጾመ ነቢያት ይባላል ።—ከኅዳር ፲፭ እስከ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ያለው ነው ። የጾሙ ወራት ፵፫ ቀን ነው ። «ልደት በታኅሣሥ ፳፱ ቀን በሚውልበት በዘመነ ዮሐንስ ቅበላው ኅዳር ፲፬ ነው ፤ ጾሙ በ፲፭ ይጀመራል ። በሌላው ግን ቅበላው በኅዳር ፲፭ ነው ፤ ጾሙ በ፲፮ ይጀመራል ። ይህን ጾም የምንጾመው ነቢያት በየዘመናቸው ስለመሲህ መምጣት በናፍቆት ይጾሙ ፤ ይጸልዩ ስለነበር የእነርሱን አርአያ ተከትለን የክርስቶስን ልደት ከማክበራችን ቀደም ብለን ይህን ጾም እንድንጾም በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተሠርቷል ። ይህ ጾም እንደ መጨረሻው በመግቢያውም ሊቃውንትን የሚያከራክር አንድ አቆጣጠር አለው ።

ባጀማመሩ ላይ (ስንክሳሩ መንፈቀ ኅዳር ስለሚል) አንዳንዶቹ ሊቃውንት የዚህ ጾም መጀመሪያው ፲፮ኛው ቀን ነው ፤ ይኸውም በዘመነ ማቴዎስ—በማርቆስ—በሉቃስ ነው ። በዘመነ ዮሐንስ ግን ልደት ወደኋላ መጥቶ በ፳፰ ቀን ስለሚውል በ ፲፭ጾሙ ይጀመራል ይላሉ ። ግማሾቹ ደግሞ «አድልው ለጾም» ነውና ባራቱም ዓመት

www.ethiopianorthodox.org

ጾሙ ፲፰ን አይለቅም ይላሉ ። በፍቅር ካደረጉት ግን የሚያከራክርና የሚያጣላ አልነበረም ።

ሠ/ አምስተኛው ጾም ገሃድ ነው ፣ ገሃድ ማለት ለውጥ ልዋጭ ማለት ነው ። ፍቹ ከዘይቤው አይገናኝም ። ወይም እንደ ዘይቤው «ግልጥ» ማለት ነው ፤ ይፋ ማለት ነው ። በገሃድ እንዲሉ ፤ በግልጥ በይፋ ሲሉ ። ገሃድ የጥምቀት ብቻ ነው ፤ ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ በሚውልበት ጊዜ በኋላው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ የፍስክ ቀን ነታቸው ወደ ጾምነት ተለውጦ ይጾማሉ ። በነሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውልባቸው የጾም ቀኖች (ረቡዕና ዓርብ) የፍስክ ቀን ሁነው ይከበራሉና ። ገሃድ የረቡዕና የዓርብ ለውጥ ነው ብለናል ። ነገር ግን በሌላም ቀን ቢውል የጥምቀት ዋዜማ ይጾማል ። ጥምቀት እሁድ ቢውል ቅዳሜ ጥሉላት አይበላም ። ሰኞ ቢውል እሑድ ጥሉላት አይበላም ። እህል ውሀ ግን አይጠምም ። አንዳንዶቹ ግን ጥምቀት ሰኞ ሲውል ከቅዳሜና ከእሑድ አዋጥተው ይጾማሉ (ቅዳሜ ስድስት ከእሑድ ሦስት)። ጥሉላት በሁለቱም ቀኖች አይቀመስም ይላሉ ፤ ነገር ግን ገሃድ አንድ ስለሆነ (ሰላም ለዕለት ዋሕድ ዘስሙ ገሃድ) 147. ሰኞ ሲውል ቅዳሜ ከጥላሉት መጾም በአጉል የገባ ልማድ ነው ። ገሃድ ለጥምቀት ብቻ ነው ፤ በልማድ ግን የልደትንም ዋዜማ ገሃድ እንለዋለን ። ነገር ግን ልደት የሚውልባቸው ዓርብ ወይም ረቡዕ የፍስክ ቀን ሁነው እንዲከበሩ ቢታዘዝም ፤ 148. በዋዜማው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስም ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ መጾማቸው የግድ ነው ። የማይጾሙ ሰዎች ግን መላውን ጾመ ነቢያት ሲበሉ ቆይተው ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ነው ብለው ይጾማሉ ።

ረ/ ስድስተኛው የነነዌ ጾም ነው ። (ነይ ነይ) ይህ ጾም የሦስት ቀን ጾም ነው ። ሰኞ ማክሰኞ ረቡዕ ። በመባጃ ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል ቁጥሩ ከአጽዋማት አዋድያት ነው ። አንድ ጊዜ በጥር አንድ ጊዜ በየካቲት ይሆናል ። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት የነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ከመዓት ከጥፋት እንደ ዳኑ ምዕ

147 ስንክሳር ጥር ፲ ቀን፤
148 ዝ.መ.



መናንም በጾምና በጸሎት ከፈጣሪያቸው ምሕረትና በረከት እንዲያገኙ በማለት ነው ። (ስለ ሙሉ ታሪኩ ትንቢተ ዮናስን ይመለከቷል) (ብሉይ ኪዳን )

ሰ/ ሰባተኛውና የመጨረሻው ጾም ረቡዕና ዓርብ ነው ። ረቡዕና ዓርብ ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ እሑድ ድረስ ከሚገኙ ረቡዕና ዓርቦች በቀር ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ ። የሚጾሙበትም ምክንያት አላቸው ።

ሀ/ ረቡዕ ፦ የአይሁድ ሸንጎ ወይም ሲንሃድሪየም ጌታን ዓርብ ዕለት ለመስቀል የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላለፈው ረቡዕ ዕለት ነው ይባላል ። መድኃኔ ዓለም ለሰው ልጆች ሲል የተወሰነበትን የሞት ውሳኔ ሁልጊዜ በማስታወስ ክርስቲያኖች በዚህ ዕለት እንዲጾሙ ታዟል ።

ለ/ ዓርብ ፦ እንደሚታወቀው ጌታ የተሰቀለበት የሞተበት ብዙ ዘመን ሲጠበቅ የነበረ ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን በጾምና በጸሎት እንዲከበር ። ታዟል ። 149. እነዚህ አጽዋማት ከሰባት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ እንዲጾማቸው ተወስኗል ። ቅዳሴ የሚቀደሰውም ከእሑድና ከቅዳሜ በቀር በጾም ወራት ከሆነ በዘጠኝ ሰዓት ነው ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች ሳይገባቸው እንደሚሉን ቅዳሴና ቁርባን ጾም ያስገድፋል ተብሎ አይደለም ። ጌታ ነፍሱን ከሥጋው የለየበትን ሰዓት ተከትሎ የተሠራ ሕግ ነው ። የምንቀበለው ሥጋ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው ። ካሣ ተፈጽሞ ሥጋው ደሙ በይፋ የተሰጠን ጌታ ነፍሱ ከሥጋው ሲለይ ነውና ። በጥንቱ ሥርዓት ግን ዛሬም በገዳማትና በታላላቅ አድባራት ይህንን ሰዓት በማክበር ከእሑድ ቅዳሜና ከበዓለ ሃምሳ በቀር መስዋዕት ዘሠርክ ነው ።

ከዚህ በላይ ከብዙ በጥቂቱ የገለጥናቸው በይፋ በትእዛዝ የሚጾሙትን የሕግ አጽዋማት ነው ። በግልና በፈቃድ የሚጾሙ ግን ለምሳሌ የጽጌ ጾም ሄሮድስ ሕፃናትን ባስፈጀ ጊዜ እመቤታችን ከልጅዋ ጋር [illegible] የምድረ ግብጽ ስደት እያስታወሱ እያሉ መነኩሳትና

www.ethiopianorthodox.org

ባሕታውያን ምዕመናንም ይጾሙታል ። ጾሙ የሚቆየው ለአርባ ቀናት ፤ ከመስከረም ፳፭ እስከ ኅዳር ፭ ነው ። በጽጌ ወራት (በአበባ) ወራት ፤ ስለሚጾም ፤ እመቤታችንም በአበባ ስለምትመሰል ጾሙም «የጽጌ ጾም» ይባላል ። ከዚህም ሌላ የዓመቱን መጨረሻ ወር ጳጉሜንን የሚጾሙ አሉ ። ታሪኩ-ዮዲት የእሥራኤልን ጠላት ሆለሆርኒስን ከመግደሏ በፊት የጾመችው ነው ይላሉ ። ዮዲት ጠላቷን ለማጥፋት የቻለችው በጾምና በጸሎት ከፈጣሪዋ ኃይል አግኝታ ነው ፤ እኛም ጠላታችንን ሰይጣንን ፈቃደ ሥጋን ድል ለማድረግ በጾም ከፈጣሪያችን ኃይልን መታጠቅ አለብን ሲሉ ምዕመናን ይጾማሉ ። ጾመ-ዮዲት እንደ ጽጌ ጾም የታወቀ አይደለም ። ምዕመናን ኃጢአታቸውን ለንስሐ አባታቸው ተናግረው ተናዘው የሚጾሙት የቀኖና ጾም አለ ። ይህን ሁሉ ያልነው ለማወቅ ያህል እንጂ በገዳም ፤ በበረሃ ያሉ መነኩሳትና ባሕታውያን ግን ከሕግ በላይ ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ ። ለጊዜው ስለ ጾም እዚህ ላይ ይበቃል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ም ዕ ራ ፍ ፰

# የአማላጅነት ትምህርት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን ድንግል ማርያም፣ የመላእክት፣ የቅዱሳን ክብርና አማላጅነት እንደ ሌሎቹ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በሰፊው የታወቀ ነው። ከመላእክትና ከቅዱሳንም በክብርም ሆነ በአማላጅነት ቅድሚያ ያላት አምላክን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። ለማንኛውም ክርስቲያን፣ ይልቁንም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለሚከታተል የሃይማኖት ሰው የድንግል ማርያም ሕይወትና የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት እንግዳ አይሆንበትም። ይህም ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሷ መወለዱና፣ መወለዱም እኛን ለማዳን ብቻ መሆኑ ከታወቀ፣ የሰውን ልጅ የመዳን ቀን ከሰው ልጆች በቅድሚያ ያወቀች፣ ለእግዚአብሔር የማዳን ሥራ መሣሪያ በመሆን አዳኙን መሲሕ የወለደች፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ የምሥጢር መዝገብ ናትና ነው። በመዳን ትምህርት (sotereology) የእመቤታችን ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር የተዋሐደ ነው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ሆና ትከበራለች። በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴያችን ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንዘምረው የድንግል ማርያምን ውዳሴ ነው። አምላክ ሰው በመሆኑ ለሰው ልጆች የዋለውን ውለታ፦— ስደቱን፣ መንከራተቱን፣ ስቅለቱንና ሞቱን በምናስታውስበት ጊዜ ድንግል ማርያምን ለመለየት አይቻልም። ወልዳ ያስገኘች ናት፣ አዝላ የተሰየደደች ናት፣ በማስተማር ጊዜው አብራ ተንከራትታለች፣ በተሰቀለበት ዕለት ከመስቀሉ ሥር አልተለየችም፣ ይህ ሁሉ የሚያሳየው እመቤታችን የሰውን ልጆች ለማዳን ከተዋረደው አምላክዋ ጋዞ አለመለየቷን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ከአዲስ ኪዳን ቀደም ብሎ ስለ እመቤታችን ክብርና ልዕልና በነቢያት የተነገሩ ትንቢቶች እያሌ ናቸው ። ከነሱም አንድ ሁለቱን ለመጥቀስ ያህል 150. አምላክን የወለደችውም በነያት ተነግሮላት ነው ። 151. በአዲስ ኪዳንም ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በቀርበመላእከት ቃል፥— « ቡርክት አንቲ እምአንስት ፤ ተፈሥሒ ፍሥሕት፤አ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ» ተብሎ የተመሰገነ አል ነበረም ። 153. እርሷም ፥— « ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ» 154. ከእንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብላ በተናገረችው መሠረት በልጅዋ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያ ዘውዳችን ፤ ጥንተ መድኃኒታችን ፤ የንጽሕና መሠረታችን ድንግል ማርያም ናት እያሉ ይዘምራሉ ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለ እመቤታችን አማላጅነት የምትሰብከው የምታስተምረው ፍጹም በሆነ ሐዋርያዊ ትውፊት ነው ። እመቤታችን ድንግል ማርያም ከሰው ወገን፤ የሰው ችግር ቶሎ የሚገባት ቶሎ የሚታያትና የሚሰማት ርኅርኅት ናት ። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል 154. ያለውን ምንባብ ብንመለከት ፤ ሠርግ ደግሰው ተጋባዥ ጠርተው ተጋባዡ ሕዝብ በመጋበዝ ላይ እንዳለ ድግሳቸው በመቋረጡ ደጋሾቹ አፈሩ ። የሰዎቹ ችግር ቶሎ ገብቷት ለልጅዋ ነገረችው ከዚህም አስከትላ ልጇ ያዘዛችሁን ሁሉ አድርጉ ብላ አሳላፊ ለነበሩት ሰዎች ምክር ሰጠቻቸው ። ልጅዋም የእናቱን አማላጅነት ተቀብሎ አሳላፊዎቹን ውኃ እንዲቀዱ አዘዛቸው ፤ አሳልፊዎችም የእመቤታቸውን ምክር ሰምተው የጌታቸውን ትእዛዝ ስለፈጸሙ የሠርጉ ቤት ከሀፍረት ድኗል ። ይህ አስደናቂ ተአምራት ሊደረግ የቻለው በእመቤታችን አማላጅነት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ፤ ምዕመ

150. መዝ. ፵፬ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ፡ ፻፳፤
151. ኢሳ. ፯ ፡ ፲፬ ፤
152. ሉቃ. ፩ ፡ ፳፰ ፡ ፴ ፡ ፴፭ ፤
153. ሉቃ. ፩ ፡ ፵፰ ፤
154. ዮሐ. ፪ ፡ ፩—፲



ናን ከዚህ ሕይወት ሲለዩ በዚህም በሚያልፈው የሕይወታቸው ጉዞ ለሚደርስባቸው ችግር ሁሉ እመቤታችን በአማላጅነት እንደማትለያቸው የታመነ ነው ። ፻፶፭ በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል፥— « ነዋወልድኪ ነያ እምከ» (እነሆ ልጅሽ እነሆ እናትህ) ብሎ አደራ በሚሰጥ ሰው ቋንቋ ጌታ የተናገረው ቃል እናቱ ድንግል ማርያም ከርሱ በቀር ሌላ ልጅ እንዳልነበራት ከማሳየቱም ሌላ ምሥጢራዊ አደራው ፤ እናቱን ለቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንንም ለእናቱ ደራ መስጠቱ ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን አደራ ስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ጠብቃ በእመቤታችን ስም እየተማፀነች ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ታካሒዳለች ። እመቤታችንም በተሰጣት አደራ የቤተ ክርስቲያን ጉዞ የተሳካ እንዲሆን ልጅዋን ወዳጅዋን በየጊዜው ትለምነዋለች ፤ ታስታውሰዋለች ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም የርኅራኄ ምንጭ ናት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትና ለአራዊት እንኳ ታዝናለች ትራራለች ። ፻፶፮ ስለ እመቤታችን ርኅራኄ የሚተረክ አንድ ታሪክ አለ ። እመቤታችን አንድ ቀን በሕጻንነት ዕድሜዋ ከጓደኞቿ ጋር ሁና ውሀ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ወረደች ፤ በውኃው ዳር እንዳለች ውኃ የጠማው ውሻ እየሮጠ መጣ ፤ በዚህ ጊዜ ጓደኞቿ ያን የተጠማ ውሻ ሲያባርሩት እርሷ ፍጹም ርኅራኄን የተመላች ስለሆነች ማጠጫ ዕቃ እንኳ ብታጣ ጫማዋን አውልቃ የተጠማውን ውሻ በጫማዋ ውሀ ማጠጣቷ ይነገራል ። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ደራሲ የሚከተለውን ተናግሯል ።—

ሴስይኒ ማርያም ለጸማድኪ ዐሳብ ፤
ኀብስተ አእምሮ ሠናይ ወወይነ ጥበብ ፤
እመኒ ፈድፈደ ኃጢአትየ እምሕዝብ ፤
ተዘከሪ እግዝእትየ በርኅራኄኪ ዕጹብ ፤
ከመ አስተይኪዮ ማየ ለፅሙዕ ከልብ ፤

155. ዮሐ. ፲፱ ፡ ፳፮
156. ነገረ ማርያም (Mareology ተመልከች

www.ethiopianorthodox.org

ማርያም ሆይ ምንደኛ አገልጋይሽን ፥
መልካም ዕውቀት ኀብስትንና ጥበብ ወይንም መግቢኝ ፤
ኃጢአቴ ከሕዝብ ኃጢአት ቢበዛም ፥
እመቤቴ በአስደናቂ ርኅራኄሽ ፥ ለተጠማው ውሻ ውሀ ማጠጣትሽን አስቢ ነው የሚለው ደራሲው ። በጸሎቱ የገለጠው የራሱን የኃጢአት ብዛትና የእመቤታችንንም አስደናቂ ርኅራኄ ነው ። ምንም ኃጢአቱ ቢበዛ ለውሻው እንኳ ርኅራኄ ያደረገች ድንግል ለሱም የምሕረት ጥላዋን እንድትጥልበት ከፈጣሪው ጋር የሚታረቅበትን መንገድ እንድታሳየው ልመናውን አቅርቧል ።

ስለ እመቤታችን ውዳሴና ክብር ፥ እንዲሁም የአማላጅነት መብት ብዙ መጻሕፍት በብዙ ሊቃውንት ተጽፈዋል ። ስለ አማላጅነቷም እያሌ ሊቃውንት ብዙ አስተምረዋል ። በልጅዋ ያመኑ ምዕመናን ሁሉ ውዳሴዎቿንና ቅዳሴዎቿን በማንበብና በመጸለይ አማላጅነቷን ይማጠናሉ ፤ የእናት አማላጅ ፊት አያስመልስ ፥ አንገት አያስቀልስ ነውና በእመቤታችን በድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ይሠራሉ ፤ በዐሎቿን ያከብራሉ ፤ ዝክር ይዘክራሉ በስሟ ይሠየማሉ (አሥራተ ማርያም ፥ ገብረ ማርያም ፥ አስካለ ማርያም ፥ አመተ ማርያም እያሉ ባጠቃላይም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ፥—መመኪያ አክሊላችን ፥ ጥንተ መድኃኒታችን ፥ የንጽሕና መሠረታችን ድንግል ማርያም መሆኗን ያውቃሉ። አማላጅነቷም የታመነ ነው ።

<u>የመላእክት ክብርና ምልጃ፡</u>—ከላይ እንደ ተገለጠው የምልጃ ትምህርት ሐዋርያዊ ውርስ (apostolic succession) ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የታወቀና የሚሠራበትም ነው ። መላእክት ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው ። በእግዚአብሔርም ፊት በባለሟልነት የሚቆሙ ናቸው ፤ 157. የእግዚአብሔርን ኃይል ለመግለጥ የሚላኩ ናቸው ፤ 158. የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ ለሰው

167. ሉቃ. ፩ ፡ ፲፱፤
168. ኢያ. ፭ ፡ ፲፫—፲፭ ፤



ልጅ የሰውን ልጅ ትሩፋትና ማንኛውንም በጎ ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡ ናቸው ፤ 159. ከዚህም ሁሉ ጋር በክርስትና ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ምሥጢር ተካፋዮችና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው ። በመጀመሪያ አምላክ ሰው ሊሆን ነው ብሎ የምሥራች የተናገረ የእግዚአብሔር መልአክ ነው ። 160. በተወለደም ጊዜ የዓለም መድኃኒት ተወለደ ብሎ መጀመሪያ ለሰው የሰበከው መልአክ ነው ። 161. የሕፃኑን መሲሀ ሕይወት ለማጥፋት እነ ሔሮድስ ያጠመዱትን ወጥመድ በመግለጥ ፥ ድንግል መቤታችንና ዮሴፍ ወደ ምድረ ግብጽ እንዲሸሹ ያደረጉ መላእክት መሆናቸውን ቅዱስ መጽሐፍ መዝግቦታል ። 162.

ክርስቶስ ወዶ ባደረገው አትሕቶ ርእስ በዲያብሎስ ተፈትኖ ሦስቱን አርዕስተ ኃጣውእ ድል ባደረገ ጊዜ የድል አድራጊነቱ ምልክት የሆኑት መላእክት መጥተው አገልግለውታል ። 163. የማስተማር ጊዜውን ፈጽሞ ለሰው ልጆች መስዋዕት ለመሆን ወደ መስቀል በሚመጣበት ጊዜ ሊፈርድበት ለተቀመጠው ለጲላጦስ ፤ እንግዳ የሆነ አስደንጋጭ ነገር ነግሮታል ፥—«እኔ ከፈለግሁ ካንተ ፊት እንዳልቆም ለማድረግ የሚችሉ መላእክትን ለማዘዝ እችላለሁ 164. በመስቀል ከተሰቀለና ከሞተ በኋላ በመቃብሩ ዙሪያ የተገኙና የትንሣኤውንም የምሥራች ለሰው ያሰሙ መላእክት ናቸው። 165. ጌታ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ወደ ሰማያዊ ክብሩ በተመለሰበት ዕለት እንጋጠው ሰማይ ሰማይ እያዩ ያለቅሱ የነበሩ ሐዋርያትን አጽናንተው ዳግመኛ መምጣቱንም ነግረዋቸዋል ። 166. መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የክርስቶስን ትንሣኤ ለመመስከር ይሯሯጡ የነ

159. ዋ. ሥ. ፲ ፡ ፫— ፤ ዕብ. ፩ ፡ ፲፬ ፤
160. ሉ. ፩ ፡ ፳፮—፴፱ ፤
161. ሉቃ. ፪ ፡ ፰—፲፬፤
162. ማቴ. ፪፤ ፲፫ ፤
163. ማቴ. ፬ ፡ ፲፩ ፤
164. ዮሐ. ፲፰ ፡ ፴፮ ፤
165. ማቴ. ፳፰ ፡ ፩—፰ ፤ ማር. ፲፮ ፡ ፩—፯ ፡ ሉቃ.፳፬፡፩—፲፤ዮሐ.፳፡፲፩—፲፫ ፤
166.

www.ethiopianorthodox.org

በሩ ሐዋርያትን ይረዷቸው የነበሩ መላእክት ናቸው ወህኒ ቤት ከፍቶ እግረ ሙቅ ፈትቶ በማውጣት አይዟችሁ በማለት ፩፻፷፯ ሰማዕታት የዐላውያን ነገሥታትን ግርማ እንዳይፈሩ የሚያበረታቱ ጻድቃን ግርማ ሌሊትን ድምጸ አራዊትን ጸብአ አጋንንትን እንዳ ይሰቀቁ የሚያደርጉ መላእክት ናቸው ። በመጨረሻም በፍርድ ቀን ጌታን ተከትለው ይመጣሉ ። የእግዚአብሔርንም ምርጦች ከአ ራቱ ማዕዘን ይሰበስባሉ ። ፩፻፷፰

ስለዚህ ሁሉ ነገር የመላእክት አገልግሎት የእግዚአብሔርን አምልኮት ለምትመሠክር ለቤተ ክርስቲያን ኃይል ድጋፍ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን መላእክትን ታከብራቸዋለች ፤ በአማላጅነታቸ ውም ትማጠናለች ። ድርሳናቸውን በማጻፍ ከፈጣሪያቸው እየተ ላኩ ያደረጉትን ተአምራት ሁሉ መዝግባ በማንበብና በመጸለይ ለመላእክት ያላትን አክብሮት ትገልጣለች ። በዐላትን በቀኖናዋ ወስና ዛሬ በዓለ ሚካኤል ነው ፣ ዛሬ በዓለ ገብርኤል ነው ፣ እያ ለች በዓላቸውን ታከብራለች ፣ ዝክር ማኅበር ትዘክራለች በስማ ቸው መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን ትሠራለች ። ልጆቿን በስማቸው ትሠይማለች ። በቤተ ክርስቲያን የምዕመናን ሕይወትና የመላእክት አገልግሎት የተሰናሰለ ነው ።

<u>የቅዱሳን ክብርና ምልጃ ቤተ ክርስቲያን፡</u>— ቅዱሳን በገድል ብዙ ክፍል አላቸው ። እስከደም ጠብታ ድረስ ለክርስቶስ የመሠ ከሩ ሰማዕታት ቅዱሳን ናቸው ። አንቀጽ አውጥተው መጽሐፍ አል በው መናፍቃንን ተከራክረው የረቱ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ያስ ጠበቁ ፣ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች (apologaties) መምህራንም ቅዱሳን ናቸው ፤ ከጣዕመ ዓለም ተለይተው ክርስቶስ ለሞተለት የሰው ዘር እየጸለዩና ፈጣሪያቸውን እየማለዱ በበረሀ ድምጸ አራ ዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሰው ሕይወታቸውን ያሳለፉ አበው ጻድ ቃን ቅዱሳን ናቸው ። እነዚህ ሁሉ ሥራ የተለያየ ድርሻ ቢኖራ

167. የሐ.ሥ. ፭፡፲፱፤፲፪፡፯—፲፩ ።
168. ማቴ.፳፬፡፴፩ ።

www.ethiopianorthodox.org



ቸውም ዓላማቸው አንድ ነው ፤ አገልግሎታቸውም ለቤተ ክርስቲ ያን ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንም መታሰቢያቸውን ታከብራለች ምሳሌነታቸውን በመግለጥ ሌሎች አማኞች እነሱን እንዲመስሉ ታስተምራለች ፤ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ትሠራለች ። የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን የምታከብረውና በአማላጅነታቸውም የምታምነው ቅዱሳት መጻሕፍትን ትውፊተ አበውን ተመርኩዛ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን ስለ አማላጅነት የምታስተምረውን ትምህርት አንዳንድ ሰዎች የተሳሳተ ትርጉም ይሰጡታል ። እምነታችን ድንግል ማርያም መላእክትና ቅዱሳን ያማልዳሉ ማለት እግዚአብሔርን መድፈርና ጻድቅነቱን ማቃለል እምልኮቱንም መቀነስ ይመስላቸዋል።እነዚህ ሰዎች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ወደ ፕላቶን አስተሳሰብ የተጓዙ ናቸው ። ፕላቶን ከክርስ ቶስ በፊት የነበረ የግሪክ ፈላስፋ ነበር ። እሱ በአረማዊ አስተሳ ሰቡ እግዚአብሔር ከፍጡራን የተለየ የማይታወቅ ነው ይል ነበር ። በፕላቶን አስተሳሰብ እግዚአብሔር የማይታወቅ የማይመረመር ስለሆነ ሰው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ሁሉ ትዝት ነው ። ሰውና እግዚአብሔር ምንም ግንኙነት የላቸውም ይላል ። በክርስ ትና ትምህርት ግን እግዚአብሔር ሰው ሆነ በሰው ቋንቋ ተናገረ ፤ ከኃጢአት በቀር እንደ ሰው ኖረ ። የማይታየው ታየ ፤ የማይታወ ቀው ተገለጠ ። በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ግንኙነት በፈጣሪና በፍጡር በገዥና በተገዥ ዓይነትና ሥርዓት ብቻ ሳይሆን የቤተ ሰብነትና የዝምድና ግንኙነት ተጀመረ ፤ 169. በምልጃ ትም ህርታችንም ውስጥ የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ለማቃለል እምልኮቱ ንም ለመቀነስ ሳይሆን እሱ ወደ በሰጠን የቤተ ሰብነት ዝምድና ለመጠቀም ነው ። ወደሱ ለመቅረብ የምንጠቀምበትን ቋንቋ እሱ ያውቀዋልና ። ሰውን ለማዳን የተደረገውን የእግዚአብሔር ስንፍና ባይመለከቱ በሕገ ጠባይአዊ (Rationalism) ብቻ የክርስትናን ትምህርት ለመረዳት አይቻልም ። ሰውን ለማዳን የተደረገው የእ ግዚአብሔር ስንፍና ከሰው ጥበብ ይበልጣልና ። 170.

169. የሐዋ.ሥ.፲፯፡፳፰—፳፱ ።
170. ፩ቆሮ.፩፡፳፭

## ምዕራፍ ፱ ፤

# የቤተ ክርስቲያን አሠራርና ክርስቲያናዊ ትውፊት ፡—

ሀ/ የቤተ ክርስቲያን አሠራር (ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሦስት ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አሠራር አለ ።

ከነዚህም አንዱ እንደ ብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ (ምኩራብ) ቅርጽ ሰቀልማ ወይም ሞላላ ቅርጽ ነው ። የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተ መቅደስና ኋላም በዘመነ ክርስትና ታላቁ ቆስጠንጢኖስና እናቱ ዕሌኒ በኢየሩሳሌምና በቤተ ልሔም ካሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት የተቀዳ ነው። ለምሳሌ ያህል የደብረ ዳሞ የአክሱምና በደብረ ሮሐ የሚገኙ የላሊበላ ሕንፃዎች ብዙዎቹ ሰቀልማ ናቸው ። ይህ ሰቀልማ ቅርጽ ቤተ ክርስቲያን በመጋረጃ ወይም በአዕማድ እንጂ በግንብ የተከፋፈለ አይደለም ። የንዑስ ክርስቲያን ፣ የፍጹማን አማንያንና ቀኖው መን በር ያለበት ቦታ የተለየ ነው ። የሰቀልማ ቤተ ክርስቲያን ጉልላቱ አንድ ብቻ አይደለም ። እንደ ትልቅነቱ ነው ፣ ለምሳሌ ፡— አፄ ዮሐንስ አራተኛ ያሠሩት የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ሰቀልማ ሁኖ ፲፰ ጉልላት ነበረው ይባላል ። የሰቀልማ ቤተ ክርስቲያን በሩ የተወሰነ አይደለም ፤ ሦስትም አራትም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል ። ይህ የሰቀልማ አሠራር በሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (የቢዛንታይን ቅርፅ ወይም ባሲሊከ) ይሉታል ።

ሁለተኛው ቅርጽ ዙሪያው ክብ ነው ። ቤተ ንጉሥ ቅርፅ ይባላል ። በግድግዳ ከሦስት ይከፈላል ፤ የመጀመሪያው ዙሪያ ፤



ክፍል) ቅኔ ማኅሌት ይባላል ። ስያሜው ከግብሩ የተወረሰ ነው።
መዘምራን ፡ ደባትር ስብሐተ እግዚአብ ፡ ማኅሌተ እግዚአብ
ሐር የሚያደርሱበት ነውና ፣ በዚሁ ክፍል በሰሜኑ አፍዛዣ ቀሳ
ውስትና መነኮሳት በመንፈቀ ሌሊት ፣ በነግህ ሰዓታት የሚቆሙ
በት ፣ ኪዳን የሚያደርሱበት ክፍል አለ ። በጥንት የቤተ ክርስቲ
ያን ሥርዓት ፣ ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸመው በዚሁ ክፍል ነበር
ለጥምቀት ፣ ለቁርባን ገና ያልበቁ በትምህርት በንስሐ የሚፈተኑ
ሐዲሳን አማንያንም (ንዑስ ክርስቲያን) ዲያቆኑ ፃዑ ንዑስ ክርስቲ
ያን እስኪል ድረስ በዚህ ይቆያሉ ። ዲያቆኑ ፃዑ ንዑስ ክርስቲያ
ብሎ ድምጹን በደወል ሲያሰማ ግን ወደ መካነ ቀናናቸው ተመል
ሰው ይሔዳሉ ። ዛሬ ግን መላው ምዕመናን ቆመው ይጸልዩበታል፤
ሲገቡ ወደቀኝ የሚገኘው ክፍል የሴቶች መቆሚያ ነው ። የሚለ
የውም በመንጠላዕት ነው (መጋረጃ) ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥር
ዓት ወንድና ሴት አብረው ቆመው አይጸልዩምና ፣ ሦስት በር አለው
ምሥራቅ ፣ ምዕራብ ፣ ደቡብ ። ሁለተኛው ክፍል ቅድስት ይባላል
ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው ። የቤተ ክር
ስቲያኑ ማዕከላዊ ቦታ ነው ፤ የኤጲስ ቆጶሱ መንበር በዚሁ ውስጥ
ነው ። በጥንቱ ሥርዓት ለቁርባን የተዘጋጁ ምዕመናን ቆመው
የሚያስቀድሱበት ነው ፡— አራት በር አለው ። ምሥራቅ ፣
ምዕራብ ፣ ሰሜን ፣ ደቡብ ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል መቅ
ደስ ነው ። እንደ ብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን ፣ የዚህም ስያሜው
ከብሉይ ኪዳን የተወረሰ ነው ። በዚህ ውስጥ ሥጋውና ደሙ የሚ
ፈተትበት መንበረ ታቦቱ ሌሎችም ንዋያተ ቅዱሳት ይገኛሉ ።
የኤጲስ ቆጶሱ ማስቀደሻ ልዩ መንበር በዚሁ ክፍል ይገኛል ። ወደ
ዚህ ክፍል ለመግባት የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው
መቅደስ ሦስት በር አለው ። ምዕራብ ፣ ደቡብና ሰሜን ፤ እያንዳ
ንዱ በር መንጠላዕት (መጋረጃ) አለው ። የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስ
ቲያን ባለ አንድ ጉልላት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ በጉልላቱ ላይ ምሳሌነት ባለው በተወሰነ ቁጥር የሰጐን ዕንቁላል ይሰካበታል ። ቁጥሩ፤ሦስት ፥ አምስት ፥ ስድስት ፥ ሰባት ወይም አሥራ ሁለት መሆን አለበት ። ሦስት ቢሆን የምሥጢረ ሥላሴ አምስት ቢሆን ጌታ የተቸነከረባቸው አምስት ቅንዋት ፥ ስድስት ቢሆን የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ፥ ሰባት ቢሆን የሰባቱ ምሥጢራት አሥራ ሁለት ቢሆን የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው ። ምሳሌነት ብቻ ሳይሆን ምሥጢርም አለው ። ሰጐን ጫጩቶቿን የምትፈለፍለው እንደ ሌሎች ወፎች በመታቀፍ አይደለም ተባዕቱም ሆነ እንስቲቱ ሰጐን ዕንቁላሉን ትክ ብለው ይመለከቱታል ፤ ዕንቁላሉም ነፍስ ዘርቶ ይፈለፈላል ፥ ለጥቂት ፊታቸውን ቢመልሱ ግን እንቁላሉ ገምቶ ይቀራል ። በእግዚአብሔርና በምዕመናን መካከል ያለው ግንኙነትም እንደዚህ የረቀቀ ነው ። ምዕመናን በጸሎታቸው ጊዜ ሕሊናቸውን በተመስጦ ወደ እግዚአብሔር ፊት ካቀረረቡ የጸሎታቸውን ፍሬ ያገኛሉ ፤ ወዲያና ወዲህ ካወላወሉ ግን ከንቱ ድካም ነው ። ለማለት ምዕመናንን በስዕል ለማስተማር ነው ። ፩፻፶ ።

ሦስተኛው ትርጽ ፥ ቀኝ ነው ፤ የቀኝ ቤተ ክርስቲያን በሩ አንድ ብቻ ነው ። ቅኔ ማኅሌት ፤ ቅድስትና መቅደሱም የሚለየው በመጋረጃ ብቻ ነው ። ላሊበላ ሠራቸው ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ቀኞች ናቸው ። የቀኝ ቤተ ክርስቲያን ጉልላት የለውም ።

የመቅደሱም በር አንድ ነው እስከዚህ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ አውስተናል በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሌሎች አያሌ ቤቶች አሉ ። በቤተ ክርስቲያኑ በምሥራቅ በኩል ዲያቆናቱ ለመስዋዕት የሚሆነውን ኅብስት የሚያዘጋጁበት ቤት አለ ፤ ይህም ቤት «ቤተ ልሔም» ይባላል ። ስያሜው የተወሰደው ጌታ በተወለደበት በቤተ ልሔም ዘይሁዳ ምሳሌ ነው ። ምሥጢሩና ቁምነገሩ

150. "Precious Pearl, Chap. LV".



ደግሞ ዲያቆናት ኅብስቱን በቤተ ልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመስዋዕት መቅረቡ በቤተ ልሔም የተወለደው በጉልጐታ ለመስዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይኸ ነው ለማለት ነው ። መቅደስ የጐልጐታ ምሳሌ ነውና ።

የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጥበት ሕንፃም በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ይኖራል ። ይህም ዕቃ ቤት ይባላል ። በገጠር ግን የአብያተ ክርስቲያናት ንዋያት የሚቀመጠው በገበዙ ቤት ነው ። ቅዳሴና ፍትሐት ባለበት ቀን ሰሞነኛው ዲያቆን ንዋየ ቅድሳቱን ባትግዳ ተሸክሞ ያመጣል ። ይህንንም ጋዜና ይሉታል ። (እትግዳውን) ለመስዋዕት የሚሆነው ስንዴ (መገበሪያ) የሚሰየምበት የሚደቀቅበት ወይም የሚፈጭበት በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ይኖራል ። ቤተክርስቲያኑ ገጠር ሆኖ ዕቃ ቤት ባይኖረውም የመገበሪያ ቤት ግን እንዲት ጐጆም ብትሆን መኖር አለባት ። ግብር ቤት ይሉታል።ስንዴው መገበሪያ ተብሏልና ፤ መፍጨቱ ደግሞ መሰየም ይባላል ይህ የልዑካኑ ቋንቋ ነው ።

ከነዚህ ከሦስቱ ሕንፃዎች ሌላ ማለት ከቤተ ልሔሙ ፤ ከዕቃ ቤቱና ከመገበሪያ ቤቱ ሌላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥርዓት ምዕመናን ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አጽማቸው የሚያርፈው በሰበካቸው በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ባንዳንድ የምዕመናን መቃብር ላይ ቤት ይሠራበታል ። ከዚያ በኋላ የቤተ ሰብ መቀበሪያ ይሆናል ። በዚህ መቃብር ቤት እንግዳ ያድርበታል ። ባሕታውያንና መነኮሳት ይኖሩበታል ። የቀድሞ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ሲያስተምሩና ሲማሩ የኖሩ እንደነዚህ ባሉ የመቃብር ቤቶች ውስጥ ነበር ። ካህናት መከፈልት የሚበሉበት ደጀ ሰላምና የሰንበቴ ቤቶችም በዚሁ ውስጥ ይገኛሉ ። አሁን ግን በቤተ ክርስ
ቲያን ቅጥር ግቢ የሚገኙ ቤቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም ።

የማጥመቂያ ቤት ፤ የሰበካ ጉባኤ ጽ/ ቤትና ሌሎችም የወጣቶች መሰብሰቢያ አዳራሾች ይኖራሉ ። ለወደፊቱም ካህናት የሚሰ

www.ethiopianorthodox.org

ለኖሩባቸው የተግባረ ዕድ መማሪያ ቤቶች በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ውስጥ እንዲኖሩ ያስፈልጋል ።

ለ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውንና ጠብቃም ያቆየችቻውን የሐዋርያት ትውፊቶች እንደሚከተለው ይመለከቷል ።

በመጀመሪያ በቅዱሳት መጻሕፍት በሐዲስ ኪዳን እንደ ተገለጠ ፤ ፩፻፶፩ በቤተ ክርስቲያንም ታሪክ እንደ ተመዘገበው የመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ከሐዋርያት ጋር በነበሩበት ጊዜ ጥሪት ቁሪታቸውን ፤ ርስት ጉልታቸውን እየሸጡ እያመጡ ለሐዋርያት ያስረከቡ እንደነበር ፤ ተገልጧል ። የሚመገቡትም ባንድነት ነበር ፤ ይህም የአንድነት ምግባቸው ፍቅር ይባል ነበር (AGAPE) በፍቅር ሆነው የሚመገቡት ስለሆነ ፤ በዚህ አኳኋን በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ የመደብ ልዩነት ሳይኖርባቸው አንዳንድ ልብ መካሪ ፤ አንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ይኖሩ ነበር ማለት ነው ። ምዕመናን እየበዙ ሲሄዱና ቤተ ክርስቲያንም ከእሥራኤል ምድር ወጥታ ወደምድረ ለሕዛብ ጉዞዋን ስትጀምር ፤ በአሕዛብ አገር ያሉ ክርስቲያኖችም የዚሁኑ ዓይነት ሥርዓተ ማኅበር አቋቋሙ ። ገንዘብ እያዋጡ በኢየሩሳሌም ላሉት ምስኪናን ለሚባሉት የሃይማኖት ወንድሞቻቸው ይልኩ ነበር ። ለመጀመሪያውና ለሁለተኛው መቶ ክፍለ—ዘመን የክርስቲያኖች ሕይወት ይህን የመሰለ ገጽታ ነበረው ።

ከሦስተኛውና ከአራተኛው መቶ ክፍለ—ዘመን በኋላ ግን ክርስቲያኖች እየበዙ ሲሄዱ ከላይ የተገለጠው የኑሮ መልክ ተለወጠ ፤ የክርስቲያን ቤተሰቦች በየቤታቸው በቁሪት ሥርዓት መተዳደር ጀመሩ።

ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የአባቶቻቸው ኑሮ ጨርሶ ትዝታው ስላልጠፉቸው ጌታ በሞቱ ሞትን ድል አድርጐ በተነሳባት

151. ቀዳ. ቆሮ. ፲፩፡፳—፴፬ ፤ ፲፮ ፡ ፩ ። የሐዋ. ሥራ. ፪፡፵፭—፵፯ ፤ ፬ ፡ ፴፪ ፡ ፭ ፡ ፴፮፡ ፴፭ ፡ ፪ ፡ ፮ ።



ዕለት በዕለተ—ሰንበትና የሃይማኖት አርበኞች ወንድሞቻቸው ሳይፈሩ ሳያፍሩ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት መስክረው በዓላውያን ሸንጎ የተሰየፉበትን ዕለት መታሰቢያ በሚያከብሩበት ዕለት ሁሉም ቤቱ ያፈራውን እያመጣ ከጸሎቱ ፍጻሜ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ገረገራ ውስጥና በየምዕመናኑ ቤት እየተሰበሰቡ ከጸሎተ ቅዳሴ በኋላ የአንድነት ማዕድ ይሳተፉ ነበር ። ይህ ዓይነቱ የክርስቲያኖች ትውፊት ከላይ እንደ ገለጥነው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ (አጋፔ) እየተባለ በብዙ ቦታ ይነገራል ። ይኸው ክርስቲያናዊ ትውፊት ቀስበቀስ መልኩን እየለወጠ ሔዶ ዛሬ በሌሎቹ የክርስቲያን ዓለማት በመረቀት ላይ ብቻ ሰፍሮ ነበርን ይዞ ቀርቷል ። በኛ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን እስካሁን ድረስ ይሠራበታል ።

ሀሳባችንን ግልጥ ለማድረግ ስለቤተ ክርስቲያናችን ዕድሜ ለሚጠይቀን ሁሉ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የምንሰራባቸውን በየሳምንቱ እሁድ በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት የሚፈትተውን ጸሪቀ መበለት ፤ ተዝካረ ሰንበት ፤ ዝክር ፤ ተዝካርንና ማኅበርን ምስክር አድርገን እናቀርባለን ።

ሀ/ ጸሪቀ መበለት ሴቶች መነኰሳይያት ወይም ወንዶች መነኮሳት በሰበካቸው በየሳምንቱ ዓርብ አቅማዳቸውን አንግበው መጻጒያቸውን ነጥቀው በመንደሩ እየዞሩ ስለ ሰንበት እያሉ ይለምናሉ ። ባለቤቲቱ ድምጻቸውን ስትሰማ በእጅዋ አልግ የሰለቀችውን ዱቄት (ዛሬ ግን የሚፈጨው በመኪና ነው) ታፍና ትሰጣቸዋለች ። እንደዚህ እያደረጉ ሰብስበው ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ከጸሎትና ከምህላ ጋር ሲጋገሩ ሲያነባብሩ ያድሩና እሁድ ማለዳ ከቅዳሴ በፊት የጋገሩትን በእንቅባቸው ተሸክመው ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ ። ጸሎተ ቅዳሴው ሲፈጸም ፤ የቀደሰው ቄስ ወይም ከአረጋውያን ቀሳውስት አንዱ መጥቶ በጸሎት ይባርከዋል ። (ይፈትተዋል ። ምዕመናኑ ተራቸውን ይዘው እንደተቀመጡ መነኩሲቷ እደገድገው ፥— «በረከተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያሉ ያድላሉ ።ምዕመ

www.ethiopianorthodox.org

ናንም፣—«ይምጻእ በረከት አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያሉ ተቀ ብለው ይላኩታል (ይበሉታል)።በቤት ከሚቀረጠው ሙግ ይልቅ ይጣፍ ጣል ይስማማል ፤ ረድኤትም አለው ። ለሁሉ ይደርሳል፤በፍቅር በእግ ዚአብሔር ስም የሚደረግ ነው ። ከዚህም ጋር ድሀ ባለጠጋ ሳይባል አንድ ላይ ሁነው የሚሳተፉት ስለሆነ ፤ ምዕመናኑን የአንድ የክር ስቶስ አባል መሆናቸውን የሚያስረዳ ምሥጢር አዘል ትምህርት አለ ው ። ለምን ጸሪቀ መበለት ተባለ ጸሪቀ መበለት የተባለው ስያሜ ከወንጌል የተወሰደ ነው ። 152. ምሳሌነቱ በወንጌል የተመዘገበ ችው ያች አርጊት ድሀ መበለት ለእግዚአብሄር ያላትን ፍቅር ለመ ግለጥ በየዋህ ልቡና በትሑት ሰብእና ሁና ፤ ያኑ ያላትን የመጨረሻ ሀብቷን (እሱውም ለምና ያገኘችው ሳይሆን አይቀርም) እንዲት ቤሳ እንደሰጠች መነኮሳይያትም (መነኮሳት) ለምነው ለእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ የሚያቀርቡት ስለሆነ ፤ ጸሪቀ መበለት ይባላል ። እግዚአብሔር የወደደው፤ እግዚአብሔር የመረጠው ከብዙ መብዓ ያበለጠው መብዓ ማለት ነው ።

ለ/ ተዝካረ ሰንበት (ሰንበቴ) ፤ ተዝካረ ሰንበቱ ወይም ሰንበቴው ደግሞ በዕለተ እሑድ በየሳምንቱ ምዕመናኑ በየሰበካቸው ሳምንታ ቱን ተከፋፍለው ፤ ካላቸው እየከፈሉ በመደገስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው መጥተው አስባርከው ፤ ድሀና ሀብታም ሳይባባሉ አብረው ይሳተፉታል ። 153.

ሐ/ ከዚህም ጋር ማለት ይህን የሚመስል ባመት አንድ ጊዜ እያንዳንዱ ምዕመን በጌታና በእመቤታችን ፤ በመላእክት ፤በቅዱሳንና በሰማዕታት ስም በዓላቸው በሚከበርበት ዕለት ደግስ ደግሶ ድሀ ሀብታም ሳይል ብድራት ሳይሻ ሁሉንም ጠርቶ ይጋብዛል ። ይህም ዝክር ይባላል ።
መታሰቢያ ማለት ነው ። 154.

---

152. ማር. ፲፪ ፡ ፵፩—፵፬ ፤
153. ቀኖ. ቀር. ፲፩ ፡ ፲፭—፳፪ ፤
154. ማቴ. ፲ ፡ ፵—፵፪ ፤



መ/ ማኅበር የሚባለው ደግሞ በወር በወሩ ምዕመናን ተራ ገብተው እየደገሱ አብረው የሚሳተፉት ነው ። ይኸውም ላንድ ምዕመን ባመት አንድ ጊዜ ይደርስበታል ። ማኅበሩ የሚደረገው በጌታ ፤ በእመቤታ ችን ፣ በመላእክትና በጻድቃን ፤ በሰማዕታት የመታሰቢያ ዕለት ነው ። ይህ ማኅበር በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ብዙውን ጊዜ ደግሞ በየምዕ መናኑ ቤት በየወሩ ይደረጋል ። እነዚህ ማኅበርተኞች ከአንድ ጽዋ ጠጥተው ከአንድ ማዕድ ተመግበው ፣ የጽዋ እኅት ፤ የጽዋ ወንድም ይባባላሉ ። በጋብቻ አይገናኙም ። ተሰብስበው የቀረበላቸውን ተባት ረው እግዚአብሔርንም ካመሰገኑ በኋላ ከወንድማቸው መካከል ችግር የደረሰበት እንዳለ እዚያው ላይ ተወያይተው ይረዱታል ። ለምሳሌ ። በአጨዳው በአረሙ በሌላውም ችግር ቤት እንኳ ሳይቀር ባንድ ቀን ሠርተውለት ይውላሉ ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከነሱ አንዱ ድንገተኛ አደጋ ቢደርስበት ፤ እክል ቢገጥመው ቀድመው የሚገኙለት እነዚህ የጥዋ ወንድሞቹና እህቶቹ ናቸው ።

ማኅበር የሚሰየመው በጌታ ፣ በእመቤታችን ፤ በጻድቃንና በሰ ማዕታት ስም ነው ብለናል አባሎቹ አሥራ ሁለት ናቸው ። አንድ ዓመት አሥራ ሁለት ወሮች ስላሉት ፤ ከልሉ ፲፪ ብቻ ነው ።

አባሎች ከበዙም በእጥፍና ከዚያም በላይ ሁነው ባሥራ ሁለቱ ወሮች ይመደባሉ ። ይህም ግልጥ እንዲሆን ከነሱ ውስጥ አንዱ በቅ ዱስ ሚካኤል ማኅበር አባል ( ማኅበርተኛ ) ሆኖ ሳለ በያመቱ የነሐሴ ተክለ ሃይማኖት ዕለት ተራውን ለመክፈል ቢፈልግ ይችላል ። ይህ የሚሆነው ጠቅላላ የማኅበርተኞቹ ቁጥር ከአሥራ ሁለት በላይ የሆነ እንደሆነ ነው ። ይህም ዓይነት አከፋፈል ድርብ ወይንም ደብል ይባላል ።

ስለ ማኅበር ካነሣን ዘንድ እግረ መንገዳችንን ስለ ስነ ሥርዓ ቱም ጨምረን ብንመለከት የኢትዮጵያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባህልና ትውፊት የበለጠ እንረዳለን ።

ሀ/ በመጀመሪያም ስለ ሊቀ ማኅበሩ ( ስለ ሙሴው ) እንናገ ... የማኅበሩ ሊቀ መንበር ከማኅበርተኞቹ መካከል በዕጣ

www.ethiopianorthodox.org

ይመረጣል (ትመረጣለች) ። ይህም ሙሴ ይባላል ። ምሳሌነት ያለው ስያሜ ነው ። ሙሴ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ለሕዝበ እግዚአብሔር ለእሥራኤል ዘሥጋ መሪ መጋቢ እንደ ነበረ ይህም ለእሥራኤል ዘነፍስ ለምእመናን መሪ መካሪ ስለሆነ ስሙን ሙሴ ይሉታል ። ሙሴ መና አውርዶ፤ ደመና ጋርዶ ፣ ውኃ ከደንጊያ አፍልቆ እሥራኤልን ዓርባ ዓመታት እንደመገባቸው ፤ ይህም በአገልግሎት ዘመኑ የጥዋ ወንድሞቹንና እህቶቹን መንፈሳዊ ምክር ይመክራቸዋል ። የፍቅር ምልክት የሚሆን ማዕዱን በክርስቲያናዊ ስነ ሥርዓት ይመግባቸዋልና ። ሌላው ደግሞ፤ ሙሴ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመግዛት ሳይሆን ለማገልገል የተሾመ ነው ። የዚህም ተቀዳሚ ተግባሩ ወንድሞቹንና እህቶቹን ምዕመናን እግዚአብሔርን ለማገልገል በዕጣ በፈቃደ እግዚአብሔር ስለሚመረጥ ሙሴ ብለውታል ።

ሙሴ የሚሆነው ወንድ ብቻ አይደለም ፣ ሴትም ትሆናለች ። በክርስትና ትምህርት የጾታ ልዩነት የለምና፤ ይህም ታላቅ ቁም ነገር እንዲህ እንደ ዛሬው የሴቶች መብት በየአደባባዩ ከመለፈፉ በፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ጀምራ ስትሠራበት መኖሩን ያመለክታል ። ሙሴው ወይም ሙሴዪቱ በድንገተኛ እክል ምክንያት በማኅበሩ ቀን ያልመጣ(ች) እንደሆነ ምክትሉ ተተክቶ ይሠራል ። ይህንም ግልገል ሙሴ ይሉታል ። ከሙሴው ጋር ሆነው የሚሠሩ ከማኅበሩ አባላት የተመረጡ ፈቃደኞች ሰዎች ደርገ ሙሴ ይባላሉ ።

የሙሴው (የሙሴዪቱ) ተግባር ፡—

ሀ. አዲስ አባል ወደ ማኅበሩ ለመግባት በጠየቀ ጊዜ ከማኅበሩ ጋር መክሮ ፈቃድ መስጠት፤

ለ. ከማኅበሩ አባሎቹ የታመመ እና ወይም ሌላ እክል የደረሰበት እንዳለ ለማኅበሩ ነግሮ ርዳታ መሰብሰብ፤

ሐ. አብረውት ከሚሠሩት ወይም ደርገ ሙሴ ከሚባሉት ጋር ሆኖ የማኅበሩን ስነ ሥርዓት ማስከበር ፤ በማኅበር በሚሰበሰቡበት ቀን ጠቃሚ ምክር መስጠት



መ. በየወሩ ምዕመናኑ ሲሰበሰቡ አደግድጎ ቁሞ ማገልገል ምዕመናኑ ወደ የቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት የባለተራዎቹን ስም እየጠራ ማስተዋወቅ፤ ምንም እንኳ የባለተራዎቹ ስም ዝርዝር በመዝገብ የተያዘ ስለሆነና እያንዳንዱም ምዕመን ተራውን ቢያውቀው ፤ ማኅበራዊ ስሜቱን እንዳያጣ እያንዳንዱ በፈቃዱ እኔ አለሁ እንዲል ነው ። አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ነው ። ሙሴው (ዋ) ጽዋውን አንስቶ በከንዱ ይዞ ( ባንዳንድ ክፍሎች ደግሞ የሚጠጣበትን ዋንጫውን ጽዋውን ከፍ አድርጎ (ይዞ) በማዕከል ይቆምና የሚከተለውን ያውጃል ። « ማነህ ባለሳምንት ያስጠምድህ ባሥራ ስምንት እኔ ነኝ የምትል የዕገሌ ወዳጅ» ይላል ። በዚህ ጊዜ ባለ ተራው አፈፍ ብሎ ተነሥቶ እኔ አለሁ የዕገሌ ወዳጅ ፤ ቢያውለኝ ቢያውላችሁ ፤ ማይ ሹሜ ቁጠማ ጉዝጉዤ እጠብቃችኋለሁ «ብሎ በማኅበሩ መካከል ይሰግዳል (ይወድቃል ። ) በዚህ ጊዜ ቄሱ፡—»አለሁ እንዳልህ አለሁ ይበልህ ፤ እንደ ወደቅህ ኃይለ— አጋንንትን ይጣልልህ ፤ለቀጠሮ ያብቃን » ብሎ አቡነ ዘበሰማያት ይሰጣል ። ሙሴው በተመሳሳይ ድምፅ እስከ ሦስት ጊዜ ያውጃል ። በሁለተኛው የሁለተኛውን ወር ባለ ተራ ማነህ ባለ ሁለት ያስጠምድህ ባሥራ ሁለት እኔ ነኝ የምትል የዕገሌ ወዳጅ» ፤ በሦስተኛው ፡— «ማነህ ባለ ሦስት ያስጠምድህ ባሥራ ሦስት፤ እኔ ነኝ የምትል የዕገሌ ወዳጅ » ይላል ። ሌላው አይለወጥም፤ እንደ መጀመሪያው ነው ። ባለ ተራው እንደ አጋጣሚ ሳይመጣ ቀርቶ እንደሆነ ወኪል ይልካል ፤ ያለዚያ ግን ወንበር ገፍ የሆነው እኔ አለሁ ብሎ ተመርቆ ጽዋውን ይወስዳል ። ሁሉም ካልተገኙ ሙሴው ራሱ ይመረቃል ። ማኅበሩን ግን ባለ ተራው ይከፍላል ። ባለ ተራው አደጋ ደርሶበት ለመክፈል ያልቻለ እንደሆነ ያስተላልፉለታል ። ያለዚያም አዋጥተው ይከፍሉለታል ። አራተኛው ባለተራ ስሙ አይጠራም፤ እሱም እኔ ነኝ ብሎ አይነሣም። ሙሴው ግን፡— «ባለ አራት ቤት ቨን አትሳት፤ ተጠራጠር፤ብቅል ስቀል ብሎ»

www.ethiopianorthodox.org

በሽፍን ያስታውቀዋል ። እጥኜና ተራ መንገሩ ሲፈጸም ሙሴው እንደቆመ ፤ በራሱ ፤ በደርገ ሙሴውና በደጋሹ ወንድሙ ስም ሆኖ የሚከተለውን በመናገር ማኅበሩን ይቅርታ ይጠይቃል ።— «ለሙሴ ለደርገ ሙሴ ፤ዓይኑ በሳሳ ፤ እጁ ባዳላ ፤ ባለቤት ጠላው በቀጠነ ፤ቆሎው ባረረ ፤ ዳቦው በቀነ በረ፤ማኅሩን ይላሉ» ፤ ይህን ተናግር እሱም ፤ ግልገል ሙሴውም ባለቤቱም በማኅበሩ ፊት ይሰግዳሉ ( ይወድቃሉ ) ። በዚህ ጊዜ ማኅበሩ በሙሉ ተነሥተው ባንድ ድምፅ ፣— ሙሴው ዓይኑ አልሳሳም ፤ እጁ አላዳላም ፤ ባለቤት፣— ጠላው አልቀጠነም ፤ ወይነ ቃና ነው ፤ ዳቦውም አላረረ ፤ ኅብስተ መና ነው ፤ ወሰዉ ወሰዉ ፣ እንዲህ ያለ የለም ብለው ደስታቸውን በጭብጨባና በዕልልታ ይገልጣሉ ። ቄሱ መርቆና አሳርጎ ሁሉም ወደየቤታቸው ይሔዳሉ ።

እያንዳንዱ ባለተራ በጻድቁ ወይም በቅዱሱ ስም ከጠበሉ በጽዋው (በገንቦው) ፤ ከኅብስቱ በመሶበ ወርቅ አድርጎ እየተሸኘ ወደ ቤቱ ይሔዳል ። ይህ በአዲስ አበባና ባንዳንድ ከተሞች ነው ። በገጠር ደግሞ ጽዋ (ገንቦ) ና መሶበ ወርቅ አያደርጉም ። ሌላው አፈጻጸም ግን የሁሉም አንድ ነው ።

ሰንበቴም ሆነ ዝክሩ ወይም ማኅበሩ በቤተ ክርስቲያን ሲያያዝ የመጣ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ መዝገብ የሚያውቀው ስለ ሆነ ፤ በሀገራችን ተጠብቆና ተከብር እስካሁን መቆየቱ የሚያስመሰግን ነው ። የሚያኩራም ነው ። ለትውልድም ሊተላለፍ የሚገባ ቅርስ ነው ። ነገር ግን በዚህ መንፈሳዊ ትውፊት ውስጥ ሐሜትንና ነቀፋን የሚያስከትሉ ስካርና ጠብ ፤ ክርክር ወይም ሌላ ሥጋዊ ፍላጎት ሥርገው እንዳይገቡ ፤ በትምህርት መካከል የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ተግባር ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን እንደነዚህ ያሉትን ትውፊቶቿን በትምህርት መሥርታ ለትውልድ ካላስተላለፈች ደግሞ ልጆቿ እናታቸው መሆኗን ለማወቅ ይከብዳቸዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሥጋ በሞት የተለዩትን የክርስቲያን ወገኖች የምታስታውስበት ሥርዓት አላት



«ዝሩ እክለከ ላዕለ መቃብረ ጻድቃን ፤» 155። «ወባሕቱ ግበር ሎቱ ተዝካር ፤» 156። «መፍትው ንግበር ተዝካርሙ ለምውታን በዕጣን ወበመስዋዕት » 157። ቤተ ክርስቲያን ይህን ዓለም ድል ነስተው የሔዱና በዚህ ዓለም በተጋድሎ ላይ ያሉ ምዕመናን ማኅበር እንደ መሆኗ መጠን ፤ ዓለምን በሃይማኖታቸው አሸንፈው ያለፉት በተጋድሎ ላሉት ይጸልያሉ በተጋድሎ ያሉትም በአፀደ ነፍስ ላሉት ይጸልያሉ ። በአፀደ ነፍስ ያሉት እነዚያ በተጋድሎ በአፀደ ሥጋ ላሉት የሚያቀርቡት ምህላና ጸሎት እነሱና እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቁት ምሥጢራዊ አቀራረብ ነው ። በአፀደ ሥጋ ያሉት እነዚህ ግን ተጋድሏቸውን ፈጽመው ላለፉት ወገኖቻቸው መታሰቢያ እንዲሆን ዕጣን ቋጥረው መብዓ ሠፍረው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ቅዳሴ በማስቀደስ ድግስ ደግሰው ለካህናትና ለነዳያን በመግብ ነው ።

ከዚህ በላይ እንዳየነው ሰንበቴውም ማኅበሩም ዝክሩም ሆነ ተዝካሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትታወቅባቸው ቅርሶች ስለሆኑ ፤ ትውልዱ እንዳይዘነጋቸው ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ነው ። ነገር ግን ስካርና ሌሎችም ሥጋውያን ነገሮች ይህን ቅዱስና ሃይማኖታዊ ትውፊት እንዳያረክሱት የቤተ ክርስቲያን መምህራንና ካህናት አስቀድመው ራሳቸውን አጽድተው ለምዕመናንም ምሳሌ መሆን አለባቸው ። ይህ ከሆነ ደጀ ሰላማችንን «የሰካራሞች ኩሴጅ ናት» እያሉ የሚያሸሟጥጡብን ሐሜተኞች ያፍራሉ ፤ ትውልዱም የቤተ ክርስቲያኑን ትውፊት ደስ እያለው ይከተለዋል ።

155. ጦቢት ፬፡፲፯ ፤
156. ሲራክ ፴፰፡፳፫ ፤
157. ማንዘት ፩፻፶፯ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፲ ፤

# ኤኩሜኒዝም ( Ecumenism ) ና
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ኢኩሜኒዝም ማለት በአብያተ ክርስቲያናት ያለውን ጥላቻና ክፉ አስተሳሰብ ለማስወገድና አብሮ ለመሥራት የተቋቋመ ዓለም አቀፍ የክርስቲያኖች ንቅናቄ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን « የኢኩሜኒዝምን » መንፈስ በትክክለኛ ዓላማው ትቀበለዋለች ፤ ማለትም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ጥላቻን አልይህ አልይህ መባባልን አርቆ ሁሉም የየራሱን ጠብቆና አክብሮ የሌላውንም መብት ጠብቆ መኖር «የኢኩሜኒዝም» ዓላማ ነውና ። «በኢኩሜኒዝም» ስም ለገንዘብ ብሎ ራስን መቸርቸር ወይም የሌላውን ትውፊት ከራስ ጋር ማዳበል ግን በታሪክና በትውፊት ላይ ማመፅ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከላይ የተጠቀሰው የኢኩሜኒዝም መን... መተዋወቅን ፤ መጠናናትንና መረዳዳትን የሚያስገኝ ድልድይ መሆኑን ተረድታ የዓለም አብየተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል ናት ። ራቅ ባሉት ዘመናት በተመዘገበው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ፤ ምንም እንኳ እንደዛሬ ስም ባይወጣለት ኢኩሜኒዝም» ነበረ ። ለዚህም ክርስቲያኖች የጋራ ጠላት በተነሳባቸው ጊዜ የምሥራቁ ከምዕራቡ ጋር ያደርጉት የነበረው ግንኙነት ያስረዳል ።

በኢትዮጵያም አፄ ካሌብ የመን ተሻግረው የሀገረ ነግራንን ክርስቲያኖች ከወራሪ ያዳኗቸው በዚሁ መንፈስ ነው ። በአካባቢያቸው ከሚኖሩ አረባውያን ጋር ግጭት ሲገጥማቸው ክርስቲያኖች ይላላኩ ነበር ። ለምሳሌ ፤ የሀገረ ናግራን ዕልቂት ዜና ከቁስጥንጥንያ ወደ እስክንድርያ ከዚያ ወደ አኩስም እንደመጣ እናውቃለን ።



«የኢኩሜኒዝም» መንፈስ ይኸ ከሆነ ጥንዲት አገር ከተመቁባት ቤተ ክርስቲያን ተታለው የወጡትን በማኅበር ተደራጅተዋልና ፤ «በኢኩሜኒዝም» መንፈስ ራሳቸውን የቻሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው እንቀበላቸው ማለት ግን በቲዎሎጂ አለመብሰልና የቤተ ክርስቲያንን ማዕከላዊ አሠራር መናድ ነው ። የኢኩሜኒዝምን መንፈስ በሚቃረን ሁኔታ አንዳንድ በሀብታቸውና በገዘፋቸው የሚመኩ አብያተ ክርስቲያናት በሀብትና በገዘፍ ከነሱ በታች የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት ንዑሳን እያሉ በመሰየም ሲንቋቹውና ሲያዋርዷቸው ምዕመናቻቸውንም እየነጠቁ ሲወስዱባቸው ኑረዋል ። ለዚህም አድራጎት አንጋፋዋ ፤ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪካችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተዋወቁት በፍሎሬንስ ጉባኤ ነው 158። የጉባኤው መንፈስ « በኢኩሜኒዝም » ላይ የተመሠረተ ነው ፤ ማለትም የክርስቲያኖች ጠላት የነበረውን የኦቶማን መንግሥት መስፋፋት የሚመለከት ነበር ። ነገር ግን በጉባኤው የነበሩት የሮማ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ንግግር ፤ ዓላማውን የለቀቀ ስለነበር ፤ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ሳይስማሙ ተመልሰዋል ።

ከዚያ ወዲህ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱሳውያን እየተባሉ የሚጠሩ ሚሲዮናቹዋን እየላከች ፤ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መረጃዎችን ሰብስባለች ። መረጃዎቹ ግን በጥላቻና በንቀት ቀለም የተጻፉ ስለሆኑ ፤ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሕልውና የሚያንቋሽሹ ነበሩ ። እርግጥ ነው በ፲፮ኛው መቶ ክፍለ— ዘመን ግራኝ መሐመድ የኢትዮጵያን ክርስቲያናት ለመደምሰስ ቢነሳ ፤ ኢትዮጵያ «በኢኩሜኒዝም» መንፈስ የፖርቱጋልን ካቶሊካዊ መንግሥት ርዳታ ጠይቃለች ። ነገር ግን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ካቶሊካዊ የሆነውን መንግሥት ሁሉ በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በሌላም ስለሚያዙት ንጉሡ የኢትዮጵያን መል

www.ethiopianorthodox.org

እከተኞች ወደቫቲካን ላካቸው ። ይህም የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተቀጽላ ስላልሆነች ፤ ለፓፓው ሳያማክር ርዳታውን ቢሰጥ ፓፓው እንዳይቆጣው ነው ። በዚሁም ምክንያት ርዳታው ዘግይቶ ደረሰ ። ግራኝም የልቡን ሠራ ፤ በአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ከፖርቱጋል ወታደሮች ጋር አብረው መጥተው የነበሩ ኢየሱሳውያን ደግሞ ኢትዮጵያን የቫቲካን ሀገረ ስብከት ለማድረግ የነበራቸው ሙከራ አልሳካላቸው ስላለ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኦሬታዊት እንጅ ወንጌላዊት አይደለችም በማለት አንዳንድ በሕዝቡ ዘንድ የሚፈጸሙ ባህሎችን እንደ ነውር በመቁጠር ወሬውን ያናፍሱት ጀመር ።

በዚህ ምክንያት ንጉሡ አፄ ገላውዴዎስ የኢትዮጵያን ትክክለኛ እምነት የሚያስረዳ ጽሑፍ በወሬው ለተወናበዱት ሁሉ አስተላለፉ ። (ጽሑፉ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያቀናበሩት መሆኑ አያጠራጥርም ፤ በንጉሡ ስም መሆኑ ግን የሃይማኖት ኀላፊ አቡኑ ግብጻዊ ስለነበሩ ፤ የሀገሪቱን ቋንቋ አያውቁም ። ነገሩ ደግሞ ኀላፊነት ያለበት እንደመሆኑ በባለሥልጣን መነገር ስላለበት ፤ ሊቃውንቱ አርቀው በንጉሡ በኩል እንዲተላለፍ ያደረጉት ይመስላል ።)

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤ ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥት እሥራኤላውያን ወሃይማኖተ መርኤትየ እለ ሀለው በአጸደ መንግሥትየ ። ንሕነ ነአምን በአሐዱ አምላክ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ውእቱ ቃሉ ፤ ወውእቱ ኃይሉ ፤ ውእቱ ምክሩ ፤ ወውእቱ ጥበቡ ፤ ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ፤ ወበደኃሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየአርቅ እመንበረ መለኮቱ ወተሰብአ በመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ፤ ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በሠላሳ ክረምት ወኮነ ብእሴ ፍጹመ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ፤ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት ፤ ወእምዝ በአርብዓ ዕለት አርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ፤ ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ፤ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ፤ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ፤ ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ለሕይወት ዘይመጽዕ ለዓለም አሜን ። ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዱሕ አማናዊ ወኢናጸንን ኢለየማን ወኢለጸጋም እምትምህርተ አበዊነ ፤ አሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት ፤ ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ፤ ወሰብዓ ወክልኤቱ አርድዕት ፤ ወሰለስቱ ምዕት አሰርቱ ወሰመንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ዘተጋብኡ በኒቅያ ፤ ወምዕት ወሃምሳ በቍስጥንጥንያ ወክልኤቱ ምዕት በኤፌሶን ፤ ከመዝ እሰብክ ወከመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ ፤ ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አኮ ዘናከብራ ከመ አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ ፤ እስመ እሙንቱሰ አይሁድ ኢይቀድሁ ማየ ወኢያነድዱ እሳተ ወኢያበስሉ ጸብሐ ፤ ወኢየኀብዙ ኅብስተ ፤ ወኢይትፋለሱ እምቤት ውስተ ቤት ። ወባሕቱ ንሕነሰ ናከብራ እንዘ ናአርግ ባቲ ቍርባነ ወንገብር ባቲ ምሳሐ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ ፤ አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ እሑድ እንተ ይዕቲ ዕለት ሐዳስ ዘይቤ ዳዊት በእንቲአሃ ፤ ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ፤ ባቲ ፤ እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት ፤ በጽርሐ ጽዮን ፤ ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሰ ቅድስት ማርያም ድንግል ። በኩሉ ጊዜ ፤ ወባቲ ይመጽዕ ዳግመ ለዕሴተ ጻድቃን ወለፍዳ ኃጥአን ፤ ወበእንተ ሥርዓተ ግዝረትኒ አኮ ዘንትገዘር ከመ አይሁድ ፤ እስመ ንሕነ ነአምር ቃለ ምህርሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘይቤ ተገዝሮሂ ኢይበቍዕ ፤ ወኢተገዝሮሂ ኢያሰልጥ ዘእንበለ ዳዕሙ ሐዳስ ፍጥረት ዘውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ ዘሂ ነሥአ ግዝረተ ኢይንሣእ ቈልፈተ ። ኵሉ መጽሐፈ ትምህርቱ ለጳውሎስ ሀለወ በኀቤነ ወይሜህረነ በእንተ ግዝረት ወበእንተ ቈልፈት ። ወባሕቱ ግዝረትሰ ዘኮነ በኀቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥሐተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወኖባ ፤ ወከመ ስቁረተ ዕዝን ዘሰብአ ሕንድ ፤ ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በአቂበ ሕገ ኦሪት ዳዕሙ በልማደ ሰብእ ።

ወበእንተ በሊዓ ሐራውያኒ አኮ ዘንትከላዕ በአቂበ ሕገገ ኦሪት ከመ አይሁድ ፤ ለዘኒ በልዓ ኢናስቆርሮ ወኢናረኵሶ ፤ ወለዘኒ ኢበ



www.ethiopianorthodox.org

ልዓ ከመ ይብላዕ ኢናገብር ፤ በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል ዘኢ በልዓ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ ወለኩሉሙ እግዚአብሔር ተወክፎሙ ። መንግሥተ እግዚአብሔርሰ ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ ፤ ኩሉ ንጹሕ ለንጹሓን ፤ ወእኩይሰ ለሰብእ በሊዕ ምስለ ዕቅፍት ፤ ወማቴዎስ ወንጌላዊ ይቤ አልቦ ዘይክል አርኩሶቶ ለሰብእ ዘእንበለ ዘይወጽእ እምአፉሁ ፤ ወዘሰ ውስተ ከርስ ይበውእ ወይትገመር ጽመ ፤ ወይትገደፍ ወይትከዐው ፤ ወያነጽህ ኩሉ መባልዕተ ፤ ወብዝኃ ዝንቱ ቃል ነበተ ኩሉ ሕንፃ ስህተቶሙ ለአይሁድ እለ ተምህሩ እመጽሐፈ ኦሪት ።

ሊተሰ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለ ይሚ ሁሩ በትእዛዝየ በአጽደ—መንግሥትዩ ፤ ወኢይትገሐሡ እምፍኖተ ወንጌል ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማን ወኢለጸጋም ።

ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሉ በመጽሐፈ ዜአነ እስመ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ሐዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለኩሉሙ እለተጠ ምቁ አይሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤ ሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባሁቱ በከመ አደዎ ልቡ ለሰብእ ይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ እንስሳ ። ቦ ዘያፈቅር ሥጋ ዓሣ ወቦ ዘያፈ ቅር በሊዓ ሥጋ ዶርሆ ፤ ወቦ ዘይትኄረም እምበሊዓ ሥጋ በግዕ ፤ ወ ኩሉ በከመ አደዎ ልቡ ይተሉ ፤ ከመዝ ውእቱ ስምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ በእንተ መብልዓ ሥጋ እንስሳ አልቦ ሕግ ወአልቦ ቀኖና ውስ ተ መጽሐፍ ሐዲስ ፤ ኩሉ ንጹሕ ለንጹሓን ፤ ወጳውሎስኒ ይቤ ዘሰ የአምን ኩሉ ለይብላዕ ።

ዝንተ ኩሉ ጽሕቀ ለጽሒፍ ከመ ታእምር ጽድቀ ሃይማኖትየ ተጽሕፈ በዐሥርቱ ወሃምስቱ ምዕት በሃምሳ ወሃምስቱ ዓመት እም ልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ እሥራ ወሠሉሱ ለሰኔ በሀ ገረ ዳሞት ።»

በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በአንድ አምላክ ሃይማኖቴና የአባቶቼ የእሥራኤላውያን ነገሥታት ሃይማኖት በመ ንግሥቴም (በረት) ግዛት ውስጥ የሚገኙ ምዕመናን (የመንጋየ) ሃይማኖት ይህ ነው ። እኛ በአንድ አም



የሱስ ክርስቶስ እናምናለን ፤ ይኸውም ቃሉ ፣ ኃይሉ ፣ ምክሩ ፣ ጥበቡ ነው ። ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር የነበረ ነው ። በኋለኛው ዘመን ከመለኮታዊ መንበሩ ሳይለይ ወደኛ መጣ ፤ ከመንፈስ ቅዱ ስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ ። በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፣ ፍጹም (ምሉዕ) ሰው ሆነ ። በጰንጤናዊው ጲላ ጦስ ዘመን በእንጨት ላይ ተሰቀለ ፣ ታመመ ፣ ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በሦስተኛውም ዕለት ተነሣ ፤ ከዚህ በኋላ በአርባ ቀን በክብር ወደ ሰማይ አረገ ፣ ባባቱ ቀኝ ተቀመጠ ፣ ዳግመኛም በክብር ይመጣል፣ በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድ ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ፣ ከአብ በሠረጸ ጌታ አዳኝ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እና ምናለን ። ባንዲት ጥምቀትም እናምናለን ። ኃጢአትን ለማስተሰ ረይ ፣ ትንሣኤ ሙታንን (የሙታንንም መነሣት) ተስፋ እናደርጋ ለን ፣ ለዘለዓለም ሕይወት ፣ አሜን ። እኛስ እውነተኛ በሆነው በጥርጊያውና በጥናው መንገድ እንሔዳለን ፤ ከአባቶቻችን ትምህ ርት ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ አናዘነብልም ፤

እሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፣
የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ፣
ሰባ ሁለቱ አርድእት ፣

በኒቅያ የተሰበሰቡ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ኦርቶዶክሳው ያን ፣ በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡ አንድ መቶ ሃምሳው ፣

በኤፌሶን የተሰበሰቡ ሁለት መቶው ፣ የናኦድ ልጅ የወናግ ሰገድ ልጅ በመንግሥቱ አጽናፍ ሰገድ የምባል የኢትዮጵያ ንጉሥ እኔ ገላውዴዎስ፣እንዲህ እሰብካለሁ እንዲህ አስተምራለሁ ። ቀዳሚት ሰንበትን የምናከብርበት ምክንያት፣ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን ብን ብለው ክርስቶስን እንደ ሰቀሉት እንደ አይሁድ የምናከብራት አይደለንም ። 159. እነዚህ አይሁድ ውሀ አይቀዱም ፣ እሳት አያ

159. ማቴ. ፳፯፡፳፭ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ንዱም ፡ ወጥ አይሠሩም ፡ እንጀራ አይጋግሩም ፡ ከቤት ወደቤት አይሔዱም እኛ ግን የምናከብራት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንዳ ዘዙ ቅዳሴን በመቀደስና ግብር (ማዕድ) በመሥራት ነው ። (ስንበቴ—ማኅበር-ተዝካር ።) እንደ እሑድ ሰንበት አይደ ለም የምናከብራት ይህችውም አዲሲቱ ዕለት ናት ። እግ ዚአብሔር የሠራት ዕለት ይህች ናት ፤ እንደሰትባት ሐሤትም እናድርግባት ብሎ ዳዊት ስለርሷ የተናገረላት ። 160. በዚች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና ፡ በዚችው ዕለት መን ፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን ለሐዋርያት ወርዶአልና ፡ በዚች ዕለት ሁል ጊዜ ድንግል በሆነች በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕጸን ሰው ሆኗልና ፤ በዚች ዕለት ዳግመኛ ይመጣል ፡ ለጻድቃን ሽል ማት ለኃጥአን ውርደት (ዕዳ) ።

ስለ ሥርዓተ ግዝረትም እንደ አይሁድ የምንገዘር አይደለንም የጥበብ ምንጭ የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና ።—«መገዘር አይጠቅምም ፡ አለመገዘርም ግዳጅ አይደለም ፡ አዲስ ፍጥረት ነው እንጅ ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው ። 161. ዳግመኛም ለቆሮንቶስ ሰዎች «የተገዘረ ቁልፈትን አይሻ » አለ ። 162. የጳውሎስ የትምህርቱ መጽሐፍ ሁሉ በኛ ዘንድ አለ። ስለ ግዝረትና ስለቁልፈት ያስተምረናል ። ነገር ግን በኛ ዘንድ ያለው ግዝረት እንደ ኢትዮጵያና እንደ ናባ የፊት መተልተል እንደ ህንድ ሰዎች የጆሮ መነደል ያለ የአገር ልማድ ነው ። ይህን የምና ደርገው በኦሪት ሕግ አይደለም ። በሰው ልማድ ነው እንጅ ።

አሳማንም ስለ መብላት ፡ ከመብላት የተከለከለ ነው እንደ አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም ። የሚበላው ንም አንጸየፈውም ፡ አናረክሰውም ፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም ፤ አባታችን ጳውሎስ ለሮም እንደ ጻፈው «የሚበላ

160. መዝ.፻፲፯፡ ፳፬።
161. ገላ. ፭ ፡ ፮።
162. ቀዳ. ቆር. ፯ ፡ ፲፰ ።



የማይበላን ፡ አይንቀፈው (አይናቀው) እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀ ብሏቸዋልና የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደ ለችም ። ለንጹሖን ሁሉ ንጹሕ ነው ፡ ለሰው ከተው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው 163. ። ወንጌላዊ ማቴዎስም ፡—«ከአፉ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም ፤ ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል ፡ ይፈሳል ፡ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል » አለ ። 164. ይህ አባባሉ ከኦሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስህተት ሕንፃ ሁሉ አፈረሰው ። የኛና በግዛቱ ውስጥ ያሉ በትእዛዜ የሚያስተምሩ አዋ ቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው ። ከወንጌል መንገድ ፡ ከጳው ሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም ። በኛም የታሪክ መጽሐፋችን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት ያሳማ ሥጋ እንዲያበሏቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ ።

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ እንዳለው የእንስሳትን ሥጋ ከመ ብላት ይወሰናል ፡—የአሣ ሥጋ የሚወድ አለ ፤ የዶሮ ሥጋ መብ ላት የሚወድ አለ ። የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ ። ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል ። የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደ ዚህ ነው ። ስለ እንስሳት ሥጋ መብል በአዲሲቱ መጽሐፍ ውስጥ (አዲስ ኪዳን) ሕግም ቀኖናም የለም ። ለንጹሖን ሁሉ ንጹሕ ነው ጳውሎስም፡—«የሚያምን ሁሉን ይብላ» አለ 165. የሃይማኖቴን እውነት ታውቅ ዘንድ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ተጋሁ ። ዳሞት በሚ ባል አገር በሰኔ ፳፫ ቀን ፲፭፻፵፭ ዓ.ም. ተጻፈ ።

ከዚያም ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች በጽሑፋቸው የሚያሰፍሩአቸው አስተ ያየቶች ሁሉ ምርቅና ፍትፍት የሆኑ ናቸው ፡ ማለትም ባንድ ፊት ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስበው

163. ሮሜ፡፲፬፡፫፡፲፯ ፡ ቲቶ ፩፡፲፭ ። ቀዳ.ቆር.፰፡፱—፲፫።
164. ማቴ.፲፭፡፲፩—፳፩ ፡ ማር.፯፡፲፰።
165. ሮሜ.፲፬፡፪፡፳።

www.ethiopianorthodox.org

ለመጽፍ የሰንዙሩ ይመስሉና በዚያው ውስጥ ደግሞ ቤተ ክርስቲያ ኒቱ የምትጥረድበትንና የምትጋለጥበትን ፤ ማንኛውንም ሁሉ እን ደመሰላቸው በመተርጐም ለአንባቢ ያቀርባሉ ። በእኛም በኩል የቤተ ክርስቲያናችን ሊታወንት በሁቡት አጥሪት ምክንያት እንደ ነሱ በማኅተም ባያሳትሙትም ፤ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት በትጌያ ቸውም ሆነ በጽሑፋቸው መልስ ሲሰጡበት ኑረዋል ፤ የሮማ ካቶ ሊክ ቤተ ክርስቲያን ፤—«ወአሆርኩ ኀበ ተሰምየ ክርስቶስ ከመ ኢይሕንጽ ዲበ መሠረተ ባዕድ ፤» የክርስቶስ ስም ወደተጠራበት አልሔድሁም ፤ በሌላ መሠረት ላይ እንዳላንጽ 166. ያለውን የቅ ዱስ ጳውሎስን አርአያነት ረስታ በጐችን ከእረኞቻቸው ስትነጣ ጥል ኑራለች ።

አሁን በኢትዮጵያ ከሚገኙት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ብዙዎቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲ ያን የተጠመቁ ናቸው ። ይህ ሁሉ ተዕዕኖና ግፊት ቢኖርም ፤ ከቅ ርብ ጊዜ ወዲህ ባንዳንድ ስብሰባዎች የኢትዮጵያና የሮማ ቤተ ክርስቲያናች ተወካዮች መገናኘት ጀምረዋል ፤ ለወደፊትም ቢሆን በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን የምናሳስበው በሃይማኖት ስም እኛን ለመከፋፈል የዘመቱብንን የፈረንጆች አስተሳሰብ እንዲያስወግዱና አንዲት ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያናችውን እንዳይረሷት ነው ። ስለ ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመጠኑ ይህ ነው ።

ለ/ ሌሎች የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ባንዳንድ የቀናና ሥርዓታት ቢለዩም ምንጫቸው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስ ቲያን ስለሆነች ፤ ሰበካን የማስፋፋቱን መንፈስ ከሷ ወርሰው ራሳ ቸውን በማመሳደት ሌሎችን በማቋሸሽ በየዕለቱ አዳዲስ ዶግማዎችን በመፍጠር የኢኩሚኒዝምን መንፈስ ሲያቃውሱት ይታያሉ ። ያም ሆነ ይህ ፋሚውና ትግሉ ሕዝብን ከሕዝብ በማለያየት ሰው ማንነ ቱን እንዲያጣ ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስ ቲያን ከነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የዶግማም ሆነ የቀናና ግን ኙነት የላትም ።

166. ሮሜ.፲፭ ፥ ፳፤



/ ከአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ—ዘመን ጀምረው መልካቸ ውን በመለዋወጥ ሀገሪቱን ሲሰልሉ ኑረዋል ። አሁንም ብዙ ምዕ መናንን ከቤተ ክርስቲያናቸው እየጠለፉ በመውሰድ ላይ ናቸው ። ይህ አሠራር ግልጥ የሆነ ወረራ እንጂ የወንጌላውያን ተልዕኮ አይ ደለም ። ብዙ ገንዘብ እያፈሰሱ ሰውን ከታሪኩና ከትውፊቱ መለ የት ሰይጣናዊ ግብር እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አይደለም ። ምዕመናንም ብኩርናውን ለምስር ንፍሮ እንደሸጠው እንደ ኤሳው እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል ።

ከላይ የሮማ ካቶሊክ ተከታዮች ነን ለሚሉ ኢትዮጵያውያን እንዳሳሰብነው ሁሉ በሌሎች የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት በዝ ርወት ላሉት ወንድሞቻችን ኢትዮጵያንም ሀገራቸው አንዲት ኢት ዮጵያ ፤ መታወቂያ ሃይማኖታቸው አንዲት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለሆነች ፤ ዛሬውኑ እንዲያስቡበት እናሳስባ ችዋለን ። በውጭ ካሉትም ጋር በኢኮሚኒዝም መንፈስ ውይይታ ችንን እንቀጥላለን ።

ሐ/ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ፤—እነዚህ አብያተ ክር ስቲያናት በግሪክ ኦርቶዶክስ የሚመሩ ፤—፩- የራሷ የግሪክ ፤ ፪- የሩሲያ ፤ ፫- የሩማንያ ፤ ፬- የዩጎዝላቢያ ፤ ፭- የቡልጋሪያና የሌሎ ችም ናቸው ። ትምህርተ ሃይማኖታቸው በምሥጢረ ሥጋዌ የኬ ልቄዶንን መንግሥታዊ ውሳኔ ተቀብለው «ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ» ነው [illegible] መለካውያን ተብለዋል ። (መላካዊ) ማለትም የንጉሥ ፈቃድ ፈጻሚ እንደ ማለት ነው ። ከጉባኤ ኬልቄዶን በኋላ ተለያይተን እንኖራለን ። ነገር ግን አልፎ አልፎ አንዳንድ የጋራ ጉዳይ ሲያጋጥም በይፋም ሆነ በግል መገናኘታቸውና መወያየታቸው አልቀረም ። የግሪክና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ወዳጅ ነበሩ ። ይህንኑ ወዳጅነት ይበ ልጥ ሊያጠነክረው የቻለው የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የምታበረክተው የነገረ ትምህርት ነው ። በንግድና በሌላም ሥራ በሀገራችን የሚኖሩ [illegible] በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ ቤተ ክርስቲ

www.ethiopianorthodox.org

ያናቸውን ሠርተው ፣ የሃይማኖት መሪዎች ካህናትና ጳጳሳትም ከሀገራቸው እየተላኩላቸው ይኖራሉ ። ዜጎቻቸውን ለማገልገል ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ካህናትና ጳጳሳት የራሳቸውን ከመጠበቅ በቀር አልፈው ተርፈው የኛን ምዕመናን አይተናኮሉም ። ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የግሪክ ጳጳሳት በማንተማቸው ራሳቸውን የአክሱም ጳጳስ እያሉ ይጠራሉ ፤ ምናልባትም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ ግሪካዊ ነበር ብለው ስለሚያምኑ ፣ የሱም መጠሪያው «ጳጳስ ዘአክሱም» ስለ ነበር ያንን ጠበቅን ብለው ነው ፤ ነገር ግን በሰው ሀገር ገብቶ የራሱ ባል ሆነ ስም መጠራት ምንጥቅም ይኖረው ብለው ነው ። በዚያውም ላይ እነሱ የሚቀመጡ አዲስ አበባ ነው ። አክሱምን አያውቋትም ። ለእኛም አክሱም የታሪክና ሃይማኖት እናት ከተማችን ስትሆን ይህ አድራጐት አጠያያቂ አይሆንም ወይ ?

በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ—ዘመን አጋማሽ ላይ የሩሲያና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ወዳጅነት መሠረቱ ። ይህም የሆነው በኢየሩሳሌም በሚኖሩ የኢትዮጵያና የሩሲያ መነኮሳት አማካይነት ነው ። የሩማንያና የሌሎች መለካውያን አብያተ ክርስቲያናትም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በኢኩሚኒዝም መንፈስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያፈቅራሉ ። በተለይ የሩማንያና የሩሲያ አብያተ ክርስቲያናት የግሪክን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ተከትለው ለኢትዮጵያውያን የነፃ ትምህርት ይሰጣሉ ። ብዙ ምሁራንም ተገኝተዋል ። በኛ በኩል ሊረሳ የማይገባው አንድ ነገር አለ ። ርግጥ ብዙ ሊታወንት ያንዱ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ ከሌላው ሐዋ የቴኦሎጂን ምሥጢር ያራቅቃል ። የዶግማ ልዩነት ቢኖርም አስቀድሞ የራሱን ስለሚያውቅ ሥጋት የለም ። በሀገራችንም የተዋህዶ መምህራን በጠፉበት ወቅት የተዋህዶ ልጆች ከጸጉች መምህራን ገብተው ትርጓሜውን እያረሙ ይማሩ እንደ ነበር አባቶቻችን ይነግሩናል ። ወደ ውጭ ለተጨማሪ ዕውቀት የሚሔዱ ወንድሞቻችንም አስቀድመው ዶግማቸውንና ቀኖናቸውን በሚገባ አጥንተው ቢሔዱ ሊሎቹ የሚሉትም ይገባቸዋል ። እነሱም ራሳቸውን ለሌላው ያስ

www.ethiopianorthodox.org



ረዳሉ ፤ ተመልሰውም ለቤተ ክርስቲያናቸው አዕማድ ይሆናሉ ። ምሥክርነታቸውም ታማኝ ይሆናል ።

መ/ የግብፅ ፣ የሶርያ ፣ የአርመንና የህንድ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ኦሪየንታል ይባላሉ ። የኬልቄዶንን ውሳኔ ያልተቀበሉ ናቸው ። ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑንም ያምናሉ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የታሪክና የዶግማ አንድነት አላቸው ። በሌላው ክፍል የሚታወቁትም በቤተሱብነት ነው ። አብረው ይቀድሳሉ ፤ አብረው ይቆርባሉ ። 167.

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪቃ ቀንድ ላይ የምትገኝ እንደ መሆኗ መጠን በውስጧም ሆነ በአካባቢዋ ክርስቲያን ያልሆኑ ብዙ ስላሉ ፣ እነዚያን የማስተማር ግዴታ አለባት ። በሃይማኖት ስም እጇን ለማዳከም ብዙ ገንዘብ የሚያፈሱ ድርጅቶች ሁሉ ከዚህ ይልቅ በኢኩሚኒዝም መንፈስ ያላንዳች ተፅዕና ሐዋርያዊ ተልእኮዋን እንድታሟን ቢረዷት መልካም ነው ። ይህም ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ግልጥ መሆን አለበት ።

167. Inter — Communion.

# ምዕራፍ ፲፩ ፤

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥ ሪ ት ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥሪት ሦስት ክፍል አለው ። ይኸውም ፤ ፩. የገዳም ፤ ፪. የደብር ፤ ፫. የገጠር ሥሪት ነው ።

ሀ ፤ የገዳም ሥሪት ሁለት ዓይነት ነው ፤ ሀ. የንፍር ገዳም ፤ ለ. የሕግ ገዳም ፤ የንፍሮ ገዳም በመነኰሳት አንድነት ((Cenobitic) ) የሚተዳደር ነው ። ቤተ ክርስቲያኑ ከመነኰሳቱ አስተዳደር ጋር የተያያዘ ነው የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር የሚመራው በዚያው በሊቀ ማኅበሩ ነው (አበ ምኔት ይባላል ፤—ለሴቶች ገዳም ግን እመ ምኔት ናት) ይህ የገዳም ሥሪት ሊሠራ የሚችለው ባንድ በገለልተኛ ቦታ ተወስና በተጋድሎ ሕይወቷን ያሳለፈ ጻድቅ ባረፈበት የታሪክና የሃይማኖት ቦታ ነው ። መነኰሳት ተሰብስበው በጻድቁ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ባንድነት እየሠሩና ባንድነት እየተመገቡ ይተዳደራሉ ። ገዳሙ እየታወቀና ዝናን እያተረፈ በሐዶ ቁጥር ርስትና ጉልት እየተሠራበት መነኰሳቱ እያረሱና እየቆፈሩ የእጅ ሥራም እየሠሩ በተለይም ብዙ መንፈሳውያን መምህራን የሚኖሩበት ስለሆነ እየተማሩና እያስተማሩ ይኖራሉ ። መነኰሳቱ ባንድነት የሚመገቡት ንፍሮ ቀቅለው ፤ ዳቤ ጋግረው ስለሆነ የንፍሮ ገዳም ይባላል ።

ለ. ሥሪታቸውና አስተዳደራቸው የአድባራትሁነው ሳለ በቤተ ክህነት ወይም በመንግሥት ስያሜ ብቻ ገዳማት የሚባሉ አሉ ። እነዚህ ገዳማት የርስት ሥሪታቸውና አስተዳደራቸው እንደ አድባራት ነው።ከአድባራት የሚለዩት ግን ቆሞሳትብቻ ስለሚያስተዳድሯቸው ነው።የሕግ ገዳማት ያልናቸውም ገዳማት ተብለው እንዲጠሩ ከባለ ሥልጣን ከመታዘዙ በቀር በገዳማት ሥርዓት ስለማይመሩ ነው ።



፪. የደብር ሥሪት ብዙውን ጊዜ በከተማና በታሪክ ቦታዎች ፤ የታሪክ ቦታዎችም ባይሆኑ በዘመኑ ባሉ ባለ ሥልጣናት ትእዛዝ ደብር እየተባሉ የሚተከሉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ፤ የእነዚህ አድባራት አስተዳደር በርስትና በጉልት ነበር ፤ ርስትና ጉልቱን የሚተከሏቸው በዘመኑ የነበሩ ነገሥታት ወይም መሳፍንትና መኳንንት ነበሩ ፤ በእነዚህ የሥሪት ደንብ ቤተ ክርስቲያን አልተጠቀመችም ። ምክንያቱም ሀ. ደብሩ ሲደበር ለደብሩ አገልግሎት ርስቱን የተተከለው ካህን በሚሞትበት ጊዜ ርስቱ እየተከፋፈለ እያነሰ ስለሚሔድ ነው ። ለምሳሌ ባንድ ደብር አንድ ጋሻ መሬት ያለው አንድ ካህን አሥር ልጆች ቢኖሩት አንዱ ጋሻ መሬት ከአሥር ይሸነሸናል ። እንዲህም እያለ በትውልድና በቀን ብዛት ለገር መቆሚያ ያህል እንኳ አይገኝም ። ይልቁንም ደግሞ የካህን ልጅ ካህን ስለማይሆን የካህኑ ልጆች ርስታቸውን እየበሉ የቤተ ክርስቲያኑን አገልግሎት በቅጥረኛ ያሰሩት ነበር ። ይህም ተቀጣሪ የሚሠራ ካህን ባመት አሥር ብር ወይም ሃያ ብር ያገኛል ።

ለዚያውም ደግሞ ከእያንዳንዱ ተወላጅ ዙር አጠራቅሞ እንጂ ሰብስቦ የሚሰጠው አልነበረም ለዚህ ቅጥረኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በባለርስቶች ዘንድ ተፋ /መጪ/ የሚል ስመ ጽእለት ነበረው ይህ ስው ጥቅም የሚያገኘው በደጀሰላም መክፈልት ነበር ለዚያውም ቢሆን በሱ አገልግሎት የተገኘውን ተዝካርና ድግስ የባለርስቶች ልጆች እየተሻሙ ሲያሳዝኑት ይኖሩ ነበር ። ለ/የደብር ርስት ትክል ቤተ ክርስቲያንን ያልጠቀመበት ሁለተኛውም ምክንያት ርስቱን ጉልቱን በቤተ ክርስቲያን ስም የሚያስመዘግቡ ነገሥታትና መሳፍንት ከአታቢና ከቀራፊ ጀምር እስከ ግብዝና ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በልጆቻቸውና በቅርብ ተወላጆቻቸው ስም ስለ ሚያደርጉት ክርስቱ የሚገኘው አበል ከእጃቸው ሳይወጣ የሚያገለግሉት ካህናት ግን ኩርማን መሬት ወይም ባመት ይህን ያህል ዳውላ እህል ይሰጣል እየተባሉ የእነሱ ድርጉኞች ሆነው ይኖሩ ነበር ። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኒቱ የንግድ ምልክት ሆና ለብዙ ጊዜ ኑራ ነበር ። ይህ ዓይነቱ አሠራር ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን የጉዳው

www.ethiopianorthodox.org

አገራቸውንም ነበር ፤ ካህናትን በፍርፋሪ እየሸነገሉ በቤተ ክርስቲያን ስም ሲጠቀሙ የኖሩ እነዚህ ሰዎች ግብር እንኳ ለመንግሥት እንዳይከፍሉ የቤተ ክርስቲያን ርስት ነው እያሰኙ ያስወሩ ነበርና ።

ሐ. ሦስተኛው ደግሞ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ሥሪት ነው ፤ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ርስተ ጉልት የለውም ገበሬው በሃይማኖት ስሜት ቤተ ክርስቲያን ይሠራል ለቤተ ክርስቲያኑ መተዳደሪያ የሚሆን የተወሰነ የእርሻ ቦታ ይመድባል ይህም «ሪም» ይባላል ካህናቱ የሚተዳደሩት በእርሻና በመከር ወራት ከገበሬው በሚሰበሰበው የእህል አስተዋጽኦ ነው እንደ ገበዝና እንደ አለቃ ሆነው የሚያስተዳድሩት ገበሬው ባመት ባመት በመስከረም አንድ ቀን ምርጫ እያደረገ በመፈራረቅ ነው የቤተ መቅደሱን ሁኔታ የሚከታተል ግን ውስጠ ገበዝ የሚባል ሹመት አላቸው ከካህናቱ አንዱ ተመርጦ ለእድሜ ልክ ይሾም ነበር ። ከነዚህ ከሦስቱ የሥሪት ዓይነቶች ቤተ ክርስቲያንን በጣም የጐዳት በመሳፍንትና በመኳንንት ርስተ ጉልት የሚተዳደሩ አድባራት ናቸው በሁለተኛው ተራ ቁጥር እንደተገለጠው ስሙ በቤተ ክርስቲያን ጥቅሙ ግን የሌላ ነበርና እንዲያውም በሕዝቡ ዘንድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲሶ መንግሥት አላት እየተባለ ይነገር ነበር በዘመኑ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ይህ ለሕዝብ ግልጥ እንዲሆን አላደረጉም በቤተ ክርስቲያን ስም የተመዘገበው የነገሥታት የመሳፍንትና የመኳንንት ርስት ለራሳቸው ጥቅም እንጂ ካህናቱ ምንም ጥቅም እንደማያገኙበት አልተናገሩም ። ይኸውም በሁለት ምክንያት ነው አንዱ ባለማወቅ ሁለተኛ ደግሞ በፍርሃት ነው ። መሳፍንቱ ከተቆጡና ካኰረፉ ተፍነቱንም ቢሆን ሊከለክሉ ስለሚችሉ ፤

ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ጊዜ ስትገፋ ከኖረች በኋላ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. እንደ ሌሎች ክርስቲያኖች የሰበካ ምዕመናንን በማስተባበርና ከካህናቱ ጋር አብረው እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል የመተዳደሪያ ደንብ ቃለ ዓዋዲን አውጥታ የሰበካ ጉባኤን መሠረተች አሁን በዚህ የሰበካ ጉባኤ ምዕመናን የምዕመንነት ደረጃቸውን ካህናትም የካህናት ድርሻቸውን ይዘው ት...



ደንብና ሕግ መሠረት ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን መልካሙን ነገር ሁሉ ለመሥራት ሁሉም እየተዘጋጀ ነው ።

ዛሬ ምዕመናን ለየሰበካቸው ካህናት በቃለ ዓዋዲው መሠረት ደመወዝ እየከፈሉ ነው ፤ ስለ ሰበካ ጉባኤ ዓላማ ለማወቅና ለመረዳት ያህል ቃለ ዓዋዲው በሚያዘው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን እንደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ሁለት ነገሮችን እንዲያሟሉ ትጠይቃለች ፩—ሁ ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን መዝገብ እንዲታወቁ ምዕመናን ስማቸውና ቁጥራቸው ካልታወቀ ላጠባበቅ ችግር የሚፈጥር ስለሆነ (ዮሐ ፲፣ ፫) ምዕመናን የጥምቀትና የሞት መዝገብ እንዲኖራቸው ነው፤—ቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉ በፊት ስንትልጆች በየቀኑ ፤ በየወሩና በየዓመቱ እንደምትወልድና ፤ በዚሁ አንፃር ደግሞ ስንት ምዕመናን ከዚህ ሕይወት እየፈለሱ ወደ ዘለዓለማዊ ቤታቸው እንደሚሄዱ ማወቅ ስላለበት ይህን ለማሟላት የምትችለው በሰበካ ጉባኤ በኩል እንደሆነ ተረድታ ሰበካ ጉባኤን አጽቁማለች ለ፤—ምዕመናን በመንፈሳዊ ልደት በጥምቀት የተወለዱባት እናታቸው ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ያላቸውን ኃላፊነት በመረዳት ካላቸው ካሥር አንድ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጡ ያም ባይቻል ቃለ ዓዋዲው የመደበውን ገመታዊ ክፍያ እንዲከፍሉና በነሱ ሱታፌ እየተረዳች እናት ቤተ ክርስቲያናቸው አገልግሎቷን እንድትቀጥል ፤ ትምህርት ቤቶች እንዲቋቋሙ የአረጋውያን መጦሪያዎች የሙት ልጆች ማሳደጊያዎች የበሽተኞች ማስታመሚያዎች እንዲቋቋሙ ማድረግ የሚቻለው በዚህ በሰበካ ጉባኤ የተዘጋጁ ምዕመናንና ካህናት በየድርሻቸው የበኩላቸውን አገልግሎት ሲያበረክቱ ነው በሌሎች አገሮች ፓትርያርኮችና ጳጳሳት የሃይማኖት እንግዶች ጥሪ እያደረጉ የሚጋብዙትና እነሱም ጥሪ ሲደረግላቸው የሚሄዱት በግንኙነታችውም ጥሪና የስብሰባ ቦታ የቤተ ክርስቲያናቸውን ድምፅ ለማሰማት የሚያገኙት ከምዕመናን በሚደረግላቸው አስተዋጽኦ ነው ። ፓትርያርኩ ወይም የክፍሉ ጳጳስ ለክብሩ በማይመጥን መኪና ሲሄድ ያየው እንደሆን ምዕመኑ ሃይማኖት እንደተዋረደና ቤተ ክርስቲያኑም ዝቅ እንዳለች ይቆጥረዋል ።
... ዓላማው የተቻለውን ያህል ለቤተ ክርስ

www.ethiopianorthodox.org

ቲያን የሚገባውን ይከፍላል ። እንዲያውም ሀብት ያላቸው ምዕመ ናን ከሆኑ መንግሥ መኪና እንኳን ባይቀር ለፓትርያርኮቻቸውና ለጳጳሶቻቸው ገጸ በረከት የሚሰጡ አሉ ። የኛም ቤተ ክርስቲ ያን ብዙ ምዕመናን አሉዋት በሰበካ ጉባኤ ከተደራጁና የሰበካ ጉባኤ ገላግ ከገባቸው ለመንበረ ፓትርያርካቸውና ለከፍላቸው ጳጳስ ክብር የክብር መጠበቂያ ባጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያናቸው አስተዳ ደር አስተዋጽኦ ለማድረግ ከሌላው የሚሰንፉ አይደሉም ። ቤተ ክር ስቲያናችን በይፋ መመሪያ እንዲሆን ባወጣችው ቃለ ዓዋዲ ውስጥ ከሰበካ (አጥቢያ) ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርኩ ድረስ ያለው ያስ ራር መዋቅር ተተንትኖ የቀረበ ስለሆነ እሱን መመልከት ይበቃል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓት ርያርክ አስተዳደሩን የሚመሩ ልዩ ልዩ መመሪያዎች አሉ ለእነዚህ መመሪያዎች ኃላፊያቸው የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈ ሥራ አስኪያጅ ነው ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውም ጉዳይ— በቅዱስ ፓት ርያርክ ሊቀ መንበርነት በሲኖዶስ አባላት ተወስኖ ወደ ጠቅላይ ጽሕፈቱ ይተላለፋል ጠቅላይ ጽሕፈቱ በሥራ ላይ እንዲውል ያደር ገዋል ሥልጣነ ክህነትን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ግን ወደቅ/ሲኖ ዶስ ይቀርባል ፤ ቅዱስ ሲኖዶስ የጉዳዩን ጠባይ አይቶ ወደ መንፈ ሳዊ ፍርድ ቤት ይልከዋል ።

መንፈሳዊ ፍርድ ቤትም መርምሮና አጣርቶ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል ። ቅዱስ ሲኖዶስ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል ።

በየሀገረ ስብከቱ ያለው ያስተዳደር መዋቅርም የመንበረ ፓት ርያርኩን ጠቅላይ ጽ/ቤት አመራር የተከተለ ነው ልዩ ልዩ መምሪያ ዎች አሉት የመምሪያዎቹ የበላይ ሆኖ የሚሠራው ጳጳሱ ነው።ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመራው ፓትሪያርኩና የሀገረ ስብከት ጳጳሳት የሚሾሙት በምዕመናንና በካህናት ተመርጠው ነው ፤ የቅዱስ ሲኖ ዶስ ሕግ በሚያዘው መሠረት ለፓትሪያርክነትም ሆነ ለጳጳስነት ማዕረግ የሚመረጡት በድንግልና መንኩሰው በቁምስና ማዕረግ ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ የኖሩ ብቻ ናቸው ፤ ይህም ሥርዓትና ሕግ በመላው የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተጠብቆ የኖረና የሚኖር ነው ። በዓመት ሁለት ጊዜ በጥቅምት ፲፱ እና በረከበ ካህ



ናት ከትንሣኤ በኋላ በሸምጣው ቀን (የሲኖዶስ ስብሰባ ይደረጋል) የሲኖዶስ ሰብሳቢ ቅዱስ ፓትሪያርክ ናቸው ። የሲኖዶስ አባላት ጳጳ ሳት የየሀገረስስብከታቸው ምዕመናንና ካህናት ተጠሪ እንደመሆና ቸው መጠን ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይቀመጣሉ ። ስለቤተ ክርስቲ ያን አመራር ውይይት ያደርጋሉ ውሳኔም ያስተላልፋሉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጉዳይ በራስዋ ለመወሰን ምዕመናኖቿን እያስተባበረች ሕልውናዋን ለማስከበር ሕጋዊ አካ ልነት አላት ። ከዚህም ጋር ቃለ ሕይወት ትምህርቷን ወደአልደረ ሰበት ለማዳረስ ጥረት እያደረገች ነው ። ይህንንም ጥረት ለማሳካት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዕርዳታ በአምስት ሀገረ ስብከቶች የካ ህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ለመክፈት እየተዘጋጀች ነው።ይህ ም ማለት ዘመናዊውን ችግር የሚፈታ በዘመናዊ ዕቅድ የተቀናበረ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንዲኖራት ማለት ነው እንጂ በ፳ የሚ ቆጠር ዕድሜ ያላት ቤተ ክርስቲያናችን እምነቷንና ሥርዓቷን ጠብቃ የኖረችባቸው አያሌ ትምህርት ቤቶች እንደነበሩዋትና አሁንም እን ዳላት የታወቀ ነው ። የነበረው የመምህራኑና የተማሪዎቹ ኑሮ ግን ለአሁኑ ዘመን ትውልድ ያስቸግራል ። ዛሬ መንደር ለመንደር ዞሮ ለምኖ የሚበላ ተማሪና ተማሪዎቹን አስለምኖ ከነሱ ጋር ኮቸሮ የ ሚበላ ወጥንቅጥ (ድብልቅ ጥሬ) የሚቆላ መምህር አይገኝም ታዲያ በዚህ ጊዜ «አሳውም እንዳያልቅ ውሀውም እንዳይደርቅ» እንዲሉ ምዕመናንና ካህናትን በማስተባበር አስተዋጽኦ እየተሰበሰበ በየሀ ገረ ስብከቱ መሠረተ እምነት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች እን ዲቋቋሙና ፤ ከፍተኛ የሃይማኖት ትምህርት የሚሰጥባቸው የካህናት ማሰልጠኛዎች በዘመናዊ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንዲስፋፉ ቢደ ረግ ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም አቀፍ የክርስቲያኖች መድረክ የአ ቻነት መንበሯን ጠብቃ ለመኖር ትችላለች ።

ይቆየን ፤

ወለእግዚአብሔር ስብሐት ።

www.ethiopianorthodox.org